# ምዕራፍ 4 ሊተኮሩ የሚገቡ ጉዳዮችና ችግሮች ማጠቃለያ

## 4.1 በተመረጡ ሰብሎች ሊተኮሩ የሚገባ ጉዳዮች

### 4.1.1 የብርዕና አገዳ ሰብሎች

የደ/ብ/ብሔ/ክ/ የብርዕና አገዳ ሰብሎችን በማምረት ከሀገሪቱ በ3ተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ አብዛኛው የብርዕና አገዳ ሰብሎች ከጤፍ በስተቀር ለቤት ውስጥ ፍጆታ ነው የሚመረቱት፡፡ የብርዕና አገዳ ሰብል ምርት የሀገር ውስጥ ፍላጐት ስለማያሟላ ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ የሚመረተው ምርት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ይውላል፡፡

የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃ ባለሥልጣን፣ የዓለም ምግብ ፕሮግራም እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ እያንዳንዳቸው ለብርዕና አገዳ ሰብል ምርት የየራሳቸው የጥራት መለኪያ መመዘኛ አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ በአብዛኛው ጊዜ እነዚህ የጥራት መመዘኛዎች ለሀገር ውስጥ ገበያ ተግባራዊ አይሆኑም፡፡ የዓለም ምግብ ፕሮግራም ወይም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በሚያደርጓቸው ግብይቶች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ የሀገር ውስጥ የብርዕና አገዳ ሰብል ግብይት በዓይን እይታ እና በመነካካት ዋጋቸው ይወሰናል፡፡

<u>ለዓለም ምግብ ፕሮግራም/ግዥ ለዕደገት እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጨረታ የብርዕና አገዳ ሰብሎች የጥራት ቁጥጥርና የማበጠር ቴክኖሎጂ ሥርጭት</u>

ከላይ እንደተገለጸው የዓለም ምግብ ፕሮግራም እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚያካሄዷቸው የብርዕና አገዳ ሰብሎች ግብይት የተፈለገውን የጥራት መመዘኛ መከተል የግድ ይሆናል፡፡ ጥራቱ የተበላሸ ከሆነ ተቀባይነት ስለማያገኝ ከግብይቱ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ በግዥ ለዕድገት የታቀፉ የሕ/ሥራ ዩኒየኖች የብርዕና አገዳ ሰብሎች ብቃት ያለው ግብይት ለማመቻቸት የጥራት ቁጥጥርና የማበጠሪያ ቴክኖሎጂ ለአባል ሕ/ሥራ ማህበራት ማሠራጨት አለባቸው፡፡

<u>የሕ/ሥራ ማህበራት የምርት መሰብሰብ፣ ማበጠርና የግብይት ሥራ አቅም ማሳደግ</u>

በግዥ ለዕድገት የታቀፉም ሆኑ ያልታቀፉ የሕ/ሥራ ማህበራትን በጥራት ቁጥጥርና የቴክኒክ አቅማቸውን ማሳደግ ብቀት ያለውን የግብይት ሥራ ለመፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጨረታ ግብይት የሚሳተፉ የሕ/ሥራ ዩኒየኖችም ሆኑ የሕ/ሥራ ማህበራት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንቦችን ማወቅና የእርጥበት ማስተካከያና ማበጠሪያ የመሳሰሉትን የጥራት ቁጥጥር እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡ አርሶ አደሮችን በሚመለከት የሕ/ሥራ ማህበራት የሚፈልጉትን የጥራት ደረጃ ማወቅ አለባቸው፡፡ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጨረታ ግብይት ለወደፊት እየተለመደ ሲሄድ የግል ነጋዴዎችም የሚፈለገውን የጥራት ደረጃና ዝርዝር ደንብ አውቀው በብርዕና አገዳ ሰብሎች ግብይት የሚሳተፉበት ሥርዓት መመቻቸት ይገባል፡፡

<u>ትክክል ያልሆነ መጋዘንና የጥራት ቁጥጥር</u>

አብዛኛው መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና የሕ/ሥራ ዩኒየኖች የራሳቸውም ሆነ የተከራዩት መጋዘኖች ለረዥም ጊዜ ሰብል ለማከማቸት የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ መጋዘኖች የመያዝ አቅማቸው መጠነኛ ነው፡፡ በተጨማሪም በጭቃ የተሠሩ ግድግዳዎች ለፀሐይ ብርሃንም ሆነ አየር ለማስገባት ክፍተቶች የሏቸውም፡፡ አግባብነት ያላቸውን የመጋዘን ዲዛይኖችና የመጋዘን አስተዳደርና ቴክኖሎጂ በማዘጋጀት ለረዥም ጊዜ ሰብሎችን ለማቆየት የሚያስችል ሞዴል መጋዘን መሥራት አስፈላጊ ነው፡፡ በዓለም ምግብ ፕሮግራም እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት የሰብል ጥራት ለመጠበቅ እንዲቻል ባዕድ ነገሮች

ለማበጠር የሚያስችል የመለያ ማሽን በመጠቀም ትላልቅ ግብይቶችን ለማስፋፋትና የሰብሉን ተመሳሳይነት በመጠበቅ በቂ ገበያ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

### 4.1.2 ጥራጥሬ

<u>የገበያ ሥፍራ ማሻሻል</u>

በምርት አካባቢ ያለው ገበያ ቦታ የግብርና ምርት ከሚሰብሰብበት ቦታ ነው፡፡ እንደእነዚህ ያሉ የገበያ ቦታዎች በመሠረታዊ አገልግሎት መስጫ ቁሳቁሶችና መሠረተልማት እንደ ፈሳሽ ማስወገጃና ጣሪያ በመሳሰሉት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት ከማሻሻልና ከማደራጀት በተጨማሪ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ዝርዝር የሌሎች አካባቢዎችም ጨምሮ ማስታወቂያ ቦርድ በመጠቀም ለአርሶአደሮች ወቅታዊ ዋጋ እንዲያውቁ ስለሚያስችል በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

<u>ለዓለም የምግብ ፕሮግራም/ግዥ ለዕድገት እና የኢትዮጵያ ጨረታ የጥራጥሬ ሰብሎች የጥራት ቁጥጥርና የማበጠር ቴክኖሎጂ ሥርጭት</u>

የዓለም ምግብ ፕሮግራም እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚያካሄዷቸው የጥራጥሬ ሰብሎች ግብይት የተፈለገውን የጥራት መመዘኛ መከተል የግድ ይሆናል፡፡ ጥራቱ የተበላሸ ከሆነ ከግብይቱ ይወገዳል፡፡ በግዥ ለዕድገት የታቀፉ የሕ/ሥራ ዩኒየኖች የጥራጥሬ ሰብል ብቃት ያለው ግብይት ለማመቻቸት የጥራት ቁጥጥርና የማበጠሪያ ቴክኖሎጂ ለአባል ሕ/ሥራ ማህበራት ማሠራጨት አለባቸው፡፡

<u>የሕ/ሥራ ማህበራት የምርት መሰብሰብ፣ ማበጠርና የግብይት ሥራ አቅም ማሳደግ፣</u>

በግዥ ለዕድገት የታቀፉ ሆኑ ያልታቀፉ የሕ/ሥራ ማህበራት በጥራት ቁጥጥርና የቴክኒዎሎጂ አቅማቸውን ማሳደግ ብቃት ያለውን የግብይት ሥራ ለመፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት ለመሳተፍ የሚፈልጉ የሕ/ሥራ ዩኒያኖችም ሆኑ የሕ/ሥራ ማህበራት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንቦችን ማወቅና የእርጥበት ማስተካከያና ማበጠሪያ የመሳሰሉትን የጥራት ቁጥጥር እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡ አርሶአደሮችን በሚመለከት የሕ/ሥራ ማህበራት የሚፈልጉትን የጥራት ደረጃ ማወቅ አለባቸው፡፡ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት ለወደፊት እየተለመደ ሲሄድ የግል ነጋዴዎችም የሚፈለገው የጥራጥሬ ጥራት ደረጃ በሚሟላት ሊሳተፉ ይችላል፡፡

<u>ትክክል ያልሆነ መጋዘንና የጥራት ቁጥጥር</u>

የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና የሕ/ሥራ ዩኒያኖች የራሳቸውም ሆነ የተከራዩት መጋዘኖች ብዙ መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ምንም እንኳን ለጥራጥሬ ሰብል ከብርዕና አገዳ ሰብል የተለየ መጋዘን መገንባት ባያስፈልግም የጥራት ቁጥጥር የመጋዘን አስተዳደር ቴክኖሎጂ ለብርዕና አገዳ ሰብል እንደሚያስፈልገው ሁሉ ለጥራጥሬ ሰብልም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 4.1.3 አትክልት

#### (1) በቀላሉ የሚበላሹ አትክልቶች

<u>የከተሞች አካባቢ ፍላጐት የሚያሟላ የአትክልት ምርት ማስፋፋት</u>

በከተሞች አካባቢ የሚመረቱና በገበያ ላይ የሚውሉ የአትክልት ዓይነቶች በአርሶአደሮችም ሆነ ለንግድ ዓላማ የሚመረቱ በጣም የተወሰኑ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በሀዋሣ ከተማ ያሉ የአትክልት ግሮሰሪዎች በውጭ ላኪ ኩባኒያዎች ባለቤትነት የሚንቀሳቀሱት የተለያዩ ጥራት ያላቸውን አትክልቶች ለገበያ በማቅረብ እየበለፀጉም ይገኛሉ፡፡ በከተሞች አካባቢ በህዝብ መጨመርና ከአመጋገብ ባህል መቀየር ጋር ተያይዞ የአትክልት ፍላጐት በመጠንም

በዓይነትም እየጨመረ መሄዱ አይቀርም፡፡ ስለሆነም የአትክልት ምርት በመጠንም በዓይነትም ከከተማ ነዋሪዎች ፍላጐት ጋር በሚጣጣም መልክ ማስፋፋት አስፈላጊ ነው፡፡

በተለምዶ ምርቱ በማይመረትበት ወቅት የአትክልት ምርት አቅርቦት ማስፋፋት
አሁን ያለው የአትክልት ምርት አመራረት ወቅታዊነት አለው፡፡ ስለሆነም የገበያ ዋጋም በተመሳሳይ መልኩ ይዋዥቃል፡፡ በተቃራኒው አትክልት ቀደም ሲል በተለምዶ በማይመረትበት ወቅት ከተመረተ አትራፊ ይሆናል፡፡ ይህንኑ የአትክልት ምርት ለማስፋፋት የሚከተሉ የግብርና አመራሮች 1) አርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ፣ 2) አነስተኛ የመስኖ ልማት ማስተዋወቅ፣ 3) በምርምርና ሠርቶ ማሳያ አዳዲስ የአመራረት ቴክኖሎጂ እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ማስፋፋት፣ እና 4) የምርት ጥራት ማሻሻል (የተሻሻሉ ዝሪያዎችን ማስተዋወቅ፣ የተሻሻለ ተባይ መከለከያ ሥርዓት ማቋቋም ወዘተ../ መደገፍ ያስፈልጋል፡፡

ለከተማ ገበያዎች ምርት በብቃት መሰብሰብና ማሠራጨት
ለከተሞች አካባቢ ገበያዎች ምርት በብቃት ለመሰብሰብና ለማሠራጨት 1) በማምረቻ አካባቢ የምርት አሰባሰብን ማሳደግ (አምራቹ በጋራ/በወል ግብይት በማካሄድ)፣ 2) ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት የምርት አያያዝ በማሻሻል ምርት ሲጓጓዝ ጥንቃቄ በመውሰድ ብልሽት/ብክነት መቀነስ፣ እና 3) የተሻሻለ ምርት ማጓጓዣ ዘዴ እንደ ኮንቴነር የመሳሰሉትን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

የቲማቲም ምርት በተመለከተ ወንዶገነት አካባቢ ለሀዋሣ ገበያ በዋናነት ከሚያቀርቡ አንዱ ነው፡፡ የተሻሻሉ ዝሪያዎችን ነገርግን ጥንቃቄ ለሚሹ የአርሶአደሩን የምርት መሰብሰብ፣ አያያዝና የትራንስፖርት ሥርዐት በማሻሻል የተሻለ ዋጋ እንዲያገኙ ስለሚረዳ ማስተዋወቅና እንዲያመርቱ ማድረግ ይችላል፡፡

የግብይት መሠረተልማት እንደ መንገድና የገበያ ሥፍራ ማሻሻል የምርት መሰብሰብና ሥርጭት ብቃት ለመጨመር አስፈላጊ ነው፡፡

አብዛኛዎቹ አርሶአደሮች ምርት ለማጓጓዝ መሰብሰቢያ ሣጥን ወይንም ኮንቴይኔር የላቸውም፡፡ የተሻሉ ኮንቴነየሮች እና ለመጫን የሚመቹ ሣጥኖችን አርሶአደሮች እንዲጠቀሙ የገንዘብ ድጋፍ (ድጐማ) ማድረግ  የግድ ነው፡፡

አርሶአደሮች ትርፍ ምርታቸውን የሚሸጡት በአካባቢው የገበያ ሥፍራዎች ነው፡፡ ምቹ ያልሆኑ የገበያ ሥፍራዎች በተለይ በዝናብ ቀናት ብቁ የሆነ የምርት ልውውጥ ማካሄድ አያስችሉም፡፡ በቀላሉ የሚበላሹ አትክልቶች በቀጥታ ለፀሐይ ብርሃን ይጋለጣሉ፡፡ ስለዚህ ይህንን የተበላሸ የገበያ ሥፍራ በመጠኑም ቢሆን ጣሪያ በመሥራትና የፍሳሽ ማስወገጃ በማበጀት ማሻሻል የግድ ያስፈልጋል፡፡

በከተማ ገበያዎች የመቀበያና የሥርጭት አገልግሎት ማጠናከር
በከተሞች አካባቢ የምርት መሰብሰብን ከማጠናከር ጎን ለጎን የምርት መቀበያና ሥርጭት ሥርዓትን ማጠናከር አስፈላጊ ነው፡፡ የሥርጭት ሥርዓቱ ማነቆዎች ካሉት የመቀበያ ሥርዓቱ ብቃት ያለው ሊሆን አይችልም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በአግባቡ ዲይዛን ተደርጎ የጅምላ ሽያጭ ገበያ ሥፍራ ለማቋቋም ለግል ነጋዴዎች የድጋፍ እርምጃዎች መስጠት አስፈላጊ ሲሆን ለጅምላ ንግድ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችና መሣሪያዎች እንዲሁም መሠረተልማት ማሟላት እንዲችሉ ለጅምላ ሻጮች፣ ችርቻሪዎች፣ ትላልቅ የአትክልት መሸጫ መደብሮች፣ የጭነት መኪናዎች ወዘተ.. ግንዛቤ መፍጠርና ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡

### (2) በርበሬ

የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ በሀገር ደረጃ ከፍተኛውን በርበሬ የሚያመርት ሲሆን በጣም የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያለውና ለገበያ የሚመረት ምርት ነው፡፡ ከሌሎች ክልሎች ጋር ያለውን ተወዳዳሪነት ለመጠበቅ የጥራት ማሻሻልና ለየት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ የጥራት ደረጃ በመጠበቅ የተሻለ ዋጋ ለማግኘት ሸማቾች ወይም ገዥዎች እነማን እንደሆኑ በትክክል መታወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪ የገበያ ስንሰለቱም ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በሸማች በኩል የተወሰነ ነው የሚፈለገው፡፡ አርሶአደሮች በጥራት ማሻሻል ለመሥራት ከፈለጉ በቡድን መሥራት የግድ ይላል፡፡

በርበሬን በማሰባሰብ ረገድ የገበያ ሥፍራ፣ ዕቃዎችና የአመራር ሥርዓትና ደንቦች/ሕጐች ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ ብቃት ያለው ግብይት በተመለከተ በተለይ በአላባ ቁሊቶ ገበያ ሥፍራ የአስተዳደር ሥርዓት እና ሕግ/ደንብ ሊኖረው ይገባል፡፡ ምክንያቱም የገበያ ልውውጡ በትልቅ ደረጃ የሚጀምረው በምሽት ስለሆነና በጣም ብዙ ደላላዎች ስላሉ ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡

የገበያ መረጃ ማቅረብ በተመለከተ (የዋና ዋና ከተሞች ዋጋ፣ የአድስ አበባ ገበያና በሌሎች ክልሎች ያለው የምርት ሁኔታ ወዘተ.) በግብርና የሥራ ኃላፊዎች አማካኝነት በክልል ውስጥ በርበሬ አምራች አካባቢዎች መረጃ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የበርበሬ የድህረ ምርት አያያዝ የምርምር ሥራ በተመለከተ በጣም ደካማ ነው፡፡ የምርምር ሥራ የብክነትን መንስኤ በመዳሰስ ባህላዊ የመጋዘን አያያዝ ዘዴ የሚሻሻልበትን፣ ጥሩ ቀለምና ቅርጽ እንዲኖር ማድረግ የሚቻልበትን፣ አግባብ ያለው የእርጥበት መጠን የመለየት፣ የተሻሻለ የማድረቂያ ዘዴ ወዘተ.. በተመለከተ ጥናት መካሄድ አለበት፡፡

### 4.1.4 ፍራፍሬ

<u>ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የማንጎና የአቮካዶ ዝሪያዎችን ማስተዋወቅና ማልማት</u>

በደቡቡ ክልል ከፍተኛ መጠን ያላቸው የማንጎና የአቮካዶ ምርቶች ያሉ ሲሆን አብዛኛው የፍራፍሬ ዛፎች ያለምንም እንክብካቤ ያድጋሉ፡፡ የማምረት ዘዴው "መሰብሰብ" እንጂ "ማልማት" አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለተለያዩ ዝሪያዎች ምንም ትኩረት አልተሰጠም፡፡ አብዛኘው ማንጎ ብጫና ትንሽ ሆኖ ቃጫ የበዛበት ሲሆን አብዛኛው የአቮካዶ ዝሪያ ደግሞ ካልተወቀ ዝርያ ጋር የተዳቀለ ነው፡፡

በአዋሽ ሸለቆ ኦሮሚያ ክልል የሚመረተው አፕል ማንጎ በአዲስ አበባ ገበያ በከፍተኛ ዋጋ ይሸጣል፡፡ ይሁን እንጂ በደቡብ ክልል ያሉ አብዛኛው አርሶአደሮች ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው እንደ አፕል ማንጎ የመሳሰሉት መኖራቸውን አያውቁም፡፡ በቀላሉ በማዳቀል የአፕል ማንጎ ዝርያ ማግኘት እንደሚችሉም አያውቁም፡፡ ይህንን ሁኔታ በመገንዘብ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ዝሪያዎች ማስተዋወቅና ማልማት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ዓላማ የግብርና ቢሮ የዝሪያ ምርጫ በማድረግ፣ ችግኝ ማፍላትና ማሠራጨት እና አግባብ ያለውን የማልማት ዘዴ ማስተማር አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዛፍ መገረዣ መጋዝ ከውጭ ሀገር በማስገባት የፍራፍሬ ዛፎችን በአግባቡ ለማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡

<u>የአርሳአደሮችን ማንጎ እና አቮካዶ የማምረትና አያያዝ ልምምዶችን ማሻሻል</u>

ከላይ እንደተገለፀው የማንጎና የአቮካዶ ዛሮች ያለምንም እንክብካቤ የሚያድጉ ናቸው፡፡ ለፍራፍሬዎች መሰብሰብ የሚጠቀሙት መሣሪያ ስለሌለ፣ ዛፎቹ በጣም ትላልቅ ስለሆኑ እና ምናልባት ፍራፍሬ በእርካሽ ስለሚሸጡ ሊሆን ይችላል፤ የአርሶአደሮች ምርት መሰብሰብና አያያዝ ልምድ በጣም ደካማ ሊሆን የቻለው፡፡ አርስአደሩ ዛፍ ላይ መውጣትና በበትር ፍሬውን በመምታት እንዲወድቅ ይደረጋል፡፡ የዚህ ዓይነት ምርት አሰባሰብ ፍራፍሬ

እንዲቂስልና እንዲጎዳ ያድርጋል፡፡ በመሆኑም ምርቱ ሲጓጓዝ ከፍተኛ ብክነት እንዲደርስ ዋናውና አንደኛው መንስኤ ይሆናል፡፡

ስለሆነም ለአርሶአደሮች የጥራት ግንዛቤ በማስጨበጥ የምርት መሰብሰብና አያያዝ እንዲሻሻልና ተስማሚ የፍራፍሬ ማውረጃ ዘዴን ማስተዋወቅ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

<u>የምርት ማጓጓዝ ዘዴ ማሻሻል</u>
ወደ ሰሜናዊ ክልሎች ረዥም ርቀት አጓጉዞ በሚሰራጭበት ሂደት ብዙ የምርት ብክነት ይደርሳል፡፡ አሜሪካ ተርአዶ ድርጅት/አግሪብዝነስና ንግድ ማስፋፊያ ፕሮጀክት በአርባምንጭ የሙዝ ምርት ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ እየሠራ ነው፡፡ ሆኖም በምርት መሰብሰብና ማሸግና በመጫን ወቅት የሚደርሰውን የጥራት መጓደል ማስቀረት ብዙ ትኩረት የሚሻና መፍትሔ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ለአርሶአደሮች ምርት ከመሰብሰብና ማሸግ በተጨማሪም የተሻለ የጭነት መኪና አጠቃቀም ዘዴዎችን (እርካሽና ዕድሜ ያለው ኮንቴነየር/ሣጥን፣ እና አግባብነት ያለው አደራደር/መጫንና ማውረድ ሥራ) ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡

<u>በገበያ አካባቢ ያለው ደካማ ሁኔታዎችን ማሻሻል</u>
በአርባምንጭ አካባቢ በሕ/ሥራ ማህበራት ከሚንቀሳቀሱ ሙዝና ማንጎ በስተቀር ሌሎቹ የፍራፍሬ በምርቶች በአካባቢው የገበያ ቦታ ከተከማቹ በኋላ ወደ ዋና ዋና ከተሞች ይጓጓዛሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያልተመቻቹ የገበያ ሥፍራዎች መኖር ብቃት ያለው የምርት ግብይት እንዳይኖር እንቅፋት ሆኗል፡፡ ስለዚህ በገበያ አካባቢ ቢያንስ ቢያንስ ጣሪያና የፍሳሽ ማስወገጃ ያለው መሸጫ ቦታ አጠቃቀም ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡

<u>ለአፍሪካ- ጂውስ ኩባኒያ የሚደረግ ማንጎ ሽያጭ</u>
በከፍተኛ የምርት ወቅት የማንጎ ዋጋ መውደቅ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ሲሆን በ2010 (እ.ኤ.አ) ቲቢላ ከሚገኘው ከአፍሪካ ጂውስ ኩባኒያ የቀረበው ከፍተኛ የማንጎ ፍላጐት የተፈጠረውን የዋጋ መውደቅ ያቃልላል የሚል ግምት ተሰጥቶት ነበር፡፡

አፍሪካ ጂውስ ኩባኒያ በነሐሴ ወር 2010 (እ.ኤ.አ) ከሁለት የሕ/ሥራ የኒያኖች ጋር ከፍተኛ መጠን ያለውን ማንጎ ለመግዛት ውል ገብቶ ነበር፡፡ በ2010/11 (እ.ኤ.አ) የምርት ዘመን የተደረገው የማንጎ ግብይት የምርት ብክነት ችግር፣ የክፍያ ችግር እና በምርቱ ጥራት ላይ ደስተኛ አለመሆን ተከሰቶ ነበር፡፡ ይህ የሆነው በኩባኒያው ደካማ የንግድ አሠራር ነው፡፡ ምንም እንኳን የችግሩ ምንጭ ባይረጋገጥም በ2011012 (እ.ኤ.አ) የኩባኒያው የማንጎ ምርት ግዥ አልተፈጸመም፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የግድ የለሽ የማቴሪያል ግዥ (የጭነት መኪና አለማመቻቸት፣ ከዩኒያን ጋር ያለው ደካማ ግንኙነት፣ የምርቱ የጥራት መጓደል) በ2010/11 (እ.ኤ.አ) ተፈጽሟል፡፡ ከዚህ የተነሣ የኩባኒያው የንግድ ብቃቱ ከፍ ያለ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ሆኖም የኩባኒያው የማንጎ ፍላጐት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛው ነው፡፡ ከአቅርቦት በኩል (ዩኒያን፣ ሕ/ሥራ ማህበራት፣ ወረዳና ክልል ግብይት ሕ/ሥራ መ/ቤቶች) የገዥውን የጥራትና የመጠን ፍላጐት ለማሟላት እንዲሁም የተረጋጋ የንግድ (ብዝነስ) ግንኙነት ለመፍጠር ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የክልሉ ግብይት ቢሮ የመሪነቱን ሚና መጫወት አለበት፡፡

### 4.1.5 ሥራሥር ሰብሎች

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በአንዳንድ ዞኖች ከእንሰት በስተቀር ሥራሥር ሰብሎት መደበኛ ምግብነት በአብዛኛው ለቤት ውስጥ ፍጆታ በአነስተኛ ማሣ ላይ ይለማሉ፡፡ አምራቾች ሲያስፈልጋቸው ከተራሮች ወርደው ምርቱን ተሸክመው ወደ ገበያ ሥፍራ አምጥተው ይሸጣሉ፡፡ በአጠቃላይ የሥራሥር ሰብሎች የግብይት ሥርዓት ኋላቀር ነው፡፡ ደርቅ ካሳቫና ከእንሰት የሚሠራው ቆጮና ቡልአ የእሴት የተጨመረላቸው ምርቶች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ለእነዚህ ምርቶች የምርት ማቆያ ቴክኖሎጂ የለም፡፡ የሥራሥር ሰብሎች ዋጋ በጣም እርካሽ ሲሆን ብዙ ጊዜ አንድ ኪ.ግ ከብር 1.00 በታች ይሸጣል፡፡

#### (1) ካሳቫ

ካሳቫ ድርቅን የሚቋቋም ሰብል እንደመሆኑ መጠን አርሶአደሮች በባህላዊ አስተሳሰብ ለድንገተኛ የድርቅ ወቅት ደራሽ ነው በማለት ያለሙታ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከቤታቸው ጓሮ እንደ አጥር እንዲያገለግልም ይተክላሉ፡፡ ደረቅ ካሳቫ ለኢንዱስትሪ እንደጥሬ ዕቃም ያገለግላል፡፡ እንደ ድንገተኛ ደራሽ፣ የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ በመሆን ወይንም ለመለስተኛ የቤት ፍጆታ የሚሆነው ዝሪያ፣ ለልማትና ድህረ-ምርት አያያዝ አንድ ዓይነት መሆን የለበትም፡፡ ሆኖም ትክክለኛ ዝሪያ ለቤት ፍጆታ የመምረጥ ፍላጐት ገና አልዳበረም፡፡ አብዛኛዎች አርሳአደሮች በ3 ዓመት የሚደርሰውን ዝሪያ ለምግብ ዋስትና ዓላማ ይጠቀማሉ፡፡ ከዚያ ቀድሞ የሚደርስ ዝሪያ በምግብና ግብርና ድርጅት (ፋኦ) እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይኝነት እንዲተዋወቁ እየተደረገ ነው፡፡

የደረቀ ካሳቫ ፍጆታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያደገ መጥቷል፡፡ ምክንያቱም የደረቅ ካሳቫ ዱቄት ከጤፍ ዱቄት ጋር ተዋህዶ የሚሠራው እንጀራ ተቀባይነቱ እየጨመረ መጥቷል፡፡ የደረቅ ካሳቫ የአነስተኛ አርሶአደሮችን የገቢ ምንጭ ሰብል በመሆን ትኩረት በመሳብ ላይ ቢሆንም የምርት ጥራት ጉዳይ ትልቅ ችግር ነው፡፡

የሚከተሉት የመፍትሔ እርምጃዎች ተጠናክረው ሊወሰዱ ይገባል፡፡

- ቀድሞና በአጭር ጊዜ የሚደርስ ካሳቫ ዝሪያ በገንዘብ ምንጭነት ስለሚያገለግል መስፋፋት አለበት፣
- አግባብነት ያለው የምርት ማቀነባበሪያ ዘዴና ተያያዥ ዕቃዎች አጠቃቀም በመፍጠር ኤክስቴንሽን አገልግሎት ማስፋፋት፣
- ለኢንዱስትሪዎች በጥሬ ዕቃነት ማቅረብ ማስቀጠል፣
- የተሻለ ዋጋ ለማግኘት ያስችል ዘንድ የካሳቫ ጥራት ማሻሻልን መደገፍ፣
- ለደረቅ ካሳቫ የምግብነት ጠቀሜታ ማስታወወቅና ማስፋፋት ናቸው፡፡

#### (2) እንሰት

እንሰት በደቡብ ክልል በብዙ ቦታዎች መደበኛ ምግብ ሆኖ ያገለግላል፡፡ እንሰት ቆጮና ቡልአ ሆኖ ከተሠራ በኋላ መደበኛ ምግብ ይሆናል፡፡ እነዚህን የማዘጋጀት ሥራዎች በመንደር አካባቢ በሴቶች ይከናወናል፡፡ ብዙ ዓይነት የእንሰት ማዘጋጃ ዕቃዎች ተሠርተው ሕ/ሰቡ እንዲያውቃቸው ተደርገዋል፡፡ ይሁንና በእጅ የሚሠሩ ሆነው የተፈበረኩ ሲሆን በሞተር ኃይል እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ገና ይቀራል፡፡

ቆጮና ቡልአ በአብዛኛው በአርሳአደሮች ቤት ለፍጆታ ሲውል ትርፍ ምርት በአካባብው ገበያ ይሸጣል፡፡ አንዳንድ ነጋዴዎች ይህንን ቆጮና ቡልአ ገዝተው በመሰብሰብ ለትላልቅ እንደ አድስ አበባ ላሉ ገበያዎች ይቀርባሉ፡፡ ቆጮና ቡልአ የሚያመርቱ አርሶአደሮች የተወሰኑ ናቸው፡፡ እነዚህ አርሶአደሮች በደቡብ ክልል ያሉት በባህላዊ የእንሰት ዝግጅት ይቀጥሉ

ወይንም ወደ በለጠ ንግድ አትራፊ ምርቶች እንደ በቆሎ፣ ጥራጥሬና ሩዝ ይሸጋገሩ አልታወቀም ቆጮና ቡልአ በኢትዮጵያ ባህላዊ ምግብ ሲሆን የእነርሱም ዝግጅት ዘዴ ባህላዊ ነው፡፡ የግብይት ፍሰቱም ከምርት አካባቢ እስከ ሸማቾች አካባቢ የተዘረጋ ነው፡፡ አንዳንድ የግል ድርጅቶች ቀላል የእንሰት መላጫ ማሽን ሠርተዋል፡፡ ነገር ግን ይበልጥ ግልፅና ለሁሉም አገልገሎት የሚውሉ ማሽኖች እስኪዘጋጁ ብዙ ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል ይገመታል፡፡ በሀዋሣ ዩኒቨርስቲ የተዘጋጀው ማሽንና በተመሳሳይ ብዙ ብላዋ ያለው የቆጮ መቁረጫ አርሶአደሮችና ቸርቻሪ ነጋዴዎችን ለእሴት መጨመር እንደሚጠቅሙ ይገመታል፡፡

### (3) ስኳር ድንችና ጎደሬ

የስኳር ድንችና ጎደሬ ደበቡብ ክልል በማዕከላዊ እና በምዕራብ አካባቢዎች በተለይም የአየሩ ንብረት ፀባይ ለጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ የጥራጥሬ እህሎችና እንሰት ለማምረት አመቺ ባልሆነበት የክልሉ ዝቅተኛ እና መካከለኛ ቦታዎች በብዛት ይመረታል፡፡ የአመጋገብ ሥርዓቱን በተመለከተ ከተቀቀለ በኂላ ለምግብነት ይውላል፡፡ በእነዚህ ሰብሎች ላይ በተሻለ ቴክኖሎጂ የምግብ ዝግጅት ሂደት አይታይም፡፡ የደረሰው ስኳር ድንች አንዳንድ ጊዜ ለክምችት ስባል በመሬት ውስጥ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ ጎደሬ ግን ተቆፍሮ ከወጣ በኂላ ተቀቅሎ ለምግብነት ይውላል፡፡ እነዚህን ሰብሎች ከጤፍ ዱቄት ጋር ቀላቅሎ እንጀራ የመጋገር ሁኔታ በአብዛኛው ጊዜ አይትይም፡፡ የስኳር ድንችና ጎደሬ በዋናነት ለቤት ውስጥ ፍጆታ ሲሆን ትርፍ ሆኖ ስገኝ በአካባቢው ባለው ገበያ በዝቅተኛ ዋጋ ይሸጣል፡፡

እነዚህን ምርቶች በተሻለ የዋጋ ሥርዓት ለማስገባት መከተል የሚገቡ አቅጣጫዎች
- የምርት ማዕከላትን በማቋቋም ሰፊና ዋስትና ያለው ገበያ መፍጠር፣
- የተቀናጀ የገበያ ሥርዓት በማስተዋወቅ ውጤታማ ግብይት እንዲኖር ማድረግ፣
- ሌሎች ሰብሎችን በማካተት በገበያ ላይ የሸማቹን ምርጫና ፍላጐት ማሟላት፣
- የምግብ ማቀነባበርና የገበያ እንቅስቃሴዎችን ማስፋፋትና ማሣደግ፣

## 4.1.6 ሌሎች ሰብሎች

### (1) ሽንኮራ አገዳ

ሽንኮራ አገዳ ለገበያ ተብሎ የሚመረት ሲሆን የሽያጭ መጠኑም 50% አካባቢ ነው፡፡ ሆኖም አምራች አርሳአደሮች በምርት ላይ ተጨማሪ እሴት እንዲፈጠር እንደ ጭማቂ፣ ጃጋሪ (ቡኒ ስኳር) ወይም የአልኮል መጠጥ የመሳሰሉትን ስለማይሰሩ ገቢያቸው አነስተኛ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሽንኮራ አገዳ አምራቾች እንደ ወንዶ ገነት አካባቢ ያሉት የምርት መሰብሰብ ሥራ ለሰብሳቢዎች ወይም አገናኝ ነጋዴዎች ስለሚሸጡ ለአነስተኛ አምራቾች አርሶአደሮች ገብያቸውን ለማሣደግ በጣም ከባድ ይሆናል፡፡

የሽንኮራ አገዳ ግብይት ዘዴ ለማሻሻል ሊወሰዱ የሚገቡ አቅጣጫዎች፡-
- የምርት መሰብሰብና ግብይት ሥራ ለአርሶአደሮች በመተው የገቢ መጠኑን ማሳደግ (የአርሶአደሮች የቡድን ሥራ ማጠናከር)
- ብቃት ያለውን የግብይት ዘዴ ለነባር አነስተኛ አርሶአደሮች ማስተዋወቅ (የጋራ ግብይት ማበረታታትና በሌሎች ክልሎች አማራጭ ገበያ ማፈላለግ)
- የሽንኮራ አገዳ ተዋጽኦ የሆኑ የምርት ዝግጅቶችን ማሳደግና ለምርቱም ገበያ መፍጠር፣

### (2) ዝንጅብል

<u>የደረቅ ዝንጅብል ጥራት ማሻሻል</u>

በደቡብ ክልል ዝንጅብል በማብቀል በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ይይዛል፡፡ ደረቅ ዝንጅብል ከፍተኛው የውጭ ንግድ የሚላክ ምርት ነው፡፡ ዝንጅብል ሳይታጠብ በባህላዊ አሠራር

በመሬት በማስጣት በፀሐይ ይደርቃል፡፡ አሚፓ/የዓለም አቀፍ ገንዘብ ለግብርና ልማት በከምባታ ጠምባሮና በወላይታ ዞኖች ንፁህ ደረቅ ዝንጂቢል እንዲያመርቱ ለአርሶአደሮች የሙያ ሥልጠና ሰጥቶ ነበር፡፡ ሆኖም አሚፓ/የዓለም አቀፍ ገንዘብ ለግብርና ልማት ተግባራዊ የሚሆን የማጠቢያ ዘዴ አላስተዋወቀም፡፡ አግባብነት ያለውን የማጠቢያ ዘዴ ማስተማርና ማስተዋወቅ ለአካባቢውን ሁኔታ የሚስማማ ጥራት ያለው ንፁህ ደረቅ ዝንጅብል ለማምረት ይጠቅማል፡፡

<u>የጥራት ግንዛቤ ካላቸው ገዥዎች የገበያ ትስስር መፍጠር</u>
አሁን እየተሠራበት ያለውን የማድረቂያ ዘዴ ለመለወጥ ለአርሶአደሮች የተሻለ ዋጋ (ማበረታቻ) ለሚሠሩት ተጨማሪ ሥራ እንዲያገኙ ማድረግ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ንፁህ ደረቅ ዝንጅብል ምርት ለማግኘት አርሶአደሮችና የጥራት ግንዛቤ ካላቸው ገዥዎች ጋር ዋስትና ያለው የንግድ የሥራ ግንኙነትና ትስስር መፍጠር ለአርሶአደሩ ማበረታቻ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

## 4.2 የሁሉንም የሚነካኩ ጉዳዮች

### 4.2.1 የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት

<u>ወቅቱን የጠበቀ ትክክለኛ የገበያ መረጃ ለአርሶአደሮችና ለሌሎች የገበያ ተዋንያን ለማሠራጨት አለመቻል</u>
የተለያዩ ድርጅቶች እንደ ማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አስተዳደር፣ ዓለም የምግብ ፕሮግራም፣ የእንስሳት መረጃ አውታርና እውቀት ስርዓት፣ የኢትዮጵያ እህል ገበያ ኢንተርፕራይዝ እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያሉት የገበያ ዋጋ መረጃ ሰብስበው በሀገር ውስጥ ያሰራጫሉ፡፡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በሞባይል አጭር የጽሑፍና የድምፅ መልዕክት አገልግሎት ያሠራጫል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወቅታዊ መረጃ በሞባይል አጭር የጽሑፍና ድምፅ መልዕክት የሚሰራጨው በቡና ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የገበያ መረጃ አግልግሎት ለሽያጭ ለሚመረቱ ሁሉም ሰብሎች ማለት በሚስችል ሁኔታ ወቅታዊ የዋጋ መረጃ ለአርሶአደሮችና የገበያ ተዋንያን እየተሰራጨ አይደለም፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ሊቃለሉ የሚገቡ ችግሮችና ጉዳዮች የመፍትሔ አቅጣጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

<u>የተቀናጀ የአሠራር ስርዓት ያለመኖርና የገበያ መረጃ አገልግሎት ተመሳሳይነት ማጣት</u>
የግብርና ቢሮ/የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎትና አፈጻጸሙን በክልሉ የማደራጀትና ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡ ሆኖም እስከአሁን ግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት አሠራር አልተዘጋጀም፡፡ አስከ 2010 (እ.ኤ.አ) (የዚህ ጥናት የመጀመሪያ ዓመት) የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት በግብርና ቢሮ በኩል በደንብ የተደራጀና የተሠራ አሠራር (የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት) እንዲሁም ግልጽ የሆነ የጋራ ግንዛቤ አልነበረውም፡፡

ለዚህ ደካማ የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችለው በግብርና ቢሮ በኩል የግብርና ገበያ መረጃ ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ለማሰባሰብ የሚያስችል ሰነድ፤ ምን መሠራት እንዳለበት፣ እንዴት መሠራት እንዳለበት የሚለውን በሚያሳይ መልኩ የተነደፈ ያሠራር መመሪያ ያለመኖር ሲሆን በተጨማሪ የሰው ኃይልና በጀት ጭምር በአግባቡ አለመመደብ ናቸው፡፡

<u>በጣም ደካማ መገናኛ አገልግሎት</u>
በብዙ ወረዳ ጽ/ቤቶች ለግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውሉ እጅግ ውስን/ጥቂት የመገናኛ ማሣሪያዎች ይገኛሉ፡፡ አአሁኑ ወቅት በደ/ብ/ብ/ሕ/ ለግብርና ገበያ መረጃ አግልግሎት ኢንቴርነት የመጠቀም ልምድ የለም፡፡ የሞባይል አገልግሎት (ድምፅና አጭር የጽሑፍ መልዕክት) ብቻ ነው በአሁኑ ጊዜ በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች መካካል የገበያ መረጃ ለመለዋወጥ የሚያስችለው፡፡

የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 መጀመሪያ ያሳየው ነገር ቢኖር አሁን አገልግሎት እየሰጠ ያለው የሞባይል ኔትወርክ (አጭር የጽሑፍ መልዕክት አገልግሎት) በጣም አስተማማኝ እንዳልሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም የኔትወርክ መቋረጥ ብዙ ጊዜ ወዲያውኑ የአጭር የጽሑፍ መልዕክት መላክና መቀበል አላስችልም፤ እንዲሁም የመረጃ ልውውጥን ያስተጓጉላል፡፡ ከዚህ ሌላ የተላኩ መረጃዎች የሚጠፉበት አጋጣሚዎችም ተከስተዋል፡፡

<u>ለግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት በወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በቂ ሀብት አለመኖር፡-</u>
ለግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ዕቃዎችና መሣሪያዎች (የመገናኛ መሣሪያዎች፣ የቢሮ ዕቃዎች በተለይም ኮምፒተር) በተለይ አዳዲስ በተቋቋሙ ወረዳ ጽ/ቤቶች በቂ አይደሉም፡፡ በበቂ ሁኔታ የመገናኛ መሣሪያዎች መኖር በግብይት የሥራ ሂደቶች መካካል መረጃ ለማስተላለፍና ለመቀበል ወሳኝ ነው፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ያለው የመደበኛ ስልክ መስመር ብቻ ነው፡፡

<u>ስለግብርና ገበያ መረጃ አግልግሎት ዓላማ በቂ ግንዛቤ አለመኖርና የተሰበሰበውን መረጃ አለመጠቀም</u>
በመሠረቱ የመንግሥት የገበያ መረጃ አገልግሎት ዓላማ ማድረግ ያለበት አርሶአደሮችና ነጋዴዎች እንዲሁም ለሌሎችም የገበያ ተዋኒያን የገበያ መረጃ በተሟላ መልክ ማቅርብን ነው፡፡ ሆኖም የዋጋ መረጃ በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የተሰበሰበው ፋይል ያደረጋል እንጂ ጥቅም ላይ አይውልም፡፡ በጣም ጥቂት መረጃ ነው ለተዋንያኑ የሚተላለፈው፡፡ በግብርና አስተዳደር ጽ/ቤቶች መካከልም የመረጃ ልውውጥ በአግባቡ ተግባራዊ አይሆንም፡፡

<u>የወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የሥራ ማስኬጃ በጀት፡-</u>
የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የሚሠሩ አቻ ባለሙያዎች እንደገለጽት የሥራ ማስኬጃ በጀት እጥረት በመኖሩ የዋጋ መረጃ በማስታወቂያ ቦርድ ለመለጠፍ የሚያስፈልግ ለአላቂ ዕቃዎች መግዛት እንኳን አስቸጋሪ መሆኑን ነው፡፡ በየካቲት 2011 (እ.ኤ.አ) በተደረገው የክትትልና ግምገማ ስብሰባ የ14ቱም አቻ ባለሙያዎች የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት አጭር ጽሑፍ መልዕክትና ማስታወቂያ ቦርድ በመጠቀም የሚያካሂደው የመረጃ ልውውጥ መቀጠል ጥሩ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የሥራ ማስኬጃ በጀት ስለአልተመቻቸ (ለእያንዳንዱ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በወር ለሞባይል ካርድ መግዣ ከብር 100-150 በአጠቃላይ በወር ብር 1850 በጀት ያሰፈልጋል)፡ ነገር ግን የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ተቋርጧል፡፡

የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በጀት በወረዳ አስተዳደር ነው የሚመደበው፡፡ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ለወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በጀት ለመመደብ ምንም ሥልጣን የለውም፡፡ ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 እንቅስቃሴ ለመቀጠልም ሆነ ወደ ሌሎች ወረዳዎች ለማስፋፋት የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በክልሉ ግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ተግባራዊ ለማድረግ ኃላፊነት ያለበት እንደመሆኑ መጠን ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የሥራ ማስኬጃ በጀት እንዲመድብ መሥራት አለበት፡፡

### 4.2.2 የግብይት መሠረተልማት

የመንገድ ጥገናና የትራንስፖርት አገልግሎት

ክልሉ ከተቋቋመ ከ1993 (እ.ኤ.አ) ወዲህ የመንገድ መስፋፋትና የመንገድ ጥጊጊት በተከታታይ ተሻሽሏል፤ አሁንም በክልሉ የመንገድ ዕቅድ 2010/11--2014/15 (እ.ኤ.አ) መሠረት እየተሸሻለ ይገኛል፡፡ ሆኖም በቂ ነው አይባልም፡፡ ዋንኛዎቹ የግብይት መስመሮች፡ 1) ሀዋሣ መስመር፣ 2) ሆሣዕና-አርባምንጭ መስመር፣ እና 3) ጂማ መስመር አስፋልት መንገድ ሲሆኑ አገልግሎታቸውን እንደ ደም ሥር ሆነው በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ሌላ የሕ/ሰብ መንገዶች በመስፋፋት ላይ ያለ ሲሆን በወረዳ በጀት ወይንም እንደ ግብርና ዕድገት ፕሮግራም ባሉ እየተገነባ ነው፡፡ ሆኖም አካባቢዎች በሞተር ኃይል የሚሠራ መጓጓዣ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው የሚገኘው፡፡ ይህም የሆነበት የመግዛት አቅም አነስተኛ ስለሆነ ነው፡፡ ባለሶስት ጎማ ባጃጅና ፈረስና ጋሪ አሁንም በአካባቢ ከተሞች ዋናው መጓጓዣ ናቸው፡፡ አብዛኛው ሕ/ሰብ በእግር አለዚያም በጋማ ከብት ይጓጓዛል፡፡ የግብርና ምርት ወደ አካባቢ ገበያዎች ለማጓጓዝ የሕዝብ የማጓጓዣ ትራንስፖርት ማዘጋጀት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ያለ ትራንስፖርት አማራጮች በመንገድ ማስፋፋት ብቻ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ የሚመከር አይደለም፡፡

የአካባቢ ገበያዎች

በደንብ የተደራጁና አገልግሎት የሚሰጡ የአካባቢ ገበያዎች ብዛት በጣም አነስተኛ ናቸው፡፡ ጣሪያ ያላቸው የገበያ ሥፍራዎችም አልፎ አልፎ እየታዩ ነው፡፡ ስለዚህ ተግባራዊ የሆነ የገበያ ውስጥ መተላለፍያ መስመር፣ ፍሳሽ ማስወገጃና ለገበያ ተጠቃሚዎች የሚሆን መፀዳጃ ቤት የመሳሰሉ ችግሮች ሊቃለሉ ይገባል፡፡ የንፁህና ጉዳይና የምርት አያያዝ ዘዴ በተለይ በዝናብ ወቅት ሊፈቱ የሚገቡ ችግሮች ናቸው፡፡ ሆኖም ከፋይናንስ እጥረትና አግባብነት ያለው የአስተዳደር ሥርዓት ባለመኖሩ ተግባራዊ የሚሆን መፍትሔ እየተገኘ አይደለም፡፡

መጋዘን

የሕ/ሥራ ማህበራት መጋዘኖች ብዙ ያልተቀረፉ ጉዳዮች አሉት፡፡ እነዚህ መጋዘኖች አብዛኛዎቹ በጭቃ ግርግዳ የተገነቡ፣ አንድ በር ብቻ ያላቸው የአየር መዘዋወሪያ የሌላቸው ናቸው፡፡ ገቢያቸው አነስተኛ የሆነ የሕ/ሥራ ማህበራት ጽ/ቤትና መኖሪያ ቤት ለምርት መከማቻ መጋዘንነት ይከራያሉ፡፡ ስለዚህ እንዚህ መጋዘኖች በሰብል ክምችት ወቅት የሰብል ብክነት ያስከትላሉ፡፡ የሕ/ሥራ ማህበራት የመጋዘን አስተዳደር ቴክናሎጂ ማስፋፋትና ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ የምግብ ሰብል ከኬሚካል ወይም ከማዳበሪያ ለያይቶ ማከማቸትና ከዚያም አግባብ ያለው ቴክኖሎጂና መጋዘን አያያዝ ዕውቀት በሥልጠና እንዲያገኝ ማድረግ አግባብ ነው፡፡

### 4.2.3 የአርሶአደሮች ድርጅቶች/ የሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች

በመንግሥታዊ መዋቀር ያለ ተቋማዊ ችግሮች

በደቡብ ክልል የሕ/ሥራ ማህበራትን ለመደገፍና ለመቆጣጠር የሚያስችል የሕግና መመሪያ ማዕቀፍ አለ፡፡ አዋጁ የሕ/ሥራ ማህበራት ግዴታዎችና ኃላፊነታቸውን ያብራራል፡፡ የክልሉ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የምዝገባ፣ ቁጥጥርና የድጋፍ ሰጪነት ሚና (በ4 እርከኖች ከቀበሌ እስከ ክልል ደረጃ) እንዲጫወት ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአጠቃላይ በክልል ደረጃ ወደ 9000 የሚጠጉ የሕ/ሥራ ማህበራት የተመዘገቡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 1200 የሚደርሱት የግብርና አምራቾች የሕ/ሥራ ማህበራት ናቸው፡፡ የሕ/ሥራ ማህበራትን ለማደራጀት ካለው ፖለቲካዊ መፈክር ባለፈ የክልሉ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ግልፅ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅር ወይንም ተግባራዊ የሚሆን እንዴት ሕ/ሥራ ማህበራትን መደገፍ እንዳለበት የሚያሣይ እስትራቴጂ የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወቅታዊ ክለሣና ማስተካከያ

በአንዳንድ ፖሊሲዎች አለመደረግ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀጥታ የሕ/ሥራ ማህበራትን ፍላጐትና ልማት የሚደግፍ ያለመኖር ለጥሩ ዕድገት እንቅፋት ከመሆን በተጨማሪ የረዥም ጊዜ ግብና እስትራቴጂ ላይ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡

<u>የሕ/ሥራ ማህበራት በጋራ ግብይት መሳተፍ</u>

የሕ/ሥራ ማህበራትን ለማቋቋም በክልሉ መንግሥት በተደረገው ጠንካራ ዘመቻ ከ150 በላይ አዳዲስ የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራት ከ2007-20011 (እ.ኤ.አ) ባለው ጊዜ ተቋቁመዋል፡፡ ሆኖም ጥቂት ሕ/ሥራ ማህበራት በአዋጁ በተቀመጠው መሠረት የተለያዩ አገለግሎቶችን ለአባላቱ ለማቅረብ በቴክኒክና በማስተዳደር በቂ አቅም አላቸው፡፡ የብዙዎች ሕ/ሥራ ማህበራት አገልግሎት ለአባላቱ የግብርና ግብዓቶችን ከማሠራጨት ያለፈ አይደለም፡፡ አንዳንዶቹ ምንም እንቅስቃቤ የላቸውም፡፡ ጥቂት ሕ/ሥራ ማህበራት በጋራ ግብይት ሙሉ በሙሉ በእህል ሰብል ግብይት በተለይም በበቆሎ፣ ስንዴና በቦሎቄ ይሳተፋሉ፡፡ የእህል ሰብል ግብይትን በተመለከተ ሕ/ሥራ ማህበራት በአዘጋጁት አሠራር ስርዓት መሠረት ዩኒያኖች ለአባል ሕ/ሥራ ማህበራት ብድር ይሰጣሉ፡፡ ሕ/ሥራ ማህበራት ከአባሎቻቸው እህል ይገዙና ለዩኒያን መልሶ ይሸጥሉ፡፡ ሕ/ሥራ ማህበራት በኩል የሚገበያየው እህል በክልሉ ከሚገበያየው በጣም ጥቂት ነው፡፡ ከዚሁ ግብይት ተጠቃሚ የሚሆኑት አርሶአደሮችም በቁጥር በጣም አነስተኛ ናቸው፡፡ ሕ/ሥራ ማህበራት ሥራቸውን እዳያስፋፉ በጣም የተወሰነ የፋይናንስ አቅም መኖር፣ ኂላ ቀር ድህረ-ምርት አያያዝ ምክንያት ጥራቱ ዝቅተኛ የሆነ ምርት መሰብሰብ፣ አግበባነት ያለው የመጋዘን አጠቃቀም ያለመኖር፣ የመሳሰሉት እንቅፋት ሆኗል፡፡ ከዚህ የተነሣ ብዙ አርሶአደሮች የሕ/ሥራ ማህበራት አባለት ጭምር የሚሸጡት ምርት ዝቅተኛ ጥራት ያለው በዝቅተኛ ዋጋ ለአካባቢ ነጋዴዎች የሚሸጡት ነው፡፡

በሌሎች ሰብሎች ንግድ ላይ የተሳተፉ ሕ/ሥራ ማህበራት ቁጥር በእህል ንግድ ላይ ከተሳተፉት አንፃር ሲታይ በጣም ትንሽ ነው፡፡ አብዛኛው የደቡብ ክልል አርሶአደሮች ኑሮአቸው ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ሲሆን ለሽያጭ በሚሆን ምርት ማመረት የሚሳተፉ ጥቂት ናቸው፡፡ ከእነዚህ የሚለየው በጋሞጎፋ ዞን ያሉት የሙዝ አምራች አርሶአደሮች ናቸው፡፡ እነዚህ አርሶአደሮች ግልጽ የሆነ በጋራ ዓላማ ይዘው በሕ/ሥራ ማህበር ተደራጅተው የጋራ/የወል ግብይትን እያካሄዱ ነው፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ አነስተኛ አርሶአደሮች ገበያ ተኮር የሆነ የግብርና ልማት ሕ/ሥራ ማህበራት አማካኝነት ለማካሄድ እንቅፋት የሆኑ ዋናና መሠረታዊ ችግሮችና ተግዳሮቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ብዙ ሕ/ሥራ ማህበራት በደቡብ ክልል የተመዘገቡት የተቋቋሙት በመንግሥት ድጋፍ ሲሆን እንደ ግብርና ግብአት ሥርጭት የመሳሰሉ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ አባላት በጋራ ዓላማ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ የለም፡፡ አብዛኛው አባላት የተቀናጁ አይደሉም፡፡ ለሕ/ሥራ ማህበር ውጤታማነት ወሳኝ የሆነ አግባብ የሆነ የድርጅታዊ አቋም ወይም የጋራ መግባባት በመካከላቸው ያለመኖር ፡፡
- የሕ/ሥራ ማህበራት ሥራና አስተዳዳር በጥቂት የአስፈፃሚ ኮሚቴና በአነስተኛ የአባላት ተሳትፎ ቁጥጥር ሥር ያለ ነው፡፡ ሰፊው አባላት በሕ/ሥራ አመራር ላይ እምነት ስለሌላቸው ተሳትፎአቸው በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ጥቂት ዩኒየኖችና ሕ/ሥራ ማህበራት የጋራ ግብይት ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበር፡፡ ይኸውም ከውጭ ለሚቀርቡ የጋራ ሥራ ጥያቄዎች የመንግሥት ኤጀንሲውዎች የልማት አጋሮች ምላሽ ለመስጠት ጥረት አድርገው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ጥረቶች እንደተፈለገው አልሆኑም፡፡ ዋናው ምክንያትም እነዚህ አባላት ፍላጐት አልነበራቸው ምክንያቱም በውሣኔ ሰጪነት ሂደት አማክሮአቸው ወይንም አሳትፎአቸው ስለማያውቁ ነው፡፡
- አብዛኛው አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶአደሮች ሕ/ሥራ ማህበራት አባላት ጭምር ስለገበያ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ያላቸው ልምድ አነስተኛ ነው፡፡ እነሱ የግብርና ግብይት

ሥርዓትና የዋጋ አሠራር በጣም የተወሰነ ዕውቀት አላቸው። ስለሆነም ሀሳቡ አዲስ ስለሚሆንባቸው በጋራ ግብይት ለማሳተፍ በጥርጣሬ ውስጥ ይገባሉ።

ከዚህ ጋር ከተያያዘ የድረጅታዊ አስተዳዳርን በአግባቡ ለማካሄድ የዕውቀትና የክህሎት እጥረትና ከመኖሩ በተጨማሪ የንግድ ሥራ አመራር፣ የአባላት ዝቅተኛ ቁርጠኝነት፣ በአባላት ዝቅተኛ ግንዛቤ፣ የኮሚቴ አባላት በግልፀኝነትና ተጠያቂነት ማጣት፣ በሕ/ሥራ ማህበራት ላይ በጣም ከፍተኛ የሆነ ተግዳሮት ከመፍጠሩም በላይ ሕ/ሥራ ማህበራት የጋራ ግብይት ለመጀመርና ውጤታማ የንግድ ሥራ ለማካሄድ አደጋች ሆኗል።

<u>ፋይናንስና የሂሣብ ሥራ</u>
ቀደም ሲል ሕ/ሥራ ልማት ኤጀንሲ በአስቀመጠው መመሪያ መሠረት ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች በየዓመቱ የሂሣብ ሪፖርት (የሂሳብ ሚዛን፣ ገቢና ወጪ ሰነድ) እና የቢዝነስ ዕቅድ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ሆኖም አንድም ሕ/ሥራ ማህበር የሂሣብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት አቅም የለውም። ስለዚህ የወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኦዲተሮች በእነሱ ምትክ ያዘጋጅሉ። የሂሣብ ሥራና የፋይናንስ ትንተና ለማድረግ የሚረዳ ምንም ዓይነት ኮምፒውተር የለም።

የተከማቸው የፋይናራስ መረጃ አንድም ጊዜ ተተንትኖ ጥቅም ላይ ውሎ አያውቅም። በተለያዩ ዓመታት መካከል ያለው የሂሣብ ሪፖርት ማነፃፀር ቢኖር፣ የቢዝነስ ጥንካሬና ድክመት ግልፅ ይሆናል። እንዲሁም ለኢንቨስትመንትና የገንዘብ ብድር ለማቀድ በጣም ጠቃሚ ይሆን ነበር። ሆኖም የሂሣብ ሪፖርት አሠራር ዕውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ክፍያው በጣም ከፍተኛ በመሆኑ መቅጠር አይችሉም። ለሂሣብ ሪፖርትና የሂሣብ መረጃ ግልፀኛ መሆን በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በአስፈፃሚ ቦርድና በጠቅላላ ጉባኤ አባላት መካከል የጋራ መተማመን ለመፍጠር እጅግ ወሳኝ ነው። ሆኖም የቦርድ አባላት በአግባቡ የቢዝነስ እንቅስቃሴ መግለፅ ስለማይችሉና መሠረታዊ የቢዝነስ ዕውቀት ስለማይኖራቸው በመካከላቸው ያለመተማመን ስሜት ይፈጠራል።

<u>ለሕ/ሥራ ማህበራት የሚደረግ ድጋፍና ውስንነት</u>
መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለሕ/ሥራ ዩኒያኖችና ለሕ/ሥራ ማህበራት የተለያዩ ሥልጠናዎችን ብቃታቸውን ለማሳደግና የሕ/ሥራ ቢዝነስ ለማንቀሳቀስ ሲሰጡ ቆይተዋል። ሆኖም በእያንዳንዱ ሥልጠና ወቅት የሚመረጡት ሕ/ሥራ ማህበር አባላት አጠቃላይ በክልል ደረጃ ካሉት ጋር ሲነፃፀር በጣም ትንሽ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛው ሥልጠናዎች የሚሸፍኑት ርዕሶች በጣም ጥቂት ነበሩ። ከዚህ የተነሣ የተካሄደው ጥቂት ጥረቶች ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት ወይንም ሕ/ሥራ ማህበራትን ለመለወጥና ለማሳደግ አልተቻለም። ከዚህ በታች የተመለከተው ለሕ/ሥራ ማህበራት በተሰጡ ሥልጠናዎችና የትዩ ድክመቶች ናቸው።

(የሥልጠና ይዘት)
- በንድፈሀሳብ ላይ ትኩረት ማድረግ። ስለሆነም ለሠልጣኞች የተማሩት ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል።
- ለጎልማሳ ሠልጣኞች የተለመደ የተማሪ አስተማሪ የማስተማር ዘዴ መጠቀም።
- የሕ/ሥራ ማህበርና አባላት ያሉበትን ሁኔታ በመረዳት ለተሳታፊዎች በቂ ምልሽ የመስጠት እምብዛም መሆን።

(የሥልጠና ሥርዓት)
- ለአብዛኘው ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ባለሙያዎች የሚሰጠው የአሰልጣኖች ሥልጠና ባለሙያዎቹ በተዋረድ ሕ/ሥራ ማህበራትን እንዲያሰለጥኑ ነው። ይሁንና

*ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ለሥልጠና እንዲያካሂዱ በቂ በጀትና የሥልጠና ቁሳቁስ መመደብ እምብዛም ነው፡፡*

- *ለማንኛውም የሥልጠና ኘኖርግራም ተመሳሳይ የሕ/ሥራ ማህበር አባላት (በማህበሩ ያላቸው ኃላፊነት ምንም ይሁን) ይመረጣል፡፡*
- *የሥልጠና ተሣታፊዎች በሥልጠና የተገኘውን ዕውቀት ለሌሎች አባላት አያስተላልፉም፡፡ ስለሆነም ሥልጠና በአብዛኛው ለሕ/ሥራ ማህበሩ መሻሻል የሚያደርገው አስተዋጽኦ እምብዛም ነው፡፡*

### 4.2.4 የምግብ ማቀነባበር (አግሮ ፕሮሰሲንግ)

*<u>ለምግብ ዝግጅት/ማቀነባበር አጋዠ ኢንዱስትሪዎች ያልዳበረ ሁኔታ</u>-*

*ያልዳበሩ ለምግብ ዝግጅት የአጋዥ ኢንዱስትሪዎች እንደ ማሸጊያ ፋብሪካ ዓይነት የግብርና የምግብ ዝግጅት ማቀነባበርን የሥራ መጠን ሳይታይ በጣም ያዳክማል፡፡ ኤልፎራ ሜልጌ ወንዶ የምግብ ዝግጅት ፋብሪካ በደቡብ ክልል የታሸገ የቲማቲም ምርት ውጤቶችን የሚያመርት ሲሆን የምርት ውጤቱን በጣሳ ለማሸግ የውጭ ሀገር የሚያስገባው የጣሳ ቆርቆሮ ዋጋ ከፍተኛ መሆን ትለቁ ችግር ነው፡፡ አንድ ጠርሙስ ፋብሪካ በሀገር ውስጥ ያለ ቢሆንም የሚያመርቱት አንድ ዓይነት ጠርሙስ ለማመረት የሚጠይቁት ትንሹ ትዕዛዝ መጠን ከፍተኛ በመሆኑ ለአነስተኛ ቢዝነስ የሚያቀርበውን ትዕዛዝ ለማስተናገድ በጣም ከባድ ይሆናል፡፡ "ኢኮፒያ" የተባለ ፍራፍሬ በጎጆ ኢንዱስትሪ ደረጃ የማያዘጋጀው ምናልባት በሀገር አቀፍ ደረጃ ትልቁ ፍራፍሬ የሚያቀነባብር እንደሚሆን ሲገመት በሀገር ውስጥ የራሱን ብልቃጥ ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት የተነሳ አስመርቶ መጠቀም አልቻለም፡፡ በመሆኑም ለምርት ማሸግያ የሚስፈልገው ብልቃት ከውጭ ሀገር የሚያስገባ ሲሆን ዋጋው ከፍ ያለ ስለሚሆን ለአነስተኛ ቢዝነስ ገበያ አስቸጋሪ ስለሆነበት ጥቅም ላይ የዋለ ብልቃጥ መልሶ ለፍራፍሬ ጭማቂ ማሸግያ ይጠቀማል፡፡ በተመሳሳይ የጥራት ማረጋገጫ መረጃ መለጠፊያ/መጠቅለያ ለጭማቂ ምርት የሚያስፈልግ ሲሆን ዋጋው ከፍ ያለ በመሆኑ ከውጭ ሀገር ከሚመጡ ምግቦች ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን ያስቸግራል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለው የጥራት ደረጃ ያንን የደረሰ አይደለም፡፡*

*<u>የታሸጉ ምግቦችን ለማዘጋጀት ባህል ውስንነት፡-</u>*

*ዱቄት ማዘጋጀትና ማምረት በባህላዊ አሠራር በሀገቱ የተለመደ ነው፡፡ ከቅመም ጋር ተቀምሞ የተፈጨ በርበሬ ማዘጋጀት በጣም የተለመደ ነው፡፡ አብዛኛው ቤተሰቦች በዚህ ዓይነት የተለያዩ ቅመማቅመሞች ከገበያ ገዝተው በመቀመምና በማዋሃድ ለምግብነት ያዘጋጃሉ፡፡ የግል ቢዝነስ ድርጅቶች በዚህ ዓይነት በርበሬ የሚያዘጋጁ አሉ፡፡ ይሁን እንጂ አትክልትና ፍራፍሬ በባህላዊ መንገድ የምግብ ዝግጅት ልምድ የለም፡፡ ይህም በሀገሪቱ የምግብ እግጅት እንዳይዳብር ከአደረጉት ችግሮች መካከል አንዱ ነው፡፡*

## 4.3 ሰብሎችን በሥርጭት ሁኔታ መደልደል

*የመስክ ጥናት የተደረገው ሰብሉ ዓይነት ተመስርቶ ሲሆን ብርዕና አገዳ ሰብል፣ ጥራጥሬ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ሥራሥር እና ሌሎች (ቅመማቅመሞች ወዘተ..) ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ሰብሎች በደቡብ ክልል የተደለደሉት በሠንጠረዥ 4-1 እንደተመለከተው በአሁኑ ወቅት ባለው የሥልጭት ሁኔታ መሠረት ነው፡፡ ይህንን ድልድል በመጠቀም የልማት ግቦች በምርቱ ከደረሰበት ደረጃ እንደዲሁም ችግር ማስወገጃ እርምጃን መሠረት በማድረግ መጣል ይቻላል፡፡*

**ሠንጠረዥ 4-1 ሰብሎችን በሥርጭት ሁኔታ መደልደል**

| | የስርጭት ስፋት | ሳይበላሽ የሚቆይበት | በስርጭት ወቅት ብክነት | ማቀነባበር | የዋጋ መዋዠቅ | ተጨማሪ እሴት | ጥራት ቁጥጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብርዕ ሰብል | ሰፊ | ረዥም | መካከለኛ | የሚቀነባባር | በመጠኑ ከፍተኛ | ዝቅተኛ አቅም | ጥሩ |
| ጥራትሬ | በመጠኑ ሰፊ | ረዥም | መካከለኛ | በከፊል የሚቀነባበር | በመጠኑ ከፍተኛ | መካከለኛ | ጥሩ |
| አትክልት | ትንሽ | አጭር | ብዙ | የመያቀነባባር | ከፍተኛ | ከፍተኛ አቅም | መጥፎ |
| ፍራፍሬ | በመጠኑ ሰፊ | መካከለኛ አጭር | ብዙ | የመያቀነባባር | ከፍተኛ | ከፍተኛ አቅም | መጥፎ |
| ሥራሥር | በመጠኑ ሰፊ | መካከለኛ ረዥም | መካከለኛ | በከፊል የሚቀነባበር | ዝቅተኛ | መከካከለኛ | መጥፎ |
| ሌሎች | ሰፊ | መከከለኛ ረዥም | መካከለኛ | በከፊል የሚቀነባበር | ዝቅተኛ | መካከለለኛ | መካከለኛ |

ምንጭ : ጃይካ የጥናት ቡድን

በተጨማሪ የሰብሉ አቋም የምስል 4-1 እንደተመለከተው ተተንትኗል፡፡ አግዳሚ መስመሩ የምርትን የብስለት ደረጃ ሲገልፅ ከላይ ወደ ታች ያለው መስመር ሥርጭት የደረሰበትን ደረጃ ያመለክታል፡፡ የተመረጡ ሰብሎች በዚህ ዓይነት በምስሉ ላይ ተቀምጧል፡፡ አራትዮሽ ክፍልፋዮች ምርትና ሥርጭት ተብለው ተከፍለዋል፡፡ ቅጠላቅጠል አትክልቶች አነስተኛ ምርታማነትና ዝቅተኛ ሥርጭት አላቸው፡፡ ስለዚህ የመገጣጠሚያ ነጥብ (ምርት፣ ሥርጭት= አነስተኛ፣ አነስተኛ) በታችኛው ቀኝ አራትዮሽ ክፍልፍል ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም ሙዝና በቆሎ እንደ እምቅ አቅም በጣም ይመረታሉ፡፡ እንዲሁም የአመራረት ሥልቱም የረቀቀ ነው፡፡ ሆኖም የገበያ ሥርዓቱ በበቂ አልዳበረም፡፡ ስለዚህ በመገጣጠሚያ ነጥብ (ምርት፣ ሥርጭት= ከፍተኛ፣ አነስተኛ) በታችኛው ቀኝ አራትዮሽ ክፍልፍል ይገኛል፡፡

ምንም እንኳን የስንዴ ምርታማነት ከዓመት ዓመት የተሻሻለ ቢሆንም ለድህረ-ምርት ቴክኖሎጂና የሥራጭት ዘዴ ማሻሻል አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ በመገጣጠሚያ ነጥብ (ምርት፣ ሥርጭት= ከፍተኛ፣ ጥንሽ ከፍተኛ) ሲሆን በላይኛው ቀኝ አራትዮሽ ክፍልፍል ይገኛል፡፡ ቡና እንደ ዋና ግብ በዚህ መሪ ዕቅድ አልተቀመጠም፡፡ ሆኖም የመገጣጠሚያ ነጥቡ (ምርት፣ ሥርጭት= ከፍተኛ፣ ከፍተኛ) በላይኛው ቀኝ አራትዮሽ ክፍልፍል ይገኛል፡፡ በመሠረቱ በሥርጭት ግብ ስኬታማ የሆኑ ነገር ግን ኋላ ቀር አመራረት ያላቸው ሰብሎች አይኖሩም፡፡




**ምስል 4-1 በማምረትና በሥርጭት መካከል ያለው የብስለት መጠን ሃሣቦዊ ምሥል**

## 4.4 ዞናዊ ባህሪይ

### 4.4.1 ዞናዊ ባህሪይ በሰብል ልማት

የደቡብ ክልል የሚገኘው በ350-4200 ሜትር የመሬት ከፍታ ሲሆን የዝናብ መጠን ከ400-2200 ሚ.ሜ በዓመት ይሆናል፡፡ ስለሆነም የተለያ የተለያዩ ሰብሎችን ማሣደግ ይቻላል፡፡ በዚህ ክፍል የምርት መጠንና የሥርጭት መጠን በዋናና በተመረጡ ሰብሎች በዞን ተነፃፅረዋል፡፡

#### (1) ብርዕና አገዳ ሰብል

ምስል 4-2 የዋና ዋና ብርዕና አገዳ ሰብሎች የምርት መጠን በ13 ዞኖችና 8 ልዩ ወረዳዎች ያሳያል፡፡ የሰሜን ምሥራቃዊ አካባቢ ሀብታም የብርዕ አገዳ ሰብል እንደ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ገብስ እና ጤፍ የሚያመርት አካባቢ ነው፡፡ የበቆሎ ምርት በሲዳማ ዞን ከፍተኛ እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ባለሥልጣን "የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ) ጥራዝ. VII (ቡልቲን 446

**ምስል 4–2 የዋና ዋና ብርዕና አገዳ ሰብል የምርት መጠን በዞን**

የእያንዳንዱ ዞን አንፃራዊ የብርዕና አገዳ ሰብል ሽያጭ መጠን በምስል 4-2 ተመልክቷል፡፡ የስንዴ ምርት በሰሜን ምሥራቅ አካባቢ በትርፍነት የሚያመርት ሲሆን አርሶአደሮችም በጥሩ ሁኔታ ምርታቸውን በገበያ ይሸጣሉ፡፡ በሌላ አንፃር የበቆሎ ምርት ለቤት ፍጆታ ብቻ የሚመረት ሲሆን የገበያ ሁኔታ ገና ያልበሰለ/ያላደገ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 4-2 የብርና አገዳ ሰብል አንፃራዊ ሽያጭ በአምራችና ዞን (%)**

| ዞን/ ል ወረዳ | ጤፍ | ገብስ | ስንዴ | በቆሎ | ማሽሳ |
|---|---|---|---|---|---|
| ጉራጌ | 47.8 | 14.5 | 27.3 | 7.1 | 11.7 |
| ስልጤ | 53.3 | 15.3 | 42.4 | 5.5 | 5.3 |
| ሃዲያ | 51.2 | 14.9 | 42.9 | 5.9 | 7.3 |
| ከምባታ ጠምባሮ | 46.1 | 7.9 | 23.8 | 3.6 | 6.1 |
| ወላይታ | 56.6 | 13.2 | 14.9 | 9.5 | 3.9 |
| ሲዳማ | 55.0 | 29.4 | 29.2 | 11.9 | 8.6 |
| ጌዲኦ | 41.0 | 24.9 | 23.0 | 18.5 | 0.0 |
| ጋሞ ጎፋ | 44.7 | 11.7 | 18.0 | 13.9 | 8.6 |
| ዳውሮ | 19.5 | 26.9 | 23.2 | 12.1 | 11.4 |
| ከፋ | 26.8 | 21.7 | 21.9 | 26.0 | 17.9 |
| ሸካ | 15.6 | 17.6 | 35.6 | 17.0 | 15.1 |
| ቤንች ማጂ | 44.9 | 36.5 | 21.6 | 18.5 | 25.2 |
| ደቡብ ኦሞ | 54.8 | 40.8 | 43.5 | 25.4 | 18.0 |

| ዞን/ ል ወረዳ | ጤፍ | ገብስ | ስንዴ | በቆሎ | ማሽላ |
|---|---|---|---|---|---|
| አላባ ልዩ ወረዳ. | 77.5 | 18.1 | 51.2 | 5.9 | 3.6 |
| የም ልዩ ወረዳ | 21.8 | 6.7 | 16.0 | 3.4 | 6.5 |
| ኮንታ ልዩ ወረዳ | 33.8 | 22.5 | 29.8 | 22.9 | 15.2 |
| ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | 46.0 | 35.7 | 10.0 | 24.5 | 32.1 |
| አማሮ ልዩ ወረዳ | 46.4 | 33.8 | 14.8 | 7.7 | 9.3 |
| ቡርጂ ልዩወረዳ | 44.7 | 22.0 | 23.2 | 9.3 | 20.0 |
| ደራሼ ልዩ ወረዳ | 49.5 | 16.2 | 21.0 | 16.9 | 18.6 |
| ኮንሶ ልዩ ወረዳ | 42.1 | 8.0 | 12.5 | 11.9 | 6.0 |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

ምስል 4-3 የሚያሳየው የብርዕና አገዳ ሰብል የሥርጭት መጠን ሲሆን የተሰላውም ምርትን ከአርሶአደሮች አንፃራዊ የሽያጭ መጠን በማባዛት ነው፡፡




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-3 የብርዕና አገዳ ሰብል የሥርጭት መጠን በዞን**

### (2) ጥራጥሬ

የጥራጥሬ ምርትና ሥርጭት መጠን ከላይ ለብርዕና አገዳ ሰብል በታየው መልክ ተገልጿል፡፡




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-4 የጥራጥሬ ምርት መጠን በዞኖች**

### ሠንጠረዥ 4-3 የጥራጥሬ ሰብል አንፃራዊ ሽያጭ በአምራችና ዞን (%)

| ዞን/ ል ወረዳ | ባቄላ | አተር | በሎቄ | ሽምቡራ | አኩሪ አተር |
|---|---|---|---|---|---|
| ጉራጌ | 6.7 | 12.6 | 22.1 | 37.1 | 0.0 |
| ስልጤ | 8.4 | 11.2 | 4.9 | 15.6 | 0.0 |
| ሃዲያ | 23.3 | 32.4 | 11.1 | 15.0 | 0.0 |
| ከምባታ ጠምባሮ | 12.9 | 16.3 | 8.5 | 0.0 | 5.0 |
| ወላይታ | 2.9 | 10.1 | 11.1 | 19.0 | 15.0 |
| ሲዳማ | 23.2 | 21.0 | 15.1 | 0.0 | 0.0 |
| ጌዲኦ | 26.2 | 19.4 | 3.8 | 0.0 | 0.0 |
| ጋሞ ጎፋ | 15.0 | 22.5 | 11.0 | 65.0 | 0.0 |
| ዳውሮ | 19.2 | 27.6 | 10.1 | 12.5 | 0.0 |
| ከፋ | 21.2 | 24.4 | 11.2 | 25.0 | 0.0 |
| ሸካ | 18.9 | 24.2 | 0.4 | 0.0 | 0.0 |
| ቤንች ማጂ | 32.5 | 34.1 | 11.1 | 0.0 | 0.0 |
| ደቡብ ኦሞ | 49.4 | 54.1 | 16.3 | 0.0 | 35.0 |
| አላባ ልዩ ወረዳ. | 42.0 | 0.0 | 11.8 | 35.0 | 0.0 |
| የም ልዩ ወረዳ | 8.8 | 12.9 | 5.6 | 15.0 | 0.0 |
| ኮንታ ልዩ ወረዳ | 27.7 | 33.4 | 14.6 | 7.6 | 0.0 |
| ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | 0.0 | 24.7 | 18.0 | 0.0 | 0.0 |
| አማሮ ልዩ ወረዳ | 32.3 | 29.7 | 20.7 | 29.7 | 10.0 |
| ቡርጂ ልዩወረዳ | 26.2 | 26.0 | 32.0 | 28.1 | 0.0 |
| ደራሼ ልዩ ወረዳ | 18.4 | 30.3 | 25.7 | 40.0 | 0.0 |
| ኮንሶ ልዩ ወረዳ | 25.7 | 12.0 | 4.4 | 10.7 | 0.0 |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

### ምስል 4-5 የጥራጥሬ ሥርጭት መጠን በዞን

የጥራጥሬን በተመለከተ ምርትና ሽያጭ በከፋ ዞን ከፍተኛ ነው፡፡ ምርቱ በቤንች ማጂና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ብዙ አይደለም፤ ነገር ግን የሥራጭት መጠን 2000-3000 ቶን በዓመት ደርሶ ነበር፡፡ ይህም የሆነው የሽያጭ አንፃራዊ መጠን ከ50% ይበልጥ ስለነበረ ነው፡፡ ሽምብራ ጠቅላላ ምርትና ሥርጭት መጠን በጣም አነስተኛ በመሆኑ በምስሉ ላይ ሊታዩ አልቻለም፡፡ ሽምብራ የሚመረተው ለገበያ ተብሎ በመሆኑ 65% ምርት ወደ ገበያ ይቀርባል፡፡ በዚህ መሠረት በደቡብ ምዕራብ አካባቢ የጥራጥሬ እምቅ አቅም እንዳለው ያሳያል፡፡

### (3) አትክልት

ምስል 4-6 እና 4-7 በደ/ብ/ብ/ክ/ የዋና ዋና የአትክልት የምርትና የሥርጭት መጠን ያሳያል፡፡




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-6 የአትክልት ምርት መጠን በዞን**




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-7 የአትክልት ሥርጭት መጠን በዞን**

የአበሻ ጎመን ለቤት ፍጆታ የሚበቅል ሲሆን እስከ 10% ምርት ለገበያ ይመረታል፡፡ በርበሬ የሚመረተውም እንደ ገቢ መስገኛ ሰብል ነው፡፡ ከ60-75% የሚሆነው የበርበሬ ምርት ወደ ገበያ ገብቶ ይሸጣል፡፡ የበርበሬ ምርት ሽያጭን በተመለከተ በተለይም የጉራጌ ዞን፣ የስልጤ ዞንና የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ነው፡፡ የቲማቲም ንግድን በተመለከተ በሲዳማና በጋሞ ጎፋ ዞኖች የተሸሉ ሲሆን 55% እና 37% የሚደርስ ምርት ለሽያጭ እንደቅደም ተከተላቸው አላቸው፡፡

### (4) ፍራፍሬ

ምስል 4-8 እና 4-9 የፍራፍሬ የምርትና የሥራጭት መጠን ያመለክታል፡፡ ፍራፍሬ በጋሞ ጎፋ ዞን በጥሩ ሁኔታ ይመረታል፡፡ በጣም የታወቀው ሙዝ ሲሆን የሽያጭ መጠኑም 58%

ይደርሳል፡፡ ሲዳማ ዞን ሁለተኛው ትልቁ የሙዝ አምራች ሲሆን በሽያጭ ግን አንደኛ በመሆኑ የሽያጭ መጠኑ 71% ሲደርስ የዞኑ የአቪካዶ ሽያጭ መጠን 60% ነው፡፡




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-8 ፍራፍሬ ምርት መጠን በዞን**




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-9 የፍራፍሬ የሥርጭት መጠን በዞን**

### (5) የሥራሥር ሰብሎች

ዋነኛዎቹ የሥራሥር ሰብሎች የምርት አካባቢዎች ጋሞ ጎፋና ወላይታ ዞኖች ናቸው፡፡ በተዳፋት፣ ዝቅተኛና መካከለኛ ቦታዎች የወላይታ ዞን ብርዕና አገዳ ሰብል ለማምረት ስለማይስማማ የሥራሥር ሰብል በጥሩ ሁኔታ የሚመረትበት ነው፡፡




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-10 የሥራሥር ምርት መጠን በዞን**




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-11 የሥራሥር ሥርጭት መጠን በዞን**

### 4.4.2 ዞናዊ ባህርይ በሰብል ግብይት

በምስል 4-12 የሚገልፀው በእያንዳንዱ ዞን የዋና ዋና ሰብሎች የሽያጭ መጠን ነው፡፡ አንፃራዊ የሽያጭ መጠን በእያንዳንዱ ዞን በመውሰድ እስትራቴጂካዊ ለሽያጭ የሚመረቱ ሰብሎች ተለይተዋል፡፡




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-12 በእያንዳዱ ዞን ለሽያጭ የሚመረት ሰብል እምቅ አቅም (1/2)**




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክክስ ኤጀንሲ፡ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/9 (እ.ኤ.አ) , ጥራዝ VII, ቡልተን 446

**ምስል 4-12 በእያንዳዱ ዞን ለሽያጭ የሚመረት ሰብል እምቅ አቅም (2/2)**

1) ሰሜናዊ የክልሉ አካባቢ

በርበሬ በጉራጌ ዞን፣ በስልጤ ዞን እና በሃዲያ ዞን ለገበያ አንደ እምቅ አቅም ያለው ሰብል ሆኖ ይመረታል፡፡ በትርፍነት የሚመረተው ብርዕ ሰብል ብዙ ጊዜ ጤፍና ስንዴ ሽያጭ እስከ 50% ይደርሳል፡፡ ምንም እንኳን ጠቅላላ መጡኑ ዝቅ ያለ ቢሆንም የፍራፍሬ ምርት ሽያጭ መጠን በጉራጌ ዞንና በከምባታ ጠምባሮ ዞን ታዋቂ ነው፡፡

2) ማዕከላዊ የክልል አካባቢ

የሥራሥር ሰብል በወላይታ ዞን እና አትክልት (ቲማቲም በተለይ) እና ፍራፍሬ (አቮካዶና ሙዝ) በሲዳማ ዞን ለሽያጭ የሚመረት ሰብል ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ሥራሥር ሰብል በጌዲኦ ዞን የሽያጭ መጠን ከፍ ያለ ነው፡፡ የብርዕና አገዳ ሰብል በተለይ ጤፍ በዚህ በማዕከላዊ አካባቢ ይመረታል እንዲሁም ይሸጣል፡፡

3) ምዕራባዊ የክልሉ አካባቢ
የጥራጥሬ ምርትና ሽያጭ መጠን በከፋ ዞን ከፍተኛ ቢሆንም የሰብል ሽያጭ መጠን በዳውሮ ዞን በከፋ ዞንና በሸካ ዞን በአጠቃላይ ዝቅ ያለ ነው፡፡ በቤንች ማጂ ዞን የሰብል ሽያጭ መጠን በተለይም የሥራሥርና የፍራፍሬ ከፍ ያለ ነው፡፡

4) ደቡባዊ የክልሉ አካባቢ
በፍራፍሬና አትክልት ምርትና ሽያጭ የጋሞ ጎፋ ዞን ታዋቂ ነው፡፡ ሽምብራም በዚህ አካባቢ እንደ እስትራቴጂካዊ ለገበያ የሚመረት ሰብል ነው፡፡ ፍራፍሬና አትክልት በደቡብ ኦሞ ተመርተው የሚሸጡ ሲሆን በርበሬና ድንች ይበልጥ ታዋቂ ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ የተገለጸው ዞናዊ ባሕርይ በሰብል ምርትና ሽያጭ በምስል 4-13 ተመልክቷል፡፡



ምንጭ፡ የጃይካ ጥናት ቡድን

**ምስል 4-13 ሀሳባዊ ከርታ፡ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ እስትራቴጅካዊ የገቢ ማስገኛ ሰብሎች**

## 4.5 የተጠቃሚዎች ድልድል

(1) አርሶአደሮች
ግብርና ግብይት መሻሻል ተጠቃሚዎች፣ አርሶአደሮች፣ ነጋዴዎች፣ ምርት አቀናባሪዎች እና ሸማቾችን ያጠቃልላል፡፡ የአርሶአደሮች ድልድል በገበያ እንቅስቃሴ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 4-4 ተበራርቷል፡፡

### ሠንጠረዥ 4-4 የአርሶአደሮች ድልድል በገበያ እንቅስቃሴ

| | የቤት ውጥ ፍጆታ | ገቢ ማስገኛ ሰብል የሚያለሙ | በሕ/ሥራ ማህበራት ተሳትፎ | የጋራ ግብይት | ሊሰጥ የሚገባ አመራር |
|---|---|---|---|---|---|
| የአርሶ አደር ዓይነት 1 | ○ | | | | ← ምርት መጨመር |
| የአርሶ አደር ዓይነት 2 | ○ | ○ | | | ← የጋራ ሥራን ማስፋፋት |
| የአርሶ አደር ዓይነት 3 | ○ | ○ | ○ | | ← የጋራ ሥራን ማስፋፋት |
| የአርሶ አደር ዓይነት 4 | ○ | ○ | ○ | ○ | ← ትርፍ ማሳደግ |
| | ↑ | ↑ | ↑ | ↑ | |
| ተፈላጊ ክህሎትና ቴክኖሎጂ | ምርት | ድህረምርት ቴክ እሴት መጨመር | የቡድን ሥራ ማሳደግ | የገበያ መረጃ መሠረተልማት | |

| | |
|---|---|
| የአርሶአደር ዓይነት 1 | አርሶአደሮች ለቤት ፍጆታ ብቻ የሚያመርቱ ናቸው |
| የአርሶአደር ዓይነት 2 | አርሶአደሮች ገቢ መስገኛ ሰብል የሚያመርቱት ለሽያጭ ነገር ግን ሽያጩ ውስን የሆነ፡፡ ምርታቸውን ወደ አካባቢ ገበያ ራሳቸው ያጓጉዛሉ፡፡ ለስብሳቢዎች ወይም ለነጋዴዎች በማሣ ላይ ይሸጣሉ፡፡ ማንጐ አምርተው በመንገድ ዳር የሚሸጡ፣ ድንች ወይንም ዝንጅብል በጆርባ ተሸክመው በአካባቢ ገበያ የሚሸጡ በዚህ ቡድን ይመደባሉ፡፡ |
| የአርሶአደር ዓይነት 3 | ገቢ መስገኛ ሰብል የሚያመርቱና በሕ/ሥራ ማህበር አባል የሆኑ፤ ነገር ግን የሕ/ሥራ ማህበር የሥራ እንቅስቃሴ በግብርና ግብዓት (በማዳበሪያና ዘር) በመግዛት ወይንም በአነስተኛ ብድር መስጠት የተወሰነ ነው፡፡ ምንም የቡድን ሽያጭ አይከናወንም፡፡ የበቆሎና የጥራጥሬ አምራቾች በዚህ ቡድን ይመደባሉ፡፡ |
| የአርሶአደር ዓይነት 4 | ገቢ መስገኛ የሚያመርቱና በሕ/ሥራ ማህበር አባል የሆኑ የቡድን ሽያጭ የሚያካሄዱ፣<br>የስንዴ አምራቾች በሶዶ ወላይታ ዞን፣ የሙዝ አምራቾች በአ/ምንጭ ጋሞ ጎፋ ዞን በቡድን ሽያጭ የሚሳተፉ በዚህ የአርሶአደር ዓይነት ይመደባሉ፡፡ |

ለእያንዳንዱ ዓይነት አርሶአደር የሚያስፈልገው ክህሎትና ቴክኖሎጂ ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴ የሚሰጥ አመራር በሠንጠረዥ 4-4 በቀኝ በኩል ተመልክቷል፡፡ ዋና ዕቅዱ ዓላማው የግብይት ሥርዓቱን ለማሻሻልና በዓይነት 1 ያሉ አርሶአደሮች እንደ መጨረሻው ግብ ተጠቃሚ እንዳይቆጠሩ ነው፡፡

### (2) ነጋዴዎች (የገበያ ሥፍራ ተጠቃሚዎች)

በደቡብ ክልል ሁለት ዓይነት ነጋዴዎች አሉ፡፡ አምራች ሆነው የራሳቸውን ምርት የሚሸጡና የሙሉ ጊዜ ነጋዴዎች ናቸው፡፡ ነጋዴዎች የአካባቢ ገበያን ሥፍራ ምርታቸውን ለመሸጥ ወይንም ለመግዛት ይጠቀማሉ፡፡ የአካባቢ ገበያ በሣምንት አንድ ጊዜ ወይንም ሁለት ጊዜ ይቆማል፡፡ አንዳንድ አካባቢ ወቅታዊ የገበያ ሥፍራዎችም ለታወቀ ምርት ዓይነት ይኖራል፡፡ መደበኛ መደብሮች ዓመቱን በሙሉ የሚሠሩና የብርዕና አገዳ ሰብሎች የሚነግዱ የንግድ ሥራቸውን የአካባቢና የወረዳ ገበያ ቦታዎች አጠገብ በአጠቃላይ ያካሁጋሉ፡፡

ምስል 4-14 በአያንዳንዱ ዞን ያለውን የገበያ ሥፍራ እና የህዝብ ብዛት ያብራራል፡፡ የገበያ ሥፍራዎች ከህዝብ ብዛት ጋር ተነፃፃሪ ናቸው፡፡ በሲዳማ ዞንና በጋሞ ጎፋ ዞን በእያንዳንዳቸው ከ100 በላይ የገበያ ሥፍራዎች አሉ፡፡




| | Guጉራጌ | ስልጤ | ሃዲያ | ከምባታ ጠምባሮ | ወላይታ | ሲዳማ | ጌዲኦ | ጋሞ ጎፋ | ዳውሮ | ከፋ | ሸካ | ቤንች ማጂ | ደቡብ አሞ | አላባ | የም | ኮንታ | ባስኬቶ | አማሮ | ቡርጂ | ደራሼ | ኮንታ | ሃዋሣ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አካባቢ | 21 | 4 | 13 | 26 | 24 | 125 | 24 | 113 | 15 | 17 | 13 | 13 | 11 | 4 | 2 | 4 | 5 | 9 | 5 | 6 | 4 | |
| ወረዳ | 21 | 4 | 9 | 7 | 13 | 33 | 5 | 14 | 10 | 15 | 7 | 15 | 2 | 3 | 3 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | |
| ዞን | 10 | 7 | 5 | 1 | 3 | | 2 | 2 | 4 | 4 | 1 | 6 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | | | | |
| ገበያ | 1,31 | 773 | 1,28 | 704 | 1,57 | 3,05 | 907 | 1,64 | 507 | 906 | 206 | 679 | 595 | 239 | 83 | 94 | 58 | 154 | 58 | 147 | 242 | 270 |

ምንጭ፡ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፣ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ 2008 (እ.ኤ.አ)

**ምስል 4-14 የገበያ ሥፍራ ብዛትና የሕዝብ ብዛት በዞን**

የገበያ ሥፍራና መሠረተልማትን ማስተዳደር የግብይት ሂደት ፍትሐዊነትና ብቃት ላይ በእጅጉ ተጽእኖ የሚያደርጉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለገበያ ሥፍራ መሻሻል ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶ ጥናት የተካሄደ ሲሆን በምርት ዓይነትና ብዛት፣ በገበያ ሥፍራ ወይንም በተጠቃሚ ደረጃ እግንዛቤ ውስጥ ገብቷል፡፡

## 4.6 ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችና ፍላጐቶች በሰብል ዓይነትና አካባቢ

የግብርና ግብይት ማሻሻያ ዋንኛ የዕቅድ አካለት (ሀ) የገበያ መረጃ፣ (ለ) የእሴት ጭማሪ፣ (ሐ) የግብይት መሠረተልማት፣ እና (መ) የግብይት ተቋም/ሥርዓት ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 4-5 የእያንዳንዱ ሰብል/አካባቢ የዕቅድ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮችና ፍላጐቶች ማጠቃለያ ያቀርቧል፡፡

## ሠንጠረዥ 4-5 የትኩረት ጉዳዮችና ፍላጎት በሰብል ዓይነት ባ አካባቢ

| ሰብል | አካባቢ | የገበያ ደረጃ | የትኩረት ጉዳዮች | ፍላጎት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | (1) መረጃ | (2) ሕብት መመጨመር | (3) መሠረተልማት | (4) ተቋማት |
| ብርዕና አገዳ | [ ሰሜን ]<br>ጉራጌ<br>ስልጤ | ከፍተኛ | አንዳንድ ሕ/ሥራ ዩኒየኖች ስንዴ መሰብሰብና ማቀነባበር በጥሩ ሁኔታ ጀምረዋል፡፡ ሆኖም በአጠቃላይ መርቱን ለማቆየትና ለጥራት ቁጥጥር አግባብነት ያለው መረዘን አያያዝ ችግር አልፈታም፡፡ የበቆሎና የጤፍ በተመለከተ ድህረ-ምርት አያያዝ በሰው ጉልበት ሥራ ይከናወናል፡፡ ስንዴ በተመለከተ አንዳንድ ጊዜ የማበጠር ሥራ ይሠራል፡፡ የዓለም የምግብ ኘሮግራም እንደ ሙከራ የአካባቢ ብርዕና አገዳ ሰብል መግዛት ጀምሯል፡፡ የሕ/ሥራ ዩኒያኖች ከአባላት ሰብሉን ለማሰባሰብና ለማበጠር ይኸውም የዓለም የምግብ ኘሮግራም የጥራት ደረጃ ለማሟላት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም የማሰባሰቡና የጥራት ቁጥጥሩ ሥራ አሁንም የበሰጸገ አይደለም፡፡ | ◎ | ◎ | △ | ○ |
| ጥራጥሬ | [ ሰሜን፣ ምዕራብ ]<br>ከፋ<br>ቤንች ማጂ<br>ደቡብ ኦሞ | መካከለኛ | በሲዳማ ዞን ከጥራጥሬ ሰብል ጋር የተያያዙ የገበያ ሥፍራዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ የሚሰበሰበው ጥራጥሬ ወደ ጅቡቲና ኬኒያ፣ በናዝሮትና ሞያሌ በኩል ይላካሉ፡፡ ሆኖም ምርትን አሰባስቦ ብዙ መጠን ያለውን በጋራ የመሸጥ ልምድ ያልዳበረ በመሆኑ በግል ደረጃ አርሶአደሮች ትርፍ ምርታቸውን ሸጠው አነስተኛ ገቢ ያለ በቂ መደራደር አቅም ያገኛሉ፡፡ አንዳንድ ዩኒየኖች በዓለም የምግብ ኘሮግራም በተሰጣቸው የማጠቢያ ማሽን እየተጠቀሙ የጥራት ደረጃ ለማሻሻል ጥራጥሬ ማበጠር ጀምረዋል፡፡ የጥራት ቁጥጥር ግንዛቤ ማሣደግ ሥራ መጠናከር አለበት፡፡ | ◎ | ○ | ◎ | ○ |
| አትክልት | [ ማዕከላዊ ]<br>ሲዳማ<br>ጋሞ ጎፋ | የመጀመሪያ ደረጃ | አትክልቶች በአብዛኛው ለግል ፍጆታ የሚማመረቱ ሲሆን ጥቂት ትርፍ ምርቶች በአካባቢ ገበያዎች ይሸጣሉ፡፡ አትክልት በዋናነት የአካባቢ ምርት ሲሆን ለአካባቢ ፍጆታ ይሉላል፡፡ የአካባቢ ገበያ ሥፍራዎች በተፈላጊ መሠረተልማት የተሟሉ አይደሉም፡፡ በጥሩ ሁኔታ ዲዛይንም ያልተደረጉ በመሆናቸው የመሸጥና ግዥ ሂደት ኋላ ቀር ነው፡፡ ቲማቲም በአካባቢ ገበያዎች ከተማ አካባቢ ይሸጣሉ፤ ነገር ግን የምርት መጠኑ ትንሽ ነው፡፡ የሥርጭትና የግብይት ዘዴውን ለማሻሻል የቡድን ሽያጭ ሥርዓት ማጠናከር እና የሽያጭ መጠን ማሣደግ ያስፈልጋል፡፡ ቶሎ የሚበላሽ ቲማትም ለመያዝ የሚያገለግሉ መያዥያዎች አለመስራጨቱ ሊታወቅ ይገባል፡፡ | ◎ | △ | ◎ | ○ |
| | በርበሬ<br>[ ሰሜን ]<br>ስልጤ<br>ጉራጌ<br>አላባ ለዩ ወረዳ | የመጀመሪያ ደረጃ | ደቡብ ክልል ከፍተኛ የበርበሬ አምራች አካባቢ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ በርበሬ ትርጉም ያለው የገቢ ማስገኛ ሰብል ነው፡፡ ከሌሎች ክልሎች ጋር ያለውን ተወዳዳሪነት ለመጠበቅ የጥራት ማሻሻልና ልዩነት የመፍጠር እስትራቴጂ አስፈላጊ ነው፡፡ | ◎ | ◎ | △ | ○ |

| ሰብል | አካባቢ | የገበያ ደረጃ | የትኩረት ጉዳዮች | ፍላጎት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | (1) መረጃ | (2) እሴት መጨመር | (3) መሠረተልማት | (4) ተቋማት |
| ፍራፍሬ | [ ማዕከላዊ ] ጋሞ ጎፋ ሲዳማ ወላይታ ከምባታ ጠምባሮ. ሃዲያ | አርባመንጭ፡ መካከለኛ<br><br>ሌሎች አካባቢ፡ የመጀመሪያ ደረጃ | አብዛኛው ፍራፍሬ በጓሮ ይለማል፡፡ አስተዳደጉን መቆጣጠር፣ ምርት መሰብሰብና ድህረ-ምርት አያያዝ በአግባቡ የሚካሄዱ ሥራዎች አይደሉም፡፡ ከዚህ የተለየ አ/ምንጭ ሲሆን የአካባቢ የገበያ ሥፍራዎች እንደምርት መሰብሰቢያ ስፍራም ያገለግላሉ፡፡ ሆኖም የግብይት ሁኔታዎች በጣም ያልዳበሩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የፍሳሽና የጣሪያ የዝቅተኛው ተፈላጊ መመዘኛዎች ትኩረት ሊያገኙ ይገባል፡፡ የጭነት አያያዝ ከዝቅተኛ ዋጋያ ሁኔታ የተነሣ በጣም ያልተመቻቸ ነው፡፡ ጥራትን ለማሻሻል አግባብነት ባላቸው መያዣዎች በአግባቡ የመያዝ፣ ማሰራጨት እና ጥንቃቄ ባለው ሁኔታ ምርት መሰብሰብ ላይ ግንዛቤ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡<br>በከፍተኛ የምርት ወቅት የማንጎ ዋጋ ዝቅ ማለት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የአካባቢ ገበያ ማልማት አስፈላጊ ነው፡፡ አዲስ የሚቋቋመው የጭማቂ ፋብሪካ በኦሮሚያ ክልል የማንጎ ምርት እንደ ጥሬ ዕቃ ከደቡብ ክልል ከዋና ዋና የምርት አካባቢ ለመግዛት እያቀደ ያለ ሲሆን ለዋጋ መርከስ ችግር መፍትሔ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡ እዚህ ላይ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ጥራት ያለው ምርትን በብዛት የመያዝ ሥርዓት መፍጠርና የፋብሪካውን ፍላጎት ማሟላት ይሆናል፡፡<br>ሙዝ በአርባምንጭ አካባቢ በመስኖ ይለማል፡፡ የአሜሪካ ተርአዶ ድርጅት/አግሪብዝነስና ንግድ ማስፋፋያ ፕሮጀክት ሙዝ ወደ ውጭ ኤክስፖረት ለማድረግ ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል፡፡ ሆኖም ማምረቻ አካባቢ ምርቱን በማስባሰብ ሁኔታና በጉዞ ወቅት ሳይበላሽ ጥራቱን ጠብቆ የማቆየት ሂደት መፍትሔ ሊያገኙ የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡. | ◎ | ◎ | ○ | △ |
| ሥራ ሥር | [ ማዕከላዊ ፣ ደቡብ ] ወላይታ ቤንች ማጂ ደቡብ ኦሞ | የመጀመሪያ ደረጃ | በደቡብ ክልል የሥራሥር ሰብሎች ማልማት በማዕከላዊና ደቡብ አካባቢ የመሬት ከፍታው ዝቅተኛውና መካከለኛ በሆነበት ታዋቂ ነው፡፡ ሆኖም አብዛኛው ሥራሥር ለቤት ፍጆታ ነው የሚለማው፡፡ አምራቾች ምርቱን ከተራራማው አካባቢ ተሰሸክመው በማምጣት በአካባቢ ገበያ ሥፍራ ይሸጣሉ፡፡ በአጠቃላይ የሥራሥር የግብይት ሥርዓት ኋላ ቀር ነው፡፡ ከሳቫ ከጤፍ ጋር ተዋህዶ በመፍጭት ለእንጀራ ምግብነት በጣም ተፈላጊ በመሆኑ ለአነስተኛ አርሶአደሮች እንደ እምቅ አቅም ያለው በመሆን ለሽያጭ የሚመረት ሰብል ሆኗል፡፡ የቀይና ነጭ ሽንኩርት ምርት በምዕራብ አካባቢ ብዙ አይደለም፡፡ ነገር ግን የሽያጭ መጠን ከ50%--70% ይደርሳል፡፡ አብዛኛው ለአካባቢ ፍጆታ የሚውል ቢሆንም የተወሰነው ወደ አድስ አበባ ገበያ በጂማ በኩል ይሄዳል፡፡ | ◎ | ◎ | ○ | △ |
| ሌሎች | ዝንድብል [ ማዕከላዊ ] ወላይታ ከምባታ ጠምባሮ | መካከለኛ | ደቡብ ክልል የዝንጅብል ምርት ከፍተኛ አምራች አካባቢ ነው፡፡ ዝንጅብል ትርጉም ያለው ለገቢ ማስገኛ የሚመረት ሰብል ሲሆን የሚሠራጨውም በእርጥብ ወይም በደረቅ ነው፡፡ ደረቅ ዝንጅብል እምቅ ኃይል ያለው የውጭ ገበያ ምርት ሲሆን የማድረቂያ ሂደት ጥራት ማሻሻል በማሣ ላይ ዋነኛ ሊተኮር የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ | ◎ | ◎ | ○ | △ |

# ምዕራፍ 5 መሪ ዕቅድ

## 5.1 የመሪ ዕቅድ ዝግጅት መርህና ዘዴ

### 5.1.1 የመሪ ዕቅዱ አድማስ

**(1) ቆይታ ጊዜ**

የመሪ ዕቅድ የቆይታ ጊዜ 5 ዓመት ሲሆን ጥናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ከ2013 እስከ 2017 (እ.ኤ.አ) ይቆያል፡፡

**(2) የተመረጡ ሰብሎች**

የተመረጡ ሰብሎች ሀ) ብርዕ አገዳ ሰብል፣ ለ) ጥራጥሬ፣ ሐ) አትክልት፣ መ) ፍራፍሬ፣ ሠ) ሥራሥር፣ እና ረ) ሌሎች (ቅመማቅመም ወዘተ) ቡና በዚህ አልተካተተም፡፡

**(3) የተመረጡ ቦታዎች**

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በአጠቃላይ በመሪ ዕቅዱ የተሸፈነ ሲሆን ቁልፍ የሆኑ የምርት፣ የሥርጭትና ሸማች አካባቢዎች ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷዋል፡፡

**(4) ባለድርሻ አካላት**

በገበያ ሥርዓቱ ተዋኒያን የሆኑ በሙሉ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ አምራቾችን፣ ነጋዴዎችን፣ አቀነባባሪዎችን፣ ሸማቾችንና ሌሎችን ያጠቃልላል፡፡ የመርሀግብሩ አስፈፃሚ አካላት አምራቾች፣ ነጋዴዎች (ሕ/ሥራ ማህበራትን ያጠቃልላል) እና የመንግስት መ/ቤቶች ናቸው፡፡

**(5) የዕቅዱ አካላት**

የግብርና ግብይት ሥርዓት ማጠናከር መሪ ዕቅዱ አካላት፣ ሀ) የግብርና ግብይት ተቋማት/ስርዓት፣ ለ) የግብርና ግብይት መሠረተልማት፣ ሐ) የግብርና ግብይት መረጃ፣ እና መ) ከፍተኛ እሴት የተጨመረበት ምርት ናቸው፡፡

### 5.1.2 የዕቅድ ዝግጅት መሠረታዊ መርህ

የመሪ ዕቅዱ ዝግጅት ዓላማ የክልሉ የግብርና ግብይት ሥርዓት ወቅታዊ ሁኔታዎችን በማሰብ እና የደረሰበት ደረጃ በመስክ ጥናት በመረዳት ነው፡፡ ዕቅዱ የሚያጠቃልለው ተጨባጭና ተግባራዊ የሚሆን መርሃግብርና በ10 የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም የተገኙ ውጤቶችና ልምዶችን ነው፡፡ መሪ ዕቅዱ ሊሳካ የሚችልና ዘላቂነት ያለው የመንግስት መ/ቤቶችን ብቻ ሳይሆን ባለድርሻ አካላት በማሣ ላይና በገበያ ስፍራዎች የሚንቀሳቀሱትን እንዲሣተፉ የሚያበረታታ መሆን ነው፡፡

ለገበያና ለስርጭት ሥርዓት መሻሻል የዕቅዱ መሠረታዊ መርሆች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) መሪ ዕቅዱ ከአርሶ አደር እስከ ሸማቾች ድረስ ያሉትን ሰፊ የገበያ ተዋንያንን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ አስተዋጽኦ ማበርከት አለበት፣
2) መሪ ዕቅዱ በግብይት ሥርዓት ውጤታማነት ላይ በማተኮር በመካከሉ ያሉ የስርጭት ወጭዎችን የሚቀንስና በትርፍ ጭማሪ ላይ መሥራት አለበት፡፡

### 5.1.3 የዕቅድ ዝግጅት ሂደት

የመሪ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት በምስል 5-1 ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡

በመስክ ጥናቱ በመመስረት የሰብል ዓይነቶች፣ የተጠቃሚዎች ዓይነት እና በክልሉ ያሉ ዞኖች ባህሪይ መሠረት የልማት ፕሮግራሙ (እስትራቴጂና መርሐግብር) በየፊናው ያሉ ጉዳዮችና ፍላጎቶችን መሠረት በማድረግ ተከፋፍሎ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጊዜያዊነት የተዘጋጀው መሪ ዕቅድ (መርሐግብር) በአንድ ዓመት ተኩል ጊዜ በሚቆዩ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም እንዲረጋገጥ ተደርጓል፡፡ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶቹ ውጤት ለዕቅድ ዝግጅት ሂደት መጋቢ በመሆን የጊዜያዊ መሪ ዕቅዱን እንደገና እንዲታሰብና እንዲከለስ ተደርጎ የመሪ ዕቅዱ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡




**ምስል 5-1 የመሪ ዕቅዱ ዝግጅት ሂደት**

### 5.1.4 የሙከራ ፕሮጀክቶች (የማረጋገጫ ጥናት)

#### (1) የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ዓላማዎች

የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ዓላማ ከዚህ በታች በተቀመጡ በ4 ነጥቦች ተጠቃሏል፡፡

- (ሀ) በጊዜያዊ መሪ ዕቅድ ውስጥ የተቀመጡ እስትራቴጂዎችና መርሐግብር ብቃት ማረጋገጥ
- (ለ) የታቀዱት መርሃ-ግብሮች ተጨባጭነትና ውጤታማነት ማረጋገጥ
- (ሐ) የባለድርሻ አካላትን አቅም በማሣደግ የመሪ ዕቅዱን ዘላቂነት ማረጋገጥ
- (መ) ለአቻ ባለሙያዎች ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሂደት በሥራ ቦታ ሥልጠና መስጠት ናቸው፡፡

### (2) የሙከራ ፕሮጀክቶችን የማዘጋጀት ሂደት

የጃይካ ጥናት ቡድን ዝርዝር የፕሮጀክቶችን ዕቅድ ከባለድርሻ አካላትና አቻ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ጊዜያዊ እስትራቴጂ በግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ አዘጋጅቷል። የፕሮጀክቶቹ አካባቢ ወቅታዊ ሁኔታ፣ የተጠቃሚዎች ፍቃደኝነት/ቁርጠኝነት እንዲሁም የአስፈፃሚዎች እና የአካባቢው አስተዳደር ሁኔታዎች ተዳሷል። የፕሮጀክቶቹ ይዘት በአለው ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ተስተካክሎ ዝርዝር የድረጊት መርሐግብርና የአፈጻጸም ጊዜ ሠሌዳ ተቀምጧል።

<u>የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር የሚያስፈልጉ ነገሮች</u>

- በአንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ጉልህ ውጤቶች መታየት አለባቸው
- ለወደፊት ፈፃሚ አካላት መኖር ወይንም ለመለየት/ለመምረጥ መቻል
- በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች በስፋት ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻል እና ሞዴል መሆን የሚችል፣
- ራሱን የሚችል ልማት ሆኖ የቢዝነስ ሞዴል መሆን ይጠበቃል

በቅድሚያ 20 የፕሮጀክት ሃሣቦች ቀርበው ከዚያም እንዲቀናጁ ከተደረገ በኋላ ቁጥራቸው እንዲቀንስ ተደርጓል። ከዚያም የሰብል ዓይነትና ቦታን ማመጣጠን፤ የሰው ኃይልና የበጀት እጥረት ከግምት ውስጥ በማስገባት 10 የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ተመረጡ።

ከዚህ በተጨማሪ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች የታቀደውን የልማት ዕቅድ እንዲያንፀባርቁ ዲዛይን ተደርገዋል። ፕሮጀክቶቹ ከተመረጡ ሰብሎች አንፃር እርስበርስ ተደጋጋፊነት እንዲኖርአቸው ተደርጎ ጥረቶችን በማቀናጀት የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት፣ እሴት መጨመር፣ የገበያ መሠረተልማትና የመንግስት መ/ቤቶችን አቅም ለማሳደግና ለማሻሻል የታቀደ ነው። የፕሮጀክት ስም፣ የተመረጡ ሰብሎች፣ የተመረጡ ቦታዎችና የልማት እስትራቴጂዎች በሠንረዥ 5-1 ተመልክቷል።

### (3) የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ውጤት

ከሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ይዘት፣ የተገኘ ውጤት እና ተሞክሮ ተቀጽላዎች (English Report, Volume 2) ።

## ሠንጠረዥ 5-1 የጊዜያዊ መሪ ዕቅዱን ለማረጋገጥ ተግባራዊ የሆኑ 10 የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች

| መሠረታዊ እስትራቴጂዎች | እስትራቴጂዎች | የተመረጡ ሰብሎች | | | | | | የተመረጡ ቦታዎች | የፕሮጀክቱ ስም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብርዕና አገዳ | ጥራጥሬ | አትክልት | ፍራፍሬ | ሥራሥር | ሌሎች | | | |
| የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ለማጠናከር | የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ለማጠናከር | | ቦሎቄ | | | | ዝንጅብል | 5ዞኖች፣ 1 ልዩ ወረዳ | 01 | የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከር |
| ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይትን በማስተዋወቅ ትርፍ ማሳደግ | ድህረ-ምርት አያያዝና ጥራት ማሻሻል | ስንዴ በቆሎ | ባቄላ አተር | | | | | 9 ዩኒየኖች በ6 ዞኖችና በ1 ልዩ ወረዳ | 02 | የሕ/ሥራ ዩኒያኖች በብርዕና አገዳ ሰብል እና ጥራጥሬ የጥራት ቁጥጥር የአቅም ማሣደግ (ከዓለም የምግብ ፕሮግራም/ግዢ ለዕድገት ጋር መተባበር) |
| | በምርትና ድህረ-ምርት አያያዝ | | | | አቮካዶ ማንጐ | | | ሲዳማ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ወላይታ | 03 | በማንጎና አቮካዶ ምርት አሰባሰብና አያያዝ ማሻሻል |
| | ማቀነባበርና ግብይት | | | | | ካሳቫ | | ወላይታ፣ ጋሙጎፋ | 04 | የደረቅ ካሳቫ ጥራትና ገበያ ልማት ማሻሻያ ፕሮጀክት |
| | ጥራት ማሻሻልና ግብይት | | | | | | ዝንጅብል | ከምባታ ጠምባሮ፣ ወላይታ | 05 | ንፁህ ደረቅ ዝንጅብል ማምረትና ከገዢዎች ትስስር መፍጠር ( ከዓለም አቀፍ ገንዘብ ለግብርና ልማት/ አሚፕ ጋር በመተባበር) |
| የገበያ እንቅስቃሴዎች ለማጠናከር የገበያ መሠረተልማት ማጠናከር | የገበያ ቦታ | | ቦሎቄ | | | | | ሲዳማ | 06 | ቦሎቄ በሚያመርቱ አካባቢ የአካባቢ ገበያ ማሻሻል |
| | የገበያ ቦታ | | | | | | ዝንጅብል | ከምባታ ጠምባሮ | 07 | ዝንጅብል በሚያመርቱ አካባቢ ገበያ ማሻሻል |
| | መጋዘን | በቆሎ ስንዴ | ቦሎቄ | | | | | ከምባታ ጠምባሮ | 08 | ደረጃውን የጠበቀ መጋዘን ግንባታና አስተዳደር ማሳደግ |
| በተቋማዊ ሥርዓት የግብርና ግብይት ማግኘትና ማስተካከል | ደረጃውን የጠበቀ ጥራት | ስንዴ | | | | | | ሲዳማ | 09 | የኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ከገበያ ማዕከሉ ወጪ የተገዛ ስንዴ ማነፃፀሪያ ጥናት |
| | የግብይት ቢሮና የግብርና ቢሮ ማጠናከር | | | | | | | | 10 | በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ወቅት ቁጥጥርና ግምገማ ማድረግ ስለገበያ ማሻሻል ግንዛቤና አቅም ለመንግስት ሠራተኞች እንዲኖራቸው ማድረግ |

## 5.2 መሪ ዕቅድ

### 5.2.1 የልማት ግብ

በደቡብ ክልል ምንም እንኳን ብዙ ዓይነት ሰብሎችን ለማምረት ቢቻልም አብዛኛዎቹ የሚመረቱት ለቤት ውስጥ ፍጆታ ነው፡፡ ቡና ብቻ እንደ ገቢ ማስገኛ ሰብል ከሚመረት በስተቀር ሌሎች ሰብሎች ከቤት ፍጆታ የሚተርፍ ከሆነ በአካባቢው ገበያ የሚሸጡት አነስተኛ ገቢ ለማግኘት ነው፡፡ በደቡብ ክልል የግብርና ምርት በአካባቢ ገበያዎች በአብዛኛው የተወሰነ ነው፤ ምክንያቱም በአካባቢው ባለው ከፍተኛ የሕዝብ ብዛትና የመጋዘን እጥረት እንዲሁም በድህረምርትና በመጋዘን ማከማቻና እህል አጠባበቅ የክህሎት ውስንነት ስለአለ ነው፡፡ ቢሆንም አንዳንድ አርሶአደሮች የግብርና አመራራቸውን ከባህላዊ ሰብሎች ወደ ትርፋማ ሰብሎች ኢኮኖሚያቸውን ለማሻሻል ሲቀይሩ ይታያሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራት በብድር አገልግሎትና በቡድን የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ግዢ ላይ ተሠማርተዋል፡፡ አንዳንድ ያደጉ ሕ/ሥራ ማህበራት በተለይም የሰብል ሕ/ሥራ ማህበራት የቡድን ሽያጭና የማቀነባበር ቢዝነስ ሥራ ውስጡ በመግባት ትርፋማ ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ በሃዲያ ዞን እንደ ሌቻ ሃዲያ የግብርና ሕ/ሥራ ዩኒያንን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ዝንባሌ በመነሳት መሪ ዕቅዱ ዋንኛ ፋይዳ *የግብርና ግብይትን በማሻሻል የክልላዊ ኢኮኖሚ ማነሳሳት* ነው፡፡ ግቡንም እውን ለማድረግ እንዲቻል ፍትሃዊ የገበያ መድረክ እና ብቃት ያለው የገበያ አሠራር አርሶአደሮችንና ነጋዴዎችን በንግድ ሥራ እንዲሣተፉ የሚያበረታታ በክልል ውስጥ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሠረት የመሪ ዕቅዱ የልማት ግብ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

> **"ፍትሃዊና ተወዳዳሪ ገበያ በማስፋፋት ተሣትፎን ማጠናከር፣ የግብይትን ብቃትና ቅልጥፍና በማሻሻል ገቢን ማሳደግ"**

### 5.2.2 የወቅታዊ ሁኔታ እይታ

(1) በኢትዮጵያ የግብርና ግብይት ሥርዓት እንደሌሎቹ አፍሪካ ሀገራት ማደግና መበልፀግ አለበት፡፡ በኢትዮጵያ በገጠር አካባቢ የግብርና ምርት መሰብሰቢያ ሥፍራዎችና ቁሳቁሶች እዲሁም በከተሞች አካባቢ የሥርጭት ሥፍራዎችና ዕቃዎች (የጅምላ ንግድ ሥፍራዎች) ያልዳበሩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሸማቾች የጥራት ፍላጐት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ አርሶአደሮች የምርት ጥራት ለማሻሻል ለአፈሰሱት ጉልበት ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ እምብዛም አያገኙም፡፡ የአካባቢው ነጋዴዎች ከሕ/ሰቡ ለሚገዙትና ለሚያከማቹት ምርት ያልሆነ ገጽታ በመስጠት ያሳስታሉ፡፡ እንዲሁም ዋጋ ዝቅ ያደርጋሉ፡፡ በአርሶአደሮችና ነጋዴዎች መካከል መተማመን የለም፡፡ በግብርና ግብይት ሥርዓት ጠቃሚ መሻሻል ሊመጣ የሚችለው የሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉና ለጋራ ዓላማ እንዲተባበሩ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡ ስለሆነም የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ከማቋቋም ሂደት ጋር የተያያዙ ችግሮች የግብርና ምርት የጥራትና የገበያ መሠረተልማት ማሻሻል፣ እና የመንግስት መ/ቤቶች አቅም ግንባታ ጎን ለጎንና በተቀናጀ መልክ መሠራት አለበት፡፡

(2) የኢትዮጵያ መንግስት የሕ/ሥራ ማህበራት መቋቋምና እንቅስቃሴ ሲደግፍ ቆይቷል፡፡ ብዙ የሕ/ሥራ ማህበራት የግብርና ግብዓት (ማዳበሪያ ምርጥ ዘር ወዘተ) ሥርጭት ላይ ሲሣተፉ የነበሩ ሲሆን በግብርና ግብይት ላይ ብዙ ልምድ የላቸውም፡፡ ከዚህ ሌላ በቡድን ሥራ ተሳትፈው በጋራ ጥረት የምርቶቻቸውን ጥራት በማሻሻልና ብዛት ያለው ምርት ይዘው ወደ ሽያጭ በመግባት የተሻለ ዋጋ ለማግኘት የሚጥሩት ጥቂት አርሶአደሮች ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ተግባራዊ ልምድ የላቸውም፡፡

(3) ለአካባቢ የመንግስት አካላት የሚመደበው በጀት በጣም ትንሽ በመሆኑ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ በጀት ለመመደብ ይቸገራሉ። ስለሆነም በመንግስት የተዘጋጀውና ሊተገበር የሚገባው የግብርና ልማት ፕሮግራምና የድህነት ቅነሣ አስትራቴጂ በሚሰጠው የገንዘብ አነስተኛ ከመሆን የተነሣ ዝርዝር መርሃ ግብር ወጥቶ ሊተገበር አልተቻለም። መንግስት የግብርና ግብይት ሥርዓት ለማሻሻል ለአፈፃፀም የሚረዳ የድጐማ ፕሮግራም ደንብ የለውም።

(4) አብዛኛው የአስተዳደር ኃላፊዎች የፕሮጀክት ዕቅድና የማስፈፀም ችሎታና ልምዱ የላቸውም።

(5) አብዛኛዎቹ አርሶአደሮች ከራሳቸው ፍጆታ የሚተርፈውን መሸጥ እንጂ የገበያ ፍላጐት ለማሳካት የማምረት ዕቅድ የላቸውም።

(6) አብዛኛው ሽማች በጥራት ላይ ሳይሆን በዋጋ ላይ ያተኩራል።

(7) በርካታ እርዳታ ሰጪዎች ብዙ የተለያዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚደግፉ ቢሆንም በዚህች ሀገር ለሚታዩ ችግሮች ማለትም ለተስማሚ ቴክኖሎጂ ልማትና ሥርጭት ትኩረት አልሰጡም።

(8) ብዙዎቹ ፕሮጀክቶች በተወሰኑ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ባላቸው በተመረጡ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ያተኩራሉ። ሆኖም እርስበርስ ያላቸው ትብብርና ቅንጅት በጣም አነስተኛ ነው።

(9) ፍትሃዊና ብቃት ያለውን የግብርና ግብይት ሥርዓት ለማቋቋም በግብርና ምርት ዝውውር ዋና ተዋናይ ለሆኑ የግል ነጋዴዎች የተሰጠው ትኩረት በጣም አነስተኛ ነው።

(10) የሜትሮሎጂ ደረጃ ሥርዓት መቀበልና ተግባራዊ ማድረግ የግብርና ግብይት ሥርዓት ለማስፋፋት አንዱና ዋንኛ ጉዳይ ነው። ሆኖም በዚህ ረገድ የተደረገው ጥረት በጣም አናሳ ነው።

(11) የግብርና ምርት እስታትስቲካዊ መረጃ ለፓሊሲ ዝግጅት ወሳኝ የሆነው በተለያዩ የመንግስት ኤጀንሲዎች ማዕከላዊ የእስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጨምሮ ይሰበሰባል። ሆኖም ለግብርና መረጃ የተሰጠው ግምት አነስተኛ ነው። ይህም የሆነበት በቂ እውቀት በመረጃ ማሰባሰብና ማቀነባበር ስለሌለ ነው።

### 5.2.3 የልማት እስትራቴጂ ማዘጋጃ መሪ ሀሣብ

ከዚህ በላይ በተገለፁት የወቅታዊ ሁኔታዎች እይታና የሙከራ ፕሮጀክቶችን በመተግበር የተገኙ ተሞክሮዎችን በማንፀባረቅ የልማት ዕቅድ ዝግጅት እንደሚከተለው ተቀምጧል።

(1) የግብርና ግብይት ሥርዓት ማሻሻል አጠቃላይ ሥርዓቱን ለማነቃቃት የሚቻለውን ያህል የብዙ ባለድርሻ አካላትን መሳተፍና ትብብር ይጠይቃል። በሁሉ አቀፍ አቀራረብ ሁሉንም የልማት ጥረቶች በማቀናጀት የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት፣ እሴት መጨመር፣ የገበያ መሠረተልማትና ተጓዳኝ ዕቁሳቁሶችን እንዲሁም የመንግስት መ/ቤቶችን አቅም ማሳደግና ማሻሻል የተጣለውን ግብ ለመድረስ ይረዳል።

(2) እንደ መሠረታዊ እስትራቴጂ 4 ዋና ዋና ክፍሎች ተወስነዋል እነዚህም፡ (1) የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከር፣ (2) ከፍተኛ የእሴት ጭማሪ በማድረግ ትርፍ ጭማሪ ማስገኘት፣ (3) እሴት ጭማሪ ግብይትን በማስተዋወቅ ገቢን ማሳደግ፤ እና (4) የግብርና ግብይት ተቋማዊ አቅም ማሳደግ።

(3) የልማት እስትራቴጂው ተጨባጭና በክልሉ የሰው ኃይልና በጀት ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል።

(4) ተጨባጭ የሆኑ ፕሮጀክቶችንና የአፈፃፀም መርሐግብር የልማት አጋሮችን እንደ ግብርና ዕድገት ፕሮግራም ትብብር ታሳቢ በማድረግ ማዘጋጀት፡፡

(5) የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ በማድረግ የተገኙ ተሞክሮዎችን መጠቀም

## 5.2.4 የልማት አስትራቴጂ

ምስል 5-2 የመሪ ዕቅዱ ፅንሰሀሣብ በግብርና የገበያ ልማት እና 4ቱ መሠረታዊ እስትራቴጂዎች እንዴት በሁሉ አቀፍ በሆነ መልኩ በጋራ መሥራት እንደሚችሉ ያሳያል፡፡

መሪ ዕቅዱ አስፈላጊ የሆኑ የመንግስት አሠራሮችን እንደ ውጭያዊ አካል ሆኖ ተወዳዳሪ ገበያ ለመፍጠር፣ እንደ ውስጣዊ አካል ብቃት ያለው የቢዝነስ እንስቅስቃሴዎች ትርፍ ማሳደግ አድርጓል፡፡ የውጪያዊና ውስጣዊ አካላት በጋራ ሲሠሩ የክልሉ ኢኮኖሚ ይነቃቃል፤ እና የምግብ ዋስትና ጥያቄም ይፈታል፡፡ ሁለቱ ውጫዊና ውስጣዊ አካላት መካከል የመሠረተልማት እስትራቴጂ ተቀምጧል፡፡ ምክንያቱም እንደ መንግስታዊ መሠረተ ልማትና እንደ ትርፍ የሚያስገኝ ሆኖ ስለሚያገለግል ነው፡፡




ምስል 5-2 የመሪ ዕቅዱ ፅንሰ ሀሳባዊ ሥዕላዊ መግለጫ

የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶችን ውጤቶች ያካተተ 4 መሠረታዊ እስትራቴጂዎችና ንዑሳን እስትራቴጂዎች ይዘት በሚቀጥለው ክፍል ተብራርቷል፡፡

## 5.2.5 መሠረታዊ እስትራቴጂ 1: የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከር

የግብርና ግብይት መረጃ በሀገር አቀፍ ደረጃና በክልል ብዙ ድርጅቶች እንደ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ አስተዳደር፣ የዓለም የምግብ ፕሮግራም፣ የኢትዮጵያ የእህል ገበያ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ ክልላዊ መንግስታትና ሌሎችም የገበያ ዋጋ መረጃ ይሰበስባሉ እንዲሁም ያሰራጫሉ፡፡ ሆኖም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ

በስተቀር (አጭር ጽሑፍና ድምፅ መልዕክት አገልግሎት በ2010 (እ.ኤ.አ) ከጀመረው) ሌላ የትክክለኛ ጊዜ ዋጋ መረጃ ለአርሶአደሮችና ለሌሎችም የገበያ ተዋንያን የሚያሠራጭ ድርጅት የለም፡፡

የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሥርዓት ለማቋቋምና የክትትል ሥርዓት ለማደራጀት ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ሆኖም ወቅታዊው የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት አሠራር (የመረጃ የማሰባሰብን ሥርዓት) የተቀናጀ/የተደራጀ አይደለም፣ እንዲሁም ግልፅ የሆነና የጋራ ግንዛቤ ያለው አይደለም፡፡ ለምን የዋጋ መረጃ እንደሚሰበሰብ የሚታወቅ አይደለም፡፡ እንደሚታወቀው አሁን ያለው የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት በጣም ደካማ ነው፡፡ በመሠረቱ የመንግስት የገበያ መረጃ አገልግሎት ዓላማው ጠቃሚ የሆኑ የገበያ መረጃ ለአርሶአደሮችና ለሌሎች የገበያ ተዋንያን ማቅረብ ነው፡፡ ነገር ግን እንደሌሎች በሀገሪቱ ውስጥ የዋጋ መረጃ እንደሚሰበሰቡ አካላት ምንም መረጃ ለአርሶአደሮች አይሰራጭም፡፡ ለሌሎች ተመሳሳይ የመንግስት መ/ቤቶችም የመረጃ ማቀበል አልተለመደም፡፡ ለዚህ ደካማ ሁኔታ የዳረገው የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ተመሳሳይና ወጥነት በአለው መልኩ መረጃ ለማሰባሰብና ለማሰራጨት የተዘጋጀ ሰነድ መመሪያ ያለመኖሩ ነው፡፡

### እስትራቴጂ 1-1: የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት በአጭር ጽሑፍ መልዕክት እና ማስታወቂያ ቦርድ የሚካሄደው ወደ ሌሎች ጠቃሚ ሰብሎች ደረጃ በደረጃ ማስፋፋት

ከላይ በተገለፀው ሁኔታ መሠረት በግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት እስትራቴጂ እንደሚከተለው ነው፡፡

- ተጠቃሚን ያተኮረ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት፡ መሠረታዊ የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ተልዕኮ ጠቃሚ የገበያ መረጃ ለተጠቃሚዎች (አርሶአደሮችና የገበያ ተዋንያን) ማቅረብ
- መሠረታዊ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎቶችን ማጠናከር፡ ይህንን ለመፈፀም የዋጋ መረጃ መሰብሰብ ማሠራጨት ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ የመረጃ ቋት በስርዓትና በማያቋርጥ ሁኔታ ማደራጀት
- የሸቀጥ/ምርት ዋጋ ልማት፡ የሸቀጥ/ምርት ዋጋ በግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ደረጃ በደረጃ በጠቃሚ የንግድ ሸቀጦች የዋጋ መረጃ ለሚፈልጉ ማዘጋጀት፡፡

የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 ከላይ የተገለፁትን መሠረታዊ አገልግሎቶች በአስቸጋሪ የገጠር ግንኙነት መካከል በ14 የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶችና በክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በዝንጅብልና በቦሎቄ ሰብሎች እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ማጥናት ጀምሮ ነበር፡፡ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ከአጭር የጽሑፍ መልዕክትና ማስታወቂያ ቦርድ (ሞባይል አጭር የጽሑፍ መልዕክት አገልግሎት ብቸኛው በ14 ወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች መካከል፤ ወቅትን የጠበቀ መረጃ ለሌሎች ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶችና ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ማሰራጭት፣ እና የዋጋ ማስታወቂያ ቦርድ በመጠቀም በገበያዎች የተተከለውን የትክክለኛ ጊዜና ዋጋ ለተጠቃሚዎች ለማሠራጨት) ዲዛይን ተደርጐ እንደ ሙከራ እንዲሠራ ተደርጓል፡፡

የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 አፈፃፀም ግልፅ እንዳደረገው አሁን ያለው የሞባይል መስመር (አጭር የጽሑፍ መልዕክት አገልግሎት አስተማማኝ አይደለም፤ ምክንያቱም የኔተወርክ ለመላክና/ለመቀበል አዳጋች ስለሆነ ነው፡፡ እንዲሁም የተላኩ መልእክቶች የሚጠፉበትም ጊዜ አለ፡፡ ከዚህ ሌላ የኢንተርኔት አገልግሎት ወይም የሞባይል መረጃ ግንኙነት አገልግሎት በቀጣይ 5 ዓመታት በብዙ ወረዳዎች ይኖራል የሚል ግምት የለም፡፡

ስለዚህ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የአጭር የጽሑፍ መልዕክት አገልግሎት እና ማስታወቂያ ቦርድ በመጠቀም ወደ ሌሎች የተመረጡ ሰብሎች ደረጃ በደረጃ ማስፋፋት የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ልማት የቀጣይ 5 ዓመት ዋና እስትራቴጂ ሆኖ ተቀምጧል፡፡

የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ቀጣይ 6 ሰብሎችን መርጧል፡፡ ለዚሁ ተግባር በትክክል የተመረጡ ወረዳዎች 82 ሲሆኑ በመካከሉ መደራረብ አለ፡፡ 13 በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 ወረዳዎች በ82 የተመረጡ ወረዳዎች ውስጥ ተካተዋል፡፡ ስለሆነም የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሥራ ለመጀመር የመረጃ ሥርዓት መዘርጋት (ኮምፒውተር/ማስተወቂያ ቦርድ ማቆም፣ የሥራ ዝርዝርና ሥልጠና መስጠት) የሚኖርበት በ69 ወረዳዎች ይሆናል፡፡

**ሠንጠረዥ 5-2 ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማስፋፊያ የተመረጡ ሰብሎችና ዞኖች/ወረዳዎች**

| የተመረ ጠ ሰብል | ዞን/ልዩ ወረዳ | የተመረጠ ወረዳ ብዛት | የሙከራ ፕሮክ. 01 ወረዳዎች | አዲስ ወረዳዎች |
|---|---|---|---|---|
| ማንጎ | ጋሞ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ደቡብ አሞ | 7 | 4 | 3 |
| በርበሬ | አላባ ልዩ ወረዳ፣ ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ከፋ፣ሲዳማ | 7 | 1 | 6 |
| ሰሊጥ | ደቡብ ኦሞ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ባስኬቶ ልዩ ወረዳ፣ ቤንች ማጂ | 8 | 0 | 8 |
| አቮካዶ | ሲዳማ፣ ጌዲኦ፣ ወላይታ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ቤንች ማጂ፣ ሸካ | 20 | 5 | 15 |
| ስንዴ | ሲዳማ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ዳውሮ፣ ጌዲኦ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ከፋ፣ ስልጤ | 18 | 0 | 18 |
| በቆሎ | ሲዳማ፣ አላባ ሊዩ ወረዳ፣ ሃዲያ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ወላይታ፣ ዳውሮ፣ ኮንታ ልዩ ወረዳ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ብንች ማጂ፣ ሰገን አካባቢ፣ ግዲኦ | 42 | 8 | 34 |
| ድምር | | 102 | 18 | 84 |

ማስታወሻ: አንዳንድ ወረዳዎች ብዙ ሰብሎች ላይ የሚሠሩ/የሚሳተፉ አሉ፡፡ ለእያንዳዱ የተመረጠ ሰብል የተመረጡ የወረዳዎች ዝርዝር በፕሮጀክት ዕቅድ (ቁጥር 1) ምዕራፍ 7 ተመልክቷል፡፡

በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 በተገኘው ተሞክሮ መሠረት የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የጽሑፍ መልዕክትና ማስተወቂያ ቦርድ በመጠቀም በ6 በተመረጡ ሰብሎች ደረጃ በደረጃ ማስፋፋት በሚከተሉት መርህ መሠረት ታቅዷል፡፡

1/ ደረጃ በደረጃ ማስፋፋት በጥቂት የተመረጡ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ይጀምራል፡፡ 69 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ዝርዝር ሥራና ዕቃዎችን መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ከ6ቱ ሰብሎች መካከል በቆሎ ብዙ የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች (34) የሚሸፈን ሲሆን እና ከ34 ወረዳዎች መካከል በ15 ሌሎች የተመረጡ ሰብሎች ይካሄድባቸዋል፡፡ ስለሆነም በቀጣዩ ሠንጠረዥ እንደተመለከተው ጥቂት ሰብሎች (ማንጎ፣ በርበሬ፣ ወዘተ) ለመሸፈን በተመረጡ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የመረጃ አሰባበስብ ሥርዓት በመዘርጋት ሥራው ይጀምርና ወደ በቆሎ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ቀስ በቀስ እያደገ ይሄዳል፡፡

### ሠንጠረዥ 5-3 በ6 ሰብሎች ደረጃ በደረጃ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሚስፋፋት አካሄድ

| የተመረጠ ሰብል | አድስ ወረዳ | ማናጎ | በርበሬ | ሰሊጥ | አቮካዶ | ስንዴ | በቆሎ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ማንጎ | 3 | 3 | | | | | |
| በርበሬ | 6 | | 6 | | | | |
| ሰሊጥ | 8 | | | 8 | | | |
| አቮካዶ | 15 | | | | 15 | | |
| ስንዴ | 18 | | | | | 18 | |
| በቆሎ | 34 | 1 | 5 | 2 | 3 | 4 | 19 |
| ድምር | 84 | 84 | | | | | |

ለማንጎን በ3 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ሥርዓቱን መዘርጋት = የበቆሎን 1 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች መጨረስ

ለበርበሬ በ6 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ሥርዓቱን መዘርጋት = የበቆሎን 5 ሌሎች ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች መጨረስ

2/ ደረጃ በደረጃ ማስፋፋት ሥራ ሲጠናቀቅ ዝንጅብልና በሎቄን ጨምሮ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሥርዓት የ8 ሰብሎች በ83 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ይቋቋማል፡፡

እነዚህ 83 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ከ1 እስከ 3 ሰብሎች ላይ ይሠራሉ፡፡ 5 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች (አላባ ልዩ ወረዳ፣ ሃዳሮ ጡንጦ፣ ቦሎሶ ቦምቤ፣ ቦሎሶ ሶሬ እና ዳሞት ጋሌ) በ3 ሰብሎች ይሠራሉ፣ 23 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች በ2 ሰብሎች እና 55 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች በ1 ሰብል ይሠራሉ፡፡

የ83 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች በተመለከተ በሣምንት 1 አጭር የጽሑፍ መልዕክት ተቀባይ ለሆኑ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ለእያንዳንዱ ሰብል ይልካሉ፡፡ ዳሞት ጋሌ ወረዳ በሣምንት 68 አጭር የጽሑፍ መልዕክት ይቀበላል፡፡ ከ83 ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች መካከል ከፍተኛው አጭር የጽሑፍ መልዕክት የሚቀበል ወረዳ ነው፡፡ የበቆሎ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ብዙ አጭር የጽሑፍ መልዕክት ይቀበላሉ፡፡ 8 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ወደ 60 አጭር የጽሑፍ መልዕክት በሣምንት ይቀበላሉ፤ 14 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ወደ 50 አጭር የጽሑፍ መልዕክት በሣምንት ይቀበላሉ፡፡

የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 በታየው መሠረት ከ50 አጭር የጽሑፍ መልዕክቶች በላይ በሣምንት ያለችግር ማስተናገድ ከወረዳ ባለሙያዎች መጠን ከአቅም በላይ ስለሚሆን አዳጋች ነው፡፡ ስለዚህ ለበቆሎና አቮካዶ መረጃ በማሰባሰብ በአጭር የጽሑፍ መልዕክት የሚልኩት የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ቁጥር ወደ ግማሽ ዝቅ ማለት አለበት፡፡ በዚህም መሠረት መረጃ የሚቀበሉ ወረዳዎች በግማሽ ለዋጋ መለኪያ/ማውጫ ባለው ጠቀሜታ አኳያ ዝቅ ይደረጋል፡፡

3/ በአንድ ወቅት የዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ እንደ መረጃ ማጠናቀሪያና ማስተላለፊያ ነጥብ ሆኖ እንዲያገለግልና በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች መረጃ የማጠናቀር ሥራ ለመቀነስ ታስቦ ነበር፡፡ ሆኖም የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 አፈፃፀም በተገኘው ተሞክሮ መሠረት በደቡብ ክልል በአለው ተጨባጭ ሁኔታ ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሥራ የተመደበ ባለሙያው በሌለበት ወይም በሌላ ሥራ በተጠመደበት ወቅት ተክቶ የሚሠራ ሠራተኛ ተክቶ ሥራው ሳይቋረጥ ማስኬድ እንደማይቻል መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የመረጃ ማስተላለፍ ሥራ ሙሉ በሙሉ ለዞን መስጠት

በጣም ስጋት ላይ የሚጥልና አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ዞን ላይ የማስተላለፊያ ሥራ ቢቆም ወደ ወረዳ የሚፈስ መረጃ ሁሉ ሊቋረጥ ይችላል፡፡

4/ እስከዚያ ድረስ በእስትራቴጂ 1-2 ከዚህ በታች እንደተገለፀው የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ላይ ሥራ ግፊት በማድረግ አጭር የጽሑፍ መልዕክት ወደ ዞኖች እንዲላኩ እና የዕቃዎችን /ኮምፒውተርና ሞባይል/ በዞን መምሪያ ዕቅድ ውስጥ ማካተት፡፡

5/ በተመረጡ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የመረጃ አገልግሎት ሥርዓት ከመዘርጋት ባሻገር የክልሉን ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በሰው ኃይልና በበጀት አቅም ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎትን በሌሎች ሰብሎች ለማስፋፋት ቢያንስ ቢያንስ አንድ ባለሙያ የዕለት ዕለት የመረጃ አያያዝና መረጃን ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች የማሠራጨት ሥራ የሚችል መኖር አስፈላጊ ነው፡፡

6/ የተመረጡ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የሥራ ማስኬጃ እንደ አላቂ ዕቃዎች ወጪ (ወረቀት፣ የፕሪንተር ቀለም ወዘተ) እና የአውቶቡስ/ነዳጅ ወደ ገበያ ቦታዎች መመላለሻ በክልሉ ቢሮ ሊሸፈን ይገባል፡፡

7/ የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ባለሙያዎች የኮምፒውተር ዕውቀት በቂ አይደለም፣ እንደ ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 ሁሉ የኮምፒውተር ሥልጠና ለወረዳ ባለሙያዎች በክልሉ ቢሮ ሊሰጥ ይገባል፡፡

የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሥራ እንቅስቃሴ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን መግለጽ ባያስፈልግም ጠንካራ መሪነት አስፈላጊነትና በጀት መድቦ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ለወረዳ ጽ/ቤቶች መስጠት ተገቢ ነው፡፡

### እስትራቴጂ 1-2: የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ መጠቀም

ለሚመለከታቸው አካላት የተሰበሰበ የዋጋ መረጃ ወቅቱን ጠበቆ ማስራጨት እንዳለባቸው ግንኙነት ባለቸው ጽ/ቤቶች ላይ ግፊት ማድረግ

በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የተሰበሰበ መረጃ ለሌሎች ጽ/ቤቶች ለማሠራጨት የተሰጠ መመሪያ አልነበረም፡፡ ከዚህ የተነሣ ጥቂት ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ብቻ የተሰበሰበ መረጃ በየወቅቱ ለሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች አሠራጭተዋል፡፡ የተሠራጨውን መረጃ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ለእያንዳንዱ ወረዳ መስጠት አለበት፡፡

- ✓ እያንዳንዱ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት አጭር የጽሑፍ መልዕክት ለዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ መላክ አለበት፣
- ✓ እያንዳንዱ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የተሰበሰበውን መረጃ በየወሩ በማጠቃለል ለሚመለከታቸው ወረዳ ጽ/ቤቶች ማቅረብ አለበት፣
- ✓ እያንዳንዱ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ የተቀበለውን መረጃ በየወሩ በማጠቃለል ለሚመለከታቸው ዞን መመሪያዎች ማቅረብ አለበት፣
- ✓ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የተቀበለውን መረጃ በየወሩ በማጠቃለል ለሚመለከታቸው ክልል መ/ቤቶች ማቅረብ አለበት፣

የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በሬዲዮና በጋዜጣ ማሠራጨት

ምንም እንኳን የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በሬዲዮ ማሠራጨት የታቀደ ቢሆንም በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 አልተከናወነም፡፡ ምክንያቱም ለሥርጭት የሚቀርበው የመረጃ መጠን በጣም ውሱን በመሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዋጋ መረጃ የማሠራጨት ሥራ በኤፍ.ኤም100.9 እና በጋዜጣ ሊሠራጭ እንደሚችል የደቡብ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት አረጋግጧል፡፡ በዱራሜ የከምባታ ማህበረሰብ ሬዲዮ መጠቀም እንደሚቻል ተረጋግጧል፡፡

ምንም እንኳን ከክፍያ ነፃ እንዳልሆነ ቢገለጽ በአማሮ የኮሬ ማህበረሰብ ሬዲዮ እና የትምህርት ሬዲዮ በሶዶ ያለው የዋጋ መረጃ ለማሠራጨት አማራጭ እንደሚሆኑ ይታሰባል፡፡ ለመጀመር ያህል የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ ከክፍያ ነፃ የሆኑ ሬዲዮና ጋዜጣ በመጠቀም ለማሠራጨት የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በየወቅቱ የዋጋ መረጃ በሀዋሣ ለሚገኝ ለብዙሃን መገናኛ ድርጅት  እንዲሁም የከምባታ ጠምባሮ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ መረጃውን ዱራሜ ለሚገኘው ለከምባታ ማህበረሰብ ሬዲዮ ማቅረብ አለባቸው፡፡

<u>የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በቢሮ ዌብ ሳይት አማካይነት ማሠራጨት</u>
በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት አፈጻጸም ወቅት የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ድህረገጽ በቢሮ አነሣሽነት ተዘጋጅቶ በዌብ (www.snnprbomc.gov.et) የተለቀቀ ቢሆንም ይዘቱ (ገጾች) አሁንም በመሠራት ላይ ነው፡፡

መረጃን በግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ድህረገጽ ማሠራጨት ለአርሶአደሮችና ለአካባቢ ነጋዴዎች በአሁኑ ወቅት አይሠራም፡፡ ሆኖም በዕቅድ ውስጥ እንደ ደጋፊ ሥራ ሊካተት ይቻላል፡፡

<u>ከሌሎች የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ጋር የወደፊት ትስስር</u>
የፌደራል መንግስት አሁንም እያንዳንዱን ክልል በግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት በማስተሳሰር (በማዋሃድና የዳታቤዝ መጋራት) የማገናኘት ሀሳብ ቢኖረውም ተጨባጭ እርምጃ አይታይም፡፡

የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የኢንተርኔት ተደራሽነት የላቸውም፡፡ የፋኦ-የግብርና ግብይት (ዳታ ቤዝ የኮምፒውተር ፕሮግራም) ጥቅም ላይ እየዋለ አይደለም፡፡ ስለዚህ የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በኤሲኤሌ/አክሰስ በማከማቸት የወደፊት ትስስር ከሌሎች የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ጋር ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡

### እስትራቴጂ 1-3: ያለውን የመረጃ ሀብት መጠቀም

<u>ከኦሮሚያ ግብይት ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ገበያ መረጃ ማግኘት</u>
የኦሮሚያ ግብይት ኤጀንሲ የዋጋ መረጃ በአዲስ አበባ ገበያ ሥፍራዎች ሲሰበሰብ ነበር፡፡ ወቅታዊ መረጃ ሥርጭት በድህረገጽ ማሰራጨት በመጋቢት 2011 (እ.ኤ.አ) ለመዘርጋት አቅደው ነበር፡፡ (www.promiyaa.gov.et) ድህረገጽ በአንድ ወቅት በ2011 (እ.ኤ.አ) ተደራሽ ነበር፡፡ ነገር ግን እስከአሁን ሙሉ በሙሉ ተደራሽ አልሆነም፡፡ ስለዚህ የትብብር ግንኙነት ከኦሮሚያ የግብይት ኤጀንሲ ጋር በመፍጠር የገበያ መረጃ በየወቅቱ ኢሜል ወይም በሌላ አማራጭ ማግኘት ይቻላል፡፡ ቢሮው የተገኘውን መረጃ ለወረዳ በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ማሰራጨት አለበት፡፡

<u>የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መረጃ መጠቀም</u>
የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሞባይል የአጭር የጽሑፍና የድምፅ መልዕክት አገልግሎት በ2010 (እ.ኤአ) መጨረሻ አከባቢ ጀምሯል፤፤ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሰሊጥ ጨረታ ዋጋ በዚህ አገልግሎት ያሠራጫል፡፡ ይህንን አገልግሎት በመጠቀም ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና የሰሊጥ አምራች ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች በዚህ ዓይነት መረጃ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚያም መረጃውን በቦርድ ይለጥፋሉ ወይም ለሌሎች ጽ/ቤቶች ያሠራጫሉ፡፡

### 5.2.6 መሠረታዊ እስትራቴጂ 2፡ ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ ትርፍ ማሳደግ

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ወደ 85% የሚጠጋ ሕዝብ ሕይወት የተመሠረተው በግብርና ሲሆን ባህላዊ የግብርና አስተራረስ የጎላ ቦታ አለው፡፡ ለትርፍ የሚሠራ የእርሻ፣ በገበያ ፍላጎት ላይ

ተመስርቶ የሚሠራ ገና አሁንም አልዳበረም፡፡ የአርሶአደሮች ድህረምርት ሥራና የጥራት ቁጥጥር ውሱን ነው፡፡ ነጋዴዎች የማጠብ፣ የመለየት/ደረጃ የመስጠት ሥራ በተሰበሰበው ምርት ላይ አድረገው ወደ ንግድ ሽቀጥ ለመለወጥ ይሠራሉ፡፡

በገበያ ቦታዎችና በሥርጭት መስመሮች የሚታየው የግብርና ምርት ጥራት በአጠቃላይ ሲታይ ከሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው፡፡ በሀገር ውስጥ ካለው ዝቅተኛ የጥራት ተፈላጊነት ጋር ሲታይ ለጥራት ማሻሻል ያለው ክፍተት ከቴክኒክ እይታ አኳያ ብዙ ነው፡፡

ምንም እንኳን በሀገር ውስጥ ለጥራት የሚሰጠው ስፍራ በአጠቃላይ ዝቅ ያለ ቢሆንም በጥራት ላይ ተመስርተው ግዥ የሚፈጽሙ እንደ ዓለም ምግብ ፕሮግራም፣ አድስ አበባናበሌሎች ትላልቅ ከተሞች የሚገኙ ሱፐር ማርኬቶች፣ (ሀብታም የከተማ ሸማቾች) ወዘተ አሉ፡፡ በሀዋሣ ከተማ እንኳን የአትክልት ሱቆች (ለውጪ ገበያ የሚያመርቱ) ጥሩ የንግድ ሥራ ይሠራሉ፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ የጥራት ግንዛቤ ያላቸው ገዢዎች የተወሰኑ ናቸው፡፡ ግን የኢኮኖሚ ልማትና የከተማ ኗሪዎች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የጥራት ፈላጐት ወደፊት እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ስለሆነም የጥራት ችግሮችን ለማሻሻልና ተጨማሪ እሴት ለማስገኘት ለአርሶአደሮችና ነጋዴዎች[1] የድጋፍ እርምጃዎች መሰጠት አለባቸው፡፡

የጥራት ማሻሻልና እሴት ጭማሪ ማለት አንድ ሰው ሌላ ተጨማሪ ሥራ ይሠራል፡፡ ማንም ሰው ተጨማሪ ሥራ ተጨባጭ የሆነ ትርፍ ካላገኘ አይሠራም፡፡ አሁን በአለው ሁኔታ በደቡብ ክልል አርሶአደሮች (ሕ/ሥራ ማህበራትን ጨምሮ) የንግድ ሥራ ትስስር ከአሉት ጥቂት የጥራት ግንዛቤ ካላቸው ገዢዎች ለመፍጠር አቅም የላቸውም፡፡ አርሶአደሮችና ሕ/ሥራ ማህበራት በራሳቸው የጥራት ማሻሻያ ፈፃሚ አካላት ሊሆኑ አይችሉም ሌላ አካል (መንግስት፣ እርዳታ ሰጪዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) የግብይት ድጋፍ ካላደረጉ በስተቀር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንደ ቡድን የገዢዎችን የመጠን ፍላጐት ለማሟላት መሥራት አለባቸው፤ የተወሰነ ምርት መጠን ሁልጊዜ ያስፈልጋል፡፡

በ5 ዓመት መሪ ዕቅድ (2013-2017) በተመረጡ ሰብሎች የጥራት ግንዛቤ ያላቸው ገዢዎች ተለይተዋል፤ ለወደፊት ከዚህ በተጨማሪ ከቴክኒካል እይታ አንፃር እሴት ጭማሪ ተጨባጭ የሚሆነው "በአካባቢ በሚገኝ ቴክኖሎጂ ወይንም ተስማሚ ቴክኖሎጂ ከውጭ በማስገባት" ነው፡፡

የምርት ሁኔታ፣ የድህረ-ምርት ማቀነባበርና ግብይት እንዲሁም የእሴት ጭማሪ የቴክኒክ ይዘቱ በሰብል ዓይነት ይለያያል፡፡ ስለሆነም ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት ዕቅዱ ሰብል በሰብል መዘጋጀት አለበት፡፡

### እስትራቴጂ 2-1፡ የፍራፍሬና አትክልት መሰብሰብና አያያዝ ዘዴ ማሻሻያ

እስከአሁን የተጠቃሚዎች የጥራት ፍላጐት ብዙ አይደለም የአብዛኛው ሸማች የመግዛት አቅም ከፍተኛ አይደለም፡፡ እንደሚታየው ከሆነ የሚቀርበውን ጥራት እንደተለመደው መደበኛ አድርገው ይቆጥሩታል ምክንያቱም ከፍተኛ ጥራት /ዋጋ/ ያላቸውን ፍራፍሬና አትክልት አያውቁም፡፡ በወረዳ ጥራት የተጠቃሚ ፍላጐትና በተሳሳተ የአርሶአደር አስተሳሰብ ፍራፍሬና አትክልት በመሰብሰብና በማከፋፈሉ ወቅት በግምት መመልከት የተለመደ ነው፡፡ አርሶአደሮች ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው የግብርና ምርትን በግዢ ፕሮግራም የሙከራ

[1] ምንም እንኳን በምርት ሂደት ብዙ የጥራት ማሻሻያ ለአርሶአደሩ ምርት ማድረግ ቢያስፈልግም ይህ ጥናት በድህረምርትና ግብይት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ አስረፈላጊ የማሻሻያ እርምጃዎች አልተጠቃለሉም፡፡

ፕሮጀክት ትግበራ ከረጢት ይሸከማሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት አርሶአደሮቹ ከውጪ የገባ ማጠራቀሚያዎችና የመሰብሰቢያ ቁሳቁሶች ተጠቅመው ፍራፍሬና አትክልት ከብልሽት ይታደጋሉ ተብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ከፍተኛ የሆነ የመጠንና የጥራት ጉድለት በሥርጭት መስመርና በማምረት ሥራ ሂደት በሚበላሹ ፍራፍሬና አትክልት ላይ ይደርሳል፡፡

<u>ማንጎ እና አቮካዶ፡ ዘመናዊ የማምረቻ መሣሪያ በማስተዋወቅ የብልሽት መጠንን መቀነስ</u>

የአሁኑ የማምረቻ ዘዴ "ዛፍ ላይ በመውጣት ፍሬውን በመምታት እንዲወድቅ ማድረግ ነው" በዚህ ሂደት ብዙ ፍራፍሬ አካላዊ ብልሽት ያጋጥማቸዋል፡፡ እስከአሁን ቀላል የሆነ የመሰብሰቢያ መሣሪያ እንኳን አልተፈጠረም፡፡ አሁን ያለውን የማንጎና አቮካዶ የማምረትና የአያያዝ ልምምድ ለማሻሻል የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 03 ተስማሚ የምርትና የአያያዝ ዘዴ/መሣሪያ ለማልማትና ለማሠራጨት ሠርቷል፡፡ በዚህ መሠረት የማምረቻ መሣሪያ በቀላሉ ሊፈበረክ የሚችልና ቀላል የሆነ ዲዛይን ተደርጐ የተሠራው ውጤታማነቱና የፍራፍሬ አካል ጉዳት እንደሚቀንስ ተረጋግጧል፡፡ እንደገና በሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ እንደተረጋገጠው የአርሶአደሮች ቡድን የሚጠቀሙትን መሣሪያዎች መጋራት እና በገበያ ትስስር ያለው ድጋፍ በጥራት ፈላጊ ገዢ ዘንድ መሣሪያውን በመስጠት ለጥራት መሻሻል ማበረታቻ በመሆን ያገለግላል፡፡

ስለዚህ የተዘጋጀውን የፍራፍሬ ማውረጃ መሣሪያ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በዋና ዋና ማንጎና አቮካዶ አምራች ወረዳዎች በማስተዋወቅ ፍራፍሬ በሚሰበሰብ ወቅት ያለውን ብክነት መቀነስ (=ለሽያጭ የሚቀርብ ፍራፍሬ መጠን መጨመር) እና ለሽያጭ የሚቀርብ ፍራፍሬ ጥራት ማሻሻል (=ለሽያጭ የቀረበ ፍራፍሬ ዋጋ መጨመር) ይቻላል፡፡

በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 አፈፃፀም የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ የፍራፍሬ ማውረጃ መሣሪያ ማስተዋወቂያ የሚከተሉትን መርህ የትኩረት ነጥቦችን በመያዝ ታቅዷል፡፡

1/ መሣሪያዎችን ለማስተዋወቅ "የምርት መሰብሰቢያ ቁሳቁስና" "የፕላስቲክ ሣጥን" ዋና ተፈላጊ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ የትራንስፓርት መሣሪያ፡ ባለሁለት ጎማ በእጅ የሚገፋ ጋሪና የአህያ ጋሪ ፕላስቲክ ሣጥን ለመጫን የሚገለግል የአርሶአደሮች ቡድን የጋራ ግብይት መሳተፍ ከጀመሩ ከክፍያ ነፃ ሆነው መንገድ እንዲሰጥ መካተት አለባቸው፡፡ የጋሪ ዓይነትና መጠን መወሰን ያለበት ፍራፍሬው ያለበት ቦታና የሥርጭት ሁኔታ፣ ወደ መሰብሰቢያ ቦታ ያለው ርቀት እና የመንገዱ ሁኔታ ታይቶ መሆን አለበት፡፡

2/ የማስተዋወቅ ሥራ የመጨረሻ ግብ መሆን ያለበት "አዲሱ የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ እንደማንኛው ለሽያጭ የሚቀርብ ማጭድና መኩትኮቻ በፍራፍሬ አምራች አካባቢ በአሉ ገበያዎች መቀረብ እንዲችሉ ነው"፡፡ በተጨማሪ ለሽያጭ በአካባቢ ብረታብረት ሥራ ድርጅቶች እንዲመረት ከፍተኛ ጥረቶች ማድረግ ነው፡፡
ይበልጥ ግልጽ ለመሆን የቴክኒክ ድጋፍ እንደ ቅርጽ ማውጫና ብረታብረት መቆልሚሚያ የመሣሪያውን ቅርፅ ተመሳሳይነት ለማረጋገጥ መስጠት አለበት፡፡ ከዚህ ሌላ የቢዝነስ ስጋት በተለይም አዲስ አመራረት በሚቀርብበት ጊዜ የአርሶአደሮች ፍላጐት እርግጠኛ ለመሆን ስለሚያዳግት፤ ይህንን ሁኔታ ለመቋቋም ለመጀመሪያ ምርት ማቴሪያል በነፃ እንዲሰጥ ያስፈልጋል፡፡

3/ የፍራፍሬ በማውጃ ቁሳቁስ ተጠቅሞ መሰብሰብ ዛፍ ላይ ወጥቶ በበትር በመምታት ከማውረድ የበለጠ ጊዜ ይፈልጋል፡፡ የማውረጃ ቁሳቁሱን እንዲጠቀሙ ማበረታቻ (ይህም ለምርት ጥራት ማሻሻል ማበረታቻ) ለአርሶአደሮች መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የገበያ ትስስር በጥራት ላይ ተመስርተው ከሚገዙ ገዥዎች ጋር መፍጠር በጣም ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የገበያ ትስስር ድጋፍ በተቻለ መጠን መስጠት እንደቀበሌው ሁኔታ የሚለያይ ቢሆንም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

4/ አርሶአደሮች ለቁሳቁሶቹ ፍላጎት እንዲኖራቸው መደበኛውን የኤክስቴንሽን ዘዴ መጠቀም፡ ሀ) የሠርቶ ማሣያና ማብራሪያ ሥራዎች (ፍራፍሬ ማውረጃ በመጠቀም ያለውን) ለቀበሌ አደራጆችና ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ባለሙያዎች መስጠት፣ ለ) ፓስተሮችን በየቀበሌዎች መለጠፍ፣ እና ሐ) ቁልፍ ለሆኑ አርሶአደሮች ቁሳቁሱን በነፃ ማደል ናቸው።

ሆኖም በዚህ ዘዴ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ። እነርሱም ሀ) ሠርቶማሣያና ለቁልፍ አርሶአደሮች የምርት መውረጃውን በነፃ ማደል በሌሎች አርሶአደሮች ዘንድ ፍላጎት እንዲኖር ያደርጋል? ለ) በቀበሌው ሰፊ ፍላጎት ለመፈጠር ስንት ቁሳቁስ በነፃ በቀበሌ ውስጥ መሠራጨት አለት? የሚሉ ናቸው። ስለዚህ የኤክስቴንሽን ዘዴዎችን የማረጋገጫ መንገድና ተገቢ የሆነ በነፃ የሚታደል ቁሳቁሶች ብዛት በዕቅዱ ውስጥ መካተት አለበት።

5/ ከአርሶአደሮች ፍራፍሬ የሚገዙ የአካባቢ ነጋዴዎች የመረጃ ሥርጭትና የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስተዋወቅ ሥራ እንዲያካሂዱ በዕቅዱ ውስጥ መካተት አለት።

6/ የማንጎ ፍራፍሬ በተመለከተ ለአፍሪካ ጁውስ ኩባንያ ማቅረብ በዋና የምርት መሰብሰቢያ ወቅት የሚከሰተውን የዋጋ ዝቅ ማለት ያስቀራል የሚል ግምት አለ። ከአቅራቢ ወገን (ዩኒየን፣ ሕ/ሥራ ማህበራት፣ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች እና ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ) የኩባንያውን የጥራትና የመጠን ፍላጎት ለማሟላት የተረጋጋ የቢዝነስ ግንኙነት ለመፍጠር ጥረት ማድረግ አለባቸው። የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በዚህ ረገድ የመሪነት ሚና መጫወት አለበት።

የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ 28 እጩ ወረዳዎችንና ከጠቀመው 18 ወረዳዎች የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስተዋወቂያ ፕሮጀክት እንዲሣተፉ መርጧል። የፕሮጀክት ዕቅድ ቁጥር 3 የ5 ዓመት ዕቅድ ሲሆን በ4 ዋና ፍራፍሬ ማመረቻ ወቅቶች አሉት። ከፍተኛው የወረዳ ብዛት (የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 ወረዳዎችን ጨምሮ) በ1 ምርት ወቅት ከ4 አይበልጥም። የተመረጡ 18 ወረዳዎች ዝርዝር በቀጣዩ ሠንጠረዥ 5-4 ተመልክቷል።

ማስታወሻ፡ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከወላይታ ዞን፣ ሲዳማ ዞንና ከምባታ ጠምባሮ ዞን የአነስተኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ወረዳዎች የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት (የፕሮጀክት ዕቅድ ቁጥር 1) የሚካሄድባቸው መሆኑ ለምርጫው አግባብነት እንዳለው ሊረዳ ይገባል።

**ሠንጠረዥ 5-4 የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ለማስተዋወቅ የተመረጡ ወረዳዎች**

| ዞን | ወረዳ | | ማንጎ | አቩካዶ | ቅድሚያ የተሰጠ * | ለሙከራ ፕሮ. 03 የተመረጠ | 2013/14 | 2014/15 | 2015/16 | 2016/17 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጋሞጎፋ | 1 | አ/ምንጭ ዙሪያ | X | | 1 | | X | | | |
| | 2 | ምዕራብ አባያ | X | | 2 | | X | | | |
| | 3 | ደንባ ጐፋ | X | | 3 | | | X | | |
| ወላይታ | 4 | ቦሎሶ ቦምቤ | X | X | 1 | | | X | | |
| | 5 | ቦሎሶ ሶሬ | X | X | 2 | | | X | | |
| | 6 | ዳሞት ጋሌ | | X | 3 | | | | X | |
| | 7 | ዳምት ፉላሣ | | X | 4 | | | | X | |
| ከምባታ ጠምባሮ | 8 | ሃዳሮ ጡንጦ | X | X | 1 | | | X | | |
| | 9 | ቃጫ ቢራ | | X | 2 | | | X | | |
| | 10 | ቀዲዳ ጋሜላ | | X | 3 | | | | X | |
| ሲዳማ | 11 | ወንዶገነት | | X | 1 | | X | | | |
| | 12 | ዳሌ | | X | 2 | | | X | | |
| | 13 | አለታ ወንዶ | | X | 3 | | X | | | |
| | 14 | ሀዋሣ ዙሪያ | | X | 4 | | | | X | |
| ጌዴኦ | 15 | ዲላ ዙሪያ | | X | 1 | | | | X | |
| | 16 | ወናጐ | | X | 2 | | | | X | |
| ቤንች ማጂ | 17 | ሰሜን ቤንች | X | X | 1 | | | | | X |
| | 18 | ደቡብ ቤንች | X | X | 2 | | | | | X |

በክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያ (ሙከራትግበራ ፕሮጀክት 03 መሪ) ቅድሚያ ተከተል ተሠጥቷል።
X : የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት የተመረጡ ወረዳዎች (ፕሮጀክት ቁጥር 1)

የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስተዋወቅ በ18 ወረዳዎች ቀስ በቀስ መጀመር አለበት፡፡ ለመጀመሪያ ዓመት የተመረጡ ወረዳዎች ቁጥር የተወሰኑ መሆን አለት፡፡ ይኸውም የኤክስቴንሽን ዘዴ ለማረጋገጥና ተገቢ ቁሳቁስ በነፃ የሚታደለውን ቁጥር ለመወሰን ስለሚረዳ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ፍራፍሬ የተመረጡ ወረዳዎች ብዛት 2 ሲሆን በአንድ ዞን ውስጥ መሆን አለባቸው፡፡ ይኸውም ውጤታማነቱን ለማወዳደርና የአመራሩን ሥራ ለማቅለል ነው፡፡

- በሲዳማ ዞን ለአቮካዶ ወንዶገነትና አለታወንዶ የተመረጡ ሲሆን ከሀዋሣ ሩቅ አይደሉም፡፡ እንዲሁም ለማስተዳደር አመቺ ነው፡፡
- በጋሞ ጎፋ ዞን ለማንጎ ምዕራብ አባያና አርባምንጭ ዙሪያ የሕ/ሥራ ማህበራት (የጋራ) የማንጎ ሽያጭ በሁለቱም ወረዳዎች ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 የተመረጡ ወረዳዎች ቦሎሶ ሶሬ እና ዳሌ ለ2ኛው ዓመት የተመረጡ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የቁሳቁስ አጠቃቀም በሙከራ ትግበራፕሮጀክት በነዚህ አካባቢ ዝቅተኛ ስለነበረ እና የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽቤቶች ሁኔታውን የማመቻቸት ሥራ በቅድሚያ ለመከታተል ሲባል ነው፡፡

በክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የአቅም ውስንነት ምክንያት ከሁለተኛው ዓመት በኂላ በፕሮጀክቱ ተሳታፊ የሚሆኑ ወረዳዎች ብዛት በየዓመቱ ከ6 ሊበልጥ አይገባም፡፡ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የአመራር ብቃት ጋር ለማጣጣም በሚያስችል መልኩ የተመረጡ ወረዳዎች በቅድመ ተከተል ተቀምጠዋል፡፡

ከዓመት ወደ ዓመት የክትትልና የቁጥጥር ሥራ እያደገ ይሄዳል፡፡ ለመጨረሻው ዓመት የተመረጡ ወረዳዎች ሁለት ብቻ ሲሆኑ በቤንች ማጂ ዞን ይገኛሉ፡፡ በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት አካኝነት ለቁጥጥር የሚሆን ሥርዓት ተዘጋጅቶ በእያንዳንዱ የተመረጠ ወረዳ መኖር አለበት፡፡

<u>ቲማቲም፡ ወደ ከተማ ገበያ አትክልት የሚጓጓዝበት ዘዴ ዘመናዊ ማድረግ</u>

ከሀዋሣ አከባቢ ከሚገኙ የቲማቲም አምራች ቦታዎች ወደ ሀዋሣ ከተማ ገበያ በእንጨት ሣጥን ይጓጓዛል፡፡ የእንጨት ሣጥኖች ባለቤቶች ነጋዴዎች እንጂ የአርሶአደሮች አይደሉም፡፡ ሁለት ዓይነት የትራንስፓርት ዘዴዎች አሉ፡፡ የአህያ ጋሪ እና የጭነት መኪና ወደ ሀዋሣ ከተማ ገበያ ለማጓጓዝ ይጠቀማሉ፡፡ በኪሎ ግራም የማጓጓዣ ወጪ በአህያ ጋሪና በጭነት መኪና ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም አብዛኛው አርሶአደር የጭነት መኪና አይጠቀምም፤ ምክንያቱም የጭነቱ መጠን አነስተኛ ስለሚሆን ነው፡፡ በሀዋሣ ገበያ የእንጨት ሣጥኖችን ለአያያዝ ሲጠቀሙ ይታያል፡፡ ይሁንና ከሣጥን በላይ በመጫን ብልሽት ሲያጋጥም ይታያል፡፡

ወንዶገነት ለሀዋሣ ገበያ ዋና የቲማቲም ምርት አቅራቢ ነው፡፡፡ ሌላ ዋና አቅራቢ በኦሮሚያ ክልል የመቂና ዝዋይ አካባቢ ነው፡፡ የመቂና ዝዋይ ቲማቲም ዝሪያ ከወንዶገነት አካባቢ ዝሪያ የተለየ ነው፡፡ የመቂና ዝዋይ ዝሪያ ስስ ቆዳ ያለውና በገበያ የተሻለ ዋጋ ያለው ነው፡፡

በሸማቾች ምርጫና በገበያ ዋጋ የቲማቲም ባህሪይ ወደ ከተማ አካባቢ የሚጓጓዘው ከጠንካራ ወደ ስስ እና ከአረንጓዴ የበሰለ ወደ ቀይ የበሰለ (የበለጠ ቶሎ የሚበላሽ) ደረጃ ይደርሳል፡፡ የብልሽት መከላከል በምርት ማሰብሰብና በትራንስፓርት ወቅት በጣም አስፈላጊ ሥራ ይሆናል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፕላስቲክ ሣጥኖች የሚደራረቡ፣ ከእንጨት ሣጥን ይልቅ እርካሽ የሆኑ (ብር 50 በሣጥን) እና በጣም ጥልቅ ያልሆኑ (22 ሣንቲ ሜትር) በሀዋሣ ከተማ በጣም ታዋቂ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ ከዚያም ብዙ ልዩ ልዩ ሽቀጦችን ሊይዙ ይችላሉ፡፡ ምንም

*እንኳን ጥንካሬያቸው ዝቅ ያለ ቢሆንም እነዚህ ፕላስቲክ ሣጥኖች ለቲማቲም ማጓጓዣነት ከሚሰጡት አገልግሎትና ከዋጋ አንፃር ከእንጨት ሣጥኖች ይሻላሉ፡፡*

*በምርት መሰብሰብያ ወቅት ካለው የብልሽት ሁኔታና የትራንስፖርት ችግር አኳያ የአርሶአደሮች ተግዳሮቶች ትኩረት ሊያገኙ ይገባል፡፡ በሌላ አነጋገር የለውጥ ማፍለቅ፣ ሀ) ከእንጨት ሣጥን ወደ ተደራራቢ ፕላስቲክ ሣጥን፣ ለ) ከአህያ ጋሪ ወደ ጭነት መኪና፣ እና ሐ) ከግል ሽያጭ ወደ የጋራ መጓጓዣ (የጭነት መኪና መጠቀም) የግድ ይላል፡፡*

*በመጀመሪያ የአርሶአደሮችን ተግዳሮቶች በሞዴል ማስቀመጥ፣ ከዚያም የቅድሚያ ወጪ ድጋፍ እቅድ በማውጣት ፕላስቲክ ሣጥን ግዢ በማከናወን የፕላስቲክ ሣጥን በመጠቀም ቲማቲም ወደ ከተማ ገበያ ማጓጓዝን ማስታወቅ ያስፈልጋል፡፡*

## *እስትራቴጂ 2-2፡ ጥራት ግንዛቤ ባለው ገበያ የሚደረገውን ተሳትፎ ማፍጠንና ማጠንከር (የጥራት ቁጥጥር ክህሎት ማሰራጨት)*

*በደቡብ ክልል የግብርና ምርት የአከባቢ ፍላጐት አያሟላም፡፡ ሆኖም የትርፍ ምርትና የምርት እጥረት ያለባቸው አከባቢዎች የተበጣጠሱና የተቀላቀሉ ናቸው፡፡ የፌደራል መንግስትና እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች እንደ ዓለም ምግብ ፕሮግራም ያሉት የምግብ እርዳታ የምግብ እጥረት ላለባቸው አከባቢዎች በየዓመቱ ይሰጣሉ፡፡ የክልሉን ትርፍ ምርት የምርት እጥረት ላለባቸው አከባቢዎች የማድረሱ ጉዳይ ተጀምሯል፡፡ የዓለም ምግብ ፕሮግራም/ግዥ ለዕድገት ትርፍ እህል/ጥረጥሬ በቀጥታ ከሕ/ሥራ ማህበራትና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ በጨረታ በመግዛት ለዘመናዊ የግብይት ስርዓት የመጀመሪያ ደረጃ እንደሆነ ለእንደዚህ አይነት እንቅስቃሴ ይገመታል፡፡*

*ሆኖም በደቡብ ክልል የቢዝነስ ዘዴ ለእህልና ለጥራጥሬ የንግድ ልውውጥ የሚከተሉት ባህላዊ አሠራር ስለሆነ የጥራት ደረጃ በመጠቀም ለቢዝነስ ድርድር ለማድረግ ቦታ የሚሰጥ አይደለም፡፡ የዓለም ምግብ ፕሮግራም ማሽንና መሣሪያዎችን በመስጠት እንዲሁም የሙያ ስልጠና በማከል በግዥ ለዕድገት ለሚሳተፉ ሕ/ሥራ ማህበራት ጥራት ለማሻሻል እንዲቻል ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን አሁንም የዓለም ምግብ ፕሮግራም ከዩኒየኖች የሚቀርበውን ምርት ለመቀበል ችግሮች እያጋጠሙት ነው፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አስተማማኝ የሆኑ አቅራቢዎችን የእህልና የጥረጥሬ ምርት የጥራት ደረጃ የጠበቀ ሊያገኝ እየተቸገረ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የአህገር ውስጥ ምርት ጨረታ ስርዓት በአብዛኛው ምንም እንቅስቃሴ አይታይበትም፡፡ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ አስተማማኝ አቅራቢዎች የሉም ሲል አቅራቢዎች የሚሉት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጨረታ ውስጥ መግባት ምንም ጥቅም የለም ይላሉ፡፡*

*ጥራት ያለው ገበያና ቢዝነስ ድርድር በጥራት ደረጃዎች ተመሥርቶ በኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ እውን እንደሚሆን መላምቶች አሉ፡፡ ሁለቱም አምራቾችና ሸማቾች ፍትሃዊና ብቃት ያለውን የገበያ ሥርዓት ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ መነሻ አምራቾችና ነጋዴዎች ሁለቱም የጥራት ቁጥጥር ችሎታ ማሳደግና ዝርዝር ሁኔታዎችን እንዲገነዘቡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በግዥ ለዕድገት የዓለም ምግብ ፕሮግራም እና ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጨረታ ማለት የጥራት ግንዛቤ ያለው ገበያ በኢትዮጵያ መጀመሩን ያመለክታል፡፡ መሠረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራትና የሕ/ሥራ ዩኒየኖች በግዥ ለዕድገት የሚሳተፉትን የጥራት ቁጥጥር ችሎታ ማጠናከር ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጨረታ መግባታቸውን ለማፋጠን ይረዳል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለአቅራቢዎች ቀጥታ የቴክኒክ ድጋፍ አያደርግም፡፡ የዘመናዊ የግብርና ምርት ልውውጥ ለማፋጠንና ለማስፋፋት የዓለም ምግብ ፕሮግራም እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መተባበር እንዳለባቸው ይገመታል፡፡*

የጥራት ቁጥጥር ቴክኒክና የመጋዘን አስተዳደር ችሎታ ሁለቱም በኢትዮጵያ አልዳበሩም፡፡ መሠረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራትና የሕ/ሥራ ዩኒየኖች ሁለቱም የድህረምርት ብክነት የሚከሰተው ብቁ ባልሆነ ማከማቸት እንደሆነ ግንዛቤ የላቸውም፡፡ አንዳንድ መጋዘኖች የአየር መተላለፊያ መስኮት የላቸውም፡፡ ነገር ግን እህልንና ጥራጥሬ በዚህ መጋዘን ከፍተኛ ሙቀትና እርጥበት ባለበት ወቅት እንኳን ለተወሰነ ጊዜ ያከማቻሉ፡፡ በዚህ ምክንያት በምርቱ ላይ በእርጥበቱ የተነሳ ከቆሻሻና ወለል መለያ ከስር ምንም ንጣፍ ስለማይደረግለት ሻጋታ በእህሉ ላይ ይፈጠራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአንድ መጋዘን ውስጥ እህል፣ ማዳበሪያና ኬሚካሎች አንድ ላይ ክፍፍል ሳይኖር ይቀመጣሉ፡፡ ስለሆነም የድህረምርት አያያዝና የመጋዘን ማአስተዳደር ችሎታ የቴክኒክ ሥልጠና መስጠት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

የስልጠና ፕሮግራም በጃይካ ጥናት አማካኝነት የተካሄደው ለወረዳዎች፣ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት እና ሕ/ሥራ ዩኒየኖች መቀጠልና ማስፋፋት አለበት፡፡ ለውጤታማና ብቃት ያለው አቀራረብ ለባለድርሻ አካላት የኤክስቴንሽንና የማስፋፋት ሥልጠና ለመስጠት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ዓለም ምግብ ፕሮግራም መተባበር አለባቸው፡፡

## እስትራቴጂ 2-3፡ በአምራቾች አካባቢ የእሴት ጭማሪ ሥራዎች ማሳደግ

የግል ኢንተርፕራይዝ በመሳብ የፍራፍሬ ማቀናባበሪያ ማስፋፋት

በደቡብ ክልል ከምግብ ባህል ተጽእኖ የተነሣ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎች ፍራፍሬና አትክልት እንደጥሬ ዕቃ አይጠቀሙም፡፡ የገጠር ቀበሌዎች ለማቀነባበሪያ የጥሬ ዕቃ ያለቸው የኤሌክትሪክ አቅርቦትና የውሃ አገልግሎት የላቸውም፡፡ በተጨማሪ ከገዢዎች ወይም ከሸማቾች እንዲሁም ከአላቂ ዕቃ አቅራቢዎች ሩቅ ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ የመገናኛ አገልግሎት በጣም ደካማ ነው፡፡ በመሆኑም የገጠር ቀበሌዎች የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ቢዝነስ ለመሥራት መሠረታዊ ሁኔታዎች አልተሚሉም፡፡ በዚህ አይነት ደካማ ሁኔታ ውስጥ የጃይካ አንድ መንደር አንድ ምርት ማስተዋወቂያ ፕሮጀክት በማንጎ ጭማቂ ማቀነባበር በአ/ምንጭ የአርሶአደር ቡድንና የኢኮፒያ የሚባል የግል ኩባንያ የቴክኒክና የገበያ ድጋፍ ለአርሶአደሮች ቡድን ለመስጠት የሚችል መካከል የአርሶአደሮች የቢዝነስ ቡድን ለመፍጠር ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ እንደ አሠራር አቅጣጫ አርሶአደሮች ማንጎና የሰው ኃይል/ጉልበት ሲያቀርቡ ኢኮፒያ ሌሎች ለማንጎ ጭማቂ ማቀነባበሪያ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያቀርባል ግብይቱንም ያካሂዳል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ይህ አቀራረብ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያና ቢዝነስ በገጠር ቀበሌ ለማስተዋወቅ ብቸኛው መንገድ ተብሎ ተወስዷል፡፡

በሚቀጥሉት 10 ዓመታት የገጠር አካባቢዎች የኤሌክትሪክ አቅርቦት በመካሄድ ላይ ባለው የግድብ ግንባታ ምክንያት እንደሚሻሻል ይገመታል፡፡ ቢሆንም ለግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ቢዝነስ ጥሩ ቦታዎች (ኤሌክትሪክ መስመር፣ ውሃ፣ ጥሬ ዕቃዎች እና ለከተማ ቅርብ የሆኑ) የሚባሉት በገጠር አካባቢ አሁንም የተወሰኑ ይሆናሉ፡፡ የከተማ አካባቢዎች ከገጠር ቀበሌዎች ፍራፍሬ ከሚያመርቱ ብዙም ሩቅ ያልሆኑት የማቀነባበሪያ ቢዝነስ ለመስራት ጥሩ አጋጣሚዎች ይኖሯቸዋል፡፡

የፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ቢዝነስ ለመጀመር አንድ ሰው የሚከተሉትን ደረጃዎች ግልጽ ማድረግ አለበት፤ የማቀነባበሪያ ዕውቀት/ችሎታ መያዝ፣ ገንዘብ ማሰባሰብ፣ ዕቃዎችና መሣሪያዎች የማሸጊያ ቁሳቁሶች መግዛት፣ ምርት ማልማት፣ የሽያጭ አማራጮች ማመቻቸች ሲሆን አሁን ባለው ሁኔታ ለአርሶአደሮች ከባድ ይሆናል፡፡

ስለዚህ የግል ኩባንያ ወይም ግለሰብ የራሱን የምርት ማቀነባበሪያ ቢዝነስ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ አርሶአደሮችን ከመደገፍ ይልቅ በከተማ ወይም ገጠር አካባቢ እንዲጀምር ማበረታታት ምክንያታዊ የሚሆነው፡፡

በንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሥር ያለው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን በአንድ አካባቢ የተሰበሰበ የልማት ፕሮግራም እየተካሄደ ይገኛል፡፡ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የፍራፍሬ ማቀነባበሪያን የግል ኢንተርፕራይዞች በመሳብ እንዲሠሩ ማድረግ አለበት፡፡ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከአርሶአደሮች ጋር የትስስር ግንኙነት በመፍጠር የጥሬ ማቴሪያል አቅርቦት በቀጣይነት እንዲቀርብ መስራት አለበት፡፡ ገንዘብ ማሰባሰብ ሁልጊዜ ቢዝነስ ለመጀመር ትግል ነው፡፡ ስለሆነም ድጎማ ሥርዓት በማዘጋጀት የመነሻ ኢንቨስትመንት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

<u>በባህላዊ መንገድ የተቀነባበሩ ምግቦች የጥራት ቁጥጥር</u>

ቆጮና ቡልአ ከእንሰት የሚዘጋጁት በኢትዮጵያ በተለይም በደቡብ ክልል ያሉ ባህላዊ ምግቦች ናቸው፡፡ የማቀነባበሩ ሥራ በጉልበት በተለይ በሴቶች የሚሠራ ሲሆን ከቤት ፍጆታ የሚተርፍ ቢኖር በአካባቢው ገበያ ይሸጣል፡፡ በእንሰት ማቀነባበር የንግድ ሥራ የሚሳተፉ ቤተሰቦች ብዛት የተወሰነ ነው፡፡ በእጅ የሚንቀሳቀስ ማቀነባበሪያ ማሽኖች ለምግብነት የሚውል የቅጠል ክፍል የሚልጥ፣ እንዲሁም የቃጫ መቆራረጫና ማደባለቂያ በሙከራ ደረጃ ተሠርተዋል፡፡ ሆኖም በተግባር ላይ አልዋሉም፡፡

ምንም እንኳን የእንሰት ማቀነባበሪያ ቀለል ያለ ማሽን ሊሠራ ቢችልም የኢንቨስትመንትና ሥራ ማስኬጃ ወጪ ሽፍኖ ለመጠቀም የቆጮና ቡልአ የሽያጭ ዋጋ አነስተኛ ከመሆኑ የተነሣ ሊሳካ የሚችል አይመስልም፡፡ የ5 ዓመት መሪ ዕቅድ ከ2013 (እ.ኤ.አ) የሚጀምረው ይህንን እንቅስቃሴ በባህላዊ ምግብ ማቀነባበር አይሸፍንም፡፡

<u>የብርዕና አገዳ ሰብል ጥራጥሬና ቅመማቅመም የወፍጮ አገልግሎት (የእህል ወፍጮ)</u>

የወፍጮ ሥራ ለብርዕና አገዳ ሰብለ፣ ለጥራጥሬ እና ቅመማቅመም የሚጠቀሙት ባህላዊ የድንጋይ ወፍጮ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ሞተር ወይም የዲዚል ሞተር የድንጋይ ወፍጮ ያንቀሳቅሳል፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ከፍተኛ ኃይል ይጠቀማል፡፡ እንዲሁም የሥራ ቦታ ዱቄትና ብናኝ በመበተን ይበክላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው የወፍጮ አገለግሎት ሰቶች በኬንያ፣ ዩጋንዳ እና ታንዛኒያ ከቀላል ብረት የተሠራ የመዶሻ መፍጫ ይጠቀማሉ፡፡ በተመሳሳይ አቅጣጫ በኢትዮጵያም በቅርብ ጊዜ ተለውጦ መጠቀም ይጀመራል፡፡ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ማዕከላት የመዶሻ ወፍጮ የሚመስል እንደሚሰሩ የሚጠበቅ ሲሆን በተግባር ተስማሚነቱና የመፍጨት አቅሙ ተፈትሾ ለምግብ ማቀነባበሪያ መሆኑ እንደሚረጋገጥ ይጠበቃል፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ወደ ዘመናዊነት ማሸጋገር በ5 ዓመቱ መሪ ዕቅዱ ከ2013 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ አልተካተተም፡፡

<u>የብርዕና አገዳ ሰብልና ጥራጥሬ በፀሐይ ማድረቅን ማሻሻል</u>

የፀሐይ ማድረቅ ብቃት ለማሻሻል ጭቃና ድንጋይ መቀላቀልን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ከውቂያ በኋላ ፕላስቲክ ሸራ መጠቀም በፀሐይ ማድረቅ ይገባል፡፡ የማድረቅ ሥራ በደረቅ ወቅት ይሠራል ይህም ማድረቅም ቀላል ያደርጋል፡፡ ነገር ግን የእርጥበት መጠን ከማድረቅ በኋላ መለካት በእጅ በማሸት ወይም በመጨበጥ ወይም በጥርስ በማድቀቅ ይወሰናል፡፡ የእርጥበት መለኪያ መጠቀም በጣም ውሱን ነው፡፡

መካኒካል የእርጥበት መለኪያ የጥራት ገበያ እንደ ግዥ ለዕድገት እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለማቅረብ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የእርጥበት መለኪያ መጠቀምን ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ይህ እንቅስቃሴ በዓላም ምግብ ፕሮግራም ወይም መንግሥታዊ ያለሆኑ ድርጅቶች ተጀምሯል፡፡ የ5 ዓመት መሪ ዕቅድ ከ2013 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ያለው ይህንን ፕሮጀክት አላካተተም፡፡

<u>የደረቅ ካሳቫ ማቀነባበር የገበያ ትስስር እና የገበያ ልማት ፍጆታ ማስፋፋት</u>
የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 የቀላል ጥሬ ካሳቫ መቁረጫ ማሽንና ለፀሐይ ማድረቂያ ፕላስቲክ ሸራ አሠራርና ብቃት አሳይቷል፡፡ የገበያ ትስስር ከሀዋሣ ከተማ እንደ ሸማች አካባቢና ኪንዶ ኮይሻ ወረዳ እንደ አምራች አካባቢ በመውሰድ በክልል ግብይትና የሕ/ሥራ ቢሮ/ወረዳ ግብይትና የሕ/ሥራ ጽ/ቤት እገዛ ተቋቁሟል፡፡ የዚህ ዓይነት የግብርና ምርት ማቀነባበር በተስማሚ ቴክኖሎጂዎችና ለተጨማሪ እሴት እና ገቢ ማስገኛ ለአነስተኛ አርሶአደሮች በክልሉ መንግስት መጠናከርና መሠራጨት አለበት፡፡

<u>የበርበሬ ድህረምርት ቴክኖሎጂ ማሻሻል</u>
ባህላዊ ማድረቂያና ማከማቻ ዘዴ በማሻሻል ጥሩ ቀለምና ጥሩ ቅርጽ እንደያዘ ለረዥም ጊዜ መቆየት አለበት፡፡ የቀለም እየቀነሰ መሄድን መከላከል የሚቻልበትን ዘዴ በምርምር ለማግኘት መሠራት አለበት፡፡

<u>ከፍተኛ ጥራት ያለውን ደረቅ ዝንጅብል ምርት ማስፋፋት</u>
የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 የተግባራዊ ማጠቢያ ዘዴና የንፁህ ደረቅ ዝንጅብል ማምረት መቻልን አሳይቶ ነበር፡፡ የዝንጅብል ማጠብና የማድረቅ ስራ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 በማየት አንድ የአርሶአደር ቡድን የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት አሠራርን በመቅዳት የንፁህ ደረቅ ዝንጅብል ማምረት በራሳቸው ካፒታል ጀመሩ፡፡

የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 እንደ ሞዴል በማድረግ የሌሎች አርሶአደሮች ወይም ነጋዴዎች ንፁህ ደረቅ ዝንጅብል ማምረት በካምባታ ጠምባሮ ዛንና በወላይታ ዞን ማስተዋወቅ ያስፈለጋል፡፡ ይኸውም የአርሶአደሮች ወይም የነጋዴዎች ቡድን ዝንጅብል ለማጠብና የማድረቅ ቢዝነስ ድጋፍ እንዲያገኙ ነው፡፡ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 አፈፃፀም በተገኘው መረጃ መሠረት <u>ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ዝንጅብል የማምረት ቢዝነስ</u> ለማስፋፋት ሥራ የሚከተሉትን መርህዎችንና የትኩረት ነጥቦች መሠረት ለማድረግ ታቅዷል፡፡

1/ ተመሳሳይ የማጠቢያ መገልገያ ዕቃዎች ወይም ሁኔታ እንደ ሃዳሮ ቦታ ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 ማቋቋምና መደገፍ፡፡ የቢዝነሱ ባለቤት ሁሉንም ወጪዎች ለማድረቂያ፣ መደርደሪያ መስራት፣ መጋዘን፣ አጥር ወዘተ መሸፈን አለበት፡፡

2/ የወንዝ ውሃና ተንቀሳቃሽ ከፍተኛ ግፊት ያለው ማጠቢያ ማሽን (በኤሌክትሪክ የሚሠራ) ለማጠቢያ መጠቀም፡፡ ስለሆነም የሥራ ቦታው በወንዝ አጠገብ እንዲሆንና የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ ቦታው ማምጣት መቻል አለበት፡፡

3/ ለጥሬ ዕቃ መግዣ ገንዘብ በቢዝነስ ባለቤት (ተጠቃሚ) መሸፈን አለበት፡፡ የፋይናንስ ድጋፍ በዕቅዱ አልተካተተም፡፡

4/ የአርሶአደር ሕ/ሥራ ማህበር ድጋፍ በተመለከተ የጋራ የልማት ሥራ ወይም እንደ ንዑስ ኮንትራክተር ከሕ/ሥራ ዩኒያን ወይም የግል ቢዝነስ ጋር በመሆን የቢዝነስ ወይም የአስተዳዳር ውድቀት ለመቋቋም መሥራት፡፡

5/ የከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ዝንጅብል የመሸጫ ቦታ የውጭ ሀገር ገበያ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ የአካባቢ ፍላጐት/ አማራጭ የገበያ መስመሮች ገና አልተጠናም፡፡ ሆኖም የአካባቢ ፍላጐት ለከፍተኛ ጥራት ለአለው ደረቅ ዝንጅብል ሊኖር ይገባል፡፡ ምክንያቱም መደበኛ ሸማቾች ዝንጅብል ያለ ንፅህና ቁጥጥር በመሬት ተሠጥቶ እንደሚደረቅ አያውቁም (ከቆሻሸ ደረቅ ዝንጅብል ከመግዛት ውጭ ሌላ አማራጭ የላቸውም) የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የሀገር ውስጥ ገበያ በመፍጠርና የልዩነት ግብይት በማዘጋጀት መሥራት አለበት፡፡

6/ የውጭ ሀገር የደረቅ ዝንጅብል ገዢዎች የጥራት ፍላጐታቸውንና ዝርዝር ባህሪ ግልፅ የሆነ መረጃ በፌደራልና የክልል ኃላፊዎች ያለመኖር፡፡ የመንግስት ኤጀንሲዎች (የንግድ ሚኒስቴር ወይንም ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ) የሚከተሉትን መረጃዎች መሰብሰብ ለአካባቢ ነጋዴዎች/አርሶአደሮች እና ወረዳና ዞን ዝርዝር ማብራሪያ ማቅረብ አለባቸው፡፡

- የውጭ ሀገር ገዢዎች ፍላጐት ጥራት እና የምርት ዓይነት
- የደረቅ ዝንጅብል ምርት ደረጃና የዝንጅብል ላኪ ሀገሮች እንደ ሕንድና ናይጄሪያ የሚጠቀሙትን አሠራር ማየት
- የሸቀጦች ዝርዝር ባህሪያት በዓለም አቀፍ የዝንጅብል ንግድ የተሣተፉትን ማየት፣

በተለይ የተፈለገው ምርት ዓይነት ማብራራት (ጅምላ ወይም በነጠላ፣ የተላጠ ወይም ያልተላጠ) ይመከራል፡፡ እነዚህን ዝርዝር ባህሪያት ወዲያው ማብራራት ያስፈልጋል ምክንያቱም የማጠቢያ መንገድን በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚነካ ነው፡፡

<u>የእርድ ድህረምርት ማቀነባበሪያ ማሻሻያ ጥናት</u>

ዱቄት እርድ የመጨረሻ ምርት ውጤት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ሥር መቁረጥ፣ ማጠብና ማድረቅ አስፈላጊ የሆኑ የድህረምርት ማቀነባበሪያ ሥራዎች ፡፡ ጃፓንን በተመለከተ መላጥና በስሱ መቁረጥ የተለመዱ ሥራዎች ናቸው፡፡ በወቅታዊ ድህረምርት ማቀነባበርና መሰብሰብ ከምርት ቴክኖሎጂ ጋር መስማማትን ለማረጋገጥ የምርምር ሥራ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡

በምርምሩ የ "<u>መዘፍዘፍ + ግፍት በአለው ውሃ የማጠብ ዘዴ</u>" ለዝንጅብል ማጠቢያ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 ጥቅም ላይ የዋለውን ማካተት ከዚያም የድጋፍ ፓሊሲ/ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡

### እስትራቴጂ 2-4፡ ልዩና የበላይ ነት ያለቸው ምርቶች/ዝሪያ ግብይት ማጠናከር

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የተለያዩ የግብርና ሥነ ምህዳርና የተለያዩ ባህሪያት ያሉ ከፍታ ቦታዎችና የአየር ጠባይ አሉት፡፡ ስለዚህ የተለያዩ የእህል ዓይነቶች ይበቅላሉ፡፡ ዋና ዋና የሰብል አምራች አካባቢዎችም አሉ፡፡ ከዚህ ሌላ ልዩ ባህሪ ያላቸውና የበላይነት ያላቸው ምርት/ ዝሪያዎች በደቡብ ክልል ብቻ የሚመረቱ ወይም ክልሉ ከፍተኛ ምርት የሚያበቅላቸው አሉ፡፡ በጥሩ ጥራታቸው ታዋቂ የሆኑ ምርቶች ለምሳሌ ሙዝ በአ/ምንጭ፣ በርበሬ (ማራቆ ፋና ዝሪያ) በቡታጅራ ጎደሬና ቦሎቄ በወላይታ፣ ዝንጅብል ቆጮ (እንሰት) እና ቅመማቅመም፡፡ የግብይት ሁኔታ በተመለከተ የእነዚህ የበላይና ልዩ ምርቶች በእያንዳንዱ አካባቢ ይለያል፡፡

ማረቆ በርበሬ፣ በአዲስ አበባ ገበያ በከፍተኛ ዋጋ ይነገዳል፡፡ የአ/ምንጭ ሙዝ ወደ ዋና ዋና ከተሞች በሀገሪቱ የሥርጭት ሰንሰለት አለው፡፡ ቆጮ በቤት እመቤቶች በአብዛኛው ለቤት ውስጥ ፍጆታ ሲመረት ትርፍ ምርት በአካባቢው ገበያ ይሸጣል፡፡ ቆጮ ለገበያ የሚያቀነባብሩ ጥቂት ናቸው፡፡ ካሳቫ አዲስ ሰብል ሲሆን ፋኦ/ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከምግብ ዋስትናና ሰብል ዓይነት ከማብዛት አንፃር ምርቱን ለማስፋፋት እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ የካሳቫ ዱቄት ከፍተኛ እምቅ ኃይል ፍላጐት አለው፡፡ ከጤፍ ዱቄት ጋር ተዋህዶ እንጀራ ስለሚጋገር የሚመረጥ ቢሆንም ዝቅተኛ የደረቅ ካሳቫ ጥራት አንደ አደናቃፊ ችግር ሆኖ ይታያል፡፡

የግብርና አመራረት ዘዴ እነዚህን ታዋቂ የሆኑ ምርቶችን ጨምሮ ጥንት አያቶቻቸው እንደሚያመርቱ ሁሉ ማምረትና ትርፍ የሆነውን በአካባቢው ገበያ መሸጥ ነው፡፡ አስከአሁንም አርሶአደሮች የተጠቃሚዎች ፍላጐት ወይም የሸማቾች ምርጫ እንደ አዲስ አበባ ባሉ ትላልቅ ከተማዎች ምን እንደሆነ የሚያውቁበት የመረጃ ስርዓት የላቸውም፡፡ ስለዚህ አርሶአደሮች ገበያ ተኮር የማምረቻ ዘዴ ተጠቅመው ለማምረት የማያስቡበት መንገድ

የለም ብንል አያስደንቅም፡፡ ከዚህ በላይ የመንግስት ኤጀንሲዎች (ክልል፣ ዞንና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ) ኃላፊነት ያለባቸውም ቢሆንም ይህንን አያንቀሳቅሱም፡፡ ለምሳሌ የቦሎቄ የውጭ ገበያ እንዳለ የተነገረ ቢሆንም ለአምራች አርሶአደሮችና ነጋዴዎች በተጨባጭ የተደረገ ድጋፍ የለም፡፡

አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ አብዛኛዎች አርሶአደሮች የተጠቃሚዎች ፍላጐት የሚያውቁበት ዘዴ የላቸውም፡፡ ስለዚህ የመንግስት ኤጀንሲዎች (ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ) የገበያ መረጃ ድጋፍ ለአርሶ አደሮች ጥቅም ሲባል ማድረግ አለበት፡፡ ለክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በመጀመሪያ የውጭ ገበያ ማፈላለግና ማግኘት ከባድ ሊሆን ይችላል፣ ሆኖም በቅድሚያና በሀገር ውስጥ ገበያና ነጋዴዎች ጋር መሥራት አለበት፡፡ እምቅ የገዢ ኃይልና አርሶአደሮች ወይም የአካባቢ ነጋዴዎችን የሚያስተሳስር ሽያጭን እውን ለማድረግ መሠራት አለበት፡፡ የግብይት ድጋፍ (ምርጥ ዘር፣ ችግኝ የማራባት ዕውቀት) ክህሎት እና ድህረምርት ቴክኖሎጂ ድጋፍ ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ከምርት አከባቢ ምርቱን ሰብስቦ ለማጓጓዝ/ለማስተላላፍ የአካባቢ ነጋዴዎችን መጠቀም ይገባል፡፡ የሕ/ሥራ ማህበራት ቢዝነስ በአብዛኛው ልምድ በሌላቸው የሚሠራ ሲሆን የውድቀት ሥጋቱም ከፍተኛ ነው፡፡ የምርት ሽያጭ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ የአካባቢ ነጋዴዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ያለቸውን ዕውቀት/ ልምድ እና ካፒታል ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡ ካሳቫ፣ ዝንጅብል፣ ፍራፍሬ (ማንጎ አቮካዶ) ወዘተ እንደ የተለዩና ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለቸው ምርት ሆነው ማልማት ያስፈልጋል፡፡ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮም የገበያ ትስስርን በተመለከተ አጠናክሮ በገበያ የማፈላለግ ሥራ ማካሄድ ይጠበቃል፡፡

1/ ጥሩ ጥራት ያለው የካሳቫ ዱቄት የጤፍ ዱቄት ማሚያ ሆኖ ስለሚያገለግል ሰፊ እምቅ ፍላጐት አለው፡፡ የደቡብ ክልል ሞቃታማ አየር ተስማሚ ስለሆነ ማልማቱም ቀላል ነው፡፡ የካሳቫ ዱቄት ለማዘጋጀት (ደረቅ ካሳቫ) እንደ አዲስ የተለየ ምርት ገበያ ማስተዋወቅ ሥራ መሥራት አለበት፡፡

2/ ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ዝንጅብል የሀገር ውስጥ ፍላጐት/የገበያ አማራጭ መስመር ሊኖረው ይገባል፡፡ ምክንያቱም መደበኛ ሸማቾች ዝንጅብል በመሬት ላይ ያለንፅሕናና ቁጥጥር እንደሚደርቅ አያውቁም (ከዚህ በፊት ደረቅና ንፅሕና ያለው ዝንጅብል ለመግዛት ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም)፡፡ ስለዚህ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የሀገር ውስጥ የገበያ አማራጭ መስመር በመለየት እንዲሁም የምርት ማስተዋወቅና የገበያ ትስስር ድጋፍ ከሀገር ውስጥ ገዢዎች ጋር በመፍጠር ለውጭ ገበያ ማመቻቸት አለበት፡፡

3/ ማንጎን በተመለከተ ለአፍሪካ ጅውስ ኩባንያ ማንጎ ማቅረብ በከፍተኛ የምርት ወቅት የሚከሰተውን የዋጋ መውረድ ይቋቋማል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በአቅራቢዎች ወገን (ዩኒየኖች፣ ሕ/ሥራ ማህበራት፣ ወረዳና ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ መ/ቤቶች) የተረጋጋ የቢዝነስ ግንኙነት በመፍጠር የኩባኒያውን የጥራትና የመጠን ፍላጐት ለማሟላት መሥራት አለባቸው፡፡ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮም የመሪነት ሚና መጫወት አለበት፡፡

### እስትራቴጂ 2-5፡ የጋራ ግብይት ማፋጠን

በደቡብ ክልል ብዙ የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች አሉ፡፡ ሆኖም የእነዚህ ማህበራትና ዩኒያኖች ዋናው ሥራ የግብርና ግብዓት እንደ ማዳበሪያ፣ ኬሚካልና ምርጥ ዘር ለአባላት ማቅረብ ሲሆን የግብይት ሥራዎች በደንብ አልተደራጁም፡፡ በብዙ መልክ እንደሚታየውና በሪፖርትም እንደሚገለፀው በአርሶአደሮችና በነጋዴዎች መካከል በማሳ ላይ

ወይም በአካባቢው ገበያ በግል በሚደረገው ሽያጭ የአርሶአደሩ የመደራደር አቅም ደካማ ነው፡፡

የመደራደር አቅም ለማጠናከር የሽቀጥ መጠን በማሰባሰብ ማሣደግ /በግዙፍ ሽያጭ/ አስፈላጊ ነው የሚለው ንድፈሀሳብ ትክክል ነው፡፡ ሆኖም በተጨባጭ ሁኔታ አርሶአደሮች የግብርና ምርታቸውን በግል መሸጥ ይመርጣሉ፡፡ በተጨማሪ ከፍተኛ ጭማሪ በነጠላ ዋጋ ስሌት ማግኘት አይቻልም፡፡ ስለሆነም የግል ሽያጭን አያበረታታም፡፡

ስለዚህ አርሶአደሮችን ዝም ብሎ ግዙፍ የግብርና ምርት ሽያጭ እንዲያካሂድ ማበረታታት ጥቅም የለውም፡፡ የጋራ ግብይት ማስፋፋትን መደገፍ የጋራ ግብይት የግድ በሚሆንበት ጊዜ መሆን እንዳለበት፡፡ በተለይ የሚከተሉት ጉዳዮች ግምት ውስጥ ሊገቡ ይገባል፡፡

- ✓ አርሶአደሮች እሴትን የመጨማር ተግባር ከአካሄዱ፡
  ማንም ሰው የእሴት ጭማሪ ያለተጨማሪ ገቢ አይሠራም፡፡ ከዚህ በላይ እሴት መጨመር ያላቸውን ምርቶች ለመሸጥ ከመደበኛ ምርቶች መለየት ያስፈልጋል፡፡ የተጨማሪ እሴት ያላቸውን ምርቶች የጥራት ግንዛቤ ለአላቸው ሸማቾች በከተሞች አካባቢ መሸጥ ያስፈልጋል፡፡ ለግለሰብ አርሶአደሮች እንዲህ ያሉ ገዢዎችንና የቢዝነስ ግንኙነት መፍጠር አይቻልም፡፡
- ✓ ምርቱን በመንደር አካባቢ ለመሸጥ አስቸጋሪ ሲሆን፡
  ቦታው ከአካባቢው ገበያ በጣም የራቀ እንደሆነ፣ ወይም የገጠር መንገድ ሁኔታ በጣም የተበላሸ ሆኖ ነጋዴዎች ምርቱ ወዳለበት ለመምጣት ሳይችሉ ሲቀሩ፡፡
- ✓ አርሶአደሩ ግዙፍ መጠን ያለውን ምርት በራሱ ለመሸጥ ሳይችል ሲቀር፡

በአሁኑ ወቅት የጥራት ግንዛቤ ያላቸው የግብርና ምርት ገዢዎች በኢትዮጵያ በጣም ውሱን ናቸው፡፡ ስለዚህ ምናልባት አርሶአደሮች የተጨማሪ እሴት ለመፍጠር ሙከራ ቢያደርጉ የገበያ ትስስር ድጋፍ ለአርሶአደሮች ቡድን ወይም ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት መስጠት አለበት፡፡

### 5.2.7 መሠረታዊ እስትራቴጂ 3: የገበያ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ብቃት ያለው የገበያ መሠረተልማት ማሻሻል

#### እስትራቴጂ 3-1፡ ዋና ዋና መንገዶችን ወደ ወረዳ ገበያ ቦታዎችና አገናኝ መንገዶችን ወደ አካባቢ መንገዶች ማሻሻል

በደቡብ ክልል በጀት ውሱን ቢሆንም ዋና ዋና መንገዶች እያደጉ መጥተዋል፡፡ ክልሉ በ1993 (እ.ኤ.አ) ከተቋቋመ ወዲህ ጠቅላላ ርዝመት 4024 ኪ.ሜትር የነበረው መንገድ በ2009 (እ.ኤ.አ) ወደ 9488 ኪ.ሜትር ደርሷል፡፡ የመንገድ ጥግግት በ1993 (እ.ኤ.አ) 0.036 ኪ.ሜትር በእስኩዌር ኪ.ሜትር ከነበረው ወደ 0.066 ኪ.ሜትር በእስኩዌር ኪ.ሜትር ወይንም 0.28 ኪ.ሜትር በ1000 ሕዝብ የነበረው ወደ 0.63 ኪ.ሜትር በ1000 ሕዝብ አድጓል፡፡ በምዕራፍ 3.4 እንደተገለፀው የመንገድ ጥግግት እንደ አካባቢው መሬት ስፋት በወረዳ ደረጃ ከፍ ወይም ዝቅ የሚል ሲሆን ስብጥሩ በወረዳዎች መካከል የተሰበጣጠረ ነው፡፡ ነገር ግን የመንገድ ጥግግት በነፍስ ወከፍ ሲታይ ከወረዳ ወረዳ ያለው ልዩነት ትንሽ ነው፡፡ በምስል 3.4-1 እንደተመለከተው የመንገድ ልማት ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ውጭ በተናጠል ያደገ ይመስላል፡፡

የክልሉ መንገዶች ባለስልጣን የክልሉን የመንገድ ዕቅድ 2010/11-2014/15 (እ.ኤ.አ) መሠረት 57 አዳዲስ መንገዶች ግንባታና 11 የመንገድ ደረጃ ማሻሻል በድምሩ 1,578

ኪ.ሜትር ለመገንባት በሠንጠረዥ 3.4-3 በተገለፀው መሠረት ዕቅድ አውጥቷል፡፡ የታቀደው የመንገድ ጥግግት 0.075 ኪ.ሜ/በእስኩዌር ኪ.ሜትር ነው፡፡ መንገዶች ባለስልጣን ፕሮጀክቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ ያስቀመጣቸው መመዘኛዎች የሕዝብ ብዛት፣ የግብርና እምቅ ኃይል፣ የአካባቢ ሥነምህዳር ግንዛቤ እና የመንግስት ጥያቄ ወዘተ ናቸው፡፡ መንገዶች ባለስልጣን የተመዛዘነ ዕቅድ ላይ ሊገመገም ይችላል ምክንያቱም ቅድሚያ የተሰጠው አነስተኛ የመንገድ ልማት ላላቸው አካባቢዎች እንደ ጋሞ ጋፋ፣ ደ/ኦሞ፣ ሲዳማ፣ ሃዲያ ነው፡፡ ሆኖም በአሁኑ ሰዓት ዋና ዋና መንገዶች በበጀት እጥረት ምክንያት በመጥፎ ሁኔታ ላይ ናቸው፡፡ የመንገድ ጥገና ሥራዎች በመደበኛነትም ይከናወናሉ፡፡

የመንገዶች መሻሻል መጓተት የገጠር ልማት እንቅስቃሴዎችን ያጓትታል፡፡ ነጋዴዎችንም ምቹ ባልሆነ የመንገድ ሁኔታ ወደ ገበያ ሥርዓት መግባትን ተጎጂ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግብርና ምርት ጥራት በትራንስፖርት ምክንያት ይቀንሳል፡፡ ከዚህም የተነሳ ትርፍም ዝቅ ይላል፡፡

ከላይ የተገለፀው ችግር በዋና ዋና መንገድ ላይ ብቻ ሳይሆን የአገናኝ መንገድ ወደ ወረዳ ገበያ ሥፍራ ጭምር የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪ አብዛኛዎቹ አገናኝ መንገዶች ወደ አካባቢ ገበያ ሥፍራዎች የሚያደርሱት ክረምት ከበጋ መንገድ ሆነው አልተሻሻሉም፡፡ ከዚህ የተነሣ የአርሶአደሮች ትርፍ ከትራንስፖርት ሥርዓት ብቁ ባለመሆኑ ዝቅ ይላል፡፡ በተጨማሪ በትራንስፖርት ችግር የድህረምርት ጥራት ይቀንሳል፡፡ የአርሶአደሮች የተመረጡ ሰብሎች ማምረት ፍለጎት በደካማ ትራንስፖርት አገልግሎት ምክንያት ይቀንሳል፡፡ በጃይካ ጥናት ቡድን ባካሄደው የዳሰሳ ጥናት መሠረት 58% መላሾች (የግብርና አምራቾች ወይም በተዛማጅ ሥራ ያሉ) ባለው መንገድ ደስተኛ አይደሉም፡፡ 28.3% የሚሆኑት በጣም ከፍተኛ ችግር እንደሆነና አፋጣኝ እርምጃ ሊወስድ ይገባል ብለዋል፡፡ በሌላ በኩል መንገዶች ባለስልጣን የ2009/10 (እ.ኤ.አ) የመንገድ ግንባታ ዕቅድ መቀጠልና ለቀጣይ ጊዜ በሚከተሉት መመዘኛዎች መሠረት እንደሚሠራ ገልፆል፡፡

1. የወረዳ የሕዝብ ብዛት (40%)
2. የግብርና ምርት እምቅ ኃይል (20%)
3. የኢኮኖሚ ዕድገት (15%)
4. የቀበሌ መስፋትና የመንገድ አስፈላጊነት (10%)
5. ሌሎች (15%)

የመንገድ አውታር ማሻሻል ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚያስፈልግ እንደመሆኑ መጠን የወጪና የጥቅም ሚዛነዊነት በማገናዘብ መሆን አለበት፡፡ ጠንካራ የገበያ ትስስር ባሌለበትና ካለው የክልሉ ቆዳ ስፋት ትልቅነት አንፃር የመንገድ አውታር ዝርጋታ አግባብነት ባለው ስትራቴጂና ክልላዊ የፍትሃዊ ሀብት አጠቃቀም ጋር በተዛመድ መልክ መሆን አለበት፡፡ በምዕራፍ 3.4 እንደተገመገመው የቀድሞው የመንገድ ልማትና የአሁኑ መንገዶች ባለስልጣን አካሄድ አግባብነት አለው፡፡ ስለዚህ መንገዶች ባለስልጣን የልማት እቅዱን በመቀጠል የገጠር መንገድ ዕቅዱ በአግባቡና በወቅቱ ማከናወን እንዳለበት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በመሪ እቅዱ በዚህ እስትራቴጂ 3-1 የተያዘ እቅድ አይደለም፡፡

### እስትራቴጂ 3-2፡ በተመረጡ አካባቢዎች ወረዳ ገበያ ቦታዎች የገበያ መሠረተልማት ማሻሻል

የገበያ ቦታዎች በኢትዮጵያ ከሚገኙበት ቦታ አንፃር ውይንም ከላቸው ዕቃዎች እና ምቹ ሁኔታዎች በመነሳት ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ ይኸውም በዞን፣ ወረዳና የአካባቢ ገበያ ቦታ ተብለው ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡ የገበያ ቦታዎች የግብርና ምርቶችን ለመገበያየት ብቻ ሳይሆን እንደ ማህበራዊ ተቋም የመረጃ ልውውጥ ማዕከል ሆኖ ያገለግላሉ፡፡ የወረዳ ገበያ ቦታዎች ከ1-3 ሄክታር መሬት ያሏቸው ሲሆን ከእንጨት የሚሰሩ አመቺ ያለሆኑ ጎጆዎች/ከለላዎች

በስተቀር ያለምንም ቋሚ አገልግሎት መስጫ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፀሐይ ብርሃን ከዝናብ የሚከላከል መጠለያ እና የፍሳሽ ማስወገጃና የውሃ አገልግሎት የላቸውም፡፡ ስለሆነም የገበያ ስፍራዎች ንፅህና የጐደላቸውና ጭቃማ ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሣ በእነዚህ ሁኔታዎች በብቃት የግብርና ምርት ለማስገባትም ሆነ ለማስወጣት በጣም ያስቸግራል፡፡ በበጋ ወቅት ለመጠለያ የሚያገለግል ጣሪያ የሌለ ከመሆኑ ጋር በገበያ አገልግሎት መስጫዎች የተደራጁ ያለመሆን ጋር ተዳምሮ የግብይት ሥራ ምቹ አይደሉም፡፡

የገበያ ስፍራ አስተዳደርን በተመለከተ ብዙ ችግሮች አሉ፡፡ እንደ የጋራ መተዳደሪያና ገበያ ቦታ አጠቃቀም ሕግ ያለመኖር የሚያጠቃልል ነው፡፡ ገበያ ቦታዎች በከተማ ማዘጋጃ ቤት የሚመራ ቢሆንም የገበያ አስተዳዳር ሥራዎች በሙሉ ተሟልተው አይካሄዱም፡፡

ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል፣ ብቃት ያለው የንግድ እንቅስቃሴና የተሻለ ጥራትና የንግድ መጠን እንዲሁም መሠረተልማትና የገበያ አስተዳደርን ለማፋጠን የሚረዳ ከተመረጡ የግብርና ምርቶች አንፃር የልማት እቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ እንደ ጥናት ቡድኑ መረጃ መሠረት 79% ምላሾች አሁን ያለው ደካማ የገበያ ስፍራ እንዲሻሻል ጠንካራ ፍላጐት እንዳላቸው ግልጽ ሆኗል፡፡

ከዚህ በፊት እንደቀረበው በወረዳ የገበያ ስፍራዎች ብዙ ችግሮች ሊቃለሉ የሚገቡ ያሉ ሲሆን ብዙ ኢንቨስትመንት ወጪና ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ስለዚህ በዚህ መሪ ዕቅድ በተወሰነ በጀት እንደ ረዥም ጊዜ ራዕይ ተጨባጭ ሊሆን የሚችል ለወደፊት ለገበያ ስፍራ መስፋፋት የሚጠቅም ዕቅድ ሀሳብ ቀርቧል፡፡ ይኸውም ለተመረጠ ሰብለ በወረዳ ውስጥ የተወሰነ አከባቢ ገበያ ስፍራ ይመረጥና የገበያ መሠረተልማት በመገንባት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያ ዕቃዎች እንዲሟሉ በማድረግ ለተመረጠው ሰብል ብቻ የመገበያይበት የዋና ገበያ ስፍራ ሆኖ ይሠራል፡፡ ከዚያም ይህ አቀራረብ በሌሎች ሰብሎች በወረዳ ወይም ማዘጋጃ ቤት ቀስ በቀስ ሰፍቶ በተመሣሣይ ለሁሉ አቀፍ ገበያ ስፍራነት ይለማል፡፡

በክልሉ ግብይትና ሕ/ሥ ቢሮና የጃይካ ጥናት ቡድን መካካል ብዙ ውይይቶች ከተካሄዱ በኋላ ቦሎቄና ዝንጅብል እንደ ዋና ሰብሎች ሆነው በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ከብርዕና አገዳ ሰብሎች፣ ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬ አትክልትና ቅመማቅመም መካካል ተመርጠዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

<u>ቦሎቄ</u>፡

1. ቦሎቄ ክልሉን ከሚወክሉ ሰብሎች አንዱ ነው፡፡ በክልሉ የቦሎቄ ምርቱ ከባቄላ ምርት ቀጥሎ ሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ ሲሆን ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ምርት 18.2% ድርሻ አለው፡፡
2. በገበያ ቦታ ላይ ቦሎቄ ምርት ጥራት በጣም የወረደና ብዙ ባዕድ ነገሮች የተቀላቀሉበት ነው፡፡ በአግባቡ መጠለያ እና ወለል በአለው ቦታ መገበያየት የምርቱን ጥራት እንደሚያሻሽል ይገመታል፡፡
3. አግባብ ያላቸው መገልገያዎች በአሉበት ግብይት የሚካሄድ ፍትሃዊ ንግድ ሊኖር እንደሚችል ይገመታል፡፡
4. እንደ ኢትዮጵያ መንግስት መመሪያ ነጭ ቦሎቄ ከ2010 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ መገበያየት ተጀምሯል፡፡

<u>ዝንጅብል</u>፡

1. ዝንጅብል የደቡብ ክልልን የሚወክል ዋንኛው ምርት ሲሆን የኢትዮጵያ 99% የሚሆነው የዝንጅብል ምርት የሚመረተው በደቡብ ክልል ነው፡፡
2. ዝንጅብል በጣም ውድ ገቢ መስገኛ ሰብል ሲሆን አግባብነት ያለው የገበያ አገልግሎት ከቀረበ ፍትሃዊ ንግድ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡

3. ዝንጅብል በእርጥበት ሊሸጥ የሚችል ሲሆን እሴት በመጨመር ለምሣሌ በማድረቅ፣ አጥቦ በደረቅ ወዘተ ሊሸጥ ይችላል፡፡ ስለሆነም በድህረምርት የተቀነባበር ዝንጅብል ከፍ ባለ ዋጋ ሊሸጥ ይችላል፡፡

ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 እና ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 አማካኝነት ለተመረጡት ቦሎቄና ዝንጅብል ግብይት የሚያገለግሉ ሁለት አዲስ የሆኑ የገበያ ቦታዎችን የጃይካ ጥናት ቡድን ገንብቶ አስረክቧል፡፡ ለገበያ ማዕከሉም የአስተዳዳር ስርዓት ተዘጋጅቶ ተፈጻሚ እየሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የገበያ አሰተዳዳር አካል የተቋቋመ ሲሆን ማዘጋጃ ቤት በባለቤትነት ያስተዳደርል፡፡ በዚህ መሠረት 1) በአርሶአደሮችና የንግድ ፍቃድ በላቸው ነጋዴዎች መካከል ፍትሃዊ ንግድ እንዲኖር፣ 2) በገበያ ማዕከሉ ውስጥ በመገበያየታአቸው ሳቢያ የጥራት መሻሻል ይኖራል፣ እና 3) የማዘጋጃ ቤት ገቢ በሚሰበሰበው ታክስ የተነሳ ይጨምራል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች እውን የሆኑ ሲሆን የተገነባው የገበያ መሠረተልማት የገበያ ቦታውን እንቅሳሴ ውጤታማ ያደረገና ወደፊትም ለገበያ ቦታው ማሻሻል መነሻ ሆኖ እንሚያገለግል ይታመናል፡፡

በዓለም ባንክ ድጋፍ የሚካሄደው የግብርና ዕድገት ፕሮግራም ከጥቅምት 2010 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል፡፡ ፕሮግራሙ ካሉት 3 የስራ ክፍሎች አንዱ የገጠር መሠረተልማት ማስፋፋት ሲሆን ዓላማው የገጠር መሠረተልማት የገበያ ቦታን ጨምሮ መገንባት ነው፡፡ ሆኖም ግብርና ዕድገት ፕሮግራም ገንዘብ ድጋፍ እንጂ የቴክኒክና የገበያ ቦታ አስተዳዳር ድጋፍን አያካትትም፡፡ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በአሁኑ ወቅት ግብርና ዕድገት ፕሮግራም 7 አዳዲስ የገበያ መሠረተልማት በ6 ወረዳዎች በ4 ዞኖች በመገንባት ላይ ነው፡፡ የጃይካ ጥናት ቡድን ለገበያ መሠረተልማት ግንባታ የሚያስፈልጉ ማንኛውንም መረጃ እንደ ዲዛይን/ንድፍ፣ የሥራ መጠን፣ የሥራ ዝርዝር መግለጫ ወዘተ ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 እና ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 ለገበያ ግንባታ ያዘጋጀውን ለግብርና ዕድገት ፕሮግራም የግንባታ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ሰጥቷል፡፡ የጃይጃ ጥናት ቡድን በተጨማሪ ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 እና ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 ልምዶችን ለወረዳና ለዞን ባለሙያዎች ሰጥቷል፡፡ በአውደጥናቱ የሚከተሉትን ጉዳዮች 1) የአስተዳደር ሁኔታ፣ 2) ቴክኒክ ሁኔታ የሚከተለውን በማካተት ሀ) ዕቅድ ዝግጅት፣ ለ) ዲዛይን/ንድፍ፣ ሐ) ግንባታ፣ እና መ) የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 እና 07 ልምዶች፣ 3) የቤሊሳ ገበያ መሠረተልማት የአስተዳዳር ኮሚቴ ልምድ ማካፈል፣ እና 4) በገበያ ቀን የቤሊሳ ገበያ መሠረተልማት ጉብኝት ማድረግ ያካትትል፡፡ ከላይ እንደተብራራው የጃይካ ጥናት ቡድንና የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በቅርበት ከግብርና ዕድገት ፕሮግራም ጋር ይተባበሩ ነበር፡፡

በዚህ ልምድና በተገኘው ውጤት "የገበያ መሠረተልማት/የገበያ ቦታ ማሻሻያ ፕሮግራም" እንደ አንዱ የመሪ ዕቅድ አካል ሆኖ ቀርቧል፡፡ በዚህ ፕሮግራም ለቦሎቄና ዝንጅብል ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የፕሮጀክት ዕቅዶች ለሌሎች የግብርና ምርቶች ተዘጋጅቷል፡፡ ይህንን ፕሮግራም ለመፈፀም የገንዘብ ድጋፍ እንዲመደብ መጠበቅ የማይቀር ነው፡፡ ለፕሮግራሙ የተመረጡ ወረዳዎች በሙሉ የታቀፉ አይደሉም፡፡ ስለሆነም በቅድሚያ የቅርብ ግንኙነትና ትብብር በግብርና ዕድገት ፕሮግራም እና ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ መካከል ማደረግ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

### እስትራቴጂ 3-3፡ የሀዋሣ ከተማ የገበያ ሥፍራ መሠረተ ልማት ማሻሻል

የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች በሥልጠና ፕሮግራም ልምድ ለመቅሰም ጃፓን ሀገር ሄዶ በነበረበት ወቅት ከአገኙት ተሞክሮ በመነሳት የሀዋሣ ከተማ የገበያ ማዕከል መሠረተልማት ማሻሻያ ዕቅድ አዘጋጅተው ነበር፡፡ የግንባታው ወጪ የግብርና ዕድገት

ፕሮግራም ሊሸፈን እንደሚችል ተስፋ ስለአለ ይህ ዕቅድ "የሀዋሣ ከተማ የገበያ ሥፍራ መሠረተ ልማት ማሻሻያ ፕሮግራም" በመባል በመሪ ዕቅዱ ተካቷል፡፡

### እስትራቴጂ 3-4፡ ነባር መጋዘን ለውጤታማ አጠቃቀም ማሻሻልና አዲስ መጋዘን ግንባታ

በኢትዮጵያ የግብርና መጋዘኖች በመንግስታዊ አካል፣ ሕ/ሥራ ዩኒየኖችና በግለሰቦች ይተዳደራሉ፡፡ ሆኖም አብዛኛዎቹ መጋዘኖች አስፈላጊ የሆኑ እንደ መተላለፊያ መስመር፣ መጀመሪያ የገባ መጀመሪያ ይወጣል ለሚለው አሠራር በሚመች መልኩ የመግቢያና የመውጪያ፣ የጥራት ማረጋገጫ እርምጃዎች (የተባይ ማጥፊያ፣ የአየር ማስገቢያ ወዘተ) አያሟሉም፡፡ እነዚህ መጋዘኖች የተገነቡት ያለ እስትራቴጂክ ዕቅድ የክልሉን ሁኔታ፣ ተስማሚ መጠን ወዘተ ሳያገናዝቡ በመሆኑ ምንም ዓይነት ውጤታማ አጠቃቀም አይታይም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛዎቹ የዲዛይን ጉድለት ያለባቸውና ጠንካራ ግድግዳ ሳይኖራቸው ለረዥም ጊዜ መጋዘንነት ያገለገሉና አንዳንድ ጊዜ ማዳበሪያና ዘር ተቀላቅለው በአንድ ላይ የሚቀመጥባቸውና ደካማ መጋዘን አስተዳዳር ያላቸው ናቸው፡፡

ውጤታማ የግብርና ገበያ ሥርዓት ለማጠናከርና የመጋዘን ብክነት ለመቀነስ ለውጤታማና ጤናማ የመጋዘን አስተዳዳር ከላይ የተዘረዘሩ፣ ችግሮችን ማስወገድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አግባብነት ያለውን አገልግሎት የሚሰጥ አዲስ መጋዘን ለመገንባት ከፍተኛ በጀት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በመሪ ዕቅዱ ነባር መጋዘኖችን ማሻሻልን ተካቷል፡፡ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 08 አማካኝነት የጃይካ ጥናት ቡድን 500 ቶን የመያዝ አቅም ያለው መጋዘን በመገንባት የራሱ መጋዘን ላልነበረ አንድ ሕ/ሥራ ዩኒያን የሰጠ ሲሆን አግባብነት ያለው የመጋዘን አስተዳዳር ሥርዓትም እንዲዘረጋ አድረጓል፡፡ የነባሪ መጋዘን ማሻሻልን በተመለከተ የጥናት ቡድኑ "ነባር የግብርና መጋዘን ማሻሻያ መምሪያ" እና "የግብርና መጋዘን የሥራ ሂደት መመሪያ" አዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪ የጥናት ቡድኑ ለሌሎች ሕ/ሥራ ዩኒያኖችና በሥራቸው ለሚገኙ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት አዲስ ወደ ተገነባው መጋዘን በመጋበዝ አግባብ ያለው የመጋዘን አስተዳዳር ሥልጠና በመስጠት የዕውቀት ሽግግር አድርጓል፡፡ ሆኖም ሥልጠናው ለተወሰኑ ባለድርሻ አካላት የተሰጠ ስለሆነ ቀጣይና ተከታታይ ሥልጠና ለቀሪዎች እንደሚሰጥ ይጠበቃል፡፡ ከዚያም "የግብርና መጋዘን ግንባታና ነባር መጋዘን ማሻሻያ ፕሮግራም" በአግባቡ የግብርና መጋዘኖችን መጠቀም እንዲያስችል ታስቧል፡፡ ይህ ፕሮግራም ለባለድርሻ አካላት አግባብ ያለውን የቴክኒክ ድጋፍ ለአዲስ መጋዘን ግንባታና ለነባር መጋዘን ማሻሻያ ይሰጣል፡፡ አግባብነት ላለው የግብርና መጋዘን አስተዳዳር የስልጠና ፕሮግራም በእስትራቴጂ 2-2 ተገልፆል፡፡

### እስትራቴጂ 3-5፡ በመንገድ ዳር የግብርና ምርት ሽያጭ ማስፋፋት

ከደቡብ ክልል ዋና ዋና የገበያ መስመሮች 1) ሀዋሣ መስመር፣ 2) ሆሣዕና -አ/ምንጭ መስመር፣ እና 3) ጅማ መስመር ናቸው፡፡ በእነዚህ የንግድ መስመሮች ወይም ዋና ዋና ከተሞች አካባቢ የመንገድ ዳር የግብርና ምርት የሚሸጡ አሉ፡፡ እነዚህ መንገድ ዳር ሻጮች በግል የሚሠሩና የሽያጭ ቦታ ወይም ድርጅት የተመቻቸ ስለሌላቸው የተረጋጉ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል በእነዚህ መስመሮች ላይ በመንገድ ዳር ምርታቸውን አስቀምጠው የሚሸጡ ስላሉ ረዥም መንገድ ተጓዦችንና መንገድ ተጠቃሚዎችን ምቾች ያሳጣሉ፡፡ እነዚህን የማይመቹ ሁኔታዎችን ለማቃለልና የክልሉን የተለየ ባህሪይ ለማበረታታት፤ ጥቂት አግባብነት ያላቸው የመንገድ ዳር የመሸጫ ቦታዎች በእስትራቴጂክ ጣቢያዎች ተለይተዋል፡፡ የሽያጭ ቦታዎቹ ለተላላፊ ሾፌሮች፣ ለመንገድ ተጠቃሚዎችና ቸርቻሪዎች የመኪና ማቆሚያ፣ ሽንት ቤት ወዘተ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ ተጠቃሚዎች እየበዙ ሲሄዱ፣ የመግዛት አቅም፣ ንግድ ልውውጥ እንደሚጨምር ይጠበቃል፡፡

ሆኖም በኢትዮጵያ የሞተር አገልግሎት እምብዛም ያላደገ በመሆኑ የመንገድ ዳር የገበያ ቦታ ማልማት ለሾፌሮች ወይም ለመንገድ ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆን ለክልሉ ሕዝብ ነው። ይህ ማለት የገበያ ቦታ ማልማት ቋሚ ገበያ በመንገድ ዳር ማደራጀትና የአካባቢ ግብርና ምርት ለመንገድ ተጠቃሚዎች መሸጥ በመሆኑ የክልሉ ህ/ሰብ እርስበርስና ከመንገድ ተጠቃሚዎች ጋር መገናኘት ያስችላል። በዚህ መሠረት "የመንገድ ዳር የገጠር ማስፋፋት ማዕከል" በመባል "የገጠር ምርት ሽያጭ ማስፋፋት በመንገድ ዳር መሠረተልማት ፕሮግራም" ሥር እንዲካተት ሳብ ቀርቧል። የቦታዎቹ መረጣ የሚከተሉትን ነጥቦች መሠረት አድርጐ የሚወሰን ይሆናል።

1. የሚቋቋመውን ማዕከል በሥነ ሥርዓት የታነፀ ድርጅት ሊመራው ይገባል።
2. በቂ የትራፊክ ፍሰት መኖሩ መረጋገጥ አለበት፣
3. ማዕከሉን ለማቋቋም መሬት መኖሩን ማረጋገጥ፣
4. የተለየ የግብርና ምርት ለችርቻሮ መኖሩን ማረጋገጥ፣

የሚከተሉት አገልግሎቶች በማዕከሉ መሟላት አለባቸው።

- መግቢያና መውጪያ ተደራሽነት
- ለትላልቅ 5 መኪናዎችና ለትናንሽ /መካከለኛ/ 20 መኪናዎች የሚበቃ ጠጠር የለበሰ የመኪና ማቆሚያ መኖር
- በአከባቢው የውሃ አገልግሎት ያለ
- መጠነኛ ኪዮስክና የቡና ቤት ያለ
- ለምርቶቹ የችርቻሮ ሱቆች ያሉት ናቸው።




**ምስል 5-3 የመንገድ ዳር የገጠር ማስፋፊያ ማዕከል ሥዕላዊ ገጽታ**

የማዕከሉን ዘላቂነት በግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አስተዳደሩ በክልላዊ ተቋም የሚመራ መሆን አለበት። የአመራር አካሉ ከብዙ ተወዳዳሪዎች መካከል ሆኖ በቂ ችሎታና ለስራው ጠንካራ ፍላጐት ያለው መሆን ይገባል። የአመራር አካሉን ለመምረጥ የሚከተለውን ሂደት የመከተል ሃሣብ ቀርቧል።




**ምስል 5-4 የመንገድ ዳር የገጠር ማስፋፊያ ማዕከል የግንባታ ቦታ መምረጫ የሥራ ፍሰት**

### 5.2.8 መሠረታዊ እስትራቴጂ 4፡ የግብርና ግብይት ተቋማዊ ስርዓት መጀመርና ማስተካከል

በ1990 (እ.ኤ.አ) ኢትዮጵያ በሶሻሊስት ስርዓት ስር የእዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት ስታራምድ ነበር፡፡ የሶቬት ህብረት ከወደቀ በኋላ ኢትዮጵያ ወደ ገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት ገባች፡፡ የኢንዱስትሪ ማቴሪያሎች ብቻ ሳይሆን የግብርና ገበያ ጭምር ነፃና ከቁጥጥር ስርዓት እንዲወጡ ተደረገ፡፡ ከዚያም በኋላ የመንግሥት ለውጥ ተደርጎ አሃዳዊ ስልጣን ወደ ክልሎች እንዲወርድ በመደረጉ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግስትም የራሱን የእድገት ፖሊሲዎችን ቀርፆ እንዲተገበር ተደርጓል፡፡

የአከባቢው መንግስት የድጋፍ ስርዓትና የማስፈፀም ብቃት ማሣደግና ተግባራዊ ማድረግ ቁልፍ እስትራቴጂ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ ምክንያቱም የግብርና ግብይት ስርዓት የመንግስት ቀጥተኛ ያልሆነ ድጋፍ ለግል ንግድ የሚሰጥበት ነው፡፡ በተለይ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ብዙ ባለድርሻ አካላትን ተሣትፎ በማጠናከር እና ተግባራዊ መርሃግብር በመቅረፅ የእስትራቴጂ 1-3 ዓላማዎች ለማሣካት ማዕከላዊ ሚና መጫወት አለበት፡፡ ስለሆነም የቢሮ የማስፈፀበም ብቃት ዓላማውን ለማሣካት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ የግብይትና

ሕ/ሥራ ቢሮ የክልሉን የግብርና ግብይት ስርዓት በማሻሻል የሀገር አቀፍ የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ሂደት የራሱን ሚና ለመጫወት እንዲችል ኢኮኖሚውን ለማንቀሣቀስ ትልቅ ሃላፊነት አለበት፡፡

ስለዚህ በስርዓቱ ያሉትን ጉዳዮች ለማቃለል አስፈላጊ የሆኑ የመሪ ዕቅዱ እስትራቴጂዎች በቀጣይ 2018 (እ.ኤ.አ) ግብ የተቀመጡት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## እስትራቴጂ 4-1፡ በግብርና ግብይት ባለድርሻ አካላት መካከል የተፋጠ ትብብር ማስፈን

የመሠረታዊ እስትራቴጂ 1፣2 እና 3 ሀሣቦችን ለማከናወን የክልሉ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ብቻውን ሊፈፅመው የሚችለው ነገር ቢኖር እንኳን ትንሽ ነው፡፡ የገበያ መረጃ አገልግሎትን በተመለከተ ከሌሎች የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ከሚሰሩና ከሬዲዮ ጣቢያ ባለሙያዎች ጋር ትብብር መኖር አለበት፡፡ በተመሣሣይ የገበያ ልውውጥን በተመለከተ ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ፣ ከንግድ ምክር ቤት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጋር መተባበር አስፈላጊነት ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ የገበያ ቦታና መገልገያዎችን ለማስተዳዳር አብሮ ለመስራት ማዘጋጃ ቤት እምቅ ኃይል ያለው አጋር ነው፡፡ ለመንገድ ጥገና የክልሉ መንገዶች ባለስልጣን ፕሮጀክቶችን በጋራ ለመፈፀም ያስፈልጋል፡፡ የመንግስት የገጠር ፋይናንስ ፈንድ ወይም የግል የፋይናንስ ተቋማት በገጠር ፋይናንስ በጋራ መስራት ያለባቸው ሚና የጎላ ነው፡፡

ስለሆነም በዚህ የልማት ፕላን የክልሉ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የመደራደር ችሎታን ለማሻሻልና የሌሎችን የነቃ ትብብር ለማግኘት ከሌሎች ተባባሪ ኤጀንሲዎች ጋር ተባባሪነትን ማፋጠን እንዳለበት ሀሣብ ቀርቧል፡፡ በተለይ የሌሎች ተባባሪ ኤጀንሲዎች መልካም ትብብር በግንኙነት ማሻሻል በመንገድ መሠረተልማትና የገበያ መሠረተልማት አመራር ላይ ለክልል ቢሮ ባለሙያዎች ማጠናከር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች ሌሎች ኤጀንሲዎች በልማት ዕቅድ በንቃት እንዲሣተፉ የማብቃት አቅም እንዲያሰፉና እንዲጠናክሩ ይጠበቃል፡፡

## እስትራቴጂ 4-2፡ የሥራ ዝርዝር/የመለኪያ ደረጃ ማስተዋወቅና መጠበቅ

ወደ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ዝውውር ከተደረገ ወዲህ የምግብ እጥረት እና የምግብ ዋስትና ማሻሻል ለረዥም ጊዜ የቆየ ያልተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ ለሽያጭ የሰብል ልማት ማስፋፋት ኢኮኖሚውን ለማነቃቃች ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ መንግስት ትርፍ ምርት ያላቸውን አርሶአደሮች የገበያ ተደራሽነት እንዲያገኙና የግብርና ሴክተር በአጠቃላይ እንዲለማ የተፋጠነ የገበያ ተደራሽነት እንዲፈጠር ከፍተኛ ትኩረት እየሰጠ ነው፡፡ በእርግጥ መንግስት ያቀደው የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የግብርና ግብይት በማጠናከር ኢኮኖሚውን ማልማት ጐን ለጐን በማካሄድ ሌሎችንም አላማ ጨምሮ ግቡን እንዲመታ ነው፡፡ ይህንን አላማ ለማሳካት እንደ ግብይት ስርዓት ማሻሻያ ዕቅድ በሚያዚያ 2008 (እ.ኤ.አ) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መንግስታዊ ተቋም ተቋቋመ፡፡

የዓለም የምግብ ፕሮግራም ከውጪ የሚያስገባውን እህል የምግብ ዋስትና ችግር ላሉባቸው አከባቢዎች ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን በምግብ እርዳታ ላይ ትችት እያደገ መጥቷል፡፡ ምክንያቱም የምግብ እርዳታው ተከታታይነት ያለውን የግብርና ልማት ስለሚረብሽ እና በትርፍ ምርት አከባቢ የዋጋ መውረድ ስለሚያስከትል ነው፡፡ ስለዚህ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ከአርሶ አደሮች ቀጥታ ግዥ በማካሄድ ገቢ ለማሣደግ እና ለሚሠነዘረው ትችት ምላሽ ለመስጠት ግዥ ለዕድገት የተባለውን ፕሮግራም በ2009 (እ.ኤ.አ) ጀመረ፡፡ የዓለም ምግብ ፕሮግራም የሚያልመው የምግብ ዋስትና ችግር ለማቃለል እና ትርፍ እህል

ከአላቸው አካባቢ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ስርዓት መግዛት ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተከተለው የግብርና ኢ-ንግድ ስርዓት ነው፡፡ ሆኖም ከማዕከላዊ መንግስትና በሴክተሩ ከሚንቀሳቀሱ ኃይላት መካከል ያለው የግንዛቤ ልዩነት ሰፊ ሲሆን የመንግስት ተቋም ስርዓትና ፖሊሲ ወደ ህዝቡ በተግባራዊነቱ እየደረሰ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመለኪያ ደረጃ ስርዓት ለግብርና ምርት ንግድ ምቹ ሁኔታ ለመፈጠር በጣም ጠቃሚ የሆነው በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃ ባለሥጣን ቁጥጥር ስራ ነበር፡፡ ሆኖም ቁጥጥሩ በአሁኑ ወቅት ወደ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተዛውሯል፡፡ የንግድ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የከለኪያ መሣሪያዎቹን ለመቆጣጠርና ማረጋገጫ ለመስጠት ሀላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም ቁጥጥሩ በቂ አይደለም፡፡ ስለሆነም ብዙ የመለኪያ መሣሪያዎች ማረጋገጫ ሳይሰጣቸው ግን በአገልግሎት ላይ እየዋሉ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር የግብይት ስርዓት ለማሻሻል በጋራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

የተቋማዊ ስርዓትና ፖሊሲ በአደጉ የአውሮፖ ሀገራትና በአሜሪካ መንግስታት አማካኝነት እንዲተዋወቅ ተደርጓል፡፡ ምንም እንኳን ይዘቱ የሚስማማ ቢሆንም በንደፈ.ሀሳብና እና በተግባራዊነቱ መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ ሲሆን ክፍተቱን ለማጥበብ የተግባራዊ የሚሆን ዘዴ ማግኘት በጣም ከባድ ነው፡፡ ንድፈ.ሀሳብ ቢደጋገም እንኳን በመስኩ የሚንቀሳቀሱ ኃይላት ሊከተሉት አይችሉም፡፡ ስለዚህ መንግስት ሕግ በማውጣት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ሆኖም በመስክ ላይ ሕጉን ለመረዳት ጊዜ መውሰዱ አይቀርም፡፡ የዚህ ነገር አስፈፃሚ አካል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ስላልሆነ በመሪ ዕቅዱ አይጠቃለልም፡፡

## እስትራቴጂ 4-3፡ ለሕ/ሥራ ማህበራት/ዩኒየኖች የድጋፍ ስርዓት ማጠናከር

በደቡብ ክልል የአርሶአደሮች መተዳደሪያ በግብርና ነው፡፡ የግብርና ምርቶች በገበያ ውስጥ ልውውጥ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ ቢሆንም አርሶአደሮች ለገበያ መረጃ የመግኘት ዕድል/አጋጣሚ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ከነጋዴዎች ጋር የመደራደር አቅም የላቸውም፡፡ ምንም እንኳን የአነስተኛ አርሶአደሮችን መተዳደሪያ ለማሻሻል ሕ/ሥራ ማህበራት በጋራ ግብይት በመሳተፍ ዋነኛ ሚና እንደሚጫወቱ ቢገመትም ድርጅታዊና የቴክኒክ አቅም ያለመኖር እንዲሁም የአባላት በማህበራቸው በቂ እምነት ማጣት ሕ/ሥራ ማህበራት ሊደርሱበት የሚገባቸውን ደረጃ እንዳይደርሱ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ይህንን ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሚከተለው ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡

- ሕ/ሥራ ማህበራት በግልፀኝነት እና በተጠያቂነት መርህ መሠረት የጋራ ግብይት ቢዝነስ ወደ ፕሮፌሽናል እና ዲሞክራቲክ ድርጅት እንዲያድጉ ድጋፍ መስጠት፣
- ለሕ/ሥራ ማህበራት የሚሠራ የድጋፍ ስርዓት ለማቋቋም ከክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ አንስቶ እስከ ወረዳ ለአለው መዋቅር ባለሙያዎች ድጋፍ መስጠት፣

<u>ለእህል ሕ/ሥራ ማህበራት የጋራ ግብይት አቅም ማሣደግ</u>

ይህ ዓላማ የሚያደርገው በዓለም ምግብ ፕሮግራም/ግዥ ለዕድገት የሚሣተፉ 84 ሕ/ሥራ ማህበራትን ነው፡፡ የአስተዳዳርና የቴክኒክ አቅም ደካማነታቸውን በመገንዘብ ተከታታይ ስልጠናዎች ይካሄዳሉ፡፡ የስልጠናው አይነት በተመለከተ ድርጅታዊ አስተዳዳር፣ የፆታ እኩልነት ስርጸት፣ የሂሳብ አያየዝ፣ የጥራት ቁጥጥር፣ የመጋዘን አስተዳዳር እና የግብይት ስርዓት ይሆናሉ፡፡ በኮርሱ ሂደት የግዥ ለዕድገት ተሣታፊ ሕ/ሥራ ማህበራት የቢዝነስ ስራ አቅም ለመገመት የፍላጐት ደሰሳ ጥናት ይካሄዳል፡፡ የዳሰሳ ጥናቱ ውጤት ምን አይነት ሁኔታ ጣልቃ መግባት ብቃትና ውጤት እንደሚያስገኝ ዲዛይን ለማድረግ ወደ አፈፃፀም ለማምጣት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የአንዱ ሕ/ሥራ ማህበር ድርጅታዊ አቅም ከሌላው ስለሚለይ መደበኛ ደረጃ ያለው አቀራረብ ለሁሉም ሕ/ሥራ ማህበር ዩኒያኖች ተግባራዊና ጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

*እህል ነክ ባልሆኑ ምርቶች የሕ/ሥራ ማህበራት የመገበያየት አቅም ማሣደግ*

*እነዚያን እህል ነክ ባልሆኑ ምርቶች ላይ የሚሳተፉ ወይም በእህል ነክ ባልሆኑ ገቢ ማስገኛ እህል በጋራ ግብይት ለመሳተፍ እቅድ ያላቸውን አላማ ያደርጋል፡፡ ተነፃፃሪ ጥቅም ያላቸው እንደ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ዝንጅብል፣ ካሳቫ እና በርበሬ እንደ ገቢ ማስገኛ እህል ስለሚያስቀምጣቸው ድጋፉ የሚሰጣቸው ሕ/ሥራ ማህበራት በነዚህ ሰብሎች ግብይት እየተሳተፉ ያሉት ወይም ለመሳተፍ እቅድ ያላቸው ይሆናል፡፡ ሕ/ሥራ ማህበራቱ በድርጅታዊ አስተዳዳር፣ የፆታ እኩልነት ስርጸት፣ የሂሳብ አያየዝ፣ ድህረምርት አያያዝና ግብይት ስርዓት ከገበያ ጥናት ጋር ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ በግብይት ስርዓት የሚሰጠው ስልጠና የተጠቃሚዎችን እና የሸማቾችን ፍላጐትና ምርጫ እንዲሁም በተመረጠው ሰብል የግብይት ስርዓትና የዋጋ ትመና ዘዴ ግንዛቤ ለማሳደግ ነው፡፡ የገበያ ጥናቱ ውጤት በአመራረትና ድህረምርት አያያዝ ስልጠና ይካተታል፡፡ በነዚህ በተለዩ ሰብሎች የሚሳተፉ ሕ/ሥራ ማህበራት ጋሞ ጎፋ ሕ/ሥራ ዩኒያን (ማንጎ) ዳሞታ ወላይታ ማህበራት ዩኒያን (ዝንጅብልና) አምበርቾ ሕ/ሥራ ማህበር ዩኒያን (ዝንጅብል) ናቸው፡፡ ስለሆነም ለጊዜው ፕሮጀክቱ ከነዚህ 3 ዩኒያኖች ጋር ይሰራል፡፡*

*በግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የሕ/ሥራ ማህበራት ድጋፍ ስርዓት መዘርጋት*

*ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትን ለማሠልጠን የግብይት እና ሕ/ሥራ ቢሮ ኃላፊነት አለበት፡፡ የስልጠና ፕሮግራሙ ድርጅታዊና ቴክኒክ ጉዳዮችን የሚያጠቃልል እንደመሆኑ መጠን አንድ የኤክስፐርቶች ቡድን ከሕ/ሥራ ማህበራት ልማት እና ከግብይት የሥራ ሂደቶች ይቋቋማል፡፡ የኤክስፐርቶች ቡድን ዋና ዋና ስራዎች ከታች ተዘርዝረዋል፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ስራዎች ለቢሮው አዲስ ባይሆኑም ያለፈው ልምድ የሚያሳየው በቢሮው ትልቅ የአቀራረብ እና የስራ ለውጥ እንዳለ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በቂ እና አግባብነት ያለው የውጭ አማካሪ ተቀጥሮ ለክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡*

*ሀ) የስልጠና ማቴሪያል ማዘጋጀት*

*ለሁሉም ኮርሶች ወይም ትምህርቶች የስልጠና ማቴሪያል ይዘጋጃል፡፡ ማቴሪያሎችን በማዘጋጀቱ ረገድ የሚከተሉት ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ ይገባል፡፡ ናሙና የስልጠና ማቴሪያል በተቀጽላነት በጥራዝ 2 ታይቷል፡፡*

1. *የሠልጣኞችን ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ በመረዳት የስልጠና ይዘቱ ቀላልና ግልፅ መሆን አለበት*
2. *የስልጠና ይዘቱ በዝቅተኛ የገንዘብ ወጪ ለማከናወን ቀላል መሆን አለበት*
3. *በስልጠና የተገኘ ቴክኖሎጂ ወይም አውቀት ተግባራዊ በሆነ ጊዜ ወዲያውኑ ተጨባጭ ጥቅም ለሰልጣኙ መስጠት የሚችል መሆን አለበት*
4. *የስልጠናው ይዘት በሰልጣኞች ፍላጐት ተመርኩዞ የተዘጋጀ መሆን አለበት*
5. *የስልጠናው ማቴሪያሎች ከተጠቃሚዎች ጋር የሚስማሙ ይዘቱ ግልፅ እና በደንብ የተብራራ እና አሰልጣኙ ያለምንም ችግር ማሰልጠን የሚችልበት መሆን አለበት*

*በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 02 እንደተረጋገጠው "ስዕላዊ ካርዶች" እንደ ስልጠና ማቴሪያሎች የመጠቀም ዘዴ እና ቀላል ያሉ የስልጠና መርጃ ቁሳቁሶች ከአሰልጣኞች መመሪያ ጋር መጠቀም በገጠር አከባቢ ለአርሶአደሮች ስልጠና ለመስጠት አመቺ ናቸው፡፡ ስለሆነም ተመሳሳይ ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት የሚያስፈለግ ይሆናል፡፡*

*ለ) ከላይ ወደ ታች ገረጃ በደረጃ የሚሰጥ የስልጠና ስርዓት ማደራጀት*

*የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 02 አድርጐ ውጤታማነቱ ያረጋገጠውን ከላይ ወደ ታች ገረጃ በደረጃ የሚሰጥ የስልጠና ስርዓት መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ቢሮው የአሰልጣኞች ስልጠና ለወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ይሰጣል፡፡ የወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በተዋረድ በራሱ አከባቢ ለአሉ ለሕ/ሥራ ማህበራት ስልጠና ያዘጋጃል፡፡*

ሐ) የክትትል ስራዎችን መፈፀም
የክትትል ስራዎች የስልጠና ፕሮግራሙን ውጤታማነትና ችግሮችን ለመመርመር ይዘጋጃል፡፡ በዚህ መሠረት አስፈላጊ ከሆነ የስልጠና ማቴሪያሎች ወይም አካሄዶች ይከለሣሉ ወይም ይሻሻላሉ፡፡

መ/ ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ድጋፍ
የአሰልጣኞች ስልጠና ከተቀበሉ በኋላ የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የሕ/ሥራ ማህበራት ለስልጠና ያዘጋጃሉ፡፡ በቀጣዩ ዓመት የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ለአዳዲስ ሕ/ሥራ ማህበራት ወይም የአርሶአደሮች ቡድን በራሳቸው ስልጠና ያዘጋጃሉ፡፡ ከዚህ አይነት ስልጠና ቀደም ብሎ የክልል ቢሮ የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትን የአሠራር ዝግጅትና የበጀት እቅድ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### እስትራቴጂ 4-4፡ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች አቅም ማሣደግ

በምርት ልማት የግብርና የገበያ ምርት በማስተዋወቅ እና የገበያ መረጃ በማሰራጨት የክልሉን የግብርና ግብይት ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡ በበጀት እጥረት እና በፕሮጀክት አተገባበርና አስተዳዳር ያለው ልምድ በተጨባጭ ማነስ ምክንያት እንደ ተገመተው ተልዕኮ አልተፈፀመም፡፡ አብዛኛዎቹ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች ወደ ውጭ ሀገር ሄደው ስልጠና ወስደዋል፣ ሴሚናሮችን ተሳትፈዋል፡፡ ነገር ግን ያገኙትን እውቀት ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አዛምደውና አሻሽለው አልሰሩትም፡፡ ከዚህ የምናስተውለው እነዚህ ኤክስፐርቶች ስልጠናውን ለራሣቸው ጥቅም ብቻ እንደሚወስዱና የውጪ ጉብኚዎች እድል ለማግኘት ሲባል እንደሚሄዱ ያስመስላል፡፡ የነዚህ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርቶች አእምሮ መቀየር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ የ2 ዓመት መሪ እቅድ ጥናት ወቅት 8 ሰልጣኞች ውጭ ሀገር ተጋብዘዋል፡፡ ነገር ግን ሁለቱ ወደ ውጭ ሀገር ጉዞ ከመደረጉ ጥቂት ሣምንታት ሲቀሩ ጉዞውን ሰርዘዋል፡፡ ከ6 ሰልጣኞች 3ቱ ከስልጠናው በኋላ ወዲያው የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮን ለቀዋል፡፡ የስልጠናው ከክፍያው ነፃ መሆን እነርሱን ለስልጠው ለማዘጋጀት የፈሰሰውን ጉልበትና የገንዘብ ወጪ ከፍተኛ መሆኑን ግንዛቤ እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡ ከዚህ ሌላ የመማር ጉጉትና ለሀገራቸው ዕድገት አስተዋፅኦ ሊያደርግ የሚችል በጐ ሕሊና እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡

የስልጠናው ውጤት በአእምሮአቸው ብቻ የሚቀር ከሆነ እና ወደ ሌሎች የማይሸጋገር ከሆነ የስልጠና ፕሮግራሙን እንደገና መከለስና በመንግስት ኤክስፐርቶች ምትክ የግል ገበያ ተዋንያንን መጋበዝ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

ስለዚህ ይህ መሪ ዕቅድ ከላይ ወደ ታች ደረጃ በደረጃ የሚሰጥ ስልጠናዎች ለአርሶአደሮችና በሕ/ሥራ ማህበራት ትክክለኛ ሥራዎች ተመሠርቶ እንዲሰጥ ሀሣብ ያቀርባል፡፡

## 5.3 የመሪ ዕቅድ ፕሮግራም

### 5.3.1 የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ማልማት

እንደ መሪ እቅድ ፕሮግራም የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ለማስፋፋት <u>የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት ቁጥር 1</u> ተግባራዊ እንዲሆን ሀሣብ ቀርቧል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ስርዓት በግብይትና ሕ/ሥራ ማህበር አመራር ሥር ለማቋቋም የታቀደ ነው፡፡ ባለፈው ምዕራፍ በመሰረታዊ እስትራቴጂ 1 በተገለፀው መሠረት ከዚህ በታች 6 የሥራ ክፍሎች ተዘርዝረዋል፡፡

ክፍል 1 ፡ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት አጭር የጽሑፍ መልዕክት እና ማስታወቂያ ቦርድ በ6 የተመረጡ ሰብሎች እና በ82 ወረዳዎች ደረጃ በደረጃ ማስፋፋት፡፡
ክፍል 2 ፡ የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በክልሉ ግንኙነት ላሏቸው ቢሮዎች ማሠራጨት
ክፍል 3 ፡ የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በሬዲዮ እና በጋዜጣ ማሠራጨት
ክፍል 4 ፡ የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በቢሮ ድህረገጽ ማሠራጨት
ክፍል 5 ፡ የአዲስ አበባ ገበያ መረጃ ከኦሮሚያ ግብይት ኤጀንሲ ማግኘት
ክፍል 6 ፡ የሰሊጥ የጨረታ ዋጋ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማግኘት

እነዚህ 6 የሥራ ክፍሎች በማስተባባር እንደ አንደ ፕሮግራም ሆነው ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ ከሥራ ክፍል 2 እስከ 6 ያሉት ክፍሎች የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት አጭር የጽሑፍ መልዕክት እና ማስታወቂያ ቦርድ በ6 የተመረጡ ሰብሎች እና በ82 ወረዳዎች ደረጃ በደረጃ በማስፋፋት ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

በስትራቴጂ 1-1 በተቀመጠው የእቅድ ዝግጅት መርህ መሠረት ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት በተመረጡ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/በቶችና ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የመረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት የ5 ዓመት እቅድ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

ለአዳዲስ ሰብሎች ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የዝንጅብል ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት እና የቦሎቄ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት እንደገና ሊጀመር ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለፕሮጀክት መጀመር እንደቅድመ ሁኔታ ለፕሮጀክቱ በጀት ማዘጋጀትና ተጨማሪ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ባለሙያዎች በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በመቅጠር በአንደኛው ዓመት 2013 (እ.ኤ.አ) መካሄድ አለበት፡፡

**ሠንጠረዥ 5-5 የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሥርዓት የመዘርጋት ሂደት**

| ዋና ተግባር | የተመረጠ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ሥርዓቱ የሚዘረጋበት ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት |
|---|---|---|
| **አንደኛ ዓመት** (2013 እ.ኤ.አ) | | |
| 1. ለዝንጅብልና ቦሎቄ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት አስፈላጊ በጀት መመደብ | 5 + 9 | 0 |
| 2. ለ83 ወረዳዎች፣ 8 ሰብሎች፣ የምርት ዓይነት፣ የገበያ ቦታ ኮድ መስጠት | | |
| 3. ለበላይ መ/ቤትና ለሌሎች መረጃ የሚለክበትን የአሠራር ሕግ ማውጣት | | |
| 4. ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልግ በጀት ማግኘት፣ እና በግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የገበይት መረጃ ሠራተኛ የሚጨምርበትን ሁኔታ ማመቻቸት | | |
| 5. ለግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የሥራ ማስኬጃ በጀት የሚመደብበትን ሁኔታ ማመቻቸት | | |
| 6. በከምባታ ማህበረሰብ ሬድዮ መረጃ መስራጨት መጀመር | | |
| **ሁለተኛ ዓመት** (2014 እ.ኤ.አ) | | |
| 1. የመረጃ ቋት የኮምፒውተር ፕሮግራም ማዘጋጀት | | |
| 2. የማንጎና በርበሬ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት መዘርጋት | 7 + 7 | 3 + 6 |
| 3. በ14 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የበቆሎ ሥርዓት መዘርጋት | 14 | 0 |
| 4. በብዙሃን መገኛኛ ድርጅት ሬድዮ/ጋዜጣ መረጃ መስራጨት መጀመር | | |

| ዋና ተግባር | የተመረጠ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ሥርዓቱ የሚዘረጋበት ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት |
|---|---|---|
| 5. አድስ ሠራተኛ ለግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ መቅጠር | | |
| 6. ለተሰበሰበ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ/መረጃ ማከማቻ መፍጠር | | |
| **ሦስተኛ ዓመት** (2015 እ.ኤ.አ) | | |
| 1. ለሰሊጥና አቮካዶ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት መዘርጋት | 8 + 20 | 8 + 15 |
| 2. በ5 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የበቆሎ ሥርዓት መዘርጋት | 5 | 0 |
| 3. በግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ድህረ ገጽ መረጃ መጫን | | |
| 4. የአዲስ አበባን የዋጋ መረጃ ከኦሮሚያ ገበያ ኤጀንሲ ማግኘት | | |
| 5. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጨረታ የሰሊጥ ዋጋ መማግኘት መጀመር | | |
| **አራተኛ ዓመት** (2016 እ.ኤ.አ) | | |
| 1. ለስንዴ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት መዘርጋት | 18 | 18 |
| 2. በ4 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የበቆሎ ሥርዓት መዘርጋት | 4 | 0 |
| **አምስተኛ** (2017 እ.ኤ.አ) | | |
| 1. ለተቀሩት 19 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የበቆሎ ሥርዓት መዘርጋት | 19 | 19 |

### 5.3.2 የከፍተኛ እሴት ጭማሪ የግብይት የማስፋፋት እቅድ

በመሠረታዊ እስትራቴጂ 2 መሠረት የሚከተሉት 5 ፕሮግራሞች እና አንድ የሥራ እቅድ በመሪ ዕቅዱ እንደ ፕሮግራም ሆነው በ6 ሰብሎች ለከፍተኛ እሴት ጭማሪ ታስቧል፡፡

1. ማንጐ አቮካዶ — የፍራፍሬ ብክነት መቋቋሚያ ፕሮግራም
2. ቲማቲም — የአትክልት ማጓጓዣ ዘመናዊ ማድረግያ ፕሮግራም
3. ብርዕና አገዳ ሰብል — የጥራት ቁጥጥር ክህሎት ማሰራጫ ፕሮግራም
4. ካሳቫ — ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ ማስፋፊያ ፕሮግራም
5. ዝንጅብል — ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ዝንጅብል ማስፋፊያ ፕሮግራም
6. እርድ — የእርድ ድህረምርት ማሻሻያ እቅድ

#### (1) የፍራፍሬ ብክነት ማቋቋሚያ ፕሮግራም

በእስትራቴጂ 2-1 መሠረት ከዚህ በታች የተመለከቱ 3 ተግባራት/ፕሮጀክቶች ቀርበዋል፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 2፡ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 የተመረጡ ቡድኖች ድጋፍና ክትትል</u>

በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት እንዲሁም የቀበሌ ሕብረተሰብ አደራጆች የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 ተሣታፊ 3 ቦታዎች የተሰጡ መገልገያ ዕቃዎች ውጤታማ አጠቃቀምና ቀጣይነት ያለው የጋራ ግብይት ጥረት እንዲቀጥል መሠረታዊ ሕ/ ሥራ ማህበራት የመስክ ክትትል በማድረግ ምክርና ድጋፍ መስጠት፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 3፡ የፍራፍሬ ማምረቻ እቃዎች የማስታወቂያ ፕሮጀክት</u>

በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 የተዘጋጁ የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁሶች በተመረጡ 18 ወረዳዎች ማስተዋወቅ፡፡ በአርሶአደሮች የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ፍላጐት ለመፍጠር ሀ)

በማውረጃ ቁሳቁሱ መጠቀም ያለውን ጥቅም ማስረዳት እና በሰርቶ ማሣያ ማሣየት፣ ለ) ፖስተሮችን በቀበሌዎች መለጠፍ፣ እና ሐ) ለቁልፍ አርሶአደሮች በነፃ ማውረጃ ቁሳቁሱን መስጠት፡፡ የፕሮጀክቱ ዓላማ አዲሱ ማውረጃ ቁሳቁስ በፍራፍሬ መሸጫ አከባቢ ገበያ ላይ እንደ ማጭድ እና መኮትኮቻ ለሽያጭ የሚቀርብበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ፍራፍሬ ማውረጃውን የሚመረትበት አካባቢ ለገበያ የሚያመርቱን ማበረታታት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፕሮጀክቱ ከጥራት ፈላጊ ገዥዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 4፡ ለአፍሪካ ጀውስ ኩባንያ ጋር የማንጐ ሽያጭ እውን እንዲሆን ድጋፍ መስጠት</u>

በደቡብ ክልል ባሉ 2 በፍራፍሬ ላይ ከሚሠሩ ዩኒያኖች እና የአፍሪካ ጅውስ ኩባንያ መካከል የተረጋጋ የንግድ ግንኙነት መፍጠር፡፡ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የንግድ ግንኙነት በመፍጠር የመሪነት ሚና መጫወት ያለበት ሲሆን ዩኒያኖችን እና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትን መደገፍ አለበት፡፡

የ3ቱ ፕሮጀክቶች የአፈፃፀም ጊዜ ሰሌዳ በሚቀጥለው ቻርት ታይቷል፡፡ የሥራ እንቅስቃሴዎቹ በማንጎ ዋና የምርት ወቅት የሚካሄዱ ይሆናል፡፡




**ምስል 5-5 የፍራፍሬ ምርት ብክነት መቋቋሚያ ፕሮግራም የአፈፃፀም ጊዜ ሠሌዳ**

### (2) የአትክልት ማጓጓዣ ዘመናዊ ማድረግያ ፕሮግራም

ከእስትራቴጂ 2-1 ጋር በተጣጣመ መልክ የሚከተሉት 2 ፕሮጀክቶች ታስበዋል፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 5፡ ወደ ከተማ አካባቢ የሚደረገው የቲማቲም ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት</u>

<u>ደረጃ 1 ፡ ሞዴል ማቋቋም</u>

የአርሶአደሮች በምርት ሥራ ወቅትና በማጓጓዣ ወቅት የሚፈጠረውን የቲማቲም ምርት ብክነት ለመከላከልና ችግር ለመፍታት ፕሮጀክቱ በሀዋሣ ከተማ አከባቢ በመስኖ ቲማቲም የአምራቾች ቡድን የቲማቲም ማጓጓዣ ማሻሻያ ሞዴል ለማቋቋም ጥረት ያደርጋል፡፡ ፕሮጀክቱ ሁለት ሞዴሎች ቡድኖችን ለማቋቋም ዓላማ አድርጓል፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 6፡ ወደ ከተማ አካባቢ የሚደረገው የቲማቲም ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት</u>

<u>ደረጃ 2 : የመነሻ ወጪ ዝግጅትና የመፈፀም ድጋፍ ዕቅድ</u>

የመነሻ ወጪ እገዛ ሥርዓት በማዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ እንደ ፕላስቲክ ሣጥን ያለ ምርት መያዥያ መገልገያ በማስተዋወቅ የቲማቲም ምርት በሚሰበሰብበትና በሚጓጓዝበት

ወቅት የሚደርሰውን የአርሶአደሮች የምርት ብክነት ለማቋቋምና የጋራ ግብይት ለማስፍን እገዛ መስጠት፡፡

የሁለቱ ፕሮጀክቶች የአፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳ በቀጣዩ ቻርት ቀርቧል፡፡ ፕሮጀክት ቁጥር 6 ከፕሮጀክት ቁጥር 5 በኋላ በተከታታይነት መከናወን አለበት፡፡




**ምስል 5-6 የአትክልት ማጓጓዣ ዘመናዊ ማድረግያ ፕሮግራም የአፈፃፀም ጊዜ ሠሌዳ**

### (3) የጥራት ቁጥጥር ክህሎት ማሰራጫ ፕሮግራም

ከእስትራቴጂ 2-2 ጋር በሚጣጣም መልኩ የሚከተለው ፕሮጀክት ቀርቧል፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 7፡ የሕ/ሥራ ማህበራት በእህል ሰብልና ጥራጥሬ የጥራት ቁጥጥርና የመጋዘን አስተዳዳር አቅም ማሳደግ</u>

በጥራት ቁጥጥርና የመጋዘን አስተዳዳር ውጤታማነት የሥልጠና ዘዴና የማስተማሪያ ቁሳቁስ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 02 ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ ፕሮጀክት የሚያቅደው በየደረጃው ለአሉ አካለት ከላይ ወደ ታች ደረጃ በደረጃ ስልጠና ለ7 ሕ/ሥራ ዩኒያኖች አባል ለሆኑ ለ65 ቀደም ብለው ስልጠና ላልወሰዱ ሕ/ሥራ ማህበራት ለመስጠት ነው፡፡

### (4) ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ ማስፋፊያ ፕሮግራም

ከእስትራቴጂ 2-3 ጋር በሚጣጣም መልክ የሚከተሉት 3 ተግባራት/ፕሮጀክቶች ታስቧል፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 8፡ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 ለተመረጡ ቡድኖች የክትትል ድጋፍ</u>

የደረቅ ካሰቫ ማቀነባበርና ግብይት በአነስኛ አርሶአደር ቡድኖች የተሞከረው በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 ነበር፡፡ ክልል/ዞንና/ ወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ መ/ቤቶች ለተመረጡ ቡድኖች (12 የአርሶአደር ቡድኖች በ2 ወረዳዎች በተለይ በኦፋ ወረዳ ያሉ ቡድኖች) ድጋፉ መቀጠል ይኖርበቸዋል፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 9፡ ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ የማምረት ቢዝነስ ማስፋፊያ ድጋፍ፡</u>

በካሳቫ አምራች ወላይታ ዞንና ጋሙጎፋ ዛን ያሉ የአርሶአደር ቡድኖች የደረቅ ካሳቫ ማቀነባበሪያ ግብይት ችግሮችን ተቋቁመው ለመሣተፍ ይፈልጋሉ፡፡ የክልል/የዞንና/የወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ ለአርሶአደር ቡድኖች የቴክኒክ ስልጠና፣ የገበያ ትስስር መፍጠርና ለመነሻ ግብዓት መግዣ ብድር እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 10፡ ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ ሽያጭ ማስፋፋት፡</u>

የከፍተኛ ጥራትና ትንሽንሽ መጠን ያለው ደረቅ ካሳቫ በሀዋሣ አካባቢ ሸማቾች የሚፈለግ/የሚወደድ መሆኑ ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 አፈፃፀም ተረጋግጧል፡፡ ከፍተኛ ጥራት ያለውን የደረቅ ካሳቫ ምርት በከፍተኛ ሸማቾች እንደ አ/አበባ እና ናዝሬት

አካባቢ የገበያ በማፈላለግ ማስፋፋት ጠቃሚ ነው፡፡ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ለንፁሕ ደረቅ ካሳቫ በአ/አበባና በናዝሬት የገበያ መፈላለግ መሸጫ አውተሩን ማስፋፋት አለበት፡፡

### (5) ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ዝንጅብል ማስፋፋያ ፕሮግራም

ከእስትራቴጂ 2-3 ጋር በሚጣጣም መልክ የሚከተሉት 2 ፕሮጀክቶች ታስበዋል፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 11፡ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 የተመረጡ ቡድኖች ክትትልና ድጋፍ

የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 የንፁህ ደረቅ ዝንጅብል ምርት ለ2 አርሶአደሮች/ነጋዴዎች ቡድኖች ድጋፍ አድርጓል፡፡ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ለ2ቱ ቡድኖች በቀጣይ 2 የምርት ወቅቶች (2012/13 እና 2013/14 እ.ኤ.አ) የቢዝነስ ሥራቸው ቀጣይ እንዲሆንና እንዲጠናከር ክትትልና የምክር ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 12፡ በዝንጅብል ማጠብና ማድረቅ ቢዝነስ ፕሮጀክት

በዝንጅብል ምርት አካባቢ ያሉት ሌሎች የአርሶአደሮች/ነጋዴዎች ቡድኖችን ከሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 ተመሳሳይ በሆነ ደረጃ በዝንጅብል ማጠብና ማድረቅ ቢዝነስ እንዲገቡ መደገፍ፡፡ ፕሮጀክቱ ዓላማ የሚያደርገው 2 ቡድኖች በየምርት ወቅት በአጠቃላይ (2014/15 እስከ 2016/17 እ.ኤ.አ) 6 ቡድኖችን ለመደገፍ ነው፡፡ በመጨረሻው የምርት ወቅት (2016/17) ቡድኖቹ በፍላጐታቸው የድጋፍ ማመልከቻ (ከታች ወደ ላይ) የሚያቀርቡበት ዘዴ መሞከር አለበት፡፡

### (6) የእርድ ድህረምርት ማሻሻያ ዕቅድ

ከእስትራቴጂ 2-3 ጋር በሚጣጣም መልክ የሚከተለው ሥራ ዕቅድ ታስቧል፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 13፡ የእርድ ድህረ ምርት ማሻሻያ ማቀድ

አሁን ያለውን የእርድ ድህረምርት ማቀነባበሪያና ማሰባሰቢያ ሥራ በመለወጥ የገበያ ተኮር እና ተግባራዊ ሊሆን ወደ ሚችል "መዘፍዘፍ + ግፍት በአለው ውሃ የማጠብ ዘዴ" ቴክኖሎጂ መቀየርን የሚያችል ምርምርና ጥናት ማካሄድ፡፡ ምናልባት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ቴክኖሎጂ ከተገኘ በኋላ ማስተዋወቅያ እስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ለማድረግ የድጋፍ ፕሮጀክት ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

## 5.3.3 ለግብርና ምርቶች የገበያ መሠረተልማት ማቀድ

በመሠረታዊ እስትራቴጂ 3 በተገለፀው መሠረት የሚከተሉት 4 ፕሮግራሞች እንደ መሪ ዕቅድ ፕሮግራም ለግብርና ምርቶች የገበያ መሠረተልማት የልማት ዕቅድ እንቅስቃሴዎች አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ ታስበዋል፡፡

1. የወረዳ ገበያ ቦታ ማሻሻያ ፕሮግራም
2. የሀዋሣ ከተማ ገበያ ቦታ ማሻሻያ ፕሮግራም
3. የግብርና መጋዘን ግንባታና ነባር መጋዘን ማሻሻያ ፕሮግራም
4. የገጠር ምርቶችን በመንገድ ዳር መሸጫ መሠረተልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም

### (1) የወረዳ ገበያ ሥፍራ ማሻሻያ ፕሮግራም

በዚህ ፕሮግራም ሥር የሚከተሉት 5 ፕሮጀክቶች ለማከናወን ታስቧል፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 14፡ ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 የቦሎቄ ገበያ መሠረተልማት ድጋፍ

በቦሪቻ ወረዳ በቤሊላ ገበያ ሥፍራ በጃይካ የጥናት ቡድን ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 የተገነባው የቦሎቄ ገበያ ቦታ ትክክለኛ አመራር ያገኘ እንደሆነ ለሌሎች ለሚገነቡ ገበያ ማዕከል የቦሎቄ ገበያ መሠረተልማት ማሻሻያ ፕሮጀክት ውጤቱንና ድጋፉን ለማንፀባረቅ እንዲቻል በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 15፡ የቦሎቄ ገበያ መሠረተልማት፡

አዲስ የቦሎቄ ገበያ ማዕከል በ8 ወረዳዎች የቦሪቻ ወረዳን ሳያካትት በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 የተጀመረው የግብርና የገበያ መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ በተካሄደባቸው መገንባትና አመራር ድጋፍም መስጠት፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 16፡ ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 የዝንጅብል ገበያ መሠረተልማት ድጋፍ

በፕሮጀክት ቁጥር 16 የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ አሁን በከተማ የተገነባውን የገበያ ማዕከል አመራር ከላይ የተገለፁትን ጥቅሞች ይቀጥሉ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ክትትል በማድረግና ማረጋገጫ በመስጠት ያሁኑ ማዕከሉ ለሌሎች አዲስ ለሚተዋወቁ ገበያ ቦታ ጥሩ ናሙና እንዲሆን ይሠራል፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 17፡ የዝንጅብል ገበያ መሠረተልማት ማልማት፡

አዲስ የዝንጅብል ገበያ ሕንፃዎች በ8 ወረዳዎች ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 ለግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት የተጀመሩት ከሀዳሮ ጡንጦ ወረዳ ካምባታ ጠምባሮ ዞን በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 ከተቋቋመው በቀር መገንባት፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 18፡ ለገጠር የግብርና ምርት የገበያ መሠረተልማት ማልማት፡

የገበያ መሠረተልማት ለገጠር ግብርና ምርቶች ከቦሎቄና ዝንጅብል በቀር ለመቀጠል ይህ ፕሮጀክት ታስቧል፡፡ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በግብርና ዕድገት ፕሮግራም በሚገነባው የገበያ ማዕከል ላይ በቴክኒክና በአመራር አኳያ በአውንታዊነት ይሳተፋል፡፡

### (2) የሀዋሣ ከተማ ገበያ ሥፍራ መሠረተልማት ማሻሻያ ፕሮግራም

የገበያ ማዕከል ግንባታ በሀዋሣ ከተማ በግብርና ዕድገት ፕሮግራም በጀት ተጀምሯል፡፡ በዚህ ፕሮግራም ከዚህ ሌላ የታሰበ ፕሮጀክት የለም፡፡

### (3) የግብርና መጋዘን ግንባታና የነባር መጋዘን ማሻሻያ ፕሮግራም

በዚህ ፕሮግራም የሚከተሉት 2 ፕሮጀክቶች ለማንቀሳቀስ ታስቧል፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 19፡ ደረጃውን የጠበቀ የግብርና መጋዘን ማስፋፋት

ፕሮጀክት ቁጥር 19 ደረጃውን የጠበቀ 500 ቶን አቅም ያለው መጋዘን ዲዛይንና የኮንትራክተር ግዢ ዕውቀት እና ሌሎች ቴክኒክ ምክር ለአዲስ መጋዘን ግንባታ ይሰጣል፡፡

ፕሮጀክት ቁጥር 20፡ ነባር የግብርና መጋዘን ማሻሻያ ፕሮጀክት

የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ለባለድርሻ አካላት አግባብነት ያለው የቴክኒክ መመሪያና ለነባር መጋዘኖች ለውጤታማ አጠቃቀም የሚሆን የማሻሻያ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### (4) የገጠር ምርቶች የመንገድ ዳር መሸጫ መሠረተልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም

በዚህ ፕሮግራም የሚቀጥለው ፕሮጀክት ለማንቀሳቀስ ታስቧል፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 21፡ የገጠር መንገድ ዳር ገበያ ማዕከል ማስፋፊያ ፕሮግራም</u>

የገጠር ኢኮኖሚ ለማጠናከር ለማንቀሳቀስና የክልሉን ሕዝብ እና ከሌሎች ክልል ሕዝቦች ጋር በዋና መንገድ ዳር በተገነቡ ማዕከላት ለማስተሳሰር መሥራት ያስፈልጋል፡፡

### 5.3.4 ለሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች የአቅም ግንባታ ማጠናከሪያ ዕቅድ

በመሠረታዊ እስትራቴጂ 4 እንደተገለፀው የአቅም ግንባታ ማጠናከሪያ ለሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች ፕሮግራም የሚቀጥሉትን 2 ፕሮጀክቶች ያካትታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በእነዚህ 2 ፕሮጀክቶች አፈፃፀም የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና በመስመሩ ያሉ ጽ/ቤቶች የፕሮጀክቱ ጊዜ ካለፈ በኋላ ቀጣይ ተግባራዊ የሚሆን ሥርዓት መሥራት አለባቸው፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 22፡ የእህል ሕ/ሥራ ማህበራት የጋራ ግብይት አቅም ግንባታ ማስፋፋት</u>

ፕሮጀክቱ አጠቃላይ ስልጠና በዓለም ምግብ ፕሮግራም/ግዥ ለዕድገት ለሚሣተፉት ለ9 ዩኒያኖች እና 84 መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ይሰጣል፡፡

<u>ፕሮጀክት ቁጥር 23፡ ሕ/ሥራ ማህበራትና እህል ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ግብይት አቅም ግንባታ ማስፋፋት</u>

የግብርና ግብይት ማጠናከሪያ የጥናት ፕሮጀክት 5 የገቢ ማስገኛ ሰብሎችን (ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ዝንጅብል፣ ካሳቫና በርበሬ) አንፃራዊ ጠቀሜታ እንዳላቸው ለይቷቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት ፕሮጀክቱ አጠቃላይ የሥልጠና ፕሮግራም ለ26 መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት በጋራ ግብይት ለመሣተፍ ፍላጐት ለአላቸው ወይም ለሚሣተፉ ይሰጣል፡፡ በመጨረሻም ፕሮጀክቱ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ውስጥ ለሕ/ሥራ ማህበራት አዲስ ቢዝነስ በሚጀምሩበት ወቅት ውጤታማ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት ለማቋቋም ይፈልጋል፡፡

# ምዕራፍ 6 የፕሮጀክት ዕቅድ

## 6.1 ፕሮጀክት እቅድ ማዘጋጃ ፖሊሲ

መሪ ዕቅዱ ፕሮጀክት ዕቅዶችን ያካተተ ሲሆን እያንዳንዱ ፕሮጀክት ተግባራዊ የሚሆን ተጨባጭ የድርጊት መርሀግብር አለው፡፡ የፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅቱ ከአስሩ የሙከራ ትግበራ ፕሮጅክቶች የተገኘውን ተሞክሮና መረጃዎች መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች በተመለከተው ፅንሰሀሳብ ላይ ተንተርሶ ተዘጋጅቷል፡፡

1. ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን በጀት በአስተማማኝ ሁኔታ በማግኘትና ከሌሎች ዕርዳታ ሰጪ ድረጅቶች በተለይም በዓለም ባንክ ከሚታገዘው የግብርና ዕድገት ፕሮግራምና ከዓለም የምግብ ፕሮግራም ግኘ ለዕድገት ጋር መተባበር
2. ተግባራዊ የሚሆነው የፕሮጀክት ዕቅድ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች አፈጻጸምን ያንፀበርቃል
3. ሁሉን አቀፍ የሆነ ሰፊ አቀራረብ
4. በምርት አካባቢ ትኩረት ማድረግ (እምቅ አቅም ያለው የተመረጠ ምርትና አካባቢን ማብዛት)
5. ተጨባጭ የሆነ ትርፍ ለማሳደግ በሚያችል አካሄድ ማምረት
7. በሚኖረው በጀት መጠን መከናወን የሚችል ፕሮጀክት

## 6.2 የፕሮጀክት ዕቅድ ባህሪይ መለኪያዎች

የ 5 ዓመት መሪ ዕቅድ አካል የሆኑት ፕሮጀክቶች የተዘጋጁት በዋናነት የአስሩን የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች "ቀጣይነት"፣ "ግብ የተጣለባቸው አካባቢዎች ማስፋትን"፣ እና "በሌሎች ሰብሎች ተግባራዊ የማድረግን" ፅንሰሀሳብ ይዞ ነው፡፡

የፕሮጀክቶች ዕቅድ ይዘት በምዕራፍ 6.4 በተመለከተው ሠንጠረዥ የታየ ሲሆን ሠንጠረዡም የሚከተሉ መለኪያዎች አካቷል፡፡

1. የልማት እስትራቴጅና የመሪ ዕቅድ ፕሮግራም
2. ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ
3. የተመረጠ/ግብ የተጣለበት አካባቢና ሰብል
4. ግብ የተጣለበት ቡድን (ተጠቃሚ)
5. መነሻ ሀሳብና አላማ
6. ድርጊቶች
7. ግብአትና ወጪ
8. የማስፈጸሚያ የጊዜ ሰሌዳ
9. ምርመራ

የፕሮጀክት ወጪን በተመለከተ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ትክክለኛ ወጪ ላይ ተመሥርቶ ነው የተገመተው፡፡ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በአሁኑ ወቅት ያለውን የዋጋ ጭማሪ እግምት ውስጥ በማስገባት 10% መጠባበቂያ ተይዟል፡፡ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች (ክልል፣ ዞንና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ) አበል በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት ወቅት የነበው እንዳለ ተወስዷል፡፡ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ በወጪ ላይ አልተጨመረም፡፡

## 6.3 የፕሮጀክት ዕቅዶች ዝርዝር

ከ2013 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ይሆናሉ ተብሎ የሚገመቱ 23 ፕሮጀክቶች ዕቅድ በሚከተለው ሠንጠረዥ (1) ተመልክቷል፡፡

<u>የፕሮጀክት ዕቅዶችን ማስተዋወቅ</u>

የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በጀትና የሰው ኃይል እግንዛቤ ውስጥ በማስገባት 23 ፕሮጀክቶች እንደጠቃሚነታቸው የቀደምትነት ውሳኔ በመስጠት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ረቂቅ የፕሮጅክት ዕቅዶች ነሐሴ 2012 (እ.ኤ.አ) ለግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ቀርቦው እያንዳንዱ ፕሮጀክት ላይ ገለጻ በመስጠት ውይይት ተደርጓል፡፡ ከእያንዳንዱ አቻ ባለሙያ ስለፕሮጀክቶች ቅድመተከተል ቅኝት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ ጥቅምት 2012 (እ.ኤ.አ) ሀዋሣ በተካሄደው የመጨረሻ አውደ ጥናት ለጋሽ/አጋር ይሆናሉ ተብለው የሚጠበቁ የዓለም ባንክ/ግብርና ዕድገት ፕሮግራም፣ ዓለም አቀፍ ገንዘብ ለግብርና ልማት/አሚፕ፣ የዓለም የምግብ ፕሮግራም እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተገኙበት ስለፕሮጀክት ዕቅዶች ገለጻ ተሰጥቷል፡፡

ይሁን እንጂ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የፕሮጀክት ዕቅዶች ቅድመተከተል ለይቶ ያላስቀመጠ በመሆኑ በዚህ ሪፖርት ውስጥ አልታየም፡፡

## ሠንጠረዥ 6-1 የፕረጀክት ዕቅድ ዝርዝር

| መሠረታዊ እስትራቴጂ | እስትራቴጂ | የፕሮጀክት ዕቅድ | ጠሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት |
|---|---|---|---|
| 1. የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ለማጠናከር | 1. የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት በአጭር ጽሑፍ መልዕክት እና ማስታወቂያ ቦርድ የሚካሄደው ወደ ሌሎች ጠቃሚ ሰብሎች ደረጃ በደረጃ ማስፋፋት<br>2. የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ መጠቀም<br>3. ያለውን የመረጃ ሀብት መጠቀም | 1. የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ለማስፋፋት የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.01 የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከር |
| 2. ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይትን በማስተዋወቅ ትርፍ ማሳደግ | 1. የፍራፍሬና አትክልት መሰብሰብና አያያዝ ዘዴ ማሻሻያ | 2. በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 የተመረጡ ቡድኖች ድጋፍና ክትትል<br>3. የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁሶችን የማስታወቂያ ፕሮጀክት | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.03 በማንጎና አቮካዶ ምርት አሰባሰብና አያያዝ ማሻሻል |
| | | 5. ወደ ከተማ አካባቢ የሚደረገው የቲማቲም ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት ደረጃ 1 ፡ ሞዴል ማቋቋም | |
| | | 6. ወደ ከተማ አካባቢ የሚደረገው የቲማቲም ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት ደረጃ 2 ፡ የመነሻ ወጪ ዝግጅትና የመፈፀም ድጋፍ ዕቅድ | |
| | 2. ጥራት ግንዛቤ ባለው ገበያ የሚደረገውን ተሳትፎ ማፍጠንና ማጠንከር | 7. የሕ/ሥራ ማህበራት በእህል ሰብልና ጥራጥሬ የጥራት ቁጥጥርና የመጋዘን አስተዳዳር አቅም ማሳደግ | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.02 የሕ/ሥራ ዩኒያኖች በብርዕና አገዳ ሰብል እና ጥራጥሬ የጥራት ቁጥጥር የአቅም ማሣደግ (ከዓለም የምግብ ፕሮግራም/ግዢ ለዕድገት ጋር መተባበር) |
| | 3. በአምራቾች አካባቢ የእሴት ጭማሪ ሥራዎች ማሳደግ | 8. በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 ለተመረጡ ቡድኖች የክትትል ድጋፍ<br>9. ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ የማምረት ቢዝነስ ማስፋፊያ ድጋፍ | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.04 የደረቅ ካሳቫ ጥራትና ገበያ ልማት ማሻሻያ ፕሮጀክት |
| | | 11. በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 የተመረጡ ቡድኖች ክትትልና<br>12. በዝንጅብል ማጠብና ማድረቅ ቢዝነስ ፕሮጀክት | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.05 ንፁህ ደረቅ ዝንጅብል ማምረትና ከገዢዎች ትስስር መፍጠር |
| | | 13. የእርድ ድህረ ምርት ማሻሻያ ማቀድ | |
| | 4. ልዩና የበላይ ነት ያለቸው ምርቶች/ዝሪያ ግብይት ማጠናከር | 4. ከአፍሪካ ጀውስ ኩባንያ ጋር የማንጐ ሽያጭ እውን እንዲሆን ድጋፍ መስጠት | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.05 የደረቅ ካሳቫ ጥራትና ገበያ ልማት ማሻሻያ ፕሮጀክት |
| | | 10. ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ ሽያጭ ማስፋፋት | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.04 የደረቅ ካሳቫ ጥራትና ገበያ ልማት ማሻሻያ ፕሮጀክት |
| | 5. የጋራ ግብይት ማፋጠን | | |

| መሠረታዊ እስትራቴጂ | እስትራቴጂ | የፕሮጀክት ዕቅድ | ጠሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት |
|---|---|---|---|
| 3. የገበያ እንቅስቃሴዎች ለማጠናከር የገበያ መሠረተልማት ማጠናከር | 1. ዋና ዋና መንገዶችን ወደ ወረዳ ገበያ ቦታዎችና አገናኝ መንገዶችን ወደ አካባቢ መንገዶች ማሻሻል | | |
| | 2. በተመረጡ አካባቢዎች ወረዳ ገበያ ቦታዎች የገበያ መሠረተልማት ማሻሻል | 14. ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 የቦሎቄ ገበያ መሠረተልማት ድጋፍ | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.06 በማንጎና አቮካዶ ምርት አሰባሰብና አያያዝ ማሻሻል |
| | | 15. የቦሎቄ ገበያ መሠረተልማት | |
| | | 16. ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 የዝንጅብል ገበያ መሠረተልማት ድጋፍ | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.07 ዝንጅብል በሚያመርቱ አካባቢ ገበያ ማሻሻል |
| | | 17. የዝንጅብል ገበያ መሠረተልማት ማልማት | |
| | | 18. ለገጠር የግብርና ምርት የገበያ መሠረተልማት ማልማት | |
| | 3. የሀዋሣ ከተማ የገበያ ሥፍራ መሠረተልማት ማሻሻል | | |
| | 4. ነባር መጋዘን ለውጤታማ አጠቃቀም ማሻሻልና አዲስ መጋዘን ግንባታ | 19. ደረጃውን የጠበቀ የግብርና መጋዘን ማስፋፋት | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.08 ደረጃውን የጠበቀ መጋዘን ግንባታና አስተዳደር ማሳደግ |
| | | 20. ነባር የግብርና መጋዘን ማሻሻያ ፕሮጀክት | |
| | 5. በመንገድ ዳር የግብርና ምርት ሽያጭ ማስፋፋት | 21. የገጠር መንገድ ዳር ገበያ ማዕከል ማስፋፊያ ፕሮግራም | |
| 4. በተቋማዊ ሥርዓት የግብርና ግብይት ማግኘትና ማስተካከል | 1. በግብርና ግብይት ባለድርሻ አካላት መካከል የተፋጠ ትብብር ማስፈን | | |
| | 2. የሥራ ዝርዝር/የመለኪያ ደረጃ ማስተዋወቅና መጠበቅ | | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.09 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ከገበያ ማዕከሉ ወጪ የተገዛ ስንዴ ማነፃፀሪያ ጥናት |
| | 3. ለሕ/ሥራ ማህበራት/ዩኒየኖች የድጋፍ ስርዓት ማጠናከር | 22. የእህል ሕ/ሥራ ማህበራት የጋራ ግብይት አቅም ግንባታ ማስፋፋት | |
| | | 23. ሕ/ሥራ ማህበራትና እህል ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ግብይት አቅም ግንባታ ማስፋፋት | |
| | 4. የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች አቅም ማሣደግ | | ሙከራ ትግበራ ፕሮ.10 በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ወቅት ቁጥጥርና ግምገማ ማድረግ ስለገበያ ማሻሻል ግንዛቤና አቅም ለመንግስት ሠራተኞች እንዲኖራቸው ማድረግ |

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | እስትራቴጂ | | | | | | | | | | | የተመረጠ አካባቢ (ዞን/ልዩ ወረዳ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | የተመረጠ ሰብል | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1. የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከር | 2.1 የፍራፍሬና አትክልት መሰብሰብና አያያዝ ዘዴ ማሻሻያ | 2.2 ጥራት ግንዛቤ ባለው ገበያ የሚደረገውን ተሳትፎ ማፋጠንና ማጠንከር | 2.3 በአምራቾች አካባቢ የእሴት ጭማሪ ሥራዎች ማሳደግ | 2.4 ልዩና የበላይ ነት ያላቸው ምርቶች/ዝሪያ ግብይት ማጠናከር | 2.5 የጋራ ግብይት ማፋጠን | 3. የገበያ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ብቃት ያለው የገበያ መሠረተልማት ማሻሻል | 4.1 በግብርና ግብይት ባለድርሻ አካላት መካከል የተፋጠ ትብብር ማስፈን | 4.2 የሥራ ዝርዝር/የመለኪያ ደረጃ ማስተዋወቅና መጠበቅ | 4.3 ለሕ/ሥራ ማህበራት/ዩኒየኖች የድጋፍ ስርዓት ማጠናከር | 4.4 የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች አቅም ማሳደግ | ቤንች ማጂ | ዳውሮ | ደቡብ ኦሞ | ጋሞ ጎፋ | ጌዲኦ | ጉራጌ | ሃዲያ | ከፋ | ከምባታ ጠምባሮ | ሸካ | ሲዳማ | ስልጤ | ወላይታ | ሰገን | አላባ ልዩ ወረዳ. | ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | ኮንታ ልዩ ወረዳ | የም ልዩ ወረዳ | በርዕና አገዳ | ጥራሬ | አትክልት | ፍራፍሬ | ሥራሥር | ሌሎች: ዝንጅብል፣ ሰሊጥ፣ወዘተ |
| 1 | የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ለማስፋፋት የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ | X | | | | | | | X | | | | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | | X | X | | X | | X |
| | ሌሎች: ዝንጅብል (ሙከራ ፕሮጀክት) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | [X] | | | | [X] | | | | | | | | | | | |
| | ጥራጥሬ: ቦሎቄ (ሙከራ ፕሮጀክት) | | | | | | | | | | | | | | | | | | [X] | | | | [X] | | [X] | [X] | [X] | | | | | | | | | |
| | ፍራፍሬ: ማንጎ | | | | | | | | | | | | | | X | X | | | | | X | | | | X | | | | | | | | | | | |
| | አትክልት: በርበሬ | | | | | | | | | | | | | | | | | X | | X | | | X | X | | | X | | | | | | | | | |
| | ሌሎች: ሰሊጥ | | | | | | | | | | | | X | | X | X | | | | | | | | | | | | X | | | | | | | | |
| | ፍራፍሬ: አቮካዶ | | | | | | | | | | | | X | | | | X | | | | X | X | X | | X | | | | | | | | | | | |
| | ብርዕና አገዳ: ስንዴ | | | | | | | | | | | | | X | | X | X | | X | X | X | | X | X | | | | | | | | | | | | |
| | በርዕና አገዳ: በቆሎ | | | | | | | | | | | | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | | X | | | | | | | |
| 2 | በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 የተመረጡ ቡድኖች ድጋፍና ክትትል | | X | | | | X | | | | | | | | | X | | | | | | | X | | X | | | | | | | | | X | | |
| 3 | የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁሶችን የማስታወቂያ ፕሮጀክት | | X | | | | X | | | | | | X | | | X | X | | | | X | | X | | X | | | | | | | | | X | | |
| 4 | ከአፍሪካ ጀውስ ኩባንያ ጋር የማንጐ ሽያጭ እውን እንዲሆን ድጋፍ መስጠት | | X | | | X | X | | X | | | | | | | X | | | | | | | | | X | | | | | | | | | X | | |
| 5 | ወደ ከተማ አካባቢ የሚደረገው የቲማቲም ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት, ደረጃ 1: ሞዴል ማቋቋም | | X | | | | X | | | | | | | | | | | | | | | | X | | | | | | | | | X | | | |
| 6 | ወደ ከተማ አካባቢ የሚደረገው የቲማቲም ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት, ደረጃ 2: የመነሻ ወጪ ዝግጅትና የመፈፀም ድጋፍ | | X | | | | X | | | | | X | | | | | | | | | | | X | | | | | | | | | X | | | |
| 7 | የሕ/ሥራ ማህበራት በእህል ሰብልና ጥራጥሬ የጥራት ቁጥጥርና የመጋዝን አስተዳዳር አቅም ማሳደግ | | | X | | | | | X | | | | | | | | | X | X | | X | | [X] | X | X | | X | | | | X | X | | | | |
| 8 | በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 ለተመረጡ ቡድኖች የክትትል ድጋፍ | | | | X | X | X | | | | | | | | | | | | | | | | | | X | | | | | | | | | | X | |
| 9 | ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ የማምረት ቢዝነስ ማስፋፊያ ድጋፍ | | | | X | X | X | | | | | | | | | X | | | | | | | | | X | | | | | | | | | | X | |
| 10 | ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ ሽያጭ ማስፋፋት | | | | X | X | | | | | | | | | | (X) | | | | | | | | | (X) | | | | | | | | | | X | |
| 11 | በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 የተመረጡ ቡድኖች ክትትልና | | | | X | X | X | | | | | | | | | | | | | | X | | | | X | | | | | | | | | | | X |
| 12 | በዝንጅብል ማጠብና ማድረቅ ቢዝነስ ፕሮጀክት | | | | X | X | X | | | | | | | | | | | | | | X | | | | X | | | | | | | | | | | X |
| 13 | የእርድ ድህረ ምርት ማሻሻያ ማቀድ | | | | X | | | | | | | X | | | | | | | | | | X | | | | | | | | | | | | | | X |
| 14 | ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 የቦሎቄ ገበያ መሠረተልማት ድጋፍ | | | | | | | X | | | | | | | | | | | | | | | X | | | | | | | | | X | | | | |
| 15 | የቦሎቄ ገበያ መሠረተልማት | | | | | | | X | X | | | | | | | | | | X | | | | X | | X | X | X | | | | | | | | | X |
| 16 | ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 የዝንጅብል ገበያ መሠረተልማት ድጋፍ | | | | | | | X | | | | | | | | | | | | | X | | | | | | | | | | | X | | | | |
| 17 | የዝንጅብል ገበያ መሠረተልማት ማልማት | | | | | | | X | X | | | | | | | | | | | | X | | | | X | | | | | | | | | | | X |
| 18 | ለገጠር የግብርና ምርት የገበያ መሠረተልማት ማልማት | | | | | | | X | X | | | | X | X | X | | | X | | X | | | X | X | | | | X | | X | ? ? | | | | | |
| 19 | ደረጃውን የጠበቀ የግብርና መጋዘን ማስፋፋት | | | | | | | X | | | | | | | | | | X | X | | X | | X | X | X | | X | | | | X | X | | | | |
| 20 | ነባር የግብርና መጋዘን ማሻሻያ ፕሮጀክት | | | | | | | X | | | | | | | | | | X | X | | X | | | X | X | | X | | | | X | X | | | | |
| 21 | የገጠር መንገድ ዳር ገበያ ማዕከል ማስፋፊያ ፕሮግራም | | | | | | | X | | | | | ? ? | | | | | | | | | | | | | | | | | | ? ? | | | | | |
| 22 | የእህል ሕ/ሥራ ማህበራት የጋራ ግብይት አቅም ግንባታ ማስፋፋት | | | | | | X | | | | X | X | | | | | | X | X | | X | | X | X | X | | X | | | | X | X | | | | |
| 23 | ሕ/ሥራ ማህበራትና እህል ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ግብይት አቅም ግንባታ ማስፋፋት | | | | | | X | | | | X | X | | | X | X | | X | | | X | | X | X | X | | X | | | | | | X | X | X | X |

(X) የፕሮጀክት አከባቢ ያልሆነ ግን ተጠቃሚ አካባቢ

[X] የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት አካባቢ የነበረ ግን በመሪ ዕቅዱ ያልተሸፈነ

## ምስል 6-1 የእያንዳንዱ ፕሮጀክት እስትራቴጂዎች፣ የተመረጠ አካባቢ እና የተመረጠ ሰብል

# 6.4 የፕሮጀክት ዕቅድ

## 6.4.1 የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ልማት

### የፕሮጀክት ቁጥር 1

| የፕሮጀክት ስም | የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት |
|---|---|
| እስትራቴጂ | 1: የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ<br>1.1: ደረጃ በደረጃ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት አጭር የጹሑፍ መልዕክትና ማስታወቂያ ቦርድ በመጠቀም ወደ ሌሎች ጠቃሚ ሰብሎች ማስፋፋት<br>1.2: የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ መጠቀም<br>1.3: ነባር የመረጃ ሀብት መጠቀም |
| የመሪ ዕቅድ ፕሮግራም | የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ልማት ዕቅድ |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2013-2017 (እ.ኤ.አ) 5 ዓመት |
| የፕሮጀክት ቦታ የተመረጡ ሰብሎች | በተመረጡ ወረዳዎች ብዛት በሰብሎች ዓይነት |

| | | ዞን/ ልዩ ወረዳ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቤንች ማጂ | ዳውሮ | ደቡብ ኦሞ | ጋሞ ጎፋ | ጌዲኦ | ጉራጌ | ሃዲያ | ከፋ | ከምባታ ጠምባሮ | ሸካ | ሲዳማ | ስልጤ | ወላይታ | ሰገን | አላባ ልዩ ወረዳ. | ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | ኮንታ ልዩ ወረዳ | ድምር | አዲስ ወረዳዎች |
| 1 | ማንጎ | | | 1 | 2 | | | | | 1 | | | | 3 | | | | | 7 | 3 |
| 2 | በርበሬ | | | | | | 2 | | 1 | | | 1 | 2 | | | 1 | | | 7 | 6 |
| 3 | ሰሊጥ | 5 | | 1 | 1 | | | | | | | | | | | | 1 | | 8 | 8 |
| 4 | አቮካዶ | 2 | | | | 3 | | | | 3 | 2 | 6 | | 4 | | | | | 20 | 15 |
| 5 | ስንዴ | | 2 | | 3 | 1 | | 4 | 2 | 3 | | 2 | 1 | | | | | | 18 | 18 |
| 6 | በቆሎ | 4 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 1 | 3 | 3 | 6 | 2 | 1 | | 1 | 42 | 34 |
| | ድምር | 11 | 4 | 4 | 10 | 5 | 5 | 6 | 7 | 10 | 3 | 12 | 6 | 13 | 2 | 2 | 1 | 1 | 102 | 84 |

ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 የተመረጡ ሰብሎ

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ዝንጅብል | | | | | | | | | 2 | | | | 3 | | | | | 5 |
| 8 | ቦሎቄ | | | | | | | 2 | | | | 2 | | 2 | 2 | 1 | | | 9 |

የተመረጡ ብዙ ሰብሎችን መረጃ የሚሰበስቡ አንዳንድ ወረዳዎች አሉ፡፡ ትክክለኛው የአዳዲስ ወረዳዎች ብዛት 69 ነው፡፡

የ69 የተመረጡ ወረዳዎች ስም ዝርዝር በዕዝል 1 ተቀምጧል፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| የተመረጠ ቡድን | ለገበያ መረጃ አገልግሎት የተመረጡ አርሶአደሮችና የአካባቢ ነጋዴዎች ናቸው፡፡ | | |
| ፈፃሚ አካል | የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ፕረጀክቱ የሚካሄድበት ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ደጋፊ ኤጀንሲ | _ የደቡብ ክልል የብዙሃን መገናኛ ድርጅት<br>_ የማህበረሰብ ሬዲዮ ማዕከላት<br>_ የኦሮሚያ ግብይት ኤጀንሲ |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች ፡

የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 01 "ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ከአጭር የጽሑፍ መልዕክት እና ማስታወቂያ ቦርድ" በ14 ወረዳ ጽ/ቤቶችና ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በዝንጅብልና ቦሎቄ ሙከራ አድርጓል እና ያረጋገጠው ነገር ቢኖር የዋጋ መረጃ መላክ፣ መቀበልና ማሠራጨት በገጠር አካባቢ በአስቸጋሪ የግንኙነት አገልግሎት የሚሠራ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት ዓላማ የሚያደርገው ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት በደቡብ ክልል ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ከአጭር የጽሑፍ መልዕክት እና ማስታወቂያ ቦርድ በመትከል ለተመረጡ 6 ዓይነት ሰብሎች ደረጃ በደረጃና ከዚህ በተጨማሪ የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃና የነባር መረጃ ሀብት አጠቃቀም ማስፋት ነው፡፡

ይህ ፕሮጀክት የተጠናቀረው በሚቀጥሉት 6 ክፍሎች ነው፡፡

ክፍል 1 ደረጃ በደረጃ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት በአጭር ጽሑፍ መልዕክትና ማስታወቂያ ቦርድ በ6 የተመረጡ ሰብሎች ማስፋፋት
ክፍል 2 የተሰበሰበ የዋጋ መረጃ ግንኙነት ላላቸው የክልሉ ጽ/ቤቶች ማሠራጨት፣
ክፍል 3 የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በሬዲዮና በጋዜጣ ማሠራጨት፣
ክፍል 4 የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በክልል ግብይት ቢሮ ዌብሳይት ማሠራጨት፣
ክፍል 5 የአ/አ ገበያ መረጃ ከኦሮሚያ ግብይት ኤጀንሲ መቀበል፣
ክፍል 6 ከኢትዮጵያ የምርት ገበያ የሰሊጥ የጨረታ ዋጋ መቀበል፣

ይህ ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ በኋላ ዝንጅብልና ቦሎቄ ጨምሮ የዋጋ መረጃ ለ8 ሰብሎች በ83 ወረዳ ግብይት ጽ/ቤቶች ተሰብስቦ ይሠራጫል።

ድርጊት፡
* ለሥራዎች ተዋናይ ሌላ ካልተገለጸ በስተቀር የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ነው።

**<u>ዋና የሥራ ክፍል 1፡ ደረጃ በደረጃ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት በአጭር ጽሑፍ መልዕክትና ማስታወቂያ ቦርድ በ6 የተመረጡ ሰብሎች ማስፋፋት</u>**

የማስፋፋት ተግባር በሚቀጥለው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

| የምርት ዘመን | የተመረጠ ሰብል | የተመረጠ ወረዳ ብዛት | የመረጃ ሥርዓቱ የሚዘረጋበት ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ |
|---|---|---|---|
| 2013 | ዝንጅብል፣ ቦሎቄ (ሙከራ ፕሮጀክት 01 እንደገና ማንቀሳቀስ) | 14 | 0 |
| 2014 | ማንጎ፣ በርበሬ | 7 + 7 | 3 + 6 |
| 2015 | ሰሊጥ፣ አቮካዶ | 8 + 20 | 8 + 15 |
| 2016 | ስንዴ | 18 | 18 |
| 2017 | በቆሎ | 42 | 19 |

[ 1ኛ/ ዓመት ]
1.1 የዝንጅብል ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት እና የቦሎቄ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት እንደገና ለመጀመር በጀት መመደብ፣
1.2 የመለያ ሥርዓት መፍጠር 83 ወረዳዎች፣ 8 ሰብሎች፣ የምርት ዓይነት፣ የገበያ ሥፍራ፣
1.3 የክልል ቢሮ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት እስታፍ በጀት ማግኘት፣ በጀቱን ለመጨመር አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ፣
1.4 የተመረጡ ወረዳዎች በጀት ለመመደብ አስፈላጊ እርምጃዎች መውሰድ፣
1.5 የሥራ ቦታ ክትትል ማድረግ (ለዝንጅብልና ለቦሎቄ)፣
1.6 በወረዳ ጽ/ቤት ስብሰባ ማካሄድ (ለዝንጅብልና ለቦሎቄ)፣

[ 2ኛ/ ዓመት ]
2.1 ዳታ ቤዝ የኮምፒውተር ሶፍትዌር (በኮንትራክት የሚሠራ)
2.2 ለማንጎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት መትከልና አገልግሎቱን መጀመር
2.3 ለቃሪያ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ስርዓት መትከልና አገልግሎት መጀመር
2.4 ለቦቆሎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ስርዓት በ14 ወረዳዎች አገልግሎት መጀመር
2.5 እና 6 የሥራ ቦታ ቁጥጥር ማድረግና የወረዳ ጽ/ቤት ስብሰባ ማካሄድ
2.7 አዲስ የክልል ቢሮ ባለሙያ መቅጠር
2.8 ለወረዳ ጽ/ቤት ኮምፒውተር ማቅረብ፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥልጠና መስጠት

[ 3ኛ/ ዓመት ]
3.1 ለሰሊጥ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት መትከልና አገልግሎት መጀመር

3.2 ለአቮካዶ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት መትከልና አገልግሎት መጀመር
3.3 ለቦቆሎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት በ5 ወረዳ ጽ/ቤቶች መትከል አገልግሎት መጀመር
3.4 አና 5 ወቅታዊ የሥራ ቦታ ቁጥጥርና የወረዳ ጽ/ቤት ስብሰባ ማካሄድ
3.6 ለወረዳ ጽ/ቤት ኮምፒውተር ማቅረብ፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥልጠና መስጠት

[ 4ኛ/ ዓመት ]
4.1 ለስንዴ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት መትከልና አገልግሎት መጀመር
4.2 ለቦቆሎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት በ4 ወረዳ ጽ/ቤት መትከልና አገልግሎት መጀመር
4.3 አና 4 ወቅታዊ የሥራ ቦታ ቁጥጥርና የወረዳ ጽ/ቤት ስብሰባ ማካሄድ፣
4.5 ለወረዳ ጽ/ቤት ኮምፒውተር ማቅረብ፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥልጠና መስጠት

[5ኛ/ ዓመት]
5.1 ለቦቆሎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት በቀሪ 19 ወረዳዎች መትከል አገልግሎት መጀመር
5.2 እና 3 ወቅታዊ የሥራ ቦታ ቁጥጥርና ወረዳ ጽ/ቤት ስብሰባ ማካሄድ
5.4 ለወረዳ ጽ/ቤት ኮምፒውተር ማቅረብ፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥልጠና መስጠት

**ዋና የሥራ ክፍል 2፡ የተሰበሰበ የዋጋ መረጃ ግንኙነት ላላቸው የክልሉ ጽ/ቤቶች ማሠራጨት**
1. በመረጃ ሥርጭት ያለውን ሕጎች ለበላይ አካልና ተመሳሳይነት ላላቸው ጽ/ቤቶች ማቅረብ፣
2. ወረዳ ጽ/ቤት አጭር ጽሑፍ መልዕክት ለዞን መላክ፣
3. ወረዳ ጽ/ቤት ወርሃዊ መረጃ በማጠቃለል ለተመሳሳይ ጽ/ቤቶች ያስረክባል፣
4. የዞን መምሪያ ወርሃዊ መረጃ በማጠቃለል ለተመሳሳይ ጽ/ቤቶች ያስረክባል፣
5. የክልል ቢሮ ወርሃዊ መረጃ በማጠቃለል ለተመሳሳይ ጽ/ቤቶች ያስረክባል፣

**ዋና የሥራ ክፍል 3፡ የተሰበሰበው የዋጋ መረጃ በሬዲዮና በጋዜጣ ማሠራጨት**
1. የዋጋ መረጃ ዝግጅት በማድረግና በማቀነባበር በሬዲዮና ጋዜጣ በብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማሠራጨት፣
2. የዋጋ መረጃ ዝግጅት በማድረግና በማቀነባበር በካምባታ ማህበረሰብ ሬዲዮ ማሠራጨት፣

**ዋና የሥራ ክፍል 4፡ የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በክልል ግብይት ቢሮ ድህረገጽ ማሠራጨት**
1. የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በመረጃ ቋት ማስገባት፣ በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ፣
2. በክልል ቢሮ ድህረገጽ መጫን፣ በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ፣

**ዋና የሥራ ክፍል 5፡ የአ/አበባ የገበያ መረጃ ከኦሮሚያ የግብይት ኤጀንሲ መቀበል**
1. የዋጋ መረጃ ለመለዋወጥ የትብብር ማዕቀፍ ከኦሮሚያ የግብይት ኤጀንሲ ጋር ማዘጋጀት፣
2. የዋጋ መረጃ ዘወትር መለዋወጥ፣
3. የተገኘውን የዋጋ መረጃ በአጭር ጽሑፍ መልዕክት ለወረዳ ጽ/ቤቶች ዘወትር ማሠራጨት፣

**ዋና የሥራ ክፍል 6፡ ከኢትዮጵያ የምርት ገበያ የሰሊጥ የጨረታ ዋጋ መቀበል**
1. በሞባይል የአጭር የጽሑፍና የድምፅ መልዕክት አገልግሎት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ መመዝገብ (ለሰሊጥ በወረዳ ጽ/ቤትና ክልል ቢሮ)
2. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጨረታ ዋጋ በቡለቲን ቦርድ ዘወትር መለጠፍ (ሰሊጥ በወረዳ ጽ/ቤት)

ግብአት፡

- ክልል ግብይትና ሕ/ሥራቢሮ ኤክስፐርት ዓመት-1፡1፣ ዓመት- 2፡2 ከዚያ በኋላ ዓመት- 3፡3
- ወረዳ ግብይትና ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ኤክስፐርት 83 /1ኤክስፐርት በ1 ወረዳ/

- ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ወረዳ፡ ዴስክቶፕ ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር ፣ዩፒኤስ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ የዋጋ ቡለቲን ቦርድ
- ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ዞን፡ ዴስክቶፕ ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር፣ ዩፒኤስ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣
- ዕቃዎች ለክልል ቢሮ፡ የለም
- ወጪዎች ለወረዳ ስብሰባ፡ ኮምፒውተርና መረጃ አጠቃቀም ሥልጠና
- የሥራ ማስኬጃ ወጪ ለወረዳና ለክልል የሞባይል ካርድ፣ አላቂ /ፋይል፣ A4 ወረቀት ቶነር ወዘተ/፣ -የትራንስፓርት ወጪ ወደ ገበያ ቦታ /በወረዳ ብቻ/ የክልል ቢሮ ኤክስፐርት የጉዞ ወጪዎች /የውሎ አበል፣ የመኪና ነዳጅ/

ወጪ :

| የምርት ዘመን (እ.ኤ.አ) | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የአዲስ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ብዛት | 14 | 23 | 46 | 64 | 83 | |
| የመረጃ ሥርዓት የሚዘረጋበት ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | 0 | 9 | 23 | 18 | 19 | 69 |
| መገልገያ ዕቃዎች የሚሰጡት ዞን ብዛት | 6 | 5 | 4 | 1 | 1 | 17 |
| | | | | | | |
| የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት መገልገያዎች ዕቃዎች ወጪ | 0 | 231,300 | 591,100 | 462,600 | 488,300 | 1,773,300 |
| የመገልገያ ዕቃዎች ማጓጓዣ ወጪ | 0 | 7,000 | 16,000 | 9,000 | 12,000 | 44,000 |
| የዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ መገልገያዎች ዕቃዎች ወጪ | 127,200 | 106,000 | 84,800 | 21,200 | 21,200 | 360,400 |
| | | | | | | |
| የክልል በለሙያ የጉዞ ወጪ (አበልና ትራንስፖርት) | | | | | | |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ዳሰሳ | 0 | 8,500 | 11,000 | 10,800 | 14,700 | 45,000 |
| መገልገያ ማሣሪያዎችን መዘርጋትና ሥራ ማስጀመሪያ ስብሰ | 0 | 8,500 | 11,000 | 10,800 | 14,700 | 45,000 |
| በየወቅቱ የሚደረግ የመስክ ክትትል | 6,400 | 10,200 | 17,600 | 22,700 | 27,800 | 84,700 |
| ከኦሮሚያ ግብይት ኤጀንሲ ጋር የሚደረግ ስብሰባ | | | 5,200 | | | 5,200 |
| | | | | | | |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ስብሰባ | 11,200 | 20,500 | 40,100 | 52,900 | 68,900 | 193,600 |
| የኮምቲውተርና መረጃ አያያዝ ስልጠና | 0 | 41,000 | 61,200 | 51,200 | 53,200 | 206,600 |
| | | | | | | |
| ዳታ ቤዝ የኮምፒውተር ሶፍትዌር(በኮንትራክት የሚሠራ) | 0 | 45,000 | 0 | 0 | 0 | 45,000 |
| የኢትዮ. ቴሌኮሚንኬሽን ሰርቨር አገልግሎት ክፍያ | 1,100 | 1,100 | 1,100 | 1,100 | 1,100 | 5,500 |
| | | | | | | |
| የወረዳ ጽ/ቤት ሥራ ማስከጃ 600 በወር | 7,200 | 7,200 | 7,200 | 7,200 | 7,200 | 36,000 |
| የክልል ቢሮ ሥራ ማስከጃ 570 በወር | 47,880 | 78,660 | 157,320 | 218,880 | 283,860 | 786,600 |
| | | | | | | |
| ድምር | 200,980 | 564,960 | 1,003,620 | 868,380 | 992,960 | 3,630,900 |

መጠባበቂያ (10%) 363,100 ብር

ጠቅላላ 3,994,000 ብር

- የሥራ ማስኬጃ የወረዳ ጽ/ቤት የተገመተው የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሥራዎች በምርት መሰብሰቢያና ግብይት ወቅት ለ6 ወራት በዓመት
- ለዞን መምሪያ የሥራ ማስኬጃ ወጪ አልታቀደም፤ ምክንያቱም አጭር የጽሑፍ መልዕክት መቀበል ብቻ ስለሆነ

የጊዜ ሠሌዳ:

በዕዝል 2 በተቀመጠው መሠረት

የትኩረት ነጥቦች:

1/ የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 01 ውጤት መጠቀም
- የሥራ ማስኬጃ መመሪያ ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ከአጭር የጽሑፍ መልዕክትና የማስታወቂያ ቦርድ፡-
- ለወቅታዊ ቁጥጥር ለመጠቀም የወረዳ የሥራዎች ሊስት መከታተል፡-
- የሥልጠና ማቴሪያል ለኮምፒውተር መረጃ አያያዝ
- የዋጋ ቡለቲን ቦርድ መሣል፡-

2/ የሥራ ዝርዝር ሥርዓት ለእያንዳንዱ ሰብል በሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 01 አፈፃፀም መሠረት በሚከተሉት ደረጃዎች መሠረት መካሄድ ይኖርበታል

1. የክልል ቢሮ ኤክስፐርት የጽ/ቤት ሁኔታና ኃላፊነት ያለውን ግለሰብ በእያንዳንዱ ወረዳ ጽ/ቤት ያጣራል፣
2. የዕቅድ ስብሰባ የምርት ዓይነት መወሰን፣ የገበያ ቦታ፣ የገበያ ቀኖች ዋጋ ለመሰብሰብ ወዘተ፣
3. የክልል ቢሮ ኤክስፐርት የመለያ ቁጥር ሥርዓት የአጭር የጽሑፍ መልዕክት ቅጾችና የሥራ ማስፈፀሚያ መምሪያ ያጠናቅቃል፡፡
4. የክልል ቢሮ ኤክስፐርት የግዢና የግንባታ ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡ ቢሮው ዕቃዎችን ይገዛል፡፡
5. የክልል ቢሮ ኤክስፐርት ኮምፒውተር ያቀርባል ይተክላል ከዚያም እንዴት መጠቀም እንዳለባቸውና መጠገን እንዳለባቸው ገልፃ ያደርጋል፡፡
6. የወረዳ ጽ/ቤት ኤክስፐርት የዋጋ ማስታወቂያ ቦርድ በገበያ ሥፍራ ይተክላል፡፡
7. ስብሰባ ማጠናቀቅ፣ የአሠራር ሥርዓት ማረጋገጥና ሥራ መጀመር

3/ ለፕሮጀክት ቅድመ ሁኔታ

- የፕሮጀክት በጀት ማግኘት ዓመት 1 (2013) የጊዜ ሰሌዳ የፕሮጀክት በጀት ማግኘት ነው፡፡
- ሙከራ ፕሮጀክት 01 ቡድን መሪ አገልግሎት መቀጠል፡ ሙከራ ፕሮጀክት 01 ቡድን መሪ የአሠራር ሥርዓት "ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ከአጭር የጽሑፍ መልዕክትና የማስታወቂያ ቦርድ" ያውቃል፡፡ በተጨማሪ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ድረህረገጽ መሥራት፣ የኮምፒውተርና የዳታ አጠቃቀም ሥልጠናና የቋሚ ኮምፒውተር ችግሮች በወረዳ ጽ/ቤት ያውቃል፡፡ ያለ እርሱ የተረጋጋ የፕሮጀክት አፈፃፀም ማሰብ አይቻልም፡፡

## ዕዝል 1. ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የተመረጡ ሰብሎችና ወረዳዎች (1/2)

| ዞን ልዩ ወረዳ | | | ወረዳ | ዝንጅብል | ባቄላ | ማንጎ | በርበሬ | ሰሊጥ | አቮካዶ | ስንዴ | በቆሎ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አላባ ልዩ ወረዳ | * | 1 | አላባ ልዩ ወረዳ | | x | | x | | | | x |
| ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | | 2 | ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | | | | | x | | | |
| ቤንች ማጂ | | 3 | በሮ | | | | | x | | | |
| | | 4 | ደቡብ ቤንች | | | | | | x | | x |
| | | 5 | ጉራፋርዳ | | | | | x | | | x |
| | | 6 | ሚኒት ጎልድያ | | | | | x | | | |
| | | 7 | ሚኒት ሻሻ | | | | | x | | | |
| | | 8 | ሰሜን ቤንች | | | | | | x | | |
| | | 9 | ሸኮ | | | | | | | | x |
| | | 10 | ሼቤንች | | | | | x | | | x |
| ዳውሮ | | 11 | ገና ቦሳ | | | | | | | | x |
| | | 12 | ማራቃ | | | | | | | x | |
| | | 13 | ቶጫ | | | | | | | x | x |
| ጋሞ ጎፋ | | 14 | አርባምንጭ ዚሪያ | | | x | | | | | |
| | | 15 | ጨንቻ | | | | | | | x | |
| | | 16 | ደንባ ጎፋ | | | | | | | | x |
| | | 17 | ገረሴ | | | | | | | x | |
| | | 18 | ከምባ | | | | | | | x | |
| | | 19 | ቁጫ | | | | | | | | x |
| | | 20 | መሎ ኮዛ | | | | | x | | | |
| | | 21 | ምዕራብ አባያ | | | x | | | | | |
| | | 22 | ኡባ ደብረፀሐይ | | | | | | | | x |
| | | 23 | ዛላ | | | | | | | | x |
| ጌዲኦ | | 24 | ቡሌ | | | | | | | x | x |
| | | 25 | ዲላ ዙሪያ | | | | | | x | | |
| | | 26 | ኮቾሬ | | | | | | x | | |
| | | 27 | ወናጎ | | | | | | x | | |
| ጉራጌ | | 28 | አብሽጌ | | | | | | | | x |
| | | 29 | ማራቆ | | | | x | | | | |
| | | 30 | መስቃን | | | | x | | | | x |
| | | 31 | ሶዶ | | | | | | | | x |
| ሃዲያ | | 32 | ሌሞ | | | | | | | x | |
| | | 33 | ጎምቦራ | | | | | | | x | |
| | * | 34 | ምዕራብ ባድዋቾ | | x | | | | | | x |
| | | 35 | ሚሻ | | | | | | | x | |
| | * | 36 | ምስራቅ ባድዋቾ | | x | | | | | | x |
| | | 37 | ሶሮ | | | | | | | x | |
| ከፋ | | 38 | አድዮ | | | | | | | x | |
| | | 39 | ቢጣ | | | | | | | | x |
| | | 40 | ጨና | | | | | | | | x |
| | | 41 | ዴቻ | | | | | | | | x |
| | | 42 | ጊንቦ | | | | x | | | | x |
| | | 43 | ሳሌም | | | | | | | x | |
| ከምባታ ጠምባሮ | | 44 | አንጋጫ | | | | | | | x | x |
| | | 45 | ደምቦያ | | | | | | | | x |
| | | 46 | ዶዮገና | | | | | | | x | |
| | * | 47 | ሃዳሮ ጡንጦ | x | | x | | | x | | |
| | | 48 | ቃጫቢራ | | | | | | x | | |
| | | 49 | ቀዲዳ ጋሜላ | | | | | | | x | x |
| | * | 50 | ጠምባሮ | x | | | | | x | | |
| | * የሙከራ ትግበራ ፕሮጅክት 01 ቦታ | | | | | | | | | | |

## ዕዝል 1. ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የተመረጡ ሰብሎችና ወረዳዎች (2/2)

| ዞን ልዩ ወረዳ | | ወረዳ | | ዝንጅብል | ባቄላ | ማንጎ | በርበሬ | ሰሊጥ | አቮካዶ | ስንዴ | በቆሎ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኮንታ ልዩ ወረዳ | | 51 | ኮንታ ልዩ ወረዳ | | | | | | | | x |
| ሰገን | * | 52 | አማሮ | | x | | | | | | x |
| | * | 53 | ቡርጂ | | x | | | | | | |
| | | 54 | ደራሼ | | | | | | | | x |
| ሸካ | | 55 | ማሻ | | | | | | x | | |
| | | 56 | የኪ | | | | | | x | | x |
| ሲዳማ | | 57 | አለታ ወንድ | | | | | | x | | |
| | | 58 | ቦና | | | | | | x | | |
| | * | 59 | ቦሪቻ | | x | | | | | | x |
| | | 60 | ዳሌ | | | | | | x | | |
| | | 61 | ዳራ | | | | | | x | | |
| | | 62 | ሀዋሣ ዙሪያ | | | | x | | | | x |
| | | 63 | ሁላ | | | | | | | x | |
| | * | 64 | ሎኮ አባያ | | x | | | | | | x |
| | | 65 | መልጌ | | | | | | | x | |
| | | 66 | ወንሾ | | | | | | x | | |
| | | 67 | ወንዶ ገነት | | | | | | x | | |
| ስልጤ | | 68 | ዳሎቻ | | | | x | | | | x |
| | | 69 | ምዕራብ አዝርነት | | | | | | | x | |
| | | 70 | ሳንኩራ | | | | | | | | x |
| | | 71 | ስልጢ | | | | x | | | | x |
| ደቡብ ኦሞ | | 72 | በና ፀማይ | | | | | | | | x |
| | | 73 | ደቡብ አሪ | | | x | | | | | x |
| | | 74 | ሳላማጎ | | | | | x | | | |
| ወላይታ | * | 75 | ቦሎሶ ቦምቤ | x | | x | | | x | | |
| | * | 76 | ቦሎሶ ሰሬ | x | | x | | | x | | |
| | | 77 | ዳሞት ፉላሳ | | | | | | | | x |
| | * | 78 | ዳሞት ጋሌ | | x | | | | x | | x |
| | | 79 | ዳሞት ሶሩ | | | | | | | | x |
| | | 80 | ዳሞት ወይዴ | | | | | | x | | x |
| | | 81 | ሁምቦ | | | | | | | | x |
| | * | 82 | ኪንዶ ኮይሻ | x | | x | | | | | |
| | * | 83 | ሶዶ ዙሪያ | | x | | | | | | x |
| | | | ጠቅላላ የወረዳ ብዛት | 5 | 8 | 7 | 7 | 8 | 20 | 18 | 42 |

* የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 ቦታ

## ዕዝል 2፡ የአፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ

| | | 2013 (አ/ኤ.አ) | | | | 2014 (አ/ኤ.አ | | | | 2015 (አ/ኤ.አ | | | | 2016 (አ/ኤ.አ | | | | 2017 (አ/ኤ.አ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ዋና የሥራ ክፍል 1: ደረጃ በደረጃ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት በአጭር ጽሑፍ መልዕክትና ማስታወቂያ ቦርድ ማስፋፋት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1-1. | የዝንጅብል ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት እና የቦሎቄ ግብርና ግብይት መረጃ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | አገልግሎት እንደገና ለመጀመር በጀት መመደብ | | | X | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1-2. | የመለያ ሥርዓት መፍጠር 83 ወረዳዎች፣ 8 ሰብሎች፣ የምርት ዓይነት፣ የገበያ ሥፍራ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1-3. | የክልል ቢሮ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሠራተኛ በጀት ማግኘት፣ በጀቱን ለመጨመር አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1-4. | የተመረጡ ወረዳዎች በጀት ለመመደብ አስፈላጊ እርምጃዎች መውሰድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1-5. | በሥራ ቦታ ክትትል ማድረግ (ለዝንጅብልና ለቦሎቄ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1-6. | የወረዳ ጽ/ቤት ስብሰባ ማካሄድ (ዝንጅብልና ቦሎቄ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2-1. | ዳታ ቤዝ የኮምፒውተር ሶፍትዌር(በኮንትራክት የሚሠራ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2-2. | ለማንጎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት መዘርጋትና አገልግሎቱን | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2-3. | ለበርበሬግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት መዘርጋትና አገልግሎቱን | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2-4. | ለበቆሎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ስርዓት በ14 ወረዳዎች መጀመር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2-5. | በሥራ ቦታ ክትትል ማድረግ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2-6. | የወረዳ ጽ/ቤቶች ስብሰባ ማካሄድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2-7. | ለክልል ቢሮ አዲስ ባለሙያ መቅጠር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2-8. | ለወረዳ ጽ/ቤትና ለዞን መምሪያ ኮምፒውተር ማቅረብ፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥልጠና ለባለሙያዎች መስጠት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3-1. | ለማንጎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት መዘርጋትና አገልግሎት መጀመር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3-2. | ለአቮካዶ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት መዘርጋትና አገልግሎት መጀመር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3-3. | ለበቆሎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ስርዓት በ5 ወረዳዎች አገልግሎት መጀመር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3-4. | የወረዳ ጽ/ቤቶች ስብሰባ ማካሄድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3-5. | ለክልል ቢሮ አዲስ ባለሙያ መቅጠር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3-6. | ለወረዳ ጽ/ቤት ኮምፒውተር ማቅረብ፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥልጠና ለባለሙያዎች መስጠት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4-1. | ለስንዴግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ሥርዓት መዘርጋትና አገልግሎት መ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4-2. | ለበቆሎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ስርዓት በ4 ወረዳዎች አገልግሎት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4-3. | የወረዳ ጽ/ቤቶች ስብሰባ ማካሄድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4-4. | ለክልል ቢሮ አዲስ ባለሙያ መቅጠር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4-5. | ለወረዳ ጽ/ቤት ኮምፒውተር ማቅረብ፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥልጠና ለባለሙያዎች መስጠት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5-1. | ለበቆሎ ግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሥራ ዝርዝር ስርዓት በ4 ወረዳዎች አገልግሎት መጀመር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5-2. | የወረዳ ጽ/ቤቶች ስብሰባ ማካሄድ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5-3. | ለክልል ቢሮ አዲስ ባለሙያ መቅጠር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5-4. | ለወረዳ ጽ/ቤት ኮምፒውተር ማቅረብ፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥልጠና ለባለሙያዎች መስጠት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ዋና የሥራ ክፍል 2፡ የተሰበሰበ የዋጋ መረጃ ግንኙነት ላላቸው የክልሉ ጽ/ቤቶች** | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1. | በመረጃ ሥርጭት ያለውን ሕጎች ለበላይ አካልና ተመሳሳይነት ለአላቸው ጽ/ቤቶች ማቅረብ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2. | ወረዳ ጽ/ቤት አጭር ጽሑፍ መልዕክት ለዞን ጽ/ቤት መላክ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3. | ወረዳ ጽ/ቤት ወርሃዊ መረጃ በማጠቃለል ለተመሳሳይ ጽ/ቤቶች ያስረክባል | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4. | የክልል ቢሮ ወርሃዊ መረጃ በማጠቃለል ለተመሳሳይ ጽ/ቤቶች ያስረክባል | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5. | የክልል ቢሮ ወርሃዊ መረጃ በማጠቃለል ለተመሳሳይ ጽ/ቤቶች ያስረክባል | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| **ዋና የሥራ ክፍል 3፡ የተሰበሰበው የዋጋ መረጃ በሬዲዮና** | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1. | የዋጋ መረጃ በማዘጋጀትና በማቀነባበር በሬዲዮና ጋዜጣ በብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማሠራጨት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2. | የዋጋ መረጃ ዝግጅት በማድረግና በማቀነባበር በካምባታ ማህበረሰብ ሬዲዮ ማሠራጨት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ዋና የሥራ ክፍል 4፡ የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በክልል ግብይት ቢሮ ድህረገጽ ማሠራጨት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1. | የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በመረጃ ቋት ማስገባት፣ በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2. | በክልል ቢሮ ድህረገጽ መጫን፣ በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ዋና የሥራ ክፍል 5፡ የአ/አበባ የገበያ መረጃ ከኦሮሚያ የግብይት ኤጀንሲ መቀበል | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1. | የዋጋ መረጃ ለመለዋወጥ የትብብር ማዕቀፍ ከኦሮሚያ የግብይት ኤጀንሲ ጋር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2. | የዋጋ መረጃ ዘወትር መለዋወጥ፣ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3. | የተገኘውን የዋጋ መረጃ በአጭር ጽሑፍ መልዕክት ለወረዳ ጽ/ቤቶች ዘወትር ማሠራጨት፣ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ዋና የሥራ ክፍል 6፡ ከኢትዮጵያ የምርት ገበያ የሰሊጥ የጨረታ ዋጋ መቀበል | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1. | በሞባይል የአጭር የጽሑፍና የድምፅ መልዕክት አገልግሎት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ መመዝገብ (ለሰሊጥ በወረዳ ጽ/ቤትና ክልል ቢሮ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2. | የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጨረታ ዋጋ በቡለቲን ቦርድ ዘወትር መለጠፍ (ሰሊጥ በወረዳ ጽ/ቤት) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

በጊዜ የተገደበ ሥራ ተከታታይነት ያለው ሥራ

### 6.4.2 ለከፍተኛ እሴት ጭማሪ ማስፋፊያ ዕቅድ

**የፕሮጀክት ቁጥር 2**

<table>
<tr><td>የፕሮጀክት ስም</td><td colspan="3">ሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 03 የተመረጡ ቡድኖች የክትትል ድጋፍ</td></tr>
<tr><td>እስትራቴጂ</td><td colspan="3">2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ ትርፍ መጨመር<br>2-1: የአትክልትና ፍራፍሬ ምርትና ድህረምርት አያያዝ ዘዴ ማሻሻያ<br>2-5: የጋራ ግብይት ማፋጠን</td></tr>
<tr><td>የመሪ ዕቅድ ፕሮግራም</td><td colspan="3">ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>የፍራፍሬ ብክነት መቋቋሚያ ፕሮግራም</td></tr>
<tr><td>የፕሮጀክቱ ጊዜ</td><td colspan="3">2013-2014 (2012/13 ና 2013/2014 እ.ኤ.አ የምርት ወቅት)</td></tr>
<tr><td>የፕሮጀክት፡ ቦታ</td><td colspan="3">ማንጎ፡ ምዕራብ ዓባያ ወረዳ (ጋሞ ጎፋ ዞን)<br>ቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ (ወላይታ ዞን)<br>አቮካዶ፡ ዳሌ ወረዳ (ሲዳማ ዞን)</td></tr>
<tr><td>የተመረጠ ሰብል / ምርት</td><td colspan="3">ማንጎ፣ አቮካዶ</td></tr>
<tr><td>የተመረጠ ቡድን</td><td colspan="3">ምዕራብ ዓባያ ወረዳ፡ አሞ ላንቴ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር<br>ቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ፡ ቦሎሶ ቦምቤ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር<br>ዳሌ ወረዳ፡ ዳጊያ ቀበሌ የአትክልትና ፍራፍሬ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር</td></tr>
<tr><td>ፈፃሚ አካል</td><td>ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ<br>ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ወረዳ<br>የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት</td><td>ደጋፊ አካል</td><td></td></tr>
<tr><td colspan="4">መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች ፡<br>የፍራፍሬ አካላዊ ጉድለት ለመቀነስ ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 ተስማሚ የምርትና ድህረምርት አያያዝ ዘዴዎች ወይም ዕቃዎች ላይ የልማትና የስርጭት ሥራዎች ሠርቷል። ፕሮጀክቱ የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ዲዛይን፣ የአያያዝ ዕቃዎች (ፕላስቲክ ሣጥን፣ በእጅ የሚገፋ ጋሪና ለፍራፍሬ መሰብሰቢያ የጎጆ መስሪያ ማቴሪያሎች በትክክለኛ አፈፃፀም የሚሠሩ መሆናቸውን ለማየት ለ3 የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ተሰጥቷል። በተጨማሪም ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 ለቡድኖቹ የገበያ ትስስር ድጋፍ ሰጥቷል። የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር የዕቃዎችና የውጤታቸው አጠቃቀም ሁኔታ በጋራ ግብይት የተለየ ነበር።<br><br>የፍራፍሬ የምርት ወቅት አንድ ጊዜ ህዳር 2011 እስከ መጋቢት 2012 (እ.ኤ.አ) በሙከራ ፕሮጀክት ወቅት ነበር። ስለዚህ የተሰጡት ዕቃዎች ውጤታማ አጠቃቀም የጋራ ገበያ ሙከራ ለመቀጠልና ለማስተዋወቅ የሥራ ቦታ ቁጥጥርና የምክር ድጋፍ በክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና የቀበሌ ማህበረሰብ አደራጅ ለ3ቱ ፕሮጀክት ቦታዎች መስጠት።</td></tr>
<tr><td colspan="4">ድርጊት ፡<br>የቁጥጥርና የምክር ድጋፍ ጊዜ ከጥር አስከ የካቲት 2013 (2 ወራት) እና ህዳር 2013 እስከ የካቲት 2014 (4 ወራት)<br><br>1. የሥራ ቦታ ቁጥጥር/ክትትል<br>1.1 በክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት ጋር 1ጊዜ በወር 1 ቦታ<br>1.2 በወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ዘወትር መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር የጋራ ማጓጓዝ በሚያደርግበት ወቅት<br><br>2. የምክር ድጋፍ<br>2.1 ለዳጊያ ቀበሌ የአትክልትና ፍራፍሬ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበርና ለቦሎሳ ቦምቤ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ውጤታማ የዕቃዎች አጠቃቀም ለማስተዋወቅ የምክር ድጋፍ መስጠት አለበት። ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት እና ማህበረሰብ አደራጅ ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር መሪዎች መመሪያ መስጠት፣ የማምረቻ ዕቃዎች ጥቅም ለአባላት አርሶአደሮች በሠርቶ ማሣያ ማቅረብ አለባቸው።</td></tr>
</table>

2.2 ለቦሎሶ ቦምቤ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር መሪዎች ቁርጠኝነት ደካማ ለሆኑ የቀጣይ የጋራ ገበያ ቀጣይነት ለማስተዋወቅ የምክር ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡ የፍራፍሬ ማሰባሰቢያ ሥራና ማኔጅመንት ማነቃቂያና ድጋፍ ለመሪዎች ማመቻቸት፡፡
ለኦሞ ላንቴ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበርና ለዳጊያ ቀበሌ አትክልትና ፍራፍሬ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ከተቋማዊ ገዢዎች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ ድጋፍ መስጠት፡፡

ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት፡
- ለ3ቱ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ስለ ክትትል ድጋፍ ዕቅድና ይዘት ማስረዳት
- የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና ማህበረሰብ አደራጅ ሥራ መከታተል፤ እንደአስፈላጊነቱ መመሪያ መስጠት
- የሥራ ቦታ ቁጥጥር /1ጊዜ/ወር/ቦታ/፣ ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር መሪዎች ምክር /መመሪያ መስጠት
- ከተቋማዊ ገዢዎች ጋር የግንኙነት ድጋፍ መስጠት

ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት፡
- የማህበረሰብ አደራጅ ሥራ መከተል፣
- የጋራ ምርት ማጓጓዝ በመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር በሚደረግበት ጊዜ የቦታ ቁጥጥር በየጊዜው ማድረግ፣
- ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር መሪዎች ምክር/መመሪያ መስጠት፤ (በተለይ በጋራ ግብይት አሰተዳደር)
- ለክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት ወቅታዊ ሪፓርት ማድረግ

ቀበሌ ማህበረሰብ አደራጅ፡
- ለአባል አርሶአደሮች የማምረቻ ዕቃዎች ማሟያ ማድረግ
- ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር መሪዎች ምክር/መመሪያ መስጠት፤ በተለይ በጋራ ግብይት ማኔጅመነት
- ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት ዘወትር ሪፓርት ማድረግ
- የትራንስፖርት ክፍያ ወጪ (ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)

ግብአት ፡
- ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት 1
- ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት 3 (1 ለእያንዳንዱ ቦታ)
- ቀበሌ ማህበረሰብ አደራጅ 3 (1 ለእያንዳንዱ ቦታ)
- የሥራ ማስኬጃ ወጪ፡ ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ኤክስፐርት የጉዞ ወጪ (አበልና የመኪና ነዳጅ)፣ የግንኙነት ወጪ፣ የቢሮ አላቂ ዕቃዎች

ወጪ ፡

| የምርት ዘመን | 2012/13 | 2013/14 | ድምር |
|---|---|---|---|
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች የጉዞ ወጪ (አበል፣ ነዳጅ) | 5,200 | 10,400 | 15,600 |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የትራንፖርት ወጪ | 600 | 1,200 | 1,800 |
| | | | |
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሥራ ማስኬጃ ወጪ | 1,000 | 2,000 | 3,000 |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሥራ ማስኬጃ ወጪ | 1,200 | 2,400 | 3,600 |
| | | | |
| ድምር | 8,000 | 16,000 | 24,000 |

መጠባበቂያ (10%) 2,400 ብር
ጠቅላላ 26,000 ብር

የጊዜ ሠሌዳ:

| | 2013 | | | | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | | 2017 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| የክትትል ድጋፍ ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 የተመረጡ ቡድኖች | ■ | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | | |
| የማንጎ ማሰባሰቢያ ዋና ወቅት | | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | |
| የአቮካዶ ማሰባሰቢያ ዋና ወቅት | | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | |

## የፕሮጀክት ቁጥር 3

| የፕሮጀክቱ ስም | የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስተዋወቅ | | |
|---|---|---|---|
| | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ ትርፍ መጨመር<br>2-1: የአትክልትና ፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስና አያያዝ ዘዴ ማሻሻል<br>2-2: የተለያዩ ከፍተኛ የሆኑ የምርት ዝርያዎች ግብይት ማጠናከር<br>2-2: የጋራ ግብይት ማፋጠን | | |
| የመሪ ዕቅድ ፕሮግራም | ከፍተኛ የእሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>የፍራፍሬ ብክነት መቋቋሚያ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | 2013-2017 (እ.ኤ.አ) 5 ዓመት/ 4 ምርት ዘመን) | | |
| የፕሮጀክት ቦታ | 18 ወረዳዎች በ5 ዞኖች<br>ጋሞ ጎፋ : /ምንጭ ዙሪያ፣ ምዕራብ ዓባያ፣ ዴንባ ጎፋ<br>ወላይታ : ሎሶ ቦምቤ፣ ቦሎሳ ሶሬ፣ ዳሞት ጋሌ፣ ዳሞት ፉላሳ<br>ካ/ጠምባሮ : ዳሮ ጡንጦ ዙሪያ፣ ጣምባሮ፣ ቃጫ ቢራ፣ ቀዲዳ ጋሜላ<br>ሲዳማ : ንዶገነት፣ ዳሌ፣ አለታ ወንዶ፣ ሃዋሣ ዙሪያ<br>ጌዲኦ : ላ ዙሪያ፣ ወናጎ<br>ቤንች ማጂ : ሰማን ቤንች፣ ደቡብ ቤንች | | |
| የተመረጠ ሰብል / ምርት | ማንጎ፣ አቮካዶ | | |
| የተመረጠ ቡድን | ማንጎ ወይም አቮካዶ ዛፍ ያላቸው አርሶአደሮች<br>የአካባቢ የብረታብረት ድርጅቶች | | |
| ፈፃሚ አካል | ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ ዞን የግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ/ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ደጋፊ አካል | የግብርና ቢሮ፣ የዞን ግብርና መምሪያ የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት |

*መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች፡*
*አሁን ያለውን የማንጎና አቮካዶ የማምረትና የአያያዝ ልምድ ለማሻሻል ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03 ተስማሚ የማምረቻና የአያያዝ ዘዴዎች ወይም ዕቃዎች ልማትና ሥርጭት ላይ ሠርቷል። የማምረቻ ዕቃ በቀላሉ የሚመረትና እርካሽ የሆነ ዲዛይን ተደርጎ አካላዊ ጉዳት ለመቀነስ ውጤታማ መሆኑ በትክክለኛ ሥራ ተረጋግጧል።*

*ይህ ፕሮጀክት ዓላማ የሚያደርገው በደቡብ ክልል ዋና ዋና ማንጎና አቮካዶ በሚያመርቱ ወረዳዎች አዲስ ተሻሽሎ የተዘጋጀውን ፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ለህ/ሠቡ ማስተዋወቅ ነው። የማስተዋወቁ የመጨረሻ ግብ አዲሱ ዕቃ እንደ ማጭድና መኰትኮቻ በአካባቢ ገበያ ለንግድ በፍራፍሬ አምራች አካባቢ የሚገኝ መሆን ነው። ዕቃውን ለገበያ ማምረትና ማስፋፋት የሚችሉ ድርጅቶች በፍራፍሬ አምራች አካባቢ (ይኸውም የአካባቢ ብረታ ብረት ድርጅቶች ቁሳቁሱን ለማምረት) በፕሮጀክቱ ውስጥ መካተት አለበት።*

*ፍራፍሬ ማውረጃውን ለማስተዋወቅ ይኸውም አርሶአደሮች ማውረጃውን ጥያቄ እንዲፈጥሩ የኤክስቴንሽን ዘዴዎች ሀ) ዕቃውን በመጠቀም ያለውን ጠቀሜታ በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞችና የቀበሌ ማህበረሰብ አደራጆች ሠርቶ ማሣያ በማዘጋጀት ገለፃ ማድረግ ለ) ፓስተሮችን በቀበሌ መትከልና ሐ) ለቁልፍ አርሶአደሮች ነፃ ዕቃ ዕደላ ማድረግ ከዚህ በተጨማሪ ከጥራት ፈላጊ ገዢዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠትና የፍራፍሬ የጋራ ሽያጭ አስተዳዳር ድጋፍ መስጠት።*

ፕሮጀክቱ በ3 ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን የተመረጡትም እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።

| | |
|---|---|
| የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስተዋወቅ | የማውረጃ ቁሳቁስ በ18 የተመረጡ ወረዳዎች በደንብ ይታወቃል። ጥያቄ ከአርሶአደሮችና የአካባቢ ነጋዴዎች ይቀርባል፣ |
| ለገበያ ትስስርና የጋራ ሽያጭ ድጋፍ መስጠት | ቢያንስ አንድ የአርሶአደሮች ቡድን የጋራ ሽያጭ በእያንዳንዱ ተመራጭ ወረዳ ይጀምራል። |
| ፍራፍሬ አምራች አካባቢ ለአሉ የብረታብረት ድርጅቶች ድጋፍ መስጠት | ቢያንስ አንድ የብረታብረት ድርጅት የማውረጃ ቁሳቁስ ለሽያጭ በተመራጭ ወረዳ ማምረት ይጀምራል። |

የተመረጡ ወረዳዎች በድምር 18 ናቸው፡፡ በየዓመቱ የሚሳተፉ የተመረጡ ወረዳዎች ዝርዝር እንደሚከተለው ነው፡፡

| ዞን | ወረዳ | | ማንጐ | አቮካዶ | ቅድሚያ የተሰጠ * | ለሙከራ ፕሮ. 03 የተመረጠ | 2013/14 | 2014/15 | 2015/16 | 2016/17 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጋሞጎፋ | 1 | አ/ምንጭ ዙሪያ | X | | 1 | | X | | | |
| | 2 | ምዕራብ አባያ | X | | 2 | | X | | | |
| | 3 | ደንባ ጐፋ | X | | 3 | | | X | | |
| ወላይታ | 4 | ቦሎሶ ቦምቤ | X | X | 1 | | | X | | |
| | 5 | ቦሎሶ ሶሬ | X | X | 2 | | | X | | |
| | 6 | ዳሞት ጋሌ | | X | 3 | | | | X | |
| | 7 | ዳምት ፉላሣ | | X | 4 | | | | X | |
| ከምባታ ጠምባሮ | 8 | ሃዳሮ ጡንጦ | X | X | 1 | | | X | | |
| | 9 | ቃጫ ቢራ | | X | 2 | | | X | | |
| | 10 | ቀዲዳ ጋሜላ | | X | 3 | | | | X | |
| ሲዳማ | 11 | ወንዶገነት | | X | 1 | | X | | | |
| | 12 | ዳሌ | | X | 2 | | | X | | |
| | 13 | አለታ ወንዶ | | X | 3 | | X | | | |
| | 14 | ሀዋሣ ዙሪያ | | X | 4 | | | | X | |
| ጌዴኦ | 15 | ዲላ ዙሪያ | | X | 1 | | | | X | |
| | 16 | ወናጐ | | X | 2 | | | | X | |
| ቤንች ማጂ | 17 | ሰሜን ቤንች | X | X | 1 | | | | | X |
| | 18 | ደቡብ ቤንች | X | X | 2 | | | | | X |

ለፕሮጀክት 1 የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ የተመረጡ ወረዳዎች

ድርጊት :

ሁሉም ሥራዎች በዋና የምርት ወቅት ይከናወናሉ፡፡ ከመስከረም እስከ መጋቢት በየዓመቱ 7 ወራት፡፡

<u>ለፕሮጀክቱ በጀት ለማግኘት የሚሠሩ ሥራዎች</u>

❖ ለመጀመሪያ ዓመት በጀት ማግኘት /2013/14/ ሥራዎች ከሰኔ 2013 በፊት መጠናቀቅ አለባቸው

1. እርዳታ ሊሰጡ የሚችሉ ድርጅቶች መለየት፡ የእርዳታ ፕሮግራም፣ NGO ክልላዊ መንግስት ወዘተ
2. የፕሮጀክት ፕሮፓዛልና የገለፃ ወረቀት ማዘጋጀት /ሙከራ ፕሮጀክት 03 መጠቀም/ እንደ ተጨባጭ ግኝት
3. እርዳታ ሊሰጡ ለሚችሉ ድርጅቶች የፕሮጀክት ፕሮፓዛል ማስረዳት
4. ለበጀት ምደባ ከክልሉ መንግስት ጋር ውይይት ማድረግ
5. በተገኘው በጀት መሠረት የፕሮጀክቱን ደረጃና የጊዜ ሠሌዳ መከለስ

<u>ዋና የስራ ክፍል 1፡ የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስተዋወቅ</u>

የተመረጡ የወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና የዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ ጽ/ቤቶች በመጥራት የዓመቱን የፕሮጀክት ዕቅድና ይዘት ግልፅና ዝርዝር የሥራ አቅጣጫ ማስረዳት፤ በዚህ የገለፃ ስብሰባ ላይ የነፃ ዕቃዎችና ብዛታቸውን የሚመረጡ ቀበሌዎች ጭምር መወሰን፡፡ ነፃ የሚታደለው ዕቃ በከፍተኛ 150 የማምረቻ ዕቃና 300 ፕላስቲክ ሣጥን በአንድ ወረዳ ሲሆን በአንድ ወረዳ ለ5 ቀበሌ ይሆናል፡፡ አንድ የማምረቻ ዕቃና 2 የፕላስቲክ ሣጥን በአንድ ቁልፍ አርሶአደር ስሌት ማለት ነው፡፡ የቀበሌ ኮሚኒቲ አደራጅና ወረዳ ጽ/ቤት ሠራተኛ የማምረቻ ዕቃውን በመጠቀም ያለውን ጠቀሜታ በሥርጭት ወቅት በማስረዳትና በማሣየት ከዚያም ክትትል ማድረግ አለበት፡፡ ለቁልፍ አርሶአደሮች የሥርጭት ጊዜ መጠናቀቅ ያለበት ከጥቅምት አጋማሽ በፊት /በየዓመቱ/ መሆን አለበት፡፡

[ የሥራ ሂደት ]

1. የገለፃ ስብሰባ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ /ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት/ ዞን የግብይትና ሕ/ሥራ  መምሪያ ሀዋሣ ላይ ማካሄድ፣
2. ዕቃዎቹን መግዛትና ወደ ቦታቸው ማጓጓዝ፣ (በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ)
3. ከቀበሌ መሪዎችና ማህበረሰብ አደራጆች ጋር መወያየት፣ በእያንዳንዱ ቀበሌ ቁልፍ አርሶ አደሮችን መወሰን (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
4. ፓስተሮችን በቀበሌ መትከል፣ (ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና ማህበረሰብ አደራጅ)
5. በእያንዳንዱ ቀበሌ ዕቃዎችን በመጠቀም ያለውን ጠቀሜታ ማሣየት፣ (ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና ማህረሰብ አደራጅ)

6. የዕቃዎችን አጠቃቀም መከታተልና ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሪፓርት ማድረግ፣ (በማህበረሰብ አደራጅ)
7. የዕቃዎችን አጠቃቀም ለዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያና ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ወቅታዊ ሪፓርት ማድረግ (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
8. የሥራ ቦታ ወቅታዊ ክትትል ማድረግ (በክልልየግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ)

- ኃላፊነት ያለውን ባለሙያና የወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኃላፊ በውይይት ስብሰባ መጋበዝ፣
- ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ተወዳዳሪ ቀበሌዎች ዕቅድ በቅድሚያ ማዘጋጀት አለበት፣
- 300 ፕላስቲክ ሣጥኖች ለአይሱዙ መኪና ከፍተኛ ጭነት ነው፡፡
- የማምረቻ ዕቃዎች በገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከል ወጪን ለመቀነስ ሊመረቱ ይችላሉ፡፡
- ፓስተሮች ዲዛይንና ህትመት የተደረገ በሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 03 ነው፡፡
- በመጀመሪያው ዓመት አፈፃፀም መነሻ የ2ኛውን ዓመት የዕቃዎች መጠን በየወረዳው ማስተካከል

<u>ዋና የሥራ ክፍል 2 ጥራት ላይ ተመስርተው ከሚገዙ ጋር የገበያ ትስስር ድጋፍ መስጠት</u>

በአርሶአደሮች ፍቃደኝነትና የግል ተነሣሽነት መሠረት የገበያ ትስስርና የጋራ ሽያጭ ድጋፍ መጀመር ድንገት ብዙ መንደሮች ቡድኖች የድጋፍ ጥያቄ ካነሱ በጋራ ሽያጭ ከዚህ በፊት ልምድ ህብረት/አንድነት ያለውን መንደር (ቡድን) ወዘተ መምረጥ፣ ከአጎራባች መንደሮች ጋር በጥምረት መሥራት እንደሚቻል ማስብ ያስፈልጋል፡፡ ለእያንዳንዱ መንደር ፕላስቲክ ሣጥኖች፣ የመሰብሰቢያ ጎጆ ለመሥራት ማቴሪያሎች፣ የእጅ ጋሪዎችና የአህያ ጋሪ ማቅረብ የጥራት ፈላጊ ተቋማዊ ገዢዎች በክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ መለየትና ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና የተመረጡ ቡድኖች መረጃ ማቅረብ በየዓመቱ ከምርት መሰብሰቢያ ወቅት በፊት ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የገበያ ጥናት በአ/አ በናዝሬትና በሌሎችም ከተሞች ማካሄድ አለበት፡፡

- የፕሮጀክት ወጪ የተሰላው "ቢያንስ አንድ የአርሶአደር ቡድን የጋራ ሽያጭ በእያንዳንዱ የተመረጠ ወረዳ ይጀምራል"

[ የሥራ ሂደት ]

1. በትላልቅ ከተሞች እምቅ የመግዛት አቅም ያላቸውን ለመለየት የገበያ ጥናት ማካሄድ፣ ፍላጐታቸውን በጥራት፣ በመጠን፣ በቢዝነስ ሁኔታ ማረጋገጥ (በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ)
2. በወቅታዊ የሥራ ቦታ ክትትል ጊዜ የአርሶአደሮችን ፍቃደኝነት/ ፍላጐት በመያዝ ሪፓርት ለ ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ማድረግ /በወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት/
3. ከአርሶአደሮች ቡድን ጋር የውይይት ጥናት በማካሄድ የሚመረጡ ቡድኖችን መወሰን (በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
4. የፍራፍሬ መሰብሰቢያ ዘዴና ቦታ መወያየትና መወሰን (የአርሶአደር ቡድን፣ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት (ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ)
5. የአርሶአደሮችን ግዴታዎችን የሚያስቀምጥ የስምምነት ሰነድ ማዘጋጀት (አርሶአደር ቡድን ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ
6. ዕቃዎችንና ማቴሪያሎችን መግዛትና ወደ ሥራ ቦታ ማጓጓዝ /በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/
7. በአርሶአደሮች ቡድን የሚገነባውን የፍራፍሬ መሰብሰቢያ ጎጆ መከታተል (ማህበረሰብ አደራጅና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
8. እምቅ ኃይል ካላቸው ገዢዎች ጋር የቢዝነስ ስብሰባ ማደራጀትና ማካሄድ በሥራ ቦታ እና የሽያጭ ኮንትራት ማመቻቸት (ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
9. ለአርሶአደር ቡድን የቢዝነስ ቅጾች (የመሰብሰቢያ መመዝገቢያ፣ የሽያጭ መመዝገቢያ ወዘተ) በመሰብሰብ፣ በዓይነት በመለየት፣ የቁጥጥር ዘዴዎች መመሪያ ማቅረብ (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
10. የመሰብሰቢያ፣ በዓይነት መለየት፣ በቁጥጥር ሥራዎችን መከታተልና መመሪያ መስጠት (ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት እና ማህበረሰብ አደራጅ)
11. የሥራውን ዕድገት፣ ውጤት ሪፓርት ለዞን የግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ እና ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በየወቅቱ (በወረዳግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
12. አልፎ አልፎ የሥራ ቦታ ክትትል ማድረግ (በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ)

- የአርሶአደሮች የቡድን ውይይት ስብሰባ ወቅት ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ግልጽና ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት እና ለማህበረሰብ አደራጅ ማቅረብ

ይኖርበታል፡፡
- በሥራ ቦታ ላይ ወይም ከአካባቢው አህያ መገዛት አለበት፡፡
- የአርሶአደሮች ቡድን ድጋፍ ለጋሞ ጎፋ ዞንና ለወላይታ ዞን የሚሰጥ ከሆነ የግንኙነት ድጋፍ (የደላላ ሥራ) ለዩኒየን መስጠትን አለመዘንጋት፣

ዋና የሥራ ክፍል 3፡ በፍራፍሬ ምርት አካባቢዎች ለአካባቢ ብረታብረት ድርጅቶች ድጋፍ መስጠት
የማምረቻ ዕቃዎች በብረታብረት ድርጅቶች እንዲመረቱ ለሚደረገው ጥረት ናሙናዎችን በማቅረብ፡ ሥዕሎች፣ ምላዶች ለመፍጠርና ነፃ ማቴሪያሎች (ብረት ለ30 ዕቃዎች) ለመጀመሪያ ምርት በማቅረብ መደገፍ፡፡ የዕቃዎች የሽያጭ ዋጋ ገደብ የተዘጋጀው መወሰን አለበት፡፡

[ የሥራ ማስኬጃ ሂደት ]
1. በወረዳ ላሉት ብረታብረት ድርጅቶች የማውረጃ ቁሳቁሱንና የድጋፍ ዕቅድ ገለፃ ማድረግ፣ ፍቃደኛነታቸውን ማረጋገጥና የሚሠራበትን ብረታ ብረት ድርጅት መወሰን (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
2. ናሙናዎችን፡ ሥዕሎችን፣ ሞልዶችን ለማጠፍና ነፃ ማቴሪያሎች መግዛትና ማቅረብ (በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ)
3. የሚሠሩ ዕቃዎች ቅርጽ፣ አንድ ዓይነት መሆን፣ ጥራት መፈተሽ፣ አስፈላጊ ከሆነ መመሪያ መስጠት (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
4. በወርክሾፑ ፊት ለፊት የማምረቻ ዕቃ ፖስተሮችን መትከል ቀላል የናሙና ማስተዋወቂያ መለጠፍ፡ (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
5. ሽያጭና ማምረቱን በየወቅቱ መከታተል (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
6. የሽያጭ ውጤትና ዕድገቱን ለክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በየወቅቱ ሪፓርት ማድረግ (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)

- የጋራ ስምምነት ሰነድ ማዘጋጀት
- ነፃ ማቴሪያሎች (ብረት ለ30 ዕቃዎች/ ምናልባት በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በቦታው ሊገዛ ይችላል፡፡

ዋና የሥራ ክፍል 4፡ በአካባቢው ነጋዴዎች አማካይነት የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስፋፋት፡
በአርሶአደሮች ፍላጐት ለመፍጠር ከአካባቢው ፍራፍሬ በሚገዙ ነጋዴዎች አማካይነት የማምረቻ ዕቃ መረጃ ማሠራጨት፡፡ የማምረቻ ዕቃ ለመጠቀም ፍቃደኛ የሆኑ 5 ነጋዴዎች በእያንዳንዱ የተመረጠ ወረዳ መለየት ወይም መምረጥ ለእያንዳንዱ ነጋዴ ከ10-15 ዕቃዎች መስጠት ከጥቂት ሣምንታት በኂላ ስለጥቅሙና አጠቃቀሙ ከነጋዴዎች መስማት፣ ዕቃዎቹን ለመጠቀም ለወደፊቱም ፍቃደኛ ከሆኑ ባለቤትነቱን መስጠት፡፡

[ የሥራ ሂደት ]
1. በገበያ ቀን የማምረቻ ዕቃና የነጋዴዎች ስሜት ማስረዳት (በወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
2. 5 ነጋዴዎችን መለየት/መምረጥ ከዚያም ስማቸውን ማረጋገጥ፣ የግንኙነት ሁኔታ፣ የፍራፍሬ መሰብሰቢያ ዕቅድ /ቀበሌና ቀን/ (በወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
3. ስም፣ ግንኙነት፣ ከአደራጅ ጋር የሚገናኙበት ቀን በወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
4. ነጋዴዎች ዕቃውን እንዴት በመንደር እንደሚጠቀሙ መከታተል፣ ሪፓርት ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ማድረግ /ማህበረሰብ አደራጅ/
5. ስለጥቅሙና አጠቃቀሙ መስማት፤ ዕቃውን መጠቀም መቀጠል የሚፈልጉ ከሆነ ኃላፊነቱን መስጠት (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
6. በተመረጠው ብረታብረት ድርጅት ዕቃው እንደማገኝ ለሌሎች የአካባቢ ነገዴዎች መንገር፡ (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)
7. የአፈፃፀም ዕድገቱን /ውጤቱን ለክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ሕ/ሥራ ቢሮ በየወቅቱ ሪፓርት ማድረግ (በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)

- የጋራ ስምምነት ሰነድ ማዘጋጀት የማስተላለፊያ ማስታወሻ ማዘጋጀት
- በመጀመሪያው ዓመት (2013/14 እ.ኤ.አ) ጥቂት ነጋዴዎች ዕቃዎችን መጠቀም መቀጠል የሚፈልጉ ከሆነ የተመረጡ ወረዳዎች ቁጥር ለዚህ ሥራ አካል በ2ኛው ዓመት (2014/15 እ.ኤ.አ) መቀነስ፡፡

ግብአት :

- ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐረት 1 በ2013/14 ከሁለት በላይ ከ2014/15 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ
- ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት 18 /1 በወረዳ/
- የቀበሌ ኮሚኒቲ አደራጅ፡ 90/18ወረዳዎች x 5 ቀበሌ/ወረዳ/

1. *ዕቃዎችና ማቴሪያሎች፡*
   ክፍል 1፡ የማውረጃ ቁሳቁስ 150 x 18 ፕላስቲክ ሣጥን 300 x 18 እና ፓስተሮች
   ክፍል 2፡ ፕላስቲክ ሣጥን 50 x 18, ለመሰብሰቢያ ጎጆ ማቴሪያል x18, ትራንስፓርትx 18
   ክፍል 3፡ የማውረጃ ቁሳቁስ (ናሙና) 2x18, ሞልድ 1x18, ብረት ለ30 *ዕቃዎች* x18
   ክፍል 4፡ የማውረጃ ቁሳቁስ 70x18
2. የገለፃ ስብሰባ፡ ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ /በወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት/ ዞን የግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ የጉዞ አበል፣ መስተንግዶ
3. የገበያ ዳሰባ፡ ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት የጉዞ ወጪ /ውሎ አበል የመኪና ነዳጅ/
4. የቢዝነስ ስብሰባ ከእምቅ ኃይል ካላቸው ገዢዎች ጋር፣ የገዢዎች የጉዞ ወጪ፣ መስተንግዶ
5. ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የሥራ ማስኬጃ ወጪ፡ ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት የጉዞ ወጪ ለክትትል /ውሎ አበል የመኪና ነዳጅ/ የግንኙነት ክፍያ፣ አላቂ የቢሮ *ዕቃዎች*።
6. ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የሥራ ማስኬጃ ወጪ፡ የትራንስፓርት ክፍያ ለቦታ፣ የግንኙነት ክፍያ አላቂ የቢሮ *ዕቃዎች*

<u>የተመረጡ የአርሶአደሮች ቡድኖች ለክፍል 2</u>
መሬት፣ የባህር ዛፍ ግንድ፣ ጉልበት ለጎጆ ግንባታ

ወጪ :

ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን በጀት ለማፈላለግ የሚወጣው ወጪ አልተካተተም

| የምርት ዘመን | 2013/14 | 2014/15 | 2015/16 | 2016/17 | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| የተመረጠ ወረዳ ብዛት | 4 | 6 | 6 | 2 | 18 |
| **ዋና ሥራ ክፍል 1: የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስተዋወቅ** | | | | | |
| መገልገያዎችና ዕቃዎች | 102,000 | 153,000 | 153,000 | 51,000 | 459,000 |
| መገልገያዎችን ማጓጓዣ ወጪ | 11,000 | 16,100 | 14,600 | 10,000 | 51,700 |
| ከክልለ፣ ዞንና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ የመስምር መ/ቤቶች ስብሳ | 3,200 | 6,000 | 5,900 | 2,400 | 17,500 |
| **ዋና ሥራ ክፍል 1: የገበያ ትስስርን መደገፍ** | | | | | |
| የገበያ ጥናት (ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች የጉዞ | 4,900 | 4,900 | 4,900 | 4,900 | 19,600 |
| መገልገያዎችና ዕቃዎች | 78,200 | 117,300 | 117,300 | 39,100 | 351,900 |
| መገልገያዎችን ማጓጓዣ ወጪ | 5,500 | 10,800 | 9,300 | 5,000 | 30,600 |
| ከገዢ ጋር የቢዝነስ ውይይት ማድረግ | 9,000 | 18,000 | 22,500 | 27,000 | 76,500 |
| **ዋና የሥራ ክፍል 3 : የአካባቢ ብረታብረት ድርጅቶቸን መደገፍ** | | | | | |
| መገልገያዎችና ዕቃዎች | 4,400 | 6,600 | 6,600 | 2,200 | 19,800 |
| **ዋና የሥራ ክፍል 4 : በአካባቢው ነጋዴዎች አማካይነት የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስፋፋት** | | | | | |
| መገልገያዎችና ዕቃዎች | 16,800 | 25,200 | 6,600 | 2,200 | 50,800 |
| **የክልል ቢሮና የወረዳ ጽ/ቤት ስራ ማስኬጃ ወጪ** | | | | | |
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች የጉዞ ወጪ (አበል፣ | 18,000 | 25,200 | 36,000 | 43,200 | 122,400 |
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሥራ ማስኬጃ ወጪ | 3,500 | 3,500 | 3,500 | 3,500 | 14,000 |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የትራንፖርት ወጪ | 4,200 | 10,500 | 16,800 | 18,900 | 50,400 |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሥራ ማስኬጃ ወጪ | 6,000 | 15,000 | 24,000 | 27,000 | 72,000 |
| ድምር | 266,700 | 412,100 | 421,000 | 236,400 | 1,336,200 |

*መጠባበቂያ* (10%) 133,700 ብር
ጠቅላላ 1,470,000 ብር

የጊዜ ሠሌዳ :

የጊዜ ሠሌዳ የወጣው በበጀት ምደባ ለመጀመሪያ ዓመት /2013/2014/ ሥራዎች በሰኔ 2013 እንደሚጠናቀቁ በመገመት ነው።

| | 2013 (እ.ኤ.አ) | | | | 2014 (እ.ኤ.አ) | | | | 2015 (እ.ኤ.አ) | | | | 2016 (እ.ኤ.አ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| የፍራፍሬ ማሰብሰብ መስፋፊያ ፕሮጀክት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ለፕሮጀክት የሚስፈልግ በጀት ማግኘት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የሥራ ዋና ክፍል 1፡ ፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ማስተዋወቅ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የሥራ ዋና ክፍል 2፡ በጥራት ላይ ተመስርተው ከሚገዙ ተቋማት ጋር የገበያ ትስስር መፍጠር | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የሥራ ዋና ክፍል 3 ፡ የፍርፍሬ ማውረጃ ለሚሠሩ ብረታብረት ድርጅቶች እገዛ መስጠት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የሥራ ዋና ክፍል 4 ፡ በአካባቢ ነጋዴዎች አማካኝነት የፍራፍሬ ማውረጃ ማስተዋወቅና ማሰራጨት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ማናጎ መሰብሰቢያ ዋና ወቅት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| አቮካዶ መሰብሰቢያ ዋና ወቅት | | | | | | | | | | | | | | | | |

የትኩረት ነጥቦች / ለሁሉም ክፍሎች ፡

በእያንዳንዱ ወረዳ የክትትል ሥርዓት ማቋቋም፡

ክትትል መደረግ ያለበት ዕቃዎች በተሰጡበት ዓመት ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ወቅት በፕሮጀክት ጊዜ በአጠቃላይ መሆን አለበት ስለዚህ ጠንካራ የክትትል ሥርዓት በእያንዳንዱ ወረዳ ማቋቋም፡፡ /በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት እና የማህበረሰብ አደራጅ/ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ወቅታዊ ክትትል 1 ወይም 2 ጊዜ በወረዳ 1 ዓመት1፡ የወረዳ ቁጥር በየዓመቱ ስለሚጨምር የጉዞ ጊዜ ሠሌዳ ጥሩ ዕቅድ መዘጋጀት አለበት፡፡

የዞን የግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ ጽ/ቤት አገልግሎት ሚና

ከ2ኛ ዓመት በኂላ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የሥራ ጫና ለመቋቋም፣ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሚናና ሥራዎች ለ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ ማስተላለፍ ግልጽ አይደለም፡፡ ስለዚህ የዚህ ፕሮጀክት ዕቅድ የተዘጋጀው በጀቱ ሙሉ በሙሉ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ቁጥጥር እንደሚሆን በመገመት ነው፡፡ የሚናና የወጪ የማዘዝ ስልጣን (ይኸውም ዞን የግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ የሰው ኃይል አጠቃቀም) ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከፕሮጀክት ጅምር በፊት ማሰብ አለበት፡፡

የሥራ ድምበር በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ እና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት መካከል በክልል ግብርና ቢሮ እና ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት መካከል

ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከግብርና ቢሮ ጋር ያለውን ትብብር (ድምበር ከፕሮጀክት ጅምር በፊት መወያየት አለበት፡፡ ትብብር ጥሩ ይመስላል ነገር ግን በጥሩ ሁኔታ ያልተተረጎመ ትብብር በሥራ ቦታ ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ግልጽ ድምበር በማስቀመጥ ሚናና ኃለፊነት መገለጽ አለበት፡፡

## ዕዝል 1 ለፕሮጀክቱ የተመረጡ እጩ ወረዳዎች

| ዞን | | ወረዳ | ማንጎ | አቫካዶ | ቅድሚያ የተሰጠ * | ሙከራ ፕሮ. 03 የተመረጠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጋሞ ጎፋ | 1 | አ/ምንጭ | X | | 1 | |
| | 2 | ምዕራብ አባያ | X | | 2 | ☆ |
| | 3 | ደንባ ጎፋ | x | | 3 | |
| ወላይታ | 4 | ቦሎሶ ቦምቤ | X | X | 1 | ☆ |
| | 5 | ቦሎሶ ሶሬ | X | X | 2 | |
| | 6 | ዳሞት ጋሌ | | X | 3 | |
| | 7 | ዳሞት ፉላሳ | | x | 4 | |
| | 8 | ሶዶ ዙሪያ | | x | 5 | |
| | 9 | ኦፋ | | x | 6 | |
| | 10 | ኪነዶ ኮይሻ | | x | 7 | |
| | 11 | ዳሞት ወይዴ | | X | 8 | |
| ከምባታ ጠምባሮ | 12 | ሃዳሮ ጡንጦ | X | X | 1 | |
| | 13 | ቃጫ ቢራ | | X | 2 | |
| | 14 | ቀዲዳ ጋሜላ | | x | 3 | |
| | 15 | ጠምባሮ | | X | 4 | |
| ሲዳማ | 16 | ወንዶገነት | | X | 1 | |
| | 17 | ዳሌ | | X | 2 | ☆ |
| | 18 | አለታ ወንዶ | | X | 3 | |
| | 19 | ሀዋሣ ዙሪያ | | x | 4 | |
| | 20 | ቦና ዙሪያ | | X | 5 | |
| | 21 | ሸበዲኖ | | x | 6 | |
| | 22 | ወንሾ | | X | 7 | |
| | 23 | በንሳ | | x | 8 | |
| | 24 | ዳራ | | X | 9 | |
| ጌደኦ | 25 | ዲላ ዙሪያ | | X | 1 | |
| | 26 | ወናጎ | | X | 2 | |
| ቤንች ማጂ | 27 | ሰሜን ቤንች | x | X | 1 | |
| | 28 | ደቡብ ቤንች | x | X | 2 | |

* በክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያ (ሙከራትግበራ ፕሮጀክት 03 መሪ) ቅድሚያ ተከተል ተሠጥቷል፡፡
X : የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት የተመረጡ ወረዳዎች (ፕሮጀክት ቁጥር 1

## የፕሮጀክት ቁጥር 4

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የማንጎ ሽያጭ ለአፍሪካ ጅውስ ኩባንያ እውን ለማድረገ ድጋፍ | | |
| እስትራቴጂ: | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ ትርፍ ማሳደግ<br>2-4: የተለዩና ከፍተኛ የሆኑ የምርት ዝሪያዎች ግብይት ማጠናከር | | |
| የመሪ ዕቅድ ፕሮግራም | ከፍተኛ የእሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>የፍራፍሬ ብክነት መቋቋሚያ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2013-2017 እ.ኤ.አ (5 ዓመት) | | |
| የፕሮጀክት ቦታ | ጋሞጎፋ ዞን፣ ወላይታ ዞን | | |
| የተመረጠ ሰብል / ምርት | ማንጎ | | |
| የተመረጠ ቡድን | ዳሞታ ዩኒየን፣ ጋሞ ጎፋ ዩኒየንና አባል መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት | | |
| ፈፃሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | ደጋፊ አካል | |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች:
ለአፍሪካ ጀውስ ኩባንያ ማንጎ ማቅረብ በከፍተኛ የምርት ወቅት የሚፈጠረውን የዋጋ ዝቅ ማለት ይቋቋማል ተብሎ ይገመታል። አቅራቢ ወገን (ዩኒየኖች፣ ሕ/ሥራ ማህበራት፣ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ) ከኩባንያ የጥራትና የመጠን ፍላጎት በማሟላት የተረጋጋ የቢዝነስ ግንኙነት ለመፍጠር ጥረት ማድረግ አለበት።

ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የተረጋጋ የቢዝነስ ግንኙነት ለመፍጠር የመሪነት ማና መጫወት አለበት የኮንትራት ውሉ ከኩባንያውና ከዩኒየኖች መካከል ተግባራዊ ከሆነ በኂላ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ለመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበራት የተረጋጋ የፈራፍሬ መሰብሰብን ለማስፋፋት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ። በአቅራቢ ወገን አባላት መካከል የጋራ ሥራ በ2 ዩኒየኖች ጭምር አንድነትን ማስፋፋት።

ድርጊት:
በዋና የምርት መሰብሰቢያ ወቅት ከጥቅምት እስከ መጋቢት /6 ወራት/ በየዓመቱ ሥራዎች ይከናወናሉ። ለሥራዎቹ ተዋናይ ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ነው ሌላ ካልተገለፀ በስተቀር:

1. ሽያጭ ውል ስምምነት ከአፍሪካ ጭማቂ ጋር ማመቻቸት
   - 1.1 የግንኙነት ሰው ማረጋገጥ /ለዕቃ ግዢ ኃላፊነት ያለውን ሰው/ ከአፍሪካ ጭማቂ፣
   - 1.2 ስለፍራፍሬ ሁኔታ የተገመተ የምርት መሰብሰቢያ ወቅት ወዘተ ለአፍሪካ ጀውስ መረጃ ማቅረብ፣
   - 1.3 የቢዝነስ ስብሰባ በዩኒየኖችና አፍሪካ ጅውስ ጋር ማዘጋጀትና ማካሄድ፣
   - 1.4 የሽያጭ ስምምነት ለማጠቃለል ድጋፍ፣
   - 1.5 በዩኒየኖችና አፍሪካ ጅውስ መካከል የክለሳ ስብሰባ ማዘጋጀትና ማካሄድ፣ ከምርት መሰብሰቢያ ወቅት በኂላ፣
2. ለፍራፍሬ መሰብሰብና ማጓጓዝ የተረጋጋ ሥራ ድጋፍ
   - 2.1 የአፍሪካ ጭማቂ የጊዜ ሠሌዳና ፍላጎት ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ማስታወቅ፣
   - 2.2 የፍራፍሬ መሰብሰብን በመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበራት ክትትል ማድረግና መመሪያ መስጠት /በወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት/
   - 2.3 በወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት አማካይነት የማጓጓዝ ዕድገት መጨበጥና አስፈላጊ ከሆነ ችግሮችን ለመፍታት ድጋፍ መስጠት፣

ግብአት:
- ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት :1
- ቢዝነስ ስብሰባ: የተሣታፊዎች የጉዞ አበል፣ የመኪና ነዳጅ ወደ ጭማቂ ፋብሪካ 5 (የስብሰባ ቦታ)
- የክላስ ስብሰባ: የተሣታፊዎች የጉዞ አበል፣ የመኪና ነዳጅ፣ ወደ ጭማቂ ፋብሪካ የስብሰባ ቦታ)
- የሥራ ማስኬጃ ወጪ: ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት የጉዞ /አበል፣ የመኪና ነዳጅ/ የግንኙነት ክፍያ የቢሮ ዕቃዎች፣ ትራንስፓርት ክፍያ ወደ ቦታው (ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት)

ወጪ :

የተመረጡ ወረዳዎች ከፕሮጀክት ቁጥር 3 ጋር ተመሳሳይ ላይሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ የፕሮጀክት ወጪ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የስራ ማስኬጃ ወጪ/ የተገመተው 6 የተመረጡ ወረዳዎች እንዳሉ (መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት) ነው።

| የምርት ዘመን | 2013/14 | 2014/15 | 2015/16 | 2016/17 | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| የቢዝነስ ስብሰባ | 11,000 | 11,000 | 11,000 | 11,000 | 44,000 |
| የክለሳ ስብሳባ | 11,000 | 11,000 | 11,000 | 11,000 | 44,000 |
| | | | | | |
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያዎች የጉዞ | 9,000 | 9,000 | 9,000 | 9,000 | 36,000 |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የትራንፖርት ወጪ | 3,600 | 3,600 | 3,600 | 3,600 | 14,400 |
| | | | | | |
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሥራ ማስኬጃ ወጪ | 3,000 | 3,000 | 3,000 | 3,000 | 12,000 |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሥራ ማስኬጃ ወጪ | 7,200 | 7,200 | 7,200 | 7,200 | 28,800 |
| | | | | | |
| ድምር | 44,800 | 44,800 | 44,800 | 44,800 | 179,200 |

መጠባበቂያ (10%) 18,000 ር

ጠቅላላ 197,000 ብር

የጊዜ ሠሌዳ:




ማስታወሻ:

ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት (ቡድን መሪ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 03) የአፍሪካ ጁውስ ኩባንያ ጎብኝቶ ከጥራት ቁጥጥር ሥራ አስኪያጅ ጋር ግንኙነት አድርጓል።

## የፕሮጀክት ቁጥር 5

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም፡ | ወደ ከተማ አካባቢ የሚደረገው የቲማቲም ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት ደረጃ 1 ፡ ሞዴል ማቋቋም | | |
| እስትራቴጂ፡ | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ የትርፍ ጭማሪ<br>2-1: የአትክልትና ፍራፍሬ የምርት መሰብሰቢያና አያያዝ ዘዴ ማሻሻያ<br>2-5: የጋራ ግብይት ማፋጠን | | |
| የመሪ ዕቅድ፡<br>ፕሮግራም፡ | ከፍተኛ የእሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>የአትክልት ማጓጓዣ ዘመናዊ የማድረግ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክት ጊዜ፡ | 2013-2016 (4 ዓመት)<br>❖ የፕሮጀክቱን በጀት ማግኛ ዘዴ 1 ዓመት<br>❖ በሃዋሣ ከተማ አካባቢ በመስኖ የሚለማው ቲማቲም የምርት ወቅት ከህዳር እስከ ጥር ነው፡፡ ፕሮጀክቱ የሚሸፍነው 2 የምርት ወቅት ነው፡፡ | | |
| የፕሮጀክት ቦታ፡ | ሲዳማ ዞን<br>❖ የመስኖ ቲማቲም ምርት በሃዋሣ ከተማ አካባቢ<br>❖ የተመረጡ ወረዳዎችና ቡድኖች በፕሮጀክት ሥራ ዝርዝር ታይቷል፡፡ | | |
| የተመረጠ ሰብል / ምርት | ቲማቲም | | |
| የተመረጠ ቡድን | ❖ የተመረጠ ቡድን 2፣ የምርት ውጤታቸውን ለማወዳደር<br>❖ የመኪና ሙሉ ጭነት ቲማቲም ለማጓጓዝ ዘወትር ቢያንስ በሣምንት 1 ጊዜ በምርት ወቅት ለ2ወር እያንዳንዱ የተመረጠ ቡድን በቂ የምርት መጠን ሊኖረው ይገባል፡፡ | | |
| ፈፃሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ<br>ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ደጋፊ አካል | |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች:

በሸማቾች ምርጫና በገበያ ዋጋ መሠረት የቲማቲም ተፈጥሮው ወደ ገበያ ለማጓጓዝ ከጠንካራ ወደ ለስላሣና ከአረንጓዴ ብስል ፍሬ ወደ ቀይ የበሰለ ፍሬ ይቀየራል፡፡ (ይህ ማለት የበለጠ ቶሎ የሚበላሽ ይሆናል) ማለት ነው፡፡ የቲማቲም ፍሬ የጉዳት መከላከል በምርት መሰብሰቢያና የማጓጓዝ ጊዜ ከአሁን በኋላ የበለጠ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ይሆናል፡፡

በምርት መሰብሰቢያና ማጓጓዣ ጊዜ የሚኖረውን የምርት ብክነት ለመከላከል የአርሶአደሩን ችግር ለመፍታት ይሞክራል፡፡ ይህ ፕሮጀክት የሞከረው የቲማቲም ማጓጓዣ ማሻሻያ ሞዴል በሀዋሣ ከተማ በመስኖ በሚያለሙ የቲማቲም አምራቾች ቡድን ለማቋቋም ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ሁለት ሞዴል ቡድኖችን ለማቋቋም ያስባል፡፡

የፕላስቲክ ሣጥኖች በሚመለከት በአመራሮች ቡድንና በገዢዎች መካከል የሣጥኖች ዝውውር ስርዓት ለመፍጠር ይሞከራል፡፡ ከፕሮጀክቱ ማብቂያ በኋላ የድጎማ ስርዓት ለመዘርጋት መረጃ መሰብሰብና ዕቅድ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡

ድርጊት:

ክልል ግብይትና ሥ/ሥራ ቢሮ የሥራዎቹ ተዋናይ ነው፡፡ በሌላ መንገድ ካልተገለፀ በስተቀር ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ የግብዐትና ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት

[ 2013 ]

0. ለፕሮጀክቱ መጀመር በጀት የማፈላለግ ሥራ

[ 2014/2015 የምርት ወቅት ]

1. ወረዳዎችንና ቡድኖችን መምረጥ
2. ኃላፊነት ካለው የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት ጋር ስለአሠልጣኞች ሥልጠና መግባባት መፍጠር
3. ከተመረጡ ቡድን ጋር የድጋፍ ይዘትና የእነርሱ ኃላፊነት መግባባት መፍጠር /የጋራ የውል ስምምነት ማዘጋጀት/

4. ከተመረጠው ቡድን ጋር የጋራ ሽያጭ ፕላስቲክ ሣጥኖችን ሌሎች ዕቃዎችን በመጠቀም እንዴት መሥራት እንዳለባቸው የዕቅድ ስብሰባ ማካሄድ፡፡
5. ለጋራ ሽያጭ የምዝገባ ቅጾችና ፎርማቶች /ጥራዞች ለማዘጋጀት ድጋፍ ማድረግ፣
6. ተቋማዊ ገዢዎችን በሀዋሣና ሻሸመኔ አካባቢ ለማፈላለግ ድጋፍ ማድረግ፣
7. ከገዢዎች ጋር ዝርዝር የንግድ ሁኔታዎች ለማጠቃለል፤ ፕላስቲክ ሣጥኖችን ዝውውር ሥርዓትን ጨምሮ ድጋፍ ማድረግ፣
8. ዕቃዎችንና ማቴሪያሎችን ግዢ መፈፀም ወደ ሥራ ቦታ ማጓጓዝ፣
9. በመሰብሰብ፣ በዓይነት በመለየትና በመጋዘን ማከማቸት በሚመለከት ስለ አሠራሩ መመሪያ መስጠት፡፡ ወቅታዊ ክትትል ማድረግ /ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት/
10. የተመረጡ ቡድኖች ችግሮች ለማየት የጉብኝት ፕሮግራም ማዘጋጀትና ማካሄድ በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርቶች በሲዳማ ዞን፤ ቁልፍ የቲማቲም አምራቾች፣ ሕ/ሥራ ማህበራት፣ የአርሶአደር ቡድን መሪዎች፣
11. ክለሣና ግምገማ ማካሄድ፣

[2015/16 የምርት ወቅት]

4. ከተመረጠው ቡድን ጋር የጋራ ሽያጭ ፕላስቲክ ሣጥኖችን ሌሎች ዕቃዎችን በመጠቀም እንዴት መሥራት እንዳለባቸው የዕቅድ ስብሰባ ማካሄድ፡፡
6. ተቋማዊ ገዢዎችን በሀዋሣና ሻሸመኔ አካባቢ ለማፈላለግ ድጋፍ ማድረግ፣
7. ከገዢዎች ጋር ዝርዝር የንግድ ሁኔታዎች ለማጠቃለል፤ ፕላስቲክ ሣጥኖችን ዝውውር ሥርዓትን ጨምሮ ድጋፍ ማድረግ፣
9. በመሰብሰብ፣ በዓይነት በመለየትና በመጋዘን ማከማቸት በሚመለከት ስለ አሠራሩ መመሪያ መስጠት፡፡ ወቅታዊ ክትትል ማድረግ /ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት/
10. የተመረጡ ቡድኖች ችግሮች ለማየት የጉብኝት ፕሮግራም ማዘጋጀትና ማካሄድ በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ማስፋፊያ ጽ/ቤት ኤክስፐርቶች በሲዳማ ዞን፤ ቁልፍ የቲማቲም አምራቾች፣ ህ/ሥራ ማህበራት፣ የአርሶአደር ቡድን መሪዎች፣
11. ክለሣና ግምገማ ማካሄድ

ግብአት :

<u>ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት</u>

- ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት፡ 1. በመጀመሪያ ዓመት፣ 2. ከሁለተኛው ዓመት በኋላ (ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ 32 ወር
- ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት፡ 2 /1በወረዳ x 2 ወረዳዎች/ /ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት 18 ወር
- ዕቃዎችና ማቴሪያሎች፡ ፕላስቲክ ሣጥኖች /400 በቡድን/፣ ዝርግ ሚዛን፣ የሚገፋ ጋሪ፣ ቀላል መጋዘን ለመገንባት ፕላስቲክ ሣጥኖች ለማስቀመጥ
- ለተመረጡ ቡድኖች ለግብይት ሥራዎች ወጪ ድጐማ ማዘጋጀት
- ለመስክ ጉብኝት ጉዞ ወጪ
- የክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሥራ ማስኬጃ ወጪ፡ የመኪና ነዳጅ፣ የግንኙነት ክፍያ የትራንስፓርት ክፍያ ወደ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት፣ የቢሮ ዕቃዎች ወዘተ…

<u>የተመረጡ ቡድኖች</u>

መሬት፣ የባህር ዛፍ፣ ቀላል መገልገያ (መጋዝ)፣ የሰው ጉልበት

ወጪ :

- ለፕሮጀክቱ የበጀት ማፈላለግ ሥራ፡ እንቅስቃሴ ወጪ በፕሮጀክት ወጪ አልተካተተም
- የፕሮጀክቱ ቦታዎች በሀዋሣ ከተማ አካባቢ ስለሆነ የክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የጉዞ አበል በፕሮጀክት ወጪ አልተገመተም፡፡

<u>ዕቃዎችና ማቴሪያሎች ለተመረጡ ቡድኖች</u>
- ዕቃዎችና ማቴሪያሎች 82,000 (41,000 x 2 ቦታዎች)
- ዕቃዎችን ለማጓጓዝ 10,000
- መዝገብ አያያዝ ቅጾች/ጥራዞች 1,000

<u>የክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሥራ ማስኬጃ ወጪ</u>
- ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት የትራንስፓርት (የመኪና ነዳጅ) 14,500
- ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት የትራንስፓርት (የአውቶቡስ ክፍያ) 4,000
- የስብሰባ ወጪ 4,000
- የቢሮ መገልገያ እቃዎች 9,500
- ክልልና ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ የግንኙነት ክፍያ 7,600

<u>ተቋማዊ ገዢዎችን ለማፈላለግ የንግድ ሁኔታ ለማጠቃለል</u>
- የትራንስፓርት ወጪ ለተመረጡ ቡድን መሪዎች 1,000

<u>የመስክ ጉብኝት ወደ ተመረጡ ቡድን</u>
- ለተሣታፊዎች የትራንስፓርትና መስተንግዶ ወጪ 1,000

| | | |
|---|---|---|
| ንዑስ ድምር | 134,600 | ብር |
| መጠባበቂያ(10%) | 13,400 | ብር |
| ጠ/ድምር | 148,000 | ብር |

የጊዜ ሠሌዳ :
- ❖ የፕሮጀክት በጀት ለማግኘት የተገመተ ጊዜ 1 ዓመት ነው፡፡

| | | 2013 | | | | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 0 | ለፕሮጀክቱ መጀመር በጀት የማፈላለግ ሥራ | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | |
| 1 | ወረዳዎችንና ቡድኖችን መምረጥ | | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 2 | ከወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት ጋር በሥራው ዝርዝር መግባባት መፍጠር | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 3 | ከተመረጡ ቡድን ጋር የድጋፍ ይዘትና የእነርሱ ኃላፊነት መግባባት መፍጠር | | | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 4 | ለጋራ ሽያጭ ፕላስቲክ ሣጥኖችን አጠቃቀም ላይ የዕቅድ ስብሰባ ማካሄድ | | | | | | ■ | | | | | ■ | | | | | |
| 5 | የምዝገባ ቅጾችና ፎርማቶች /ጥራዞች ለማዘጋጀት ድጋፍ ማድረግ፣ | | | | | | | ■ | | | | | | | | | |
| 6 | ተቋማዊ ገዢዎችን ለማፈላለግ ድጋፍ ማድረግ፣ | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | | |
| 7 | ከገዢዎች ጋር ዝርዝር የንግድ ሁኔታዎች ማጠቃለል | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | | |
| 8 | ዕቃዎችንና ማቴሪያሎችን ግዢ መፈፀም ወደ ሥራ ቦታ ማጓጓዝ፣ | | | | | | | | ■ | | | | | | | | |
| 9 | በመሰብሰብ፣ በዓይነት በመለየትና በመጋዘን ማከማቸት በሚመለከት መመሪያ መስጠት | | | | | | | | ■ | ■ | ■ | | ■ | ■ | ■ | | |
| 10 | የተመረጡ ቡድኖች ችግሮች ለማየት የጉብኝት ፕሮግራም ማዘጋጀትና ማካሄድ | | | | | | | | | | | | ■ | | | | |
| 11 | ክለሣና ግምገማ ማካሄድ፣ | | | | | | | | | | ■ | | | ■ | ■ | | |
| | በመሥኖ የለማ ቲማቲም መሰባሰቢያ ጊዜ (ዋናው ጊዜ ህዳር-ጥር) | | | | | | | | ■ | ■ | ■ | | ■ | ■ | ■ | | |

ማስታወሻ:

ለክለሣና ግምገማ የአስተያየት ነጥብ
- የፕላስቲክ ሣጥኖች የዝውውር ሥርዓት ዘላቂነት
- የፕላስቲክ ሣጥኖችን የዝውውር ሥርዓት እንዴት ወደ ሌሎች ቡድኖች ማስተዋወቅ እንደሚቻል (የድጋፍ እርምጃዎች ጭምር በማካተት)

## የፕሮጀክት ቁጥር 6

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | ወደ ከተማ አካባቢ የሚደረገው የቲማቲም ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት<br>ደረጃ 2 : የመነሻ ወጪ ዝግጅትና የመፈፀም ድጋፍ ዕቅድ | | |
| እስትራቴጂ | 2. ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ የትርፍ ጭማሪ<br>2-1: የአትክልትና ፍራፍሬ የምርት መሰብሰቢያና አያያዝ ዘዴ ማሻሻያ<br>2-5: የጋራ ግብይት ማፋጠን | | |
| የመሪ ዕቅድፕሮግራም | ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>የአትክልት ማጓጓዣ ዘመናዊ የማድረግ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2016-2018 እ.ኤ.አ (24 ወራት) | | |
| የተመረጠ አካባቢ | ሲዳማ ዞን<br>❖ የመስኖ ቲማቲም ምርት በሀዋሣ ከተማ አካባቢ | | |
| የተመረጠ ሰብል | ቲማቲም | | |
| የተመረጠ ቡድን | የቲማቲም አምራቾች ቡድኖች<br>የተመረጡ ቡድኖች በፕሮጀክት ዘመን 15 ቡድኖች ይሆናሉ | | |
| ፈፃሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | ደጋፊ ኤጀንሲ | |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች፡
በምርት መሰብሰቢያና ማጓጓዣ ጊዜ የሚኖረውን የቲማቲም ምርት ብክነትና የአርሶአደሩን ችግር ለመፍታት የቲማቲም ማጓጓዣ ለማሻሻልና የጋራ ሽያጭ ተግባራዊ ለማድረግ የመነሻ ወጪ መሸፈኛ የድጎማ ሥርዓት ማዘጋጀትና በተግባር ማዋል፡፡ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ በከፊል የገንዘብ ድጎማ በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች እንደ ፕላስቲክ ሣጥኖች ግዢ ወጪ ለመሸፈን የድጎማ ሥርዓት ማዘጋጀት፡ በፕሮጀክት ቁጥር 5 የተገኘውን መረጃ በመጠቀም የድጎማ ሥርዓት ዘዴ ማቀድ፡፡

ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ቀደም ብሎ የፕሮጀክቱን በጀት ከክልሉ መንግስት ወይም ከመንሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ለማግኘት መሥራት አለበት፡፡

ድርጊት:

❖ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ለሥራዎቹ ተዋናይ ነው፡፡ በሌላ መልክ ካልተገለፀ በስተቀር፡

1. ለቲማቲም ማጓጓዣ ዕቃዎች የድጎማ ሥርዓት ማቀድ፡-
   <ለዕቅድ የሚሆኑ ነጥቦች>
- የሥራ መጠን የድጎማው ደረጃ፡ የተጠቃሚ ቡድኖች ቁጥር፣ የታቀደው ዕቃና መጠን፣
- የእገዛ መጠን፣ የላይኛው ጣሪያ፣
  ❖ ማስታወሻ፡ የፕረጀክቱን ወጪ ለለማስላት ለጊዜው 50% የድጎማ መጠን ታሳቢ ተደርጎ ተወስዷል፡፡
- የተመረተ አካባቢ፣
- የተጠቃሚ አምራቾች ቡድን ሁኔታ፣
- የሥርጭት ሥርዓት ወይም ዘዴ፣
- የተጠቃሚዎች ግዴታዎች (የድጎማ መመለሻ ጊዜ፣ የመዝገብ አያያዝ፣ ሪፓርት የማድረግ ወዘተ…)
- በፕሮጀክት ቁ.5 ለተገኘው ትምህርት ተፃራሪ እርምጃ መውሰድ፣

2. ለድጎማ ሥርዓቱ በጀት የማግኘት ሥራዎች
   እርዳታ ይሰጣል ተብሎ ለሚገመተው ድርጅት ፕሮፓዛል ሠነድ በማዘጋጀት ማስረዳት ፕሮፓዛሉ የታቀደውን ድጎማ ሥርዓት ዝርዝር የሚሸፍንና በፕሮጀክት ቁጥር 5 የተገኙ ጥቅሞችን ወይም አፈፃፀሞችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

[ የፕሮጀክቱ በጀት ከተገኘ በኂላ የሚሠሩ ሥራዎች ]

3. ለሕዝብ ማስታወቂያ፣ ማመልከትና ምርጫ ዘዴዎችን ማቀድ፡

<ለዕቅድ የሚሆኑ ነጥቦች>

- ለሕዝብ ማስታወቂያ፣ ዘዴዎች
- የማመልከቻ ቅጾችና ዶክሜንቶች የሚያያዙ (ለጋራ ሽያጭ ዕቅድ፣ በጋራ ሽያጭ ያሉ ልምዶች ወዘተ)፣ የማመልከቻ ዶክመንቶች ለማዘጋጀት መመሪያ፣
- የምርጫ መመዘኛና ዘዴ፣

4. ለድጎማ ሥርዓት የሕዝብ ማስታወቂያ
5. የቀረቡትን ማመልከቻዎች መቀበል፣ አመልካቾችን መመርመር፣ ተጠቃሚዎችን መምረጥ፣
6. ሥርጭት
7. በተጠቃሚ ቡድኖች የጋራ ማጓጓዣ መከታተልና በሥራ ቦታ መመሪያ መስጠት
8. ለሚመለከታቸው አካላት የሪፓርት ዶክመንት ማዘጋጀትና ሪፓርት ማድረግ
9. ለቀጣዩ ዓመት የድጎማ ፕሮጀክት ዕቅድ ማዘጋጀት
10. ለቀጣዩ ዓመት በጀት ለማግኘት መሥራት

ግብአት :

- ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት፡ 2 (26 ወር)
- የአካባቢ አማካሪ የድጎማ ሥርዓት ዕቅድ ዝግጅትን ያመክራል፤ የሕዝብ ማስተዋወቅ የሚቻልበትን፣ ማመልከቻና ምርጫ የሚካሄድበትን ዘዴ ያቅዳል፣
- ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የሥራ ማስኬጃ ወጪ፡ የመኪና ነዳጅ፣ የስብሰባ ወጪ፣ የቢሮ ዕቃዎች፣ የህትመት ወጪ፣ የግንኙነት ክፍያ ወዘተ…
- ለ15 አምራች ቡድኖች (ለጊዜው ግብ የተጣለው) ለመነሻ ወጪ መሸፈኛ ገንዘብ

ወጪ :

❖ የተመረጠ አካባቢ ሀዋሣ ከተማ፣ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የጉዞ አበል፣ በፕሮጀክቱ ወጪ አልተገመተም

<u>ድርጊት 1 እና 2፡</u>

| | |
|---|---|
| የአካባቢ ኮንሰልታንት (1ሰው፣ 1 ወር) | 17,500 ($1,000 የአሪሜካን ዶላር) |
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት | |
| ትራንስፓርት ወጪ (የመኪና ነዳጅ) | 1,500 |
| የስብሰባ ወጪ | 1,800 |
| የቢሮ ዕቃዎች፣ ፕሮፓዛል ህትመት | 4,000 |
| የግንኙነት ክፍያ | 1,600 |

<u>ድርጊት ከ3 እስከ 10፡</u>

| | |
|---|---|
| የአካባቢ አማካሪ (1ሰው 1 ወር) | 17,500 ($1,000 የአሪሜከን ዶላር) |
| የሕዝብ ማስታወቂያ | 2,000 |
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት | |
| ትራንስፓርት ወጪ (የመኪና ነዳጅ) | 8,000 |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት | |
| ትራንስፓርት ወጪ (የአውቶቡስ ክፍያ) | 2,600 |
| የስብሰባ ወጪ | 3,600 |
| የቢሮ ዕቃዎች የሪፓርት ዶክመንት ህትመት | 9,000 |
| የግንኙነት ክፍያ | 3,600 |
| ንዑስ ድምር | 72,700 ብር |
| መጠባበቂያ (10%) | 7,300 ብር |
| ጠ/ድምር | 80,000 ብር |

<u>ለ15ነአምራች ቡድኖች ለመነሻ ወጪ ድጎማ የሚያስፈልግ ገንዘብ</u>

- የታሰቡ ዕቃዎች ፕላስቲ ሣጥን (400 በአንድ ቡድን)፣ ሚዛን፣ በእጅ የሚገፋ ጋሪ፣ ፕላስቲክ ሣጥን ማስቀመጫ ትንስ መጋዘን መስሪያ ቁሳቁስ
- የገንዘብ መጠን = 41,000 ብር በቡድን X 15 ቡድን X ድጎ መጠን (50%)= 307,500 ብር

**የጊዜ ሠሌዳ :**

❖ ይህ ፕሮጀክት ወደ ተግባር መግባት ያለበት ፕሮጀክት ቁጥር 5 ተግባራዊ ከሂ በኂላ ነው።

| | 2016 | | | | 2017 | | | | 2018 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1. ለቲማቲም ማጓጓዣ ዕቃዎች የድጎማ ሥርዓት ማቀድ | | ■ | | | | | | | | | | |
| 2. ለድጎማ በጀት የማግኘት ሥራዎች | | | ■ | ■ | | | | | | | | |
| [የፕሮጀክቱ በጀት ከተገኘ በኂላ የሚሠሩ ሥራዎች] | | | | | | | | | | | | |
| 3.ለሕዝብ ማስታወቂያ፣ ማመልከትና ምርጫ ዘዴዎችን ማቀድ | | | | | ■ | | | | | | | |
| 4. ለድጎማ ሥርዓት የሕዝብ ማስታወቂያ | | | | | ■ | | | | | | | |
| 5. የቀረቡትን ማመልከቻዎች መቀበል፣ አመልካቾችን መመርመር፣ ተጠቃሚዎችን መም | | | | | | ■ | | | | | | |
| 6. ሥርጭት | | | | | | | ■ | | | | | |
| 7. በተጠቃሚ ቡድኖች የጋራ ማጓጓዣ መከታተልና በሥራ ቦታ መመሪያ መስጠት | | | | | | | | ■ | ■ | | | |
| 8. ለሚመለከታቸው አካላት የሪፓርት ዶክመንት ማዘጋጀትና ሪፓርት ማድረግ | | | | | | | | | ■ | | | |
| 9. ለቀጣዩ ዓመት የድጎማ ፕሮጀክት ዕቅድ ማዘጋጀት | | | | | | | | | ■ | ■ | | |
| 10. ለቀጣዩ ዓመት በጀት ለማግኘት መሥራት | | | | | | | | | | ■ | | |
| የቲማቲም መሰብሰቢያ ወቅት (ዋና ወቅት ህዳር-ጥር) | ■ | ■ | | ■ | ■ | ■ | | ■ | ■ | ■ | | ■ |

**ማስታወሻ :**

ይህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማው የእሴት ጭማሪና የጋራ ግብይትን ማስፋፋት ነው።

## የፕሮጀክት ቁጥር 7

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | በእህልና ጥራጥሬ ጥራት ቁጥጥርና የመጋዘን አስተዳዳር የሕ/ሥራ ማህበራትን አቅም ማሣደግ፡፡ | | |
| እስትራቴጂ | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ የትርፍ ጭማሪ<br>2-2: የጥራት ትውውቅ ካላቸው ገበያዎች ጋር ተሣትፎን ማፋጠንና ማጠናከር /የጥራት ቁጥጥር ክህሎት ማሠራጨት/ | | |
| የመሪ ዕቅድ፡ ፕሮግራም | ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>የጥራት ቁጥጥር ክህሎት ማሠራጨት ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2013-2017 እ.ኤ.አ (5 ዓመት) | | |
| የፕሮጀክት ቦታ | ወላይታ ዞን (6 ወረዳ)፣ ሃዲያ ዞን (3 ወረዳ)<br>ካምባታ ጠምባሮ ዞን (1 ወረዳ)፣ ጉራጌ ዞን (6 ወረዳ)<br>ሥልጢ ዞን (3 ወረዳ)፣ አላባ ልዩ ወረዳ | | |
| የተመረጠ ሰብል/ምርት | ብርዕና የአገዳ ሰብል፣ ጥራጥሬ | | |
| የተመረጠ ቡድን | 65 ሕ/ሥራ ማህበራት የዓለም ምግብ ፕሮግራም/ግዢ ለዕድገት ተሣታፊዎችና የተመረጡ 7 ዩኒየኖች | | |
| ፈፃሚ ኤጀንሲ | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ<br>ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ<br>ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ደጋፊ ኤጀንሲ | የዓለም ምግብ ፕሮግራም |

*መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች፡*

የብርዕ አገዳ ሰብልና ጥራጥሬ የሚያመርቱ አብዛኛዎቹ አርሶአደሮች ስለጥራት ቁጥጥርና በመጋዘን አስተዳዳር ዕውቀት የላቸውም፡፡ የተለመደና ባህላዊ የሆኑ የማምረቻ ዘዴዎች እንዳሉም አያውቁም፡፡

በሀገር ውስጥ ገበያ የጥራት ደረጃ በጠበቀ ሁኔታ የሚገዙት የዓለም የምግብ ፕሮግራም ና የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ብቻ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ጨረታ በሚመለከት ቡናና ሰሊጥ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ነው፡፡ ነገር ግን የብርዕና አገዳ ሰብልና የጥራጥሬ ምርት ከነጭ ቦሎቄ በስተቀር ለውጭ ገበያ አይቀርብም፡፡ የዓለም የምግብ ፕሮግራም/ግዢ ለዕድገት (ቀጥታ ግዢ ከሕ/ሥራ ማህበራት) በሚመለከት የሕ/ሥራ ማህበራት ኮሚቴዎችና አባላት የጥራት ግንዛቤና የጥራት ቁጥጥር ቴክኖሎጂ እገዳ ማከማቸት፣ ማጠብና ቆሻሻ መለየት በማሻሻል ምርቱ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ደረጃ እንዲጠብቅ ማድረግ አለባቸው፡፡ የሙከራ ፕሮጀክት በጥራት ቁጥጥርና በመጋዘን አስተዳደር የሙከራ ስልጠና በመስጠት ውጤታማ የስልጠና ዘዴ አቋቁሟል፡፡ የማስተማሪያ ማቴሪያሎች ለስልጠና ተዘጋጅተዋል፡፡ የግዥ ለዕድገት 19 ሕ/ሥራ ማህበራት በቻ ከ84 የተመረጡ ሕ/ሥራ ማህበራት በሙከራ ፕሮጀክት ስልጠና ተሣትፈዋል፡፡ ጥቂት ቁጥር ያላቸው ሕ/ሥራ ማህበራት የጥራትና የመጋዘን ማኔጅመንት ግንዛቤ ያሻሻሉት የሕ/ሥራ ማህበራት ብቻ ናቸው፡፡

ይህ ፕሮጀክት ያለመው በሙከራ ፕሮጀክት የተዘጋጀውን የስልጠና ዘዴና የማስተማሪያ ማቴሪያል በመጠቀም በ65 ስልጠና ያላገኙ ሕ/ሥራ ማህበራት ከግብርና ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ከላይ ወደ ታች አይነት ስልጠና ለመስጠት ነው፡፡

የጥራት ግንዛቤ፣ የጥራት ቁጥጥርና የመጋዘን አስተዳደር ቴክኖሎጂ መሻሻል ይጠበቃል፡፡ የዚህ ፕሮጀክት አላማ ለእውቀት መሻሻልና ለድህረምርት ማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂ ክህሎት አስተዋፅኦ በማድረግ የድህረ ምርት ብክነት እንዲቀንስና የአርሶአደሮች ገቢ እንዲያድግ ነው፡፡ የመፈፀሚያ ጊዜ 5 ዓመት በ2013 (እ.ኤ.አ) የማስተማሪያ ማቴሪያሎች ተዘጋጅተው የአሰልጣኞች ስልጠና ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ይሰጣል፡፡ ለ3 ዓመት (ከ2014 እስከ 2016 እ.ኤ.አ) የአሰልጣኞች ስልጠና ለሕ/ሥራ ማህበራት ይሰጣል፡፡ ከታች ያለው ሠንጠረዥ የስልጠና ምደባ በዓመት ያሣያል፡፡

የ4 ዓመት የስልጠናው ፕሮግራም

| ዓመት (እ.ኤ.አ) | ዩኒየን | ሕ/ሥራ ማህበር | ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ | ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | የወረዳ ስም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2013 | የስልጠና ቁሳቁስ ዝግጅት እና የአሠልጣኞች ስልጠና መስጠት (ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት አሰልጣኞች ስልጠና) | | | | | | |
| 2014 | ዳሞታ | 10 | ወላይታ | 6 | ሶዶ ዙሪያ | ዳሞት ሶሬ | ኦፋ |
| | | | | | ቦሎሶ ሶሬ | ዳሞት ጋሌ | ሁምቦ |
| | ሌቻ | 6 | ሃዲያ | 3 | ሚሻ | ሌሞ | አና ሌሞ |
| | አንጋጫ | 5 | * ከምባታ ጠምባሮ | 1 | ዶዮ ገና | | |
| 2015 | ዋልታ | 12 | ጉራጌ | 3 | መስቃን | ሶዶ | ማራቆ |
| | አድማስ | 10 | | 3 | ቸሃ | አብሽጌ | ቃቤና |
| 2016 | መልዕቅ | 5 | ስልጤ | 3 | ስልጤ | አልቾ ወሬሮ | ሳንኩራ |
| | ማንቼኖ | 17 | -- | 1 | አላባ | | |
| ድምር | 7 | 65 | 4 | 20 | | | |

1. ስልጠናው በ3 ደረጃ ከላይ ወደ ታች ደረጃ በደረጃ ዘዴ ይፈፀማል፡፡

| | |
|---|---|
| የአሠልጣኞች ሥልጠና ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/የዓለም ምግብ ፕሮግራም ➔ ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት |
| ↓ | |
| የአሠልጣኞች ሥልጠና ለሕ/ሥራ ማህበር | ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ➔ ሕ/ሥ ማህበራት ሠራተኞች |
| ↓ | |
| የውስጥ ሥልጠና ለሕ/ሥራ ማህበር አባላት | ሕ/ሥ/ማህበር ሠራተኞች ➔ ሕ/ሥራ ማህበር አባላት |

2. በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት ወቅት የዓለም የምግብ ፕሮግራም ለክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የገለፀው በሙከራ ፕሮጀክት ዘዴ ስልጠናው ቀጣይነት እንዲኖር እንደሚደግፍ ነው፡፡ (ወጪን ጭምር/ የዓለም የምግብ ፕሮግራም የማስተማሪያ ማቴሪያል እንደሚያዘጋጅና ለክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በዓይነት ይሰጣል፡፡ ስለሆነም የማስተማሪያ ማቴሪያል ዝግጅት ወጪ አልተመደበም፡፡
3. የማስተማሪያ ማቴሪያል ዝግጅት መጠን (3 ካርድ አይነት ማቴሪያል፣ 4 ዓይነት ፓስተሮች፣ 1ዓይነት ናሙና ሣጥን (90 በጠቅላላ) 65 ለሕ/ሥራ ማህበራት፣ 24 ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት /ለዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ መጠባበቂያ
4. የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የአሰልጣኞች ስልጠና ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ እንደሚከተለው ይሰጣል፡፡
   - ❖ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የአፈፃፀም ዕቅድ ያዘጋጃል፣
   - ❖ ይህ የአሠልጣኞች ስልጠና በሀዋሣ ለ2 ቀን ይካሄዳል፣
   - ❖ እንደሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 02 አስተማሪያዎች ይመደባሉ፤ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሙሉ ጊዜ ሰራተኛና የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት
   - ❖ ተሣታፊዎች 44 ሰዎች፣ 4ሰዎች ከዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ፣ 40 ሰዎች ከወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት፣
5. ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የአሠልጣኞች ስልጠና ለሕ/ሥራ ማህበራት በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ቁጥጥር እየተደረገ እንደሚከተለው ይሰጣል፡፡
   - ❖ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ባለሙያ (አስተማሪ) ከሕ/ሥራ ማህበራት ከወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሥራማስኬጃ ጋር በመመካከር የጊዜ ሰሌዳ ይወስናል፡፡ የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ለእያንዳንዱ የተመረጠ ሕ/ሥራ ማህበር ለ1 ቀን ስልጠና ይሰጣል፡፡

- ❖ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ ባለሙያ ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት አሰልጣኞች ስልጠና የተሣተፈ የተለየ ስራ የለውም፡፡ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከተጠየቀ የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞች ሥልጠና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
- ❖ ሥልጠናው ከጥቅምተና ጥር ከምርት መሰብሰብ እስከ በቆሎና በሎቄ መሸጫ ጊዜ መካከል መካሄድ አለበት፡፡

6. ለሕ/ሥራ ማህበር አባላት የሚሰጠው የውስጥ ስልጠና እንደሚከተለው ይፈፀማል፡፡
   - ❖ ከላይ በቁጥር 5 መሠረት የሕ/ሥራ ማህበር ሠራተኛ የሠለጠነ የውስጥ ስልጠና ለሕ/ሥራ ማህበር አባላት በጠቅላላ ስብሰባ ይሰጣል፡፡
   - ❖ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሠራተኛ ለሕ/ሥራ ማህበር ሠራተኞች የውስጥ ስልጠና መመሪያ ከወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞች ጋር በጋራ ይሰጣል፡፡
   - ❖ ይህ ሥልጠና በአንድ ሥልጠና አንድ አርዕስት ሲኖረው ይዘቱን በአርሶአደሮች መካከል በደንብ የታወቀ ቴክኖሎጂ ያደርገዋል፡፡ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞች ከ5 ክትትል በኂላ የውስጥ ስልጠናውን የአፈፃፀም ሁኔታ ያረጋግጣል፡፡

ድርጊት:

[ 2013 ]

1.1 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የሥልጠና ማቴሪያል በማዘጋጀት ለክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ያቀርባል፡፡
1.2 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የ65 ሕ/ሥራ ማህበራት ስማቸውን እንደገና ያረጋግጣል፣ ለክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ያስታውቃል፡፡
1.3 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ ተሣታፊዎች /44 ሰዎች/ አሠልጣኞች ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሥልጠና ያረጋግጣል፡፡
1.4 ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሠራተኛ ሁለት አስተማሪያዎችን ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የአሠልጣኞች ስልጠና ያዘጋጃል፡፡
1.5 ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሠራተኛ የአሠልጣኞች ስልጠና ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ለ2 ቀን በሀዋሣ ይሰጣል፡፡

[ 2014 ]

2.1 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የአሠልጣኞች ስልጠና ለሕ/ሥራ ማህበራት የጊዜ ሰሌዳ ያስተባብራል፡፡
2.2 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የአሠልጣኞች ስልጠና ለሕ/ሥራ ማህበራት (ለ1 ቀን ለ1 የሕ/ሥራ ማህበር ይሰጣል)፡፡
2.3 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የሠለጠኑ ሕ/ሥራ ማህበራትን ክትትል ያደርጋል፡፡ ከአሠልጣኞች ስልጠና በኂላ ለሕ/ሥራ ማህበራትና ለክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሪፓርት ያደርጋል፡፡ በዚያ ወቅት ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የሕ/ሥራ ማህበር አባላት የውስጥ ስልጠና የአፈፃፀም ሁኔታ ያረጋግጣል፡፡
2.4 ለቀጣይ ዓመት ግብረ መልስ የተለያዩ ሁኔታዎች በስልጠና ዘዴ እንዲሁም በማስተማሪያ ማቴሪያሎች ከወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በመነሳት የሚሻሻሉ ነገሮች ቢኖሩ ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የቀጣዩን ዓመት ስልጠና ግብረ መልስ ያዘጋጃል፡፡

[ 2015 ] ከ2014 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

[ 2016 ] ከ2014 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

[ 2017 ] ከ2014 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ግብአት :

1. የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሙሉ ጊዜ ሰራተኛ 1 ሠው
2. የወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ 2 ሰዎች
3. የአሠልጣኞች ስልጠና ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ የቀን አበልና የትራንስፓርት ወጪ ለሠለጠኑ ሠራተኞች ዞን የግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ /ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት

የስብሰባ አዳራሽ ክፍያና ወጪ፡፡
4. የአሠልጣኞች ስልጠና ለሕ/ሥራ ማህበራት የትራንስፓርት ወጪ ለወረዳ ጽ/ቤት ሕ/ሥራ ማህበራት ሠራተኞች፣ የጽሕፈት መሣሪያ ወጪና የመጠጥ ወጪ፡፡
5. የቁጥጥር ወጪ የውስጥ ሥልጠና ለ/ሥራ ማህበራት አባላት የትራንስፓርት ወጪ፣ የቀን አበል የሕ/ሥራ ማህበራት ለ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞች፣ የመኪና የነዳጅ ወጪ፣ የግንኙነትና እስቴሽነሪ ወጪ፣
6. የማስተማሪያ ማቴሪያል የማዘጋጀት ወጪ በዓለም ምግብ ፕሮግራም ይሸፈናል፡፡

የክልል ወጪ :

- የአሠልጣኞች ስልጠና ለሕ/ሥራ ማህበራት የ1 ቀን ሥልጠና ስለሆነ የቀን አበል ለ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞችና ለአርሶአደሮች ተመድቧል፡፡ የመጠጥ ወጪ ብቻ (የማዕድን ውሃ፣ ሻይና ቡና) የተመደበው 20 ብር ለ1 ሰው ለ1 ቀን ከሙከራ ፕሮጀክት ጋር ተመሳሳይ ነው፣ 12 ሰዎች ከ1 ሕ/ሥራ ማህበር (10 አርሶአደሮችና 2 አስተማሪዎች) ታስበዋል፡፡
- የተፈለገው የማስተማሪያ ማቴሪያል መጠን (የካርድ ዓይነት ማቴሪያሎች፣ ፓስተሮች፣ ናሙና ሣጥን)፣ 90 (60 ለ ሕ/ሥራ ማህበራት 24 ለ ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ዞን የግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያና 1 መጠባበቂያ)
- የጉዞ ወጪ ለአሠልጣኞች ሥልጠና ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ተመድቧል ምክንያቱም ማስተናገድ ያስፈልጋል፡፡ (350 ብር ለ1 ሰው፡ የቀን አበል፡ 100 ብር x 2 ቀን + ደርሶመልስ ጉዞ 150 ብር)
- የስብሰባ አዳራሽ ክፍያ ለአሠልጣኞች ሥልጠና ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ለ2 ቀን ተመድቧል፡፡ (1000 ብር ለ1 ቀን x 2ቀን)

ሀ/ የአሠልጣኞች ስልጠና ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት
1. የቀን አበልና የትራንስፓርት ወጪ ለዞን የግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ/ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞች፡ 15,400
2. የስብሰባ አዳራሽ ክፍያ፡ 2,000 (1,000 በ1 ቀን x 2ቀን)
3. የእስቴሽነሪ ወጪ፡ 1,000

ንዑስ ድምር፡ 18,400 ብር

ለ/ የአሠልጣኞች ስልጠና ለሕ/ሥራ ማህበራት
1. የትራንስፓርት ክፍያ የወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞች : 3,900
2. የጽህፈት መሣሪያ ወጪ፡ 9,750
3. የመጠጥ ወጪ፡ 15,600

ንዑስ ድምር፡ 29,250 ብር

ሐ/ የክትትል ወጪ የወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞች
1. የጉዞ ወጪና የቀን አበል፡ 2,400
2. የመኪና የነዳጅ ወጪ፡ 12,000
3. የግንኙነትና እስቴሽነሪ ወጪ፡ 3,000

ንዑስ ድምር፡ 17,400 ብር

| | |
|---|---|
| ጠቅላላ ለሀ+ለ+ሐ | 65,050 ብር |
| መጠባበቂያ(10%) | 6,500 ብር |
| ጠ/ድምር | 72,000 ብር (ከ1,000 በታች ተጠቃልሏል፡፡) |

## የጊዜ ሠሌዳ :

| ፈጻሚ አካል | ድርጊት | አፈጻጸም የጊዜ ሠሌዳ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 (እ.ኤ.አ) | | | | 2014 (እ.ኤ.አ) | | | | 2015 (እ.ኤ.አ) | | | | 2016 (እ.ኤ.አ) | | | | 2017 (እ.ኤ.አ) | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| የዓለም ምግብ ፕሮግራም | 1.1 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የሥልጠና ማቴሪያል በማዘጋጀት ለክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ያቀርባል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | 1.2 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የ65 ሕ/ሥራ ማህበራት ስማቸውን እንደገና ያረጋግጣል፣ ለክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ያስታውቃል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | 1.3 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ ተሣታፊዎች /44 ሰዎች/ አሠልጣኞች ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሥልጠና ያረጋግጣል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ | 1.4 ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሠራተኛ ሁለት አስተማሪያዎችን ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የአሠልጣኞች ስልጠና ያዘጋጃል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ክልል/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | 1.5 ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሠራተኛ የአሠልጣኞች ስልጠና ለወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ለ2 ቀን በሀዋሣ ይሰጣል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | 2.1 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የአሠልጣኞች ስልጠና ለሕ/ሥራ ማህበራት የጊዜ ሰሌዳ ያስተባብራል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ክልል/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | 2.2 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የአሠልጣኞች ስልጠና ለ65 ሕ/ሥራ ማህበራት (ለ1 ቀን ለ1 የሕ/ሥራ ማህበር ይሰጣል)። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | 2.3 ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የሠለጠኑ ሕ/ሥራ ማህበራትን ክትትል ያደርጋል። ከአሠልጣኞች ስልጠና በኋላ ለ65 ሕ/ሥራ ማህበራትና ለክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሪፓርት ያደርጋል። በዚያ ወቅት ወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኛ የሕ/ሥራ ማህበር አባላት የውስጥ ስልጠና የአፈፃፀም ሁኔታ ያረጋግጣል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | 2.4 ለቀጣይ ዓመት ግብረ መልስ የተለያዩ ሁኔታዎች በስልጠና ዘዴ እንዲሁም በማስተማሪያ ማቴሪያሎች ከወረዳ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በመነሳት የሚሻሻሉ ነገሮች ቢኖሩ ክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የቀጣዩን ዓመት ስልጠና ግብረ መልስ ያዘጋጃል። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

**ማስታወሻ:**

**ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሥራማስኬጃ ወጪ እንደ ትራንስፖርትና የቢሮ ዕቃዎች ወጪ ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞች መመደብና የመተካት ሥራ ይሠራል።**

## የፕሮጀክት ቁጥር 8

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 04 የተመረጡ ቡድኖች የክትትል ድጋፍ | | |
| እስትራቴጂ | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ ትርፍ ማሳደግ<br>2-3: በምርት ማምረቻ አካባቢ የእሴት ጭማሪ ሥራዎችን ማሳደግ<br>2-4: የተለዩና የበላይ የሆኑ ምርቶች/ዝሪያዎች መገበያያ ማጠናከር<br>2-5: የጋራ ግብይት ማፋጠን | | |
| የመሪ ዕቅድ፡ ፕሮግራም | ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሣቫ ማስተዋወቅ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2013-2014 እ.ኤ.አ (2 ዓመት) | | |
| የፕሮጀክት ቦታ | ኪንዶ ኮይሻ ወረዳና ኦፋ ወረዳ በወላይታ ዞን | | |
| የተመረጠ ሰብል / ምርት | ካሳቫ | | |
| የተመረጠ ቡድን | 12 አርሶአደሮች ቡድኖች ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 የተሣተፉ | | |
| ፈፃሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ<br>ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ<br>ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ደጋፊ ኤጀንሲ | |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች፡

ለአነስተኛ የአርሶአደር ቡድኖች ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 የደረቅ ካሳቫ ማቀነባበሪያና የግብይት ፕሮጀክት አዘጋጅቶ ሲደግፍ ነበር፡፡ ይህ ፕሮጀክት ከፍተኛ የእሴት ጭማሪ በማቀነባበርና በግብይት በማስተዋወቅ ቅልጥፍናና ውጤታማነት በአነስተኛ አርሶአደሮች በትርፍ ጭማሪ አረጋግጧል፡፡ ሆኖም የፕሮጀክቱ ዕድሜ ከጥቅምት 2011 እስከ መጋቢት መጨረሻ 2012 ለ6 ወራት ብቻ በመቆየት አጭር ነበር፡፡

በኪንዶ ኮይሻ ወረዳ ያሉ አርሶአደሮች ቡድኖች በዚህ ፕሮጀክት በመጠቀም ትርፍ ሊጨምሩ ችለዋል፡፡ ነገር ግን በኦፋ ወረዳ ያሉ አርሶአደሮች ሥራቸውን አቋርጠዋል፡፡ ምክንያቱም በኦፋ ወረዳ ያሉ ነጋዴዎች የዚህ ዓይነት ከፍተኛ ጥራት ያለውን ደረቅ ካሳቫ ስለማያዘጋጁ አርሶአደሮቹ ገበያ ስለማያገኙ ነው፡፡

የግብርና ማቀነባበሪያና የአርሶአደሮች ትርፍ ጭማሪ ማስፋፊያ ሞዴል ፕሮጀክት በማቋቋም ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ/ና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 ድጋፉን ይቀጥላል፡፡ የድጋፍ ሥራ ወቅታዊ ክትትል፣ ድጋፍና ምክር፣ የገበያ ትስስር በመፍጠርና ከፍተኛ ጥራት ያለውን ደረቅ ካሳቫ በማስተዋወቅ ያካትታል፡፡
ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት

ድርጊት:

1. በኪንዶ ኮይሻ ወረዳ ለሚገኙ አርሶአደሮች
   - 1.1 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት 6 አርሶአደሮች ቡድኖች በወር 1 ጊዜ የቡድን ስብሰባ ለማካሄድ ወቅታዊ ሁኔታ እንዲጨብጡና አስፈላጊ ምክር እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
   - 1.2 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ከአርሶአደሮች ቡድኖች የአካባቢ ነጋዴዎችና በሶዶ ከተማ ካሉ የእህል ወፍጮ ቤቶች ጋር የገበያ ትስስር ድጋፍ ያደርጋል፡፡
2. በኦፋ ወረዳ ለሚገኙ አርሶአደሮች ቡድኖች
   - 2.1 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት 6 አርሶአደሮች ቡድኖች በወር 1 ጊዜ የቡድን ስብሰባ በማካሄድ ወቅታዊ ሁኔታ እንዲጨብጡና አስፈላጊ ምክር እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
   - 2.2 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በኦፋ ወረዳ ከክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ ጋር በመተባበር የአካባቢ ነጋዴዎች በጋሱባ ከተማ ኦፋ ወረዳ ያሉትና በሶዶ ከተማና በሌሎችም የከተማ አካባቢ አ/አን ጨምሮ ያሉት መካከል የገበያ ትስስር እንዲያድግ ያደርጋል፡፡

3. የገበያ ትስስር ዕድገት መደገፍ
   3.1 የወላይታ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ በሴሚናሮችና በኤግዝቢሽን የንፁሕ ደረቅ ካሳቫ በማስተዋወቅ ከአምራች ወረዳዎች፣ ከሸማቾችና ነጋዴዎች መካከል የገበያ ትስስር ያሳድጋል፡፡
   3.2 ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከዞን ግብይትና ሕ/ሥራ ማስፋፊያ መምሪያና ከወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በሴሚናሮች፣ በኤግዝቢሽን በሀዋሣና በሻሸመኔ ከተሞች የገበያ ማሣደግና የማስታወቂያ ሥራ ይሠራል፡፡
4. ወቅታዊ የባለድርሻ አካላት ስብሰባና ማስታወቂያ
   4.1 ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ለጋራ ግንዛቤና ፍጆታ ከባለድርሻ አካላት ማለትም ከቢሮ ሠራተኞች፣ ከነጋዴዎች፣ ከወፍጮ ቤት ባለንብረቶችና ከሸማቾች ቡድኖች ጋር ወቅታዊ ስብሰባ ያዘጋጃል፡፡

<u>የተመረጡ ቡድኖች</u>

1. በአርሶአደሮች ቡድኖች ምርትና ጥራት ቁጥጥር
2. በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ/ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በተዘጋጁ ስብሰባዎች መሣተፍ፣
3. ለግብይት ሥራዎች ናሙናዎች ማቅረብ፣

ግብአት :

1. የወረደ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሠራተኞች ወቅታዊ ጉብኝት ወደ ቀበሌዎች ለክትትል /2 ቀናት በ1ጊዜ፣ 7ጊዜ በደረቅ ወራት ለ2 ዓመት/
2. በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና በዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ ለሽያጭ ማስታዋወቂያ የድጋፍ ሥራ /1ጊዜ/ወር፣ 7ወራት/ዓመት ለ2ዓመት/
3. ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ለሀዋሣና ሻሸመኔ ወፍጮ ቤቶች የሽያጭ ማስተዋወቂየ የድጋፍ ሥራ /3ጊዜ /ዓመት ለ2 ዓመት/
4. ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ለባለድርሻ አካላት ወቅታዊ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ /2ጊዜ /ዓመት ለ2 ዓመት/

ወጪ :

1. ወቅታዊ ጉብኝት ክፍያ ወደ ቀበሌዎች በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ፡ 5,600
   ( 100/ቀን x 2ቀናት/ጊዜ x 7ጊዜ/ዓመት x 2ዓመታት x 2 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት )
2. በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ ለሽያጭ ማስተዋወቂያ የድጋፍ ሥራ ፡ 8400
   ( 200 ብር x /ጊዜ/ወር x 7ወራት/ዓመት x 2ዓመታት x 3ሰዎች )
3. ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ለሃዋሣና ሻሸመኔ ወፍጮ ቤቶች የሽያጭ ማስተዋወቂያ የድጋፍ ሥራ : ብር 1,200
   ( 200 ብ/ጊዜ x 3ጊዜ/ዓመት x 2ዓመታት )
4. የባለድርሻ አካላት ስብሰባ ክፍያ : ብር 10,000
   ( 5,000/ጊዜ/ዓመት x 2ዓመታት )

| | | |
|---|---|---|
| ንዑስ ድምር | 25,200 ብር | (12,600/ዓመት x 2ዓመት) |
| መጠባበቂያ (10%) | 2,500 ብር | |
| ጠ/ድምር | 28,000 ብር | |

የጊዜ ሠሌዳ :

| ድርጊት | 2013 (እ.ኤ.አ) | | | | 2014 (እ.ኤ.አ) | | | | 2015 (እ.ኤ.አ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1. የኪንዶ ኮይሻ ወረዳ ድጋፍ | ▬ | | | ▬ | ▬ | | | ▬ | | | | |
| 2. ኦፋ ወረዳ ድጋፍ | ▬ | | | ▬ | ▬ | | | ▬ | | | | |
| 3. የገበያ ትስስር ድጋፍ | ■ | ■ | | ■ | ■ | ■ | | ■ | | | | |
| 4. የባለድርሻ አካላት ስብሰባ | ☆ | | | ☆ | ☆ | | | ☆ | | | | |

ማስታወሻ :

1. የአርሶአደሮች ቡድኖች በገበያ ትሰስር ልማት ደካሞች ናቸው፡፡ ከወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት/ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ድጋፍ የስፈልጋቸዋል፡፡
2. የንፁሕ ደረቅ ካሳቫ ፍጆታ መስፋፋት ወደ የካሳቫ ምርት በገጠር አካባቢ በስፋት እንዲለማ ምክንያት ይሆናል፡፡

## የፕሮጀክት ቁጥር 9

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | ከፍተኛ ጥራት ያለው ካሳቫ የማምረት ቢዝነስ ማስፋፊያ ድጋፍ | | |
| እስትራቴጂ | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ የትርፍ ማሳደግ<br>2-3: በምርት አካባቢ እሴት ጭማሪ ሥራዎችን ማሳደግ<br>2-4: የተለዩና የበላይ የሆኑ ምርቶች/ዝሪያዎች መገበያያ ማጠናከር<br>2-5: የጋራ ግብይት ማፋጠን | | |
| የመሪ ዕቅድ፡ ፕሮግራም | ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ ማስተዋወቅ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2013-2015 እ.ኤ.አ (3 ዓመት) | | |
| የፕሮጀክት ቦታ | ወላይታ ዞንና ጋሞ ጎፋ ዞን | | |
| የተመረጠ ሰብል / ምርት | ካሳቫ | | |
| የተመረጠ ቡድን | በወላይታ ዞንና ጋሞ ጎፋ ዞን ያሉ የአርሶአደሮች ቡድኖች | | |
| ፈፃሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ<br>ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ<br>ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ደጋፊ ኤጀንሲ | |

*መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች፡*

በዋና ዋና ካሳቫ አምራች ወረዳዎች ማለትም ኪንዶ ኮይሻና ኦፋ ወረዳዎች በወላይታ ዞን ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ሌሎች አርሶአደሮች ቡድኖች በእነዚህ ወረዳዎችና በሌሎች ካሣቫ አምራቾች አካባቢዎች እንደ ሶዶ ዙሪያ በወላይታ ዞንና ደንባ ጎፋ ወረዳ በጋሞ ጎፋ ዞን ያሉት በእሴት ጭማሪ ሥራዎች ለመሣተፍ ይፈልጋሉ፡፡

በእነዚህ አካባቢዎች ምርቱ ከፍተኛና የፕሮጀክቱ አዋጭነት ሁኔታ ከፍተኛ በመሆኑ የአርሶአደሮችን ትርፍ፣ ለመጨመር ባለው ዓላማ የማስፋፋት ሥራ መሠራት አለበት፡፡ የፕሮጀክቱ ወጪ (የመነሻ ኢንቨስትመንት ክፍያ) የብድር ፕሮግራም ከአለም አቀፍ እርዳታ ለግብርና ልማት ከግብርና ግብይት ማሻሻያ ፕሮግራም፣ ከኦሞ ማይክሮ ፋይናንስና ከሌሎችም የእርዳታ ተቋማት መሸፈን ሲኖርበት ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የብድር ፕሮግራም በማግኘት ድጋፍ ይሰጣል፡፡

*ድርጊት:*

<u>ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ጽ/ቤት</u>

1. ለወላይታ ዞንና ለጋሞ ጎፋ ዞን፣
   - 1.1 ክልል ቢሮ/ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ በተመረጡ አካባቢዎች አዳዲስ የአርሶአደሮች ቡድኖች ይመርጣል፡፡
   - 1.2 ክልል ቢሮ/ ዞን መምሪያ/ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ወደ ኪንዶ ኮይሻ ወረዳ የጥናት ጉብኝት አዲስ ለተመረጡ ተወዳዳሪዎች ያዘጋጃል፡፡
   - 1.3 የአርሶአደሮች ቡድኖች ለብድር ማመልከቻ ከአስተዳደራዊ ድጋፊ ጋራ የፕሮጀክት ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡
   - 1.4 የአርሶአደሮች ቡድኖች ከአስተዳደራዊ ድጋፍ ጋር የፕሮጀክት ብድር ያገኛሉ፡፡
   - 1.5 የአርሶአደሮች ቡድኖች ከአስተዳደራዊ ድጋፍ ጋር አስፈላጊ የሆኑ ማሽኖችና ዕቃዎች ይገዛሉ፡፡
   - 1.6 ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ለአርሶአደሮች ቡድኖች የቴክኒካል ሥልጠናዎች ይሰጣል፡፡
   - 1.7 ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት አዲስ ለሚጀምሩ ፕሮጀክት ወቅታዊ ክትትልና አስፈላጊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
2. ለገበያ ትስስር ልማት ድጋፍ መስጠት፣
   - 2.1 የወላይታ ዞንና የጋሞ ጎፋ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ በአምራች ወረዳዎችና በሶዶ ከተማና በሌሎችም ከተሞች ካሉ የከተማ ሸማቾችና ነጋዴዎች ጋር በሴሚናሮችና በኤግዝቢሽኖች የንፁሕ ደረቅ ካሣቫ በማስተዋወቅ የገበያ ትስስር ልማት ያካሂዳሉ፡፡

2.2 ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ሀዋሣና ሻሸመኔ አካባቢ በሴሚናሮችና በኤግዝቢሽኖች የገበያ ልማትና የማስታወቂያ ስራ ይሠራል።

3. ወቅታዊ የባለድርሻ አካላት ስብሰባና ማስታወቂያ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ለጋራ ግንዛቤና ፍጆታ ከባለድርሻ አካላት ማለትም ከቢሮ ሠራተኞች፣ ከነጋዴዎች፣ ከወፍጮ ቤት ባለንብረቶችና ከሸማቾች ቡድኖች ጋር ወቅታዊ ስብሰባ ያዘጋጃል።

<u>የተመረጡ ቡድኖች</u>

1. የብድር ማመልከቻ፣
2. የመነሻ ኢንቨስትመንት ወጪ ማግኘት (ብር 7000/ቡድን ጥሬ ካሣቫ መቁረጫ ማሽን፣ ብር 2500 በዓይነት x 2 ዓይነትና 4 ቁራጮች የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ ስስ ጨርቅ፣ ብር 500 x 4 ቁራጮች)
3. ማሽንና ዕቃዎችን መግዛት፣
4. የፕሮጀክቱን ሥራ መጀመር ይኸውም ማምረትና ግብይት፣
5. በአስተዳደር በተዘጋጀው የባለድርሻ አካላት ስብሰባ መሳተፍ፣

ማስታወሻ፡ ከሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 በተገኘው ትምህርት፤ ለቡድን አገልግሎት የሚሆን የምርት ማከማቻ መጋዘን አይገነባም። እያንዳንዱ አባወራ ምርቱን በራሱ ቤት አቆይቶ ምርቱን በጋራ ይሰበስባል።

ግብአት :

1. የድጋፍ ስራ ለአዲሶቹ ቡድኖች ተወዳዳሪዎችን በመምረጥ፣ የጥናት ጉብኝቶችን በማመቻቸት፣ ብድር በማግኘትና በሌሎችም ድጋፎች፣
2. የቴክኒካል ስልጠና በማመቻቸት፣
3. ክትትልና ድጋፍ፣
4. የገበያ ትስስር በማልማት ድጋፍ፣
5. የባለድርሻ አካላት ስብሰባ በማመቻቸት፣

ወጪ :

❖ የመነሻ ኢንቨስትመንት ወጪ በዚህ የፕሮጀክት ወጪዎች አልተካተተም፡

1. መነሻ የድጋፍ ክፍያ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ የጉዞ ወጪዎች : ብር 2,400
   ( 1000/ቀን x 2 ሰዎች x 2 ቀን x 3 ጊዜ x 2 ወረዳዎች )
2. የጉዞ ወጪዎች የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ወደ ቀበሌዎች : ብር 5,600
   ( 100/ቀን x 2ቀን x 7 ጊዜ/ዓመት x 2ዓመት x 2 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት )
3. የጥናት ጉዞ በአርሶአደሮች ቡድኖች ወደ ኪንዶ ኮይሻ : ብር 5,000
   ( 2000/ሚኒባስ + የጉብኝት ወጪዎች ለአርሶአደሮች ብር 50/አርሶአደር x10/ x 2 ጊዜ )
4. የሽያጭ ማስታዋወቅ በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት/ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ : ብር 8,400 ( 200/ሰው x 3 ሰዎች x 7ጊዜ/ዓመት x 2ዓመት )
5. የሽያጭ ማስተዋወቅ በእህል ወፍጮዎች በሀዋሣና ሻሸመኔ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ : ብር 1,200 ( 200/ጊዜ x 3ጊዜ/ዓመት x 2ዓመት)
6. የባለድርሻ አካላት ስብሰባ ክፍያ : ብር 2,500
   ( 5000/ጊዜ x 5ጊዜበ3 ዓመት )

| | |
|---|---|
| ንዑስ ድምር | 46,400 ብር |
| መጠባበቂያ(10%) | 4,600 ብር |
| ጠቅላላ | 51,000 ብር |

**የጊዜ ሠሌዳ :**

| ድርጊት | 2013 (እ/ኤ/አ) | | | | 2014 (እ/ኤ/አ) | | | | 2015 (እ/ኤ/አ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1. አዲስ ፕሮጀክት በመጀመር ድጋፍ መስጠት | | | | | | | | | | | | |
| 1-1. የአርሶአደር ቡድን መምረጥ | | | | | | | | | | | | |
| 1-2. የጥናት/ ልምድ ልውውጥ ጉዞ | | | | | | | | | | | | |
| 1-3. በአርሶአደር ቡድን የፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት | | | | | | | | | | | | |
| 1-4. የብድር ማመልከቻ መቅረብና የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | | | | | | | | | | | | |
| 1-5. ግዥና የሙያ ስልጠና | | | | | | | | | | | | |
| 1-6. ማምረትና ሽያጭ መጀመር | | | | | | | | | | | | |
| 1-7.የክልል/ዞን/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ክትትልና ምክር | | | | | | | | | | | | |
| 2. የክልል/ዞን/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ የገበያ ትስስር ድጋፍ | | | | | | | | | | | | |
| 3. የባለድረሻ አካላት ስብሰባ | | | | ☆ | | ☆ | | ☆ | | ☆ | | ☆ |

**ማስታወሻ :**

**የጥሬ ካሳቫ መቁረጫ ማሽን በሀዋሣና በሶዶ ገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከል ይገኛል፡፡**

## የፕሮጀክት ቁጥር 10

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሳቫ ሽያጭ ማስፋፋት |
| እስትራቴጂ፡ | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ የትርፍ ማሳደግ<br>2-3: በምርት ማምረቻ አካባቢ የእሴት ጭማሪ ሥራዎችን ማልማት<br>2-4: የተለዩና የበላይ የሆኑ ምርቶች/ዝሪያዎች መገበያያ ማጠናከር |
| የመሪ ዕቅድ፡ ፕሮግራም | ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሣቫ ማስተዋወቅ ፕሮግራም |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2013-2015 እ.ኤ.አ (3 ዓመት) |
| የፕሮጀክት ቦታ | አ/አበባ፣ ናዝሬት |
| የተመረጠ ሰብል / ምርት | ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ካሣቫ |
| የተመረጠ ቡድን | በከተማ አካባቢ ያሉ ሸማቾች |
| ፈፃሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ — ደጋፊ ኤጀንሲ: |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች :

ለከፍተኛ ጥራትና አነስተኛ መጠን ያለው ደረቅ ካሣቫ ጠንካራ የሸማቾች ፍላጐት እንዳለ በሀዋሣና ሻሸመኔ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 04 አፈጻጸም ተረጋግጧል፡፡ የከፍተኛ ጥራት የለው ደረቅ ካሳቫ ምረት ለማስተዋወቅ በትላልቅ ሸማቾች ያሉበት አካባቢ እንደ አ/አበባና ናዝሬት የገበያ ልማት ማስተዋወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ በአ/አበባ ያሉ ሸማቾች ደረቅ ካሳቫ ቆሻሻና ለምግብነት አይመችም በማለት ጥሩ ያልሆነ ሃሣብ አላቸው ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የንፁሕ ደረቅ ካሳቫ የገበያ ማስተዋወቅ ሥራ በአ/አበባና በናዝሬት ያስፋፋል፡፡

ድርጊት :

1. ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በአ/አበባ በሚካሄደው የግብርና ኤግዝቢሽን የንፁሕ ደረቅ ካሳቫ ሠርቶ ማሣያ በመሣተፍ የማስፋፋት ሥራ ይሠራል፡፡
2. ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የንፁሕ ደረቅ ካሳቫ በጋዜጣ፣ በቴሌለቪዥንና በሬዲዮ የማስታወቂያ ሥራ ይሠራል፡፡
3. ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በአ/አበባ ላሉ ሸማቾች የንፁሕ ደረቅ ካሳቫ ፍጆታ ያስፋፋል፡፡
4. ለማስታወቅ ሥራ ናሙናዎችን መሰብሰብ፡፡

ግብአት :

1. በአ/አበባ ግብርና ኤግዝቢሽን መሣተፍ፣
2. በቴሌቪዥንና ጋዜጣዎች ማስታወቂያ ሥራ መሥራት፣
3. ናሙናዎችን በመስጠት ለሸማቾች የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት፣

ወጪዎች :

1. በአ/አበባ ግብርና ኤግዝቢሽን መሣተፍ ወጪ፡ የጉዞ ወጪ ጭምር፡ 15,000
   (5000 /ዓመት x 3 ዓመት)
2. ሸማቾች የማስታወቂያ ወጪ፡ (የሴሚናር ወጪ፣ የናሙና መልእክተኛ ወጪ): 60,000
   (20000 /ዓመት x 3 ዓመት)

| | | |
|---|---|---|
| ንዑስ ድምር፡ | 75,000 ብር | (25,000 በዓመት x3 ዓመት) |
| መጠባበቂያ (10%) | 7,500 ብር | |
| ጠቅላላ ድምር | 82,500 ብር | |

ጊዜ ሠሌዳ :

| ድርጊት | 2013 (እ/ኤ.አ) | | | | 2014 (እ/ኤ.አ) | | | | 2015 (እ/ኤ.አ) | | | | 2016 (እ/ኤ.አ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1. በኤግዚቢሽን መሳተፍ | ☆ | | | | ☆ | | | | ☆ | | | | | | | |
| 2.በቴሌቪዝንና በጋዜጣ መስተዋወቅ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | | | | |
| 3. ለአ/አበባ ሸማች ቀጥታውን መስተዋወቅ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | | | | |

## የፕሮጀክት ቁጥር 11

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 የተመረጡ ቡድኖች የክትትል ድጋፍ | | |
| እስትራቴጂ | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ የትርፍ ማሳደግ<br>2-3: በምርት ማምረቻ አካባቢ የእሴት ጭማሪ ሥራዎችን ማስፋፋት<br>2-4: የተለዩና የበላይ የሆኑ ምርቶች/ዝሪያዎች መገበያያ ማጠናከር<br>2-5: የጋራ ግብይት ማፋጠን | | |
| የመሪ ዕቅድ፡ ፕሮግራም | ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ዝንጅብል ማስተዋወቅ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2012-2014 እ.ኤ.አ (2012/13 እና 2013/14 የምርት ወቅት) | | |
| የፕሮጀክት ቦታ | ሃዳሮ ጡንጦ ወረዳ (ከምባታ ጠምባሮ ዞን)<br>ቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ (ወላይታ ዞን) | | |
| የተመረጠ ሰብል / ምርት | ዝንጅብል | | |
| የተመረጠ ቡድን | ሃዳሮ ጡንጦ ወረዳ<br>ዓባይ ዝንጅብል ምርትና ግብይት ቡድን /ዓባይ ቡድን/<br>ሃደሮ የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበር<br>ቦሎሶ ቦምቤ የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበር<br>ቡድኑ ማጠብና ማድረቅ ሥራ በራሳቸው ካፒታል ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 በማየት ጀምረዋል /ዓባይ ቡድን/ | | |
| ፈፃሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | ደጋፊ ኤጀንሲ | |

መነሻ ዓላማዎች :

የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 05 በ2 አርሶአደሮች /ነጋዴዎች ቡድኖች የዝንጅብል ማጠብና ማድረቅ ቢዝነስ እንዲጀምሩ ድጋፍ አድርጓል፡፡ እነርሱ የዝንጅብል ማጠብና ማድረቅ ቢዝነስ በመጀመር የመጀመሪያ ሲሆኑ ለሌሎች ሞዴል እንደሚሆኑ ይገመታል፡፡ ሆኖም የቢዝነስ ሥራው አንድ ጊዜ ብቻ በ2011/12 የምርት ወቅት በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት ጊዜ ስለሆነ ውጤቱ ገና አልታወቀም፡፡ ስለዚህ ለቡድኖቹ በሚቀጥሉ 2 ዓመታት የምርት ወቅት /2012/13ና 2013/14/ ድጋፍ እንደ ምክርና የግብይት መረጃ በማቅረብ ቢዝነሱን ለማስቀጠልና ለማጠናከር ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በዓባይ ቡድንና በቦሎሶ ቦምቤ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር አስተዳደር ችሎታ የሥራ አስፈፃሚ አባላትና የፋይናንስ አቅም ከአንዱ አንዱ በጣም ይለያል፡፡ ስለዚህ እንደየፍላጐታቸው እንደድክመታቸው ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ድርጊት :

❖ ለሥራዎቹ ተዋናይ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ እና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ

1. ወቅታዊ የሥራ ቦታ ክትትል
   1.1 በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ /ጊዜ/ወር/ቦታ ከመስከረም እስከ ሰኔ ከወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት ጋር የሚሠራ፡፡
   1.2 በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በየጊዜው ከመስከረም አስከ ሰኔ
2. ለቢዝነስ ሥራ የምክር ድጋፍ
   2.1 በክትትል ጊዜ ችግሮችን/ ድክመቶችን መጨበጥና ድጋፍ መስጠት
   - ❖ ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ኤክስፐርት ድጋፍ ለመስጠት አስቸጋሪ ከሆነ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት ማማከር
3. ለምርቶች ግብይት ድጋፍ
   3.1 የገዢ ጥናት በአ/አ ማካሄድ /ኤክስፐርቶች፣ ጅምላ ነጋዴዎች ለአገር ውስጥ ገበያ፡ የታጠበ ትኩስ ዝንጅብል የገበያ ፍላጐት ያካትታል/ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/
   3.2 በምርት ቦታ፡ ከተለዩት ገዢዎች ጋር የቢዝነስ ስብሰባ ማዘጋጀትና ማካሄድ

4. ለማቴሪያል ግዢ ብድር ለማግኘት ድጋፍ /ለቦሎሶ ቦምቤ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ብቻ/

4.1 በደቡብ ክልል ብድር ከሚሰጡ ተቋማት ጋር ለሚደረግ ድርድር ድጋፍ (በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ)

4.2 የሚከተሉት ጉዳዮች ተግባራዊ እንዲሆኑ አማራጭና ድጋፍ መፈለግ

- የጋራ ሥራ ወይም ንዑስ ኮንትራት ከዳሞታ ዩኒየን ወይም ዓባይ ቡድን
- በተለዩ ገዢዎች የቅድሚያ ክፍያ

ግብአት :

- ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት ፡ 1
- ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ፡ 2/1/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት/
- የገዢዎች ጥገና ወጪ በአ/አ፣ የቢዝነስ ስብሰባ
- የሥራ ማስኬጃ ወጪ፡ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት የጉዞ ወጪ /አበል፣ የመኪና ነዳጅ/፣ የግንኙነት ክፍያ፣ የቢሮ መገልገያ፣ የትራንስፓርት ወጪ ወደ ቦታ /ወረዳ ግብዐትና ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት/

ወጪ :

| | 2012 (እ.ኤ.አ) | 2013 (እ.ኤ.አ) | 2014 (እ.ኤ.አ) | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| የክልል ቢሮ የጉዞ ወጪ (አበል፣ ነዳጅ) | | | | |
| ወቅታዊ መስክ ክትትል | 9,400 | 23,400 | 14,000 | 46,800 |
| አ/አበባ የገዥዎች ዳሰሳ ማድረግ | | 4,900 | 4,900 | 9,800 |
| ለቦሎሶ ቦምቤ ሕ/ሥራ ማህበር በጀት ማፈላለግ | 2,300 | 2,300 | | 4,600 |
| | | | | 0 |
| መስክ ላይ ቢዝነስ ውይይት ማድረግ | | 13,000 | 13,000 | 26,000 |
| | | | | 0 |
| የወረዳ ጽ/በት ስራማስኬጃ ወጪ | 2,000 | 5,000 | 3,000 | 10,000 |
| የክልል ቢሮ ስራማስኬጃ ወጪ | 2,400 | 6,000 | 3,600 | 12,000 |
| | | | | |
| ድምር | 16,100 | 54,600 | 38,500 | 109,200 |

መጠባበቂያ(10%) 10,900 ብር

ጠቅላላ 120,000 ብር

የጊዜ ሠሌዳ :




ማስታወሻ :

"የገዢዎች ጥናትና" "የቢዝነስ ስብሰባ" በ2014 ሊካሄዱ የታቀዱት በፕሮጀክት ቁጥር12 ሥራዎች ጋር ተደራርበዋል፡፡ ፕሮጀክት ቁጥር12 ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የተደረበውን ሥራ ወጪ ግምት ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

## የፕሮጀክት ቁጥር 12

| የፕሮጀክቱ ስም | በዝንጅብል ማጠቢያና ማድረቂያ ቢዝነስ ፕሮጀክት | | |
|---|---|---|---|
| እስትራቴጂ | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ የትርፍ ማሳደግ<br>2-3: በምርት ማምረቻ አካባቢ የእሴት ጭማሪ ሥራዎችን ማስፋፋት<br>2-4: የተለዩና የበላይ የሆኑ ምርቶች/ዝሪያዎች መገበያያ ማጠናከር<br>2-5: የጋራ የግብይት ማፋጠን | | |
| የመሪ ዕቅድ፡<br>ፕሮግራም | ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ፕሮግራም<br>ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረቅ ዝንጅቢል ማስተዋወቅ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2013-2018 እ.ኤ.አ (5 ዓመት) | | |
| የፕሮጀክት ቦታ | ወላይታ ዞንና ከምባታ ጠምባሮ ዞን | | |
| የተመረጠ ሰብል / ምርት | ዝንጅቢል | | |
| የተመረጠ ቡድን | የዝንጅቢል አምራች ቡድን፣ የዝንጅቢል ነጋዴዎች ቡድን | | |
| ቢዝነስ የሚሰሩ አካላት | የተመረጠው ቡድን ነባር ቡድን ወይም በራሱ የተደራጀ ቡድን፣ ቡድን የማደራጀትና ማመቻቸት በፕሮጀክቱ አልታቀደም፡፡<br>❖ የቡድኑ ሁኔታ ወይም ዓይነት ከሕ/ሥራ ማህበር ሁኔታ የተገደበ መሆን የለበትም፡፡<br>❖ ምናልባት ሕሥራ ማህበር የሚደገፍ ቢሆን፣ የጣምራ ሥራ ወይም ንዑስ ኮንትራክተር ሆኖ ከሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒየን ጋር እንዲሠሩ ወይም የግል ቢዝነስ ሆነው እንዲሠሩ ማበረታታት፡፡ (በ2014/15 ወቅትና 2015/16 ወቅት ብቻ)<br>❖ የጃፓን ዓለም አቀፍ ተራድኦ ኤጀንሲ አንድ መንደር አንድ ምርት ቡድን የተመረጠ ቡድን ሊሆን ይችላል፡፡<br>❖ የተመረጠ ቡድን ለዝንጅቢል መግዣ በቂ ገንዘብ ሊኖረው የገባል፡፡ | | |
| ፈፃሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ<br>ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤትና<br>ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ | ደጋፊ ኤጀንሲ | |

*መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች፡*

በዝንጅቢል አምራች አካባቢ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 ተመሳሳይ ደረጃ ያለውን የዝንጅቢል ማጠቢያና ማድረቂያ ቢዝነስ ውስጥ የሚገቡ ሌሎች አርሶአደሮች/ነጋዴዎች ቡድኖች መደገፍ፡፡ ፕሮጀክቱ ዓላማ የሚያደርገው ሁለቱን ቡድኖች በየወቅቱ ለ3 ወቅቶች (ከ2014/15 እስከ 2016/17) በድምሩ 6 ቡድኖችን ለመደገፍ ነው፡፡

የሚደገፉ ቡድኖች የዝንጅቢል አርሶአደሮች ብቻ ሳይሆኑ ነገር ግን የአካባቢ ነጋዴዎች ቡድኖች ጭምር ነው፡፡ በሥራ ቦታ ያሉ ቡድኖች በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተሻሉ አለመሆናቸውን በማገናዘብ፣

ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ /ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በቁርጠኝነት የሚደግፈው ዘዴ አስቸጋሪ የሆነው /ከላይ ወደ ታች/ አቀራረብ በመጀመሪያዎቹ 2 ወቅቶች (2014/15ና 2015/16) ተግባራዊ እንዲሆን ነው፡፡ በመጨረሻው ወቅት ቡድኖቹ ለድጋፍ እንዲያመለክቱ ፍላጐት የሚያሳድረው /ከታች ወደ ላይ/ አቀራረብ ተግባራዊ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም የቢዝነስ ቡድኑ ቁጥር 6 ስለሚደርስ /የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ ሁለት ጉደዮች ጨመሮ እንዲሁም የድጋፍ ዕቅዱ በደንብ መታወቅ ስላለበትና የአርሶአደሮች/ነጋዴዎች ፍቃደኝነት ችግሩን ለመቋቋም ከፍተኛ መሆን ስላለበት ነው፡፡

የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የድጋፍ ይዘት እንደሚከተለው ይሖናል፡፡

- የማጠቢያና ማድረቂያ ሥራዎች ዲዛይን ማድረግ፣

- የማጠቢያ ዕቃዎችን ማቅረብ፣
- የማጠቢያ ሥራዎች ወጪ (ማቴሪያሎች፣ የሠለጠነ ባለሙያ ወጪና መመሪያ)
- ማድረቂያ ቦታ/አውድማ መሥሪያ ወጪ (ቁሳቁስ፣ የሰለጠነ ባለሙያ፣ የክልል/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ አመራር)
- በሥራ ቦታ ላይ የዝንጅብል ማጠቢያ ሥራና ሥራ አመራር ስልጠና ማስጠት፣
- የምርት ግብይት ድጋፍ፡ የገዢዎች መረጃ፣ በሥራ ቦታ የቢዝነስ ስብሰባ፣ የጉዞ ወጪ ከክልል ውጭ የተፈፀመ የግብይት ሥራ፣
- ለቢዝነስ ሥራና ማኔጅመንት የምክር ድጋፍ፣

የመጀመሪያ ዓመት /2013/ የጊዜ ሠሌዳ የሚያመለክተው የፕሮጀክት በጀት ማግኘት ነው፡፡

ድርጊት :

* የሥራዎች ተዋናይ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ነው፡፡ በሌላ ካልተገለፀ በስተቀር

[ 2013 ]

<u>የፕሮጀክት በጀት ብድር ለማግኘት በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የሚሠሩ ሥራዎች</u>

1. ዕርዳታ/ብድር ሊሰጡ የሚችሉ እምቅ ኃይል ያላቸውን መለየት፣ የእርዳታ ፕሮግራም፣ ማዘጋጀት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የክልል መንግሥት ወዘተ ማሳተፍ
2. የፕሮጀክት ፕሮፓዛልና የማስረጃ ዶክመንት ማዘጋጀት፡፡ /ሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 05 እንደነባር ሞዴል መጠቀም/
3. ለተለዩ እምቅ ኃይል ላላቸው እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የፕሮጀክት ፕሮፓዛሉን ማስረደት፣
4. ስለበጀት ምደባ ከክልሉ መንግስት ጋር መወያየት፣
5. በተገኘው በጀት መሠረት የፕሮጀክቱን ደረጃና የጊዜ ሠሌዳ ማስተካከል፡፡

[ 2014 ወቅት ]

1. የተመረጡ ቡድኖችን መለየት
   - 1.1 የማስረዳት ስብሰባ ከሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች ጋር፡ የፕሮጀክቱን ዕቅድ/ ይዘት ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት፣ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያና /ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች /ዳሞታ ዩኒየን፣ አምበርቾ ዩኒየን/ በወላይታ ዞንና ካምባታ ጠምባሮ ዞን፡፡ ለመጀመሪያ ዓመት ረቂም የተወዳዳሪ ቡድኖች ሊስት ማዘጋጀት፡፡
   - 1.2 የማስረዳት ስብሰባ ከተወዳዳሪ ቡድኖች ጋር፡ የፕሮጀክቱን ዕቅድ፣ የተጠቃሚዎች ድጋፍና ኃላፊነቶች ይዘት ለተወዳዳሪ ቡድኖች ማስረደት የተወዳዳሪ ቡድኖችን ወደ ዓባይ ቡድን ሥራ ቦታ በሃዳሮ ጡንጦ ጉብኝት መውሰድ፣
   - 1.3 የተወዳዳሪዎችን መጠን በማሳጠር አጭር ሊስት ማድረግ፡ በአጭር ሊስጥ የገቡትን ቡድኖች ጥናት ማካሄድ /ጥናት በሀብታቸው/አቅማቸው/
   - 1.4 ድንገት ተወዳዳሪዉ ሕ/ሥራ ማህበር ቢሆን ወይም ቡድን ሆኖ በቂ ገንዘብ የሌለው ከሆነ የጣምራ ሥራ መመስረት ወይም ንዑስ ኮንትራክተር መፈጠርን ከዩኒየን ጋር ወይም ከግል ቢዝነስ ጋር መፈተሽ፡፡
   - 1.5 ተጠቃሚ ቡድኖችን መወሰን፡፡ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ድጋፍና የተጠቃሚዎች ኃላፊነት ላይ የጋራ የመግባቢያ ሠነድ መለዋወጥ፡፡
2. የማጠቢያና ማድረቂያ ሥራዎች ማቋቋምና ድጋፍ
   - 2.1 የማጠቢያና ማድረቂያ ሥራ ዲዛይን ማድረግ /የአካባቢ ኮንሰልታንት መጠቀም/
   - 2.2 የቦታ ማዕዳት፣ የማድረቂያና ቆጥ መሥራት፣ አጥር መሥራትና ለሥራ ቦታ መብራት ኃይል አጠቃቀም ግልፅ ሥርዓት ማስቀመጥ፣
   - 2.3 የማጠቢያ ዕቃ ግዢና ሥርጭት
   - 2.4 ለማጠቢያ ቦታ ዝግጅት የሚያስፈልግ ማቴሪያሎችን መግዛትና ማሰራጨት፡፡ ለሰለጠኑ ባለሙያዎች ስለሥራው መመሪያ መስጠት
3. ለማጠቢያና ማድረቂያ የሥራና ማኔጅመንት ድጋፍ
   - 3.1 ስለማጠቢያ አሠራር በሥራ ቦታ ላይ ሥልጠና (ለሠራተኞች፣ ለሥራ አስኪያጅ) መስጠት፣

3.2 ለማጠቢያ ቦታ አስተዳዳር በሥራ ቦታ ላይ ሥልጠና (ለሥራ አስኪያጅ፣ የቡድን መሪዎች) መስጠት፣
3.3 ወቅታዊ ክትትል በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት እና በሥራ ቦታ የምክር ድጋፍ ማድረግ

4. የምርት ግብይት ድጋፍ
4.1 ከንግድ ሚኒስቴር የገዢዎች መረጃ ማግኘት
4.2 የገዢ ጥናት በአ/አ ማካሄድ (ላኪዎች፣ጅምላ ነጋዴዎች ለአገር ውስጥ ገበያዎች፡፡ የታጠበ ትኩስ ዝንጅብል የገበያ ፍላጐት በጥናቱ ይካተታል)
4.3 ከተለዩ ገዢዎች ጋር በሥራ ቦታ የቢዝነስ ስብሰባ ማዘጋጀትና ማካሄድ
4.4 ከቢዝነስ ቡድኖች ጋር የጋራ ሽያጭ የሚቻልበት ሁኔታ መፈተሽ
4.5 የተመረጡ ቡድኖች ከደቡብ ክልል ውጭ ለገበያ ሥራዎች ያደረጉት ጉዞ ወጪ ድጎማ መስጠት

[ 2015/16 ወቅት ] /ከ2014/15 ወቅት ጋር ተመሳሳይ

[ 2016/17 ወቅት ]

1. የመነሻ ወጪ ድጎማ ሥርዐት ዕቅድ
በ2014/15ና 2015/16 የተሰጠውን ድጋፍ መከለስ፡፡ ቀጣይ ነጥቦችን ለማቀድ ካለፈው ትምህርት መቅሰም፡፡
   - የድጎማ ደረጃ የተጠቃሚ ቡድኖች ቁጥር የታቀደው ዕቃና ሥራ እንዲሁም መጠን
   - ከፍተኛውን ጣራ ዋጋ መስጠት
   - የተጠቃሚ ቡድን ሁኔታ
   - የተጠቃሚ ግዴታዎች /የድጎማ መመለሻ፣ መዝገብ አያያዝ፣ ሪፓርት ወዘተ/
   - የስርጭት ዘዴ
2. የሕዝብ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻና ምርጫ ዘዴ ማቀድ
3. የመነሻ ወጪ ድጎማ ሥርዐት የሕዝብ ማስታወቂያ፣ የድጎማ ሥርዐት ለዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ/ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት /ዩኒየን ማብራራት
4. ማመልከቻዎችን መቀበል፣ የአመልካቾች ጥናት ማካሄድ
5. የተጠቃሚ ቡድኖችን መወሰን፡፡ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ድጋፍና የተጠቃሚዎች ኃላፊነት ላይ የጋራ የመግባቢያ ሠነድ መለዋወጥ
6. ድጋፍ መስጠትና ማሠራጨት (ከ2 እስከ 4 የ2014/15 ወቅት ተመሳሳይ)

ግብአት :

- ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት፡ 2
- የማጠቢያ ዕቃ የሞተር ፓምፓ፣ ከፍተኛ ግፊት ያለው ማጠቢያ ማሽን፣ ፕላስቲክ ሣጥኖች፣ የእጅ ጋሪ፣ የቱቦ ሆዝ፣ ማጣሪያ ጌት ቫልቭ /መግጠሚያዎች፣ የጥገና ዕቃዎች፡፡
- ማጠቢያ ሥራዎች፡ 2000 ሊትር የሚይዝ የውሃ ታንከር ከነማቆሚያው፣ መንከሪያ ጉርጓዶች፣ በሲሚንቶ የተሠራ ወለል በግፊት ባለው ውሃ ማጠቢያ
- የማድረቅ ስፍራ ከቀርካሃ የተሠራ ወይንም ሽቦ ከላይ የተደረገበት (1000 ካሬ ሜትር ለእያንዳዱ ቦታ)
- የአካባቢ ኮንሰልታንት፡ የማጠቢያና ማድረቂያ ሥራዎች ዲዛይን የሚያደርግ፣ የድጎማ ሥርዐት ዕቅድ አማካሪ፣ ለሕዝብ ማስታወቂያ/ማመልከቻ/ ምርጫ ዘዴዎች ዕቅድ የሚያዘጋጅ፡፡
- ለማብራሪያ ስብሰባ ወጪ ከተወዳዳሪ ቡድኖች ጋር /የትራንስፓርት ወጪ፣ መስተንግዶ/፣ በሥራ ቦታ ቢዝነስ ስብሰባ /የገዢዎች የጉዞ ወጪዎች፣ መስተንግዶ/፣ የተመረጡ ቡድኖች ለገበያ ሥራዎች የጉዞ ወጪ ድጎማ፡፡
- ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የሥራ ማስኬጃ ወጪ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት የጉዞ ወጪ /አበል፣የመኪና ነዳጅ/፣ የግንኙነት ክፍያ፣ የቢሮ መገልገያ ወዘተ…

ወጪ :

0. በክልል ግብዐትናግብይትና ሕ/ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ የፕሮጀክቱን በጀት ለማግኘት የተደረጉ ሥራዎች የለም
1. የማጠቢያና ማድረቂያ ዕቃዎች ለማቋቋም ድጋፍ
   - የማጠቢያ ዕቃዎች 200,400
   - የማጠቢያ ሥራዎች 163,800
   - ማድረቂያ ቦታ 540,000
   - ለዲዛይን ሥራዎች የአካባቢ ኮንሰልታንት 36,000
2. ለስብሰባዎች ወጪ
   - ከተወዳዳሪ ቡድኖች ጋር የማብራሪያ ስብሰባ 7,600
   - በሥራ ቦታ የቢዝነስ ስብሰባ 39,000
   - የተመረጡ ቡድኖች የገበያ ሥራዎች ድጎማ 12,600
   - የድጎማ ሥርዐት ዕቅድ የሚያዘጋጅ የአካባቢ ኮንሰልታንት 17,500
3. ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት የሥራ ማስኬጃ ወጪ ከዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት
   - ዩኒየኖች ጋር የማብራሪያ ወጪ 27,000
   - በአ/አ የገዢዎች ጥናት 14,700
   - ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ወቅታዊ ክትትል 66,900
   - ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ስራ ማስኬጃ ወጪ 21,000
   - ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሥራ ማስኬጃ ወጪ 54,000

| | |
|---|---|
| ከ1-3 ንዑስ ድምር | 1,200,500 ብር |
| መጠባበቂያ (10%) | 120,000 ብር |
| ጠቅላላ | 1,320,000 ብር |

የእያንዳንዱ ዓመት የፕሮጀክት ወጪ በዕዝል 1 ተመልክቷል

የጊዜ ሠሌዳ :

በዕዝል 2 እንደተመለከተው ይሆናል።

የትኩረት ነጥቦች :

- ለሥራ ቦታና ዕቃዎች /መሬትና ጽዳት ሥራዎች/፣ የማድረቂያ ቆጥ ለመሥራት፣ አጥር፣ ለሥራ ቦታ የመብራት ኃይል እንዲደርስ አስፈላጊውን ሥርዓት ለመፈፀም የተመረጠው ቡድን /ተጠቃሚዎች/ ኃላፊነት አለባቸው።
- የፕሮጀክቱ ሥራ ቦታ የወንዝ ዳር ወይም ውሃ መኖር ያለበት ሲሆን ተስማሚ ቦታ የተወሰነ ሊሆን ይችላል። ሆኖም በአንድ አካባቢ እጅብ ብለው መኖር የለበትም። በዝንጅቢል ምርት አካባቢ መበታተን ጥሩ ነው።
- ድንገት የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበር የተመረጠ እንደሆነ፤ ፕሮጀክት ቁ.23 "እህል ነክ ያልሆኑ ምርቶች ግብይት ሕ/ሥራ ማህበራት ግብይት አቅም ማስፋፊያ" በድርጅት አመራር፣ በመዝገብ አያያዝ ወዘተ ሥልጠና መስጠት አለበት።

## ዕዝል1 የፕሮጀክት ወጪ በዓመቱ

| | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የስራ ቦታ ብዛት (የተመረጠ ቡድን) | | 2 | 2 | 2 | | 6 |
| | | | | | | |
| ከዞን/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ እና ዩኒየን ጋር ማብራሪያ ስብሰባ ማካሄድ | | 9,000 | 9,000 | 9,000 | | 27,000 |
| በእጩነት ከቀረቡ ቡድኖች ጋር ማብራሪያ ስብሰባ መካሄድ | | 3,800 | 3,800 | | | 7,600 |
| | | | | | | |
| ማጠቢያ ቁሳቁስ | | 61,200 | 61,200 | 61,200 | | 183,600 |
| ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን ማጓጓዝ | | 5,600 | 5,600 | 5,600 | | 16,800 |
| ማጠቢያ መገልገያ | | 54,600 | 54,600 | 54,600 | | 163,800 |
| መድረቂያ ጠረጴዛ | | 180,000 | 180,000 | 180,000 | | 540,000 |
| መገልገያ ቦታና አቀማመጥ ዲዛይን ማድረግ (በአካባቢ አማካሪ) | | 12,000 | 12,000 | 12,000 | | 36,000 |
| | | | | | | |
| የክልል ቢሮ የጉዞ ወጪ (አበል፣ ነዳጅ) | | | | | | |
| ቡደኖችን መምረጥ | | 4,700 | 4,700 | 4,700 | | 14,100 |
| የመገልገያ ዕቃዎችን መስጠት/መዘርጋት፣ የማጠቢያ ቦታ ሲሠራ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ | | 7,000 | 7,000 | 7,000 | | 21,000 |
| በማጠብ ሥራ/የሥራ አስተዳዳር በሥራ ላይ ስልጠና | | 3,600 | 3,600 | 3,600 | | 10,800 |
| ወቅታዊ መስክ ክትትል | | | 7,000 | 7,000 | 7,000 | 21,000 |
| አ/አበባ የገዥዎች ዳሰሳ ማድረግ | | | 4,900 | 4,900 | 4,900 | 14,700 |
| | | | | | | |
| መስክ ላይ ቢዝነስ ውይይት ማድረግ | | | 13,000 | 13,000 | 13,000 | 39,000 |
| ለተመረጡ ቡድኖች ለግብይት ሥራ የገንዘብ ድጋፍ (ለጉዞ ወጪ) | | | 4,200 | 4,200 | 4,200 | 12,600 |
| | | | | | | |
| የመጀመሪያ ወጪ ግምትና ድጋፍ በአካባቢ አማካሪ ማሠራት | | | | 17,500 | | 17,500 |
| | | | | | | |
| የክልል ጽ/በት ስራማስኬጃ ወጪ | | 6,000 | 6,000 | 6,000 | 3,000 | 21,000 |
| የወረዳ ቢሮ ስራማስኬጃ ወጪ | | 7,200 | 14,400 | 21,600 | 10,800 | 54,000 |
| ድምር | 0 | 354,700 | 391,000 | 411,900 | 42,900 | 1,200,500 |

## ዕዝል 2 የአፈጻጸም የጊዜ ሠሌዳ

| | | 2013 (እ.ኤ.አ) | | | | 014 (እ.ኤ.አ) | | | | 2015 (እ.ኤ.አ | | | | 2016 (እ.ኤ.አ | | | | 2017 (እ.ኤ.አ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 0 | በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የፕሮጀክት በጀት ለማግኘት የሚደረጉ ስራዎች | ■ | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | **1. የቡድኖች ምርጫ** | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | /2014/2015 ና 2015 /16 ወቅቶች/ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1-1. | ከሚመለከታቸው የዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ እና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት፣ ዩኒየኖች ጋር የማስረዳት ስብሰባ የተወዳዳሪ ቡድኖች | | | | | ■ | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 1-2. | ከተወዳዳሪ ቡድኖች ጋር የማስረዳት ስብሰባ፣ እና ተወዳዳሪ ቡድኖችን አባያ ቡድን ሀዳሮ ጡንጦ የሥራ ቦታ | | | | | ■ | | | | ■ | | | | | | | | | | | |
| 1-3. | የተወዳዳሪ ቡድኑን አጭር ሊስት ማድረግ አጭር ሊስት ከተደረገው ቡድን ጥናት ማካሄድ | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 1-4. | ከዩኒየኖች እና ከግል ቢዝነስ አባላት ጋር የጋራ ሥራ መመስረት እና ንዑስ ኮንትራክተር ማድረግ አማራጭ መፈተሸ | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| 1-5. | የተጠቃሚ ቡድኖችን መወሰን የጋራ ስምምነት ሰነድ መለዋወጥ | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | | | | | | | |
| | 2016/17 ወቅት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1-6. | 2014/15 ና 2015/16 የተሰጡ ድጋፍ ስራዎች መከለስ እና የድጎማ ስርዓት ማሰብ | | | | | | | | | | | | | ■ | | | | | | | |
| 1-7. | የሕዝባዊ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻና ምርጫ በሚመለከት የእቅድ ዘዴ ማውጣት | | | | | | | | | | | | | ■ | | | | | | | |
| 1-8. | የሕዝባዊ ማስታወቂያ የድጎማ ስርዓት | | | | | | | | | | | | | | ■ | | | | | | |
| 1-9. | የአመልካቾች ጥናት ማካሄድ ተጠቃሚ ቡድኖችን መወሰን የጋራ ስምምነት ሰነድ መለዋወጥ | | | | | | | | | | | | | | ■ | | | | | | |
| 2 | **2 ለማጠቢያና ማድረቂያ ዕቃዎች ማቋቋሚያ ድጋፍ** | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2-1. | 2.1 የማጠቢያና የማድረቂያ ሥራዎች ዲዛይን | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | | | |
| 2-2. | 2.2 ቦታ ማፅዳት፣ የማድረቂያ ቆጥ መስራት፣ አጥር መስራትና ለተጠቃሚ ቡድን መብራት ሃይል ለማስገባት ግልፅ አሠራር ማስቀመጥ | | | | | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | | |
| 2-3. | የማጠቢያ ዕቃ መግዛትና ማሠራጨት | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | | | |
| 2-4. | የማጠቢያ ስራ መስራት /በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ /የተመረጠ ቡድን | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | | | |
| 3 | **ለማጠቢያና ማድረቂያ ስራዎችና ማኔጅመንት ድጋፍ** | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3-1. | የማጠቢያ ስራ ለሠራተኞች የOJT ስልጠና መስጠት | | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | | |
| 3-2. | በስራ ቦታ ሥራ አስኪያጅ፣ ቡድን መሪዎች የስራ አስተዳዳር በሥራ ላይ ስልጠና መስጠት | | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | | |
| 3-3. | በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥያ ጽ/ቤት ወቅታዊ ክትትልና ድጋፍ በስራ ቦታ | | | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | |
| 4 | **የምርት ግብይት ድጋፍ** | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4-1. | ከንግድ ሚኒስቴር የገዢዎች መረጃ ማግኘት | | | | | | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | |
| 4-2. | በአ.አ የገዢዎች ጥናት ማካሄድ | | | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | |
| 4-3. | ከተመረጡ ገዢዎች ጋር በስራ ቦታ የቢዝነስ ስብሰባ ማዘጋጀትና ማካሄድ | | | | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | |
| 4-4. | በ5 ቢዝነስ ቡድኖች የጋራ ሽያጭ አማራጭ መፈተሽ | | | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | |
| 4-5. | ከደቡብ ክልል ውጪ የተመረጡ ቡድኖች ለገበያ ጥናት ያደረጉትን የጉዞ ወጪዎች ድጎማ መስጠት | | | | | | | | | ■ | | | | ■ | | | | ■ | | | |
| | የዝንጅብል የምርት ወቅት /የማጠብና የማድረቅ ስራዎች ጊዜ/ | | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | ■ | ■ | | | |

## የፕሮጀክት ቁጥር 13

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የእርድ ድህረ ምርት ማሻሻያ ዕቅድ | | |
| እስትራቴጂ | 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ የትርፍ ማሳደግ<br>2-3: በምርት ማምረቻ አካባቢ የእሴት ጭማሪ ሥራዎችን ማስፋፊት<br>2-4: የተለዩና የበላይ የሆኑ ምርቶች/ዝሪያዎች መገበያያ ማጠናከር | | |
| የመሪ ዕቅድ ሮግራም | ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክት ጊዜ | 2013 እ.ኤ.አ (1 ዓመት) | | |
| የፕሮጀክት ቦታ | የኪ ወረዳ (ሸካ ዞን) | | |
| የተመረጠ ሰብል/ምርት | እርድ | | |
| የተመረጠ ቡድን | የእርድ አምራቾች፣ የአካባቢ ነጋዴዎች | | |
| ፈፃሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | ደጋፊ ኤጀንሲ | ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት በጥናቱ አካባቢ |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች፡
በሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 05 የሚሠራ የዝንጅቢል ማጠቢያ ዘዴ ተመርምሮ የመንከሪያ ጉርጓድና ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚችል ከፍተኛ ግፊት ያለው ማጠቢያ ማሽን ትክክለኛ እንደሆነ ተደመደመ፡፡ በደቡብ ክልል እርድ እንደ ዝንጅብል ተመሳሳይ ሆኖ እንደ ገቢ ማስዝገኛ ሰብል ይለማል፡፡ ዱቄት የእርድ የመጨረሻ የምርት ደረጃ ነው፡፡ ሥር መቁረጥ፣ ማጠብና ማድረቅ አስፈላጊ ሥራዎች ናቸው፡፡ በባህላዊ አሠራር ከማድረቅ በፊት እንደሚፈላ ሪፓርት ያለ ቢሆንም ዝርዝር አሠራሩ ግልጽ አይደለም፡፡ ጃፓንን በተመለከተ ሥር መቁረጥና መላጥ ሥራዎች ከመድረቁ በፊት ይሠራሉ፡፡ ነገር ግን በደቡብ ክልል ሥሮችና ልጥ የሚወገዱት ከማድረቁ በፊት በመጥረግ ነው፡፡

አሁን ያለውን የድህረ ምርት ልምምድ መቀየር አስፈላጊ ስለመሆኑ ግልፅ ለማድረግ በወቃታዊ ድህረ ምርት ማቀነባበሪያና የእርድ መሰብሰቢያ ላይ ከገበያ ተኮረና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ቴክኖሎጂ ከመሆን አንፃር መፈተሽና መዘፍዘፍና ግፊት ባለው ውሃ ማጠቢያ ዘዴን በማካተት የምርምር ጥናት ማካሄድ፡፡ ምናልባት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ቴክኖሎጂ ከተገኘ፣ ስለማስተዋወቂያ እስትራቴጂ ማሰብና የድጋፍ ዕቅድ /ፕሮጀክት ማዘጋጀት፡፡

የሚከተሉት ነጥቦች በምርምር ጥናቱ ግልፅ ሊሆኑ ይገባል
- የገዢዎች ፍላጐት የሚያሟላ ምርት ለማምረት አስፈላጊ ማሻሻያዎች
- ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ቴክኖሎጂ ዕቃዎች በአገር ውስጥ መገኘት አለመገኘትና ከተቻለ ከውጭ ማስገባት/ ማልማት ወይም አለመቻል፡፡
- ተግባራዊ ሊሆን የሚችለውን ቴክኖሎጂ እንዴት ለአርሶአደሮች/ ነጋዴዎች (የተመረጠ ቡድን፣ ቅድመ ሁኔታዎች አቀራረብ ወዘተ)

ድርጊት :
1. በማምረቻ ቦታዎች የመስክ ጥናት ማካሄድ፣
2. በአ.አ የተጠቃሚዎች/ ገዢዎች ጥናት ማካሄድ፣
3. የተሻሻሉ ይዘቶችን ማሰላሰል /ምን መለወጥ እንዳለበት፣ እንዴት መለወጥ እንደሚቻል
   3.1 ከገበያ ተኮር አመለካከት አኳያ አስፈላጊ መሻሻሎች እንዲደረጉ ግልፅ ማድረግ፣
   3.2 ተግባራዊ ሊሆን የሚችሉ ዕቃዎች መፈተሽ፣

< ምናልባት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ቴክኖሎጂ ከተለየ >

   3.3 ለአዲሱ ቴክኖሎጂ ተስማሚ ኦፕሬተር ማሰብ፣
   3.4 አዲስን ቴክኖሎጂ በማስተዋወቅ በመሰብሰቢያ ሥርዓት ያለውን ለውጥ ማሰብ፣

4. የድህረምርት ማቀነባበሪያ ለማሻሻል የድጋፍ ዕቅድ/ፕሮጀክት ማዘጋጀት፣
   4.1 የድጋፍ እርምጃዎች ይዘታቸውን ማሰብ፣
   4.2 የድጋፍ ፕሮጀክት ማዘጋጀት፣

ግብአት፡
- ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት፣
- የጥናት ወጪ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት የጉዞ ወጪ /አበል፣ የመኪና ነዳጅ/፣ የአካባቢ ኮንሰልታንት *የህትመት ወጪ ወዘተ…
- የሥራ ማስኬጃ ወጪ፡ የግንኙነት ክፍያ፣ የቢሮ መገልገያ

❖ የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኤክስፐርት አቅም ለዕቅድ ሥራ በሥራ ቦታ ስልጠና ሙከራ ፕሮጀክት አፈፃፀም ተጠናክሯል ለማለት በጣም ያስቸግራል። የተወሰነ አቅም ለማካካስ በጥናቱ እንደአማካሪ እንዲያገለግል የአካባቢ ኮንሰልታንት ለመጠቀም ታቅዷል።

ወጪ :
1. የጥናት ወጪ /የጉዞ አበል /አበል፣ የመኪና ነዳጅ/፣ የህትመት ወጪ ወዘተ: 40,200
2. የጥናት ወጪ /የአካባቢ ኮንሰልታንት : 17,500
3. የሥራ ማስኬጃ ወጪ : 3,500

| | |
|---|---|
| ከ1-3 ንዑስ ድምር | 61,200 ብር |
| መጠባበቂያ (10%) | 6,100 ብር |
| ድምር | 67,000 ብር |

የጊዜ ሠሌዳ :

| | 2013 (እ.ኤ.አ) | | | | 2014 (እ.ኤ.አ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1. በማምረቻ ቦታዎች የመስክ ጥናት ማካሄድ | | | | | | | | |
| 2. በአ.አበባ የተጠቃሚዎች/ ገገርዎች ጥናት ማካሄድ | | | | | | | | |
| 3.የመሻሻል ይዘቶችን ማሰላሰል /ምን መለወጥ እንዳለበት፣ እንዴት መለወጥ እንደሚቻል | | | | | | | | |
| 3-1. ከገበያ ተኮር አመለካከት አኳያ አስፈላጊ መሻሻሎች እንዱደረጉ ግልፅ ማድረግ | | | | | | | | |
| 3-2. ተግባራዊ ሊሆን የሚችሉ ዕቃዎች መፈተሽ | | | | | | | | |
| <ምናልባት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ቴክኖሎጂ ከተለየ> | | | | | | | | |
| 3-3. ተግባራዊ ሊሆን የሚችሉ ዕቃዎች መፈተሽ | | | | | | | | |
| 3-4. ለአዲሱ ቴክኖሎጂ ተስማሚ ኦፕሬተር ማሰብ | | | | | | | | |
| 4.የድህረምርት ማቀነባበሪያ ለማሻሻል የድጋፍ ዕቅድ /ፕሮጀክት ማዘጋጀት | | | | | | | | |
| 4-1. የድጋፍ እርምጃዎች ይዘታቸውን ማሰብ | | | | | | | | |
| 4-2. የድጋፍ ፕሮጀክት ማዘጋጀ | | | | | | | | |
| እርድ መሰብሰቢያ ወቅት | | | | | | | | |

### 6.4.3 ለግብርና ምርቶች ገበያ መሰረተ ልማት ዕቅድ

**የፕሮጀክት ቁጥር 14**

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ርዕስ | የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 ለቦሎቄ ገበያ መሰረተልማት ድጋፍ ፕሮጀክት | | |
| ስልት | 3: የገበያ ተግባራትን ለማከናወን ዉጤታማ የገበያ መሰረተልማት ማጠናከር<br>3-2: በተተኮሩ አካባቢዎች የወረዳ ገበያ ቦታዎች ላይ የገበያ መሰረተልማትን ማሻሻል | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | የወረዳ ገበያ ቦታ ማሻሻያ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | 2013-2017 እ.ኤ.አ (5 ዓመታት) | | |
| የፕሮጀክት አካባቢ | በቦሪቻ ወረዳ በሊሳ ከተማ | | |
| የተተኮረ እህል / ምርት | ቦሎቄ | | |
| የትኩረት ቡድን | የቦሪቻ ወረዳ አስተዳደር፣ የበሊሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት፣ የቦሎቄ ነጋዴዎች፣ የቦሎቄ አምራች አርሶአደሮች | | |
| ፈጻሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ፣<br>ቦሪቻ ወረዳ አስተዳደር፣<br>በሊሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | ደጋፊ አካል | |

*መነሻ ሀሳብ ዓላማዎች:*
የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 ለቦሎቄ ምርት በሲዳማ ዞን ቦሪቻ ወረዳ በሊሳ ከተማ ለምርት ጥራት መጨመር፣ የገበያ ልዉዉጥ ሁኔታ እንዲሻሻልና የስራ አመራር አቅም እንዲጠናከር የገበያ ፋሲሊቲ አስገንብቷል፡፡

በዚህ መሰረት ጣሪያና ኮንክሪት ወለል ያለዉ ይህ የገበያ ፋሲሊቲ በቦሎቄ ምርት ንግድ ልዉዉጥ ዙሪያ ስርዓት እንዲሰፍን ለማስቻል በከተማዉ ዉስጥ ፈቃድ ያላቸዉ ነጋዴዎች ቦለቄን ከአርሶአገሮች እንዲገዙ አድርጓል፡፡ ስለዚህ እንደ ገበሬዎች (አምራቾች)፣ የስራ አመራር አካላት እና ነጋዴዎች ያሉ ባለድርሻ አካላት በፋሲሊቲዉና በአመራሩ ያላቸዉን ርካታ ገልጸዋል፡፡ ይኸዉ ፋሲሊቲ ካስገኛቸዉ ጥቅሞች ዉስጥ ጥቂቶቹ ከዚህ በታች የቀረቡት ይጠቀሳሉ፡

1) የንግድ ልዉዉጡ በተወሰነ ቦታ ፈቃድ ባላቸዉ ነጋዴዎች ስለሚከናወን ህገወጥ ነጋዴዎች በከፍተኛ ሁኔታ ቁጥራቸዉ ቀንሷል፡፡ ስለዚህ ከገበሬዎችና ነጋዴዎች መካከል ተገቢ የንግድ ልዉዉጥ መካሄድ ተጀምሯል፡፡ ከዚህ በፊት ግን አርሶአደሮች አንዳንድ ጊዜ በነጋዴዎች ተገደዉ ምርታቸዉን በርካሽ ዋጋ እንዲሸጡ ይደረጉ ነበር፡፡ ህጋዊ ነጋዴዎች ዓመታዊ ምርመራ በተደረገለት ሚዛን ስለሚጠቀሙ ከአርሶአደሮች ጋር የሚደረገው ኢ-ፍትሃዊ ልዉዉጥ በጣም ቀንሷል፡፡
2) ግዥዉ ከጣሪያና ወለል መሃል ስለሆነ የሚከናወነዉ በርካታ የቦለቄ ምርት ከአፈርና ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር ተቀላቅሎ ይቀርብ የነበረዉ አሁን በመቀነሱ ጥራቱ በሚታይ መልኩ ተሻሽሏል፡፡ በምርቱ ዉስጥ ቀደም ሲል የሚታየዉ አቧራ፣ ጭቃና ሌላ ባዕድ ነገር ስለቀነሰ ጥራት ያለዉ ቦሎቄ ለገበያ መቅረብ ጀምሯል፡፡
3) ከአዲሱ የገበያ ፋሲሊቲ ከነጋዴዎች የሚሰበሰበዉ ግብር ለወረዳዉ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ አስገኝቷል፡፡

የቦሎቄ ምርት ጥራትን ለማሻሻል የእርጥበት መጠን መለኪያ/መፈተሻ እና የጥራጥሬ ማበጠሪያ ለከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ተሰጥተዋል፡፡

በዚህ በቁጥር 14 የፕሮጀክት ዕቅድ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከላይ የተዘረዘሩት ጥቅሞች መታየት አለመታየታቸዉን ለፋሲሊቲዉ በሚሰጠዉ አመራርና በክትትል በማረጋገጥ የፋሲሊቲዉን አስተዳደር ለሌሎች ገበያዎች አርአያ እንዲሆኑ ድጋፍ እንዲሰጥ ይጠበቃል፡፡

| ድርጊት ፧ | |
|---|---|
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ:<br>1. በሶስት ወር አንድ ጊዜ ከወረዳና ከከተማዉ ማዘጋጃ ቤት የክትትልና የምክክር መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡<br>2. ወረዳዉ በሚያቀርበዉ ጥያቄ መሰረት በገበያ ማስፋፊያ ዕቅድ የምክር አገልግሎት<br>3. ለሌሎች ወረዳዎችና የማዘጋጃ ቤቶች የህዝብ ግንኙነት ስራ ይሰራል፡፡ | የወረዳ አስተዳደር/ የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት:<br>1. የቦሎቄ ምርት ግዥ መጠንን መመዝገብ<br>2. ከክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ጋር በየሁለት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ የአስተዳደር ስብሰባ ያደርጋል፡፡<br>3. የኤክስቴንሽን ዕቅድ ማዘጋጀት<br>4. ከአርሶአደሮች ጋር ሀሳብ መለዋወጥ<br>5. የአስተዳደር መመሪያዎችን በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በመከለስ ማሻሻል፡፡ |

| ግብዓት: | |
|---|---|
| ክልልግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ:<br>1. ሰራተኞችን በስራ ያሰማራል<br>2. በቢሮዉ ተነሳሽነት ስብሰባን ማዘጋጀት | የወረዳ አስተዳደር/ የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት:<br>1. ሰራተኞችን ወደ ስራ ያሰማራል<br>2. ለክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ስብሰባ ሰራተኞችን ይመድባል |

ወጪ:

1. በቢሮዉ ሰራተኞች ወደ ሌላ ከተማ የሚደረግ የጉዞ ወጪ (መጓጓዣ እና ዉሎ አበል): 500 ብር ለአንድ ጉዞ
2. የስብሰባ ወጪ (መጓጓዣ እና ዉሎ አበል): 5,000 ብር ለአንድ ጉዞ

የጊዜ ሰሌዳ:

| አስፈጻሚ አካል | ድርጊት | አፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ (እ.ኤ.አ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | | | | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | | 2017 | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ግብይና ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | መደበኛ ስብሰባ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ |
| | የህዝብ ግንኙነት | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ |
| ወረዳ/ ማዘጋጃ ቤት | የንግድ መረጃ መያዝ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ |
| | የሥራ አመራርር ኮሚቴ ስብሰባ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ |
| | የአርሰአደሮች ድምፅ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ |
| | የሥራ መመሪያ ማሻሻያ | | | | △ | | | | | | | | △ | | | | | | | | △ |

አስተያየት:

በተሻለ አፈጻጸም ለመስራት የክትትል ዉጤቶች በፕሮጀክት ቁጥር 15 ላይ መንፀባረቅ አለባቸዉ፡፡

## ፕሮጀክት ቁጥር 15

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ርዕስ | የቦሎቄ ምርት መሰረተልማት ማስፋፋት | | |
| ስልት | 3: የገበያ ተግባራትን ለማከናወን ዉጤታማ የገበያ መሰረተልማት ማጠናከር<br>3-2: ትኩረት በተደረገባቸዉ አካባቢዎች የወረዳ ገበያ ቦታዎችን መሰረተልማት ማሳሻሻል | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | የወረዳ ገበያ ቦታ ማሻሻያ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | ከ2013 እስከ 2017 እ.ኤ.አ (5 ዓመታት) | | |
| የፕሮጀክቱ ሳይቶች | ከዚህ በታች ያሉ ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሥርዓት ለመዘርጋት በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 የተመረጡ 8 ወረዳዎች<br>(1) በሃዲያ ዞን ምስራቅ ባዳዋቾ<br>(2) በሃዲያ ዞን ምዕራብ ባዳዋቾ<br>(3) በወላይታ ዞን ዳሞት ጋሌ<br>(4) በወላይታ ዞን ሶዶ ዙሪያ<br>(5) በሲዳማ ዞን ሎካ አባያ<br>(6) በሰገን ዞን አማሮ<br>(7) በሰገን ዞን ቡርጂ<br>(8) አላባ ልዩ ወረዳ | | |
| የትኩረት ሰብል / ምርት | ቦሎቄ | | |
| የትኩረት ቡድን | የወረዳ አስተዳደር፣ የከተሞቹ ማዘጋጃ ቤቶች፣ የቦሎቄ ነጋዴዎች፣ የቦለቄ አምራቾች | | |
| ፈጻሚዉ ድርጅት | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ<br>የወረዳ አስተዳደር፣<br>የከተሞቹ ማዘጋጃ ቤቶች | ድጋፍ ሰጪ ድርጅት | የግብና ዕድገት ፕሮግራም እና ሌሎች ለጋሾች |

*መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች*:

ቦሎቄ በኢትዮጵያ ከሚመረቱ ቁልፍ ሰብሎች አንዱ ነዉ፡፡ በተለይ ደግሞ ነጩ የቦሎቄ ምርት ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ወደ አዉሮፓ ሀገሮች ሲላክ ቀዩ ቦለቄ ወደ ሰሜን ኬኒያ ከሚላኩ የግብርና ምርቶች ዋንኛዉ ነዉ፡፡ ስለዚህ የቦሎቄ ፍላጎት ባሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡ ስለዚህ ነበር የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት ደንብ ቁጥር 178/2010 በሜይ 22 ቀን 2012 እ.ኤ.አ. ያወጣዉ፡፡ በዚህ ደንብ መሰረት ነጭ ቦሎቄ ብቻ ሳይሆን አምራቾቹ ሳይቀሩ በኢትዮጵያ ምርት ገበያን ትኩረት ስበዋል፡፡ በአጠቃላይ የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ ነጋዴዎች ነጭ ቦሎቄን በተለየ ሁኔታ በየአምራች አካባቢዎች በመግዛት ከዚያም ሲያሻቸዉ ለሀገር ዉስጥ ፍጆታ አለያም ለዉጭ ገበያ ለመላክ ወደ ናዝሬት ያጓጉዛሉ፡፡ በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ በአምራቾችና ነጋዴዎች መካከል የሚካሄድ የቦሎቄ ንግድ ልዉዉጥ ይካሄድ የነበረዉ የፀሐይን ቃጠሎና ዝናብን ለመከላከል ምንም ጥላ፣ የጎርፍ መከላከያ ቦይ በሌለበት ክፍት የገበያ ቦታ ላይ ነበር፡፡ በመሆኑም በዚያን ወቅት የቦሎቄ ምርት ጥራቱ መጥፎ ስለነበረ የገበያ ፋሲሊቲን በመገንባት ጥራቱን ማሳደግ ተፈልጓል፡፡

በዚህ ሀሳብ ዙሪያ የጃይካ ጥናት ቡድን የንግድ ልዉዉጥ ሁኔታን ለማሻሻል፣ ጥራት ላለዉ የቦሎቄ ምርት የከተማዉን አስተዳዳር አቅም ለማሳደግና ገበያን ለማስፋፋት ለቦሎቄ አዲስ የገበያ ፋሲሊቲን በሲዳማ ዞን፣ ቦሪቻ ወረዳ በሊላ ከተማ ላይ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 አማካኝነት ገንብቷል፡፡

በዚህ ምክንያት ጣሪያና ኮንክሪት ወለል ያለዉ ፋሲሊቲ ፈቃድ ባላቸዉ የቦሎቄ ነጋዴዎችና በአምራቾች መካከል የሚካሄደዉ የንግድ ልዉዉጥ በከተማዉ ዉስጥ ስርዓት እንዲይዝ አስችሏል፡፡ የስራ አመራር አካላት፣ አርሶአደሮች (አምራቾች)፣ ነጋዴዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በፋሲሊቲዉና በአመራሩ ያላቸዉን ርካታ ገልጸዋል፡፡ ይኸዉ ፋሲሊቲ ካስገኛቸዉ ጥቅሞች ዉስጥ ጥቂቶቹ ከዚህ በታች የቀረቡት ይጠቀሳሉ፡

1) የንግድ ልዉዉጡ በተወሰነ ቦታ ፈቃድ ባላቸዉ ነጋዴዎች ስለሚከናወን ህገወጥ ነጋዴዎች በከፍተኛ ሁኔታ ቁጥራቸዉ ቀንሷል፡፡ ስለዚህ ከአርሶአደሮችና ነጋዴዎች መካከል ተገቢ የንግድ

ልዉዉጥ መካሄድ ተጀምሯል፡፡ ከዚህ በፊት ግን ገበሬዎች አንዳንድ ጊዜ በነጋዴዎች ተገደዉ ምርታቸዉን በርካሽ ዋጋ እንዲሸጡ ይደረጉ ነበር፡፡ ህጋዊ ነጋዴዎች የተመረመረ ሚዛን ስለሚጠቀሙ ከገበሬዎች ጋር ኢ-ፍትሃዊ ልዉዉጥ በጣም ቀንሷል፡፡

2) ግቢዉ ከጣሪያና ወለል በአለው የገበያ ቦታ ስለሆነ የሚከናወነዉ በርካታ የቦሎቄ ምርት ከአፈርና ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር ተቀላቅሎ ይቀርብ የነበረዉ አሁን በመቀነሱ ጥራቱ በሚታይ መልኩ ተሻሽሏል፡፡ በምርቱ ዉስጥ ቀደም ሲል የሚታየዉ አቧራ፣ ጭቃና ሌላ ባዕድ ነገር ስለቀነሰ ጥራት ያለዉ ቦሎቄ ለገበያ መቅረብ ጀምሯል፡፡
3) ከአዲሱ የገበያ ፋሲሊቲ ከነጋዴዎች የሚሰበሰበዉ ግብር ለወረዳዉ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ አስገኝቷል፡፡

በዚህ በቁጥር 15 የፕሮጀክት ዕቅድ በወረዳ ገበያ መሰረተልማት የገበያ ቦታ ማሻሻል ፕሮግራም የቦሎቄ ገበያ መሰረተልማት ማሻሻያ በሌሎች ወረዳዎች እንዲሰራ ታቅዷል፡፡

ድርጊት:

| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ : | የወረዳ አስተዳደር/ የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት: | ሌሎች ለጋሾች : |
|---|---|---|
| 1. ደረጃዉን የጠበቀ ዲዛይን ማቅረብ<br>2. ደረጃዉን የጠበቀ ጨረታ ዶክመንት ማቅረብ<br>3. የዲዛይን ንድፉ እና የጨረታ ሰነድ ለማጠናቀቅ ቴክኒካዊ እገዛ መስጠት<br>4. ረቂቅ የአስተዳደር መመሪያን ጨምሮ በመሰረተልማቱ ስራ አመራር ላይ አዉደ ጥናት ማካሄድ | 1. በነጋዴዎቹ የንግድ ልዉዉጥ መጠን መሰረት የፋሲሊቲዉን ስኬል መወሰን፣<br>2. የታሰበዉን ቦታ የመሬት ገጽ አቀማመጥና ስፋትን አገናዝቦ የፋሲሊቲዉን ንድፍ ማዘጋጀት<br>3. የዲዛይንና የዋጋ ግምት በመከለስ ማጠናቀቅ (በተመረጠ አማካሪ መሀንዲስ የሚሰራ)<br>4. የጨረታ ሰነዶችን ማዘጋጀት<br>5. ማጫረት፣ መገምገምና የጨረታ ዉል መግባት<br>6. ግንባታና የግንባታ ቁጥጥር (በተመረጠ የስራ መሀንዲስ).<br>7. የስራ አመራር ኮሚቴን ማቋቋም<br>8. የስራ አመራር መመሪያን ማዘጋጀት<br>9. መሰረተልማቱን ማስተዳደር | ለስራዉ የሚሰጥ ቴክኒካዊና የፋይናንስ ድጋፍ በወረዳዉና በከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ይሆናል፡፡ |

ግብዓት:

| ክልል/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ: | ግብርና ዕድገት ፕሮግራም: | ሌሎች ለጋሾች : |
|---|---|---|
| 1. በቢሮ ስር ያሉ ሰራተኞችን በስራ ያሰማራል<br>2. በወረዳዉ ስር ያሉ ሰራተኞችን ወደ ስራ ያሰማራል | 1. የፋሲሊቲዉ ግንባታ ወጪ መቻል<br>2. ለዲዛይን ክለሳና ለግንባታ ቁጥጥር ስራ ለአማካሪ መሀንዲስ የሚከፈል ወጪ | የአማካሪ መሐንዲስ ክፍያ እና የሌሎች ተግባራት ወጪ |

የፋሲሊቲዉ ንድፍና ዲዛይን:

<u>የንድፉ ሀሳብ</u>

1. አዲሱ ፋሲሊቲ የሚገነባዉ በነባሩ የገበያ ቦታ ይሆናል፡፡
2. አዲሱ ፋሲሊቲ በነባሩ የገበያ ቦታ ጥግ የሚገነባ ይሆናል፡፡
3. በፋሲሊቲዉ ዙሪያ የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች ይሰራለታል፡፡
4. የፋሲሊቲዉ ሕንፃ፣ የቦታ አቀማማጥና ንድፍ በአንድ ወይም በሁለትን ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

<u>የዲዛይኑ ሀሳብ፡</u>

1. ፋሲሊቲዉ ኮንክሪት ወለል ይኖረዋል፡፡
2. ፋሲሊቲዉ በኮንክሪት ኮለኖችና ቢሞች ተደግፎ የቆመ ጣሪያ ይኖረዋል፡፡
3. ለንግድ ልዉዉጡ ለእያንዳንዱ ነጋዴ የሚቀርብ ቦታ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ ቦታ ሲሆን ይህ ግን

ከንግድ ልዉዉጡ መጠን አንጻር ሊሻሻል ይችላል፡፡
4. ፋሲሊቲዉ በቂ የፍሳሽ መዉረጃና መፀዳጃ ቤት አገልግሎት ይኖረዋል፡፡
5. በተቻለ መጠን ከፋሲሊቲዉ ፊት ለፊት ያለዉ መገበያያ ስፍራ በድንጋይ ንጣፍ መልበስ አለበት፡፡
6. ወደ ፋሲሊቲዉ የሚያስገባ መንገድ መኖር የግድ ይላል፡፡
7. ከመሬቱ ከፍታ አንጻር ደረጃን የጠበቀ የካርታዉ ስዕል እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡

1) ዓይነት A1: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 5 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ አስር የንግድ ቦታዎች
2) ዓይነት A2: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 3 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ አስር የንግድ ቦታዎች
3) ዓይነት A3: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 2 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ አስር የንግድ ቦታዎች
4) ዓይነት A4: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 1 የወለል ደረጃ (ለጥ ያለ)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ አስር የንግድ ቦታዎች
5) ዓይነት B1: መጠን 12ሜ. x 42ሜ.=504 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 3 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ 28 የንግድ ቦታዎች
6) ዓይነት B2: መጠን 12ሜ. x 42ሜ.=504 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 1 የወለል ደረጃ (ለጥ ያለ)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ 28 የንግድ ቦታዎች

ወጪ፡

1. የፋሲሊቲዉ ግንባታ ወጪ
የፋሲሊቲዉ ግንባታ ወጪ የፋሲሊቲዉ ስፋት፣ የመሰረቱ ተዳፋትነት፣ የፋሲሊቲዉ እና የድንጋይ ንጣፍ ዓይነትና ብዛት ከተወሰነ በኋላ ስሌቱ ይታወቃል፡፡
ከጥር 2011 (እ.ኤ.አ) በነበረው የተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር የእያንዳንዱ ዓይነት ግምታዊ ዋጋ ቀጥሎ እንደታየዉ ይቀርባል፡
   1) ዓይነት A1: 340,000 ብር በብሎክ
   2) ዓይነት A2: 290,000 ብር በብሎክ
   3) ዓይነት A3: 280,000 ብር በብሎክ
   4) ዓይነት A4: 260,000 ብር በብሎክ
   5) ዓይነት B1: 670,000 ብር በብሎክ
   6) ዓይነት B2: 620,000 ብር በብሎክ
   7) የፋሲሊቲዉ የድንጋይ ንጣፍ ግንባታ በ40 ሳ.ሜ. ዉፍረት: 150 ብር/ስኩዬር ሜ.
2. የጉልበት ስራ የሚጠይቀዉ ወጪ
   1) ዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥር ስራ ፡ 16,000 በየወሩ ብር x በ5 ወራት= 80,000 ብር
   2) ቴክኒክ አማካሪ ክፍያ ወጪ ፡ $15,000 በየወሩ ዶላር x በ2 ወራት= $30,000 ዶላር
3. የስልጠና ወጪ    5,000 ብር ለአንድ ጊዜ ስልጠና

የጊዜ ሰሌዳ:

ይህ ፕሮጀክት ከግብርና ዕድገት ፕሮጀክት ጋር የሚተባበር እና የነሱን በጀት በመከተል የሚተገበር ነዉ፡፡ ነገር ግን በቀረበዉ ሀሳብ መሰረት የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ቀጥሎ እንደሚዘረዘሩ ዞኖች የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይሆናል፡፡ ይህም ማለት በየዞኑ ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም አንድ ዓመት ይጠይቃል፡፡ የፕሮጀክቱ አካሄድ ሁለት ክፍሎችን ያካትታል፡፡ አንደኛዉ የግንባታዉና አስተዳደር ስልጠና ሲሆን ሌላዉ ደግሞ የልምምድ ጊዜ ነዉ፡፡ ለኮንትራቱ የዝግጅት ስራ 2 ወራት፣ ለግንባታዉ 4 ወራት፣ ለስልጠናዉና ለልምምዱ 5 ወራት እንደሚያስፈልግ ተገምቷል፡፡

| ዞን | ወረዳ | ምዕራፍ | | የአፈጻጸም ዕቅድ (እ.ኤ.አ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | | | | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | | 2017 | | | |
| | | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ወላይታ | ዳሞት ጋሌ | I | ግንባታ | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ሶዶ ዙሪያ | I | ግንባታ | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ሲዳማ | ሎኮ አባያ | I | ግንባታ | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | ■ | | | | | | | | | | | | | |
| ሃዲያ | ምዕራብ ባድዋቾ | I | ግንባታ | | | | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | ■ | | | | | | | | | |
| ስልጤ | አማሮ | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | ■ | ■ | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | ■ | | | | | |
| | ቡርጂ | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | ■ | ■ | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | ■ | | | | | |
| አላባ ልዩ ወረዳ | | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | ■ | ■ | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | ■ | |

አስተያየት:

በዚህ ቁጥር 15 ፕሮጀክት ከቀረቡት ዉስጥ 8ቱ ወረዳዎች የግብርና ዕድገት ፕሮግራም ፕሮጀክት አይሸፍናቸውም፡፡ የእያንዳንዱ የግብርና ዕድገት ፕሮግራም ወረዳ የገበያ ቦታ ግንባታ ማቀዱ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ስለዚህ ፕሮጀክቱ እዉን ለማድረግ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከግብርና ዕድገት ፕሮግራም ጋር የዚህን ፕሮጀክት አስፈላጊነትንና የየግብርና ዕድገት ፕሮግራም ድጋፍ ወሳኝነትን በተመለከቱ በቅርብ መወያየት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህም ሌላ በፕላን፣ ዲዛይን ለዉጥ እና የግንባታ ቁጥጥር ወቅት የቴክኒክ አማካሪ መኖር ወሳኝ ነዉ፡፡ ስለዚህ ከሌሎችም ለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ ይጠበቃል፡፡

እዝል ፡ የፋሲሊቲዉ ብሎኮች አመዳደብ (በቦለቄ ንግድ ገበያ ቦታ)

**ንድፍ ፕላን 1**




ለቦታ አቀማመጥ 1 የፕረጀክት ወጪ (የቴክኒክ ማማከር ስልጠና ወጪ ሳይጨምር)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1) የፋስሊቲ ግንባታ | ዓይነት A1 x 2 = | : | 680,000 ብር |
| 2) የደንጋይ ንጣፍ | 360 $m^2$ = | : | 54,000 ብር |
| 3) ዲዛይንና ቁጥጥር | | : | 80,000 ብር |
| 4) መጠባበቂያ | | : | 86,000 ብር |
| | ድምር | : | 900,000 ብር |

**ንድፍ ፕላን 2**




ለቦታ አቀማመጥ 1 የፕረጀክት ወጪ (የቴክኒክ ማማከር ስልጠና ወጪ ሳይጨምር)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1) የፋስሊቲ ግንባታ | ዓይነት A3 x 2 = | : | 1,020,000 ብር |
| 2) የደንጋይ ንጣፍ | 570 $m^2$ = | : | 85,500 ብር |
| 3) ዲዛይንና ቁጥጥር | | : | 80,000 ብር |
| 4) መጠባበቂያ | | : | 118,500 ብር |
| | ድምር | : | 1,304,000 ብር |

## ፕሮጀክት ቁጥር 16

| የፕሮጀክቱ ርዕስ | የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 የዝንጅብል ምርት መሰረተልማት ማስፋፋት ድጋፍ ፕሮጀክት | | |
|---|---|---|---|
| ስልት | 3: የገበያ ተግባራትን ለማከናወን ዉጤታማ የገበያ መሰረተልማት ማጠናከር<br>3-2: ትኩረት በተደረገባቸዉ አካባቢዎች የወረዳ ገበያ ቦታዎችን መሰረተ ልማት ማሳደግ | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | የወረዳ ገበያ ቦታ ማሻሻያ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | ከ2013 እስከ 2017 እ.ኤ.አ (5 ዓመታት) | | |
| የፕሮጀክት አካባቢ | ሃዳሮ ከተማ (ሃዳሮ ጡንጦ ወረዳ) | | |
| የትኩረት ሰብል / ምርት | ዝንጅብል | | |
| የትኩረት ቡድን | የሃዳሮ ጡንጦ ወረዳ አስተዳደር፣ የሃዳሮ ማዘጋጃ ቤት፣ የዝንጅብል ነጋዴዎች፣ የዝንጅብል አምራቾች | | |
| ፈጻሚዉ ድርጅት | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ<br>የሃዳሮ ጡንጦ ወረዳ አስተዳደር፣<br>የሃዳሮ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | ድጋፍ ሰጪ ድርጅት | የግብርና ዕድገት ፕሮግራም እና ሌሎች ለጋሾች |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች:
በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 መሰረት የከተማዉን ዝንጅብል ንግድ ልዉዉጥ ሁኔታ ለማሻሻል፣ የማስተዳደር አቅምን ለማሳደግ እንዲሁም የዝንጅብል ጥራት ለማሻሻል የጃይካ ጥናት ቡድን በከምባታ ጠምባሮ ዞን ሃዳሮ ጡንጦ ወረዳ ለሃዳሮ ከተማ አዲስ የዝንጅብል ገቤ ፋሲሊቲ ገንብቷል፡፡

በዚህ ምክንያት ጣሪያና ኮንክሪት ወለል ያለዉ ፋሲሊቲ ፈቃድ ባላቸዉ የዝንጅብል ነጋዴዎችና በአምራቾች መካከል የሚካሄደዉ የንግድ ልዉዉጥ በከተማዉ ዉስጥ ስርዓት እንዲይዝ አስችሏል፡፡ የስራ አመራር አካላት፣ አርሶአደሮች (አምራቾች) እና ነጋዴዎች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት በፋሲሊቲዉና በአመራሩ ያላቸዉን ርካታ ገልጸዋል፡፡ ይኸዉ ፋሲሊቲ ካስገኛቸዉ ጥቅሞች ዉስጥ ጥቂቶቹ ከዚህ በታች የቀረቡት ይጠቀሳሉ፡

1) የንግድ ልዉዉጡ በተወሰነ ቦታ ፈቃድ ባላቸዉ ነጋዴዎች ስለሚከናወን ህገወጥ ነጋዴዎች በከፍተኛ ሁኔታ ቁጥራቸዉ ቀንሷል፡፡ ስለዚህ ከአርሶአደሮችና ነጋዴዎች መካከል ተገቢ የንግድ ልዉዉጥ መካሄድ ተጀምሯል፡፡ ከዚህ በፊት ግን ገበሬዎች አንዳንድ ጊዜ ተገደዉ ምርታቸዉን በርካሽ ዋጋ እንዲሸጡ ይደረጉ ነበር፡፡ ህጋዊ ነጋዴዎች በተመረመረ ሚዛን ስለሚጠቀሙ ከገበሬዎች ጋር ኢ-ፍትሃዊ ልዉዉጥ በጣም ቀንሷል፡፡
2) ግዥዉ ከጣሪያና ወለል መሃል ስለሆነ የሚከናወነዉ በርካታ የዝንጅብል ምርት ከአፈርና ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር ተቀላቅሎ ይቀርብ የነበረዉ አሁን በመቀነሱ ጥራቱ በሚታይ መልኩ ተሻሽሏል፡፡ በምርቱ ዉስጥ ቀደም ሲል የሚታየዉ አቧራ፣ ጭቃና ሌላ ባዕድ ነገር ስለቀነሰ ጥራት ያለዉ ዝንጅብል ለገበያ መቅረብ ጀምሯል፡፡
3) ከአዲሱ የገበያ ፋሲሊቲ ከነጋዴዎች የሚሰበሰበዉ ግብር ለወረዳዉ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ አስገኝቷል፡፡

በዚህ በቁጥር 16 ፕሮጀክት የክልል ቢሮ በከተማዉ ዉስጥ አሁን ያለዉን የገበያ ፋሲሊቲ ማኔጅሜንት ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሞች እስካሁን የቀጠሉ መሆን አለመሆናቸዉን መከታተልና ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የፋሲሊቲዉን አመራርንም በሌሎች ወረዳዎች ለሚሰሩ የገበያ ፋሲሊቲዎች አርአያነት ያለዉ እንዲሆን መደገፍ ይኖርበታል፡፡

| ድርጊት: | |
|---|---|
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ :<br>1. ክትትልና የምክር አገልግሎት ለመስጠት በየ3 ወሩ ከወረዳዉና ከከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ጋር መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡<br>2. በወረዳዉ ጥያቄ ተንተርሶ በገበገያዉ ማስፋፊያ ዕቅድ ላይ ምክር ይሰጣል፡፡<br>3. ለሌሎች ወረዳዎችና ማዘጋጃ ቤቶች የህዝብ ግንኙነት በመሆን ያገለግላል፡፡ | የወረዳ አስተዳደር/ የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት:<br>1. የዝንጅብል ምርት ግዥ መጠንን መመዝገብ<br>2. ከክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ጋር በየሁለት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ የሥራ አመራር ስብሰባ ያደርጋል፡፡<br>3. የኤክስቴንሽን ዕቅድ ማዘጋጀት<br>4. ከአርሶአደሮች ጋር ሀሳብ መለዋወጥ<br>5. የአስተዳዳር መመሪያዎችን በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በመከለስ ማሻሻል፡፡ |

| ግብዓት: | |
|---|---|
| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ :<br>1. ሰራተኞችን በስራ ያሰማራል<br>2. በቢሮዉ ተነሳሽነት ስብሰባን ማዘጋጀት | የወረዳ አስተዳደር/ የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት :<br>1. ሰራተኞችን ወደስራ ያሰማራል<br>2. ለክልል ቢሮ ስብሰባ ሰራተኞችን ይመድባል |

ወጪ:

1. በቢሮዉ ሰራተኞች ወደ ሌላ ከተማ የሚደረግ የጉዞ ወጪ (መጓጓዣ እና ዉሎ አበል): 500 ብር/ጊዜ
2. የስብሰባ ወጪ (መጓጓዣ እና ዉሎ አበል): 5,000 ብር ለአንድ ጊዜ ስልጠና

የጊዜ ሰሌዳ:

| አስፈጻሚ አካል | ድርጊት | አፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ (እ.ኤ.አ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | | | | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | | 2017 | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ግብይና ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | መደበኛ ስብሰባ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ | ▽ |
| | የህዝብ ግንኙነት | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ |
| ወረዳ/ ማዘጋጃ ቤት | የንግድ መረጃ መያዝ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ | ━ |
| | የሥራ አመራርር ኮሚቴ ስብሰባ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ |
| | የአርሰአደሮች ድምፅ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ |
| | የሥራ መመሪያ ማሻሻያ | | | | △ | | | | | | | | △ | | | | | | | | △ |

አስተያየት:

በተሻለ አፈጻጸም ለመስራት የክትትል ዉጤቶች በፕሮጀክት ቁጥር 17 ላይ መንፀባረቅ አለባቸዉ፡፡

## ፕሮጀክት ቁጥር 17

| የፕሮጀክቱ ርዕስ | የዝንጅብል ምርት መሰረተልማት ማስፋፋት | | |
|---|---|---|---|
| ስልት | 3: የገበያ ተግባራትን ለማከናወን ዉጤታማ የገበያ መሰረተልማት ማጠናከር<br>3-2: ትኩረት በተደረገባቸዉ አካባቢዎች የወረዳ ገበያ ቦታዎችን መሰረተልማት ማሳደግ | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | የወረዳ ገበያ ቦታ ማሻሻያ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | ከ2013 እስከ 2016 እ.ኤ.አ (4 ዓመታት) | | |
| የፕሮጀክት አካባቢ | ከዚህ በታች ያሉ ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሙከራ ትግበራ ፕሮጅክት ከሸፈናቸው ወረዳዎች ውስጥ የተመረጡ 4 ወረዳዎች<br>(1) ቦሎሶ ሶሬ<br>(2) ቦሎሶ ቦምቤ<br>(3) ኪንዶ ኮይሻ<br>(4) ጠምባሮ | | |
| የትኩረት ሰብል / ምርት | ዝንጅብል | | |
| የትኩረት ቡድን | የወረዳ አስተዳደር፣ የከተማ ማዘጋጃ ቤት፣ የዝንጅብል ነጋዴዎች፣ ዝንጅብል አምራቾች | | |
| ፈጻሚዉ ድርጅት | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ<br>የወረዳ አስተዳደር<br>የከተማ ማዘጋጃ ቤት | ድጋፍ ሰጪ ድርጅት | የግብርና ዕድገት ፕሮገራም እና ሌሎች ለጋሾች |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች:

በሀገራችን ከሚቀርበዉ አጠቃላይ የዝንጅብል ምርት ዉስጥ 99% የሚመረተዉ ከደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል ነዉ፡፡ ዝንጅብል በእርጥቡ ወይም በደረቁ ሊሸጥ የሚችል ሲሆን ለገበሬዎች በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ገንዘብ የሚያስገኝ ሰብል በመሆን ይታወቃል፡፡ በአጠቃላይ በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ በወረዳ ገበያ ቦታዎች ላይ እርጥቡን ዝንጅብል ደላላ ነጋዴዎች በመሰብሰብ አዲስ አበባ ላሉ ተረካቢ ነጋዴዎች ያቀርባሉ፡፡ ነገር ግን የደረቀ ዝንጅብል ሀ) እንደ ሻይ ለመጠቀምና ከቅመም ጋር ለመደባለቅ፣ ለ) ወደ መካከለኛ ምስራቅ ኤክስፖርት ለማድረግ ይሸጣል፡፡ በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ ደረጃ ይህን ቢዝነስ የሚያካሂድ ከፍተኛ ነጋዴ የለም፡፡ ነገር ግን ደላሎች በክፍት የገበያ ቦታዎች ላይ ከፀሐይና ዝንብ የሚከልል ምንም ዓይነት ጥላ እና የፍሳሽ መዉረጃ ቦይ በሌለበት ግዥ ይፈጽማሉ፡፡ ስለዚህ ለክልሉ ዝንጅብል ንግድ የገበያ ፋሲሊቲን በመገንባት ማሻሻል ይጠበቃል፡፡

በዚህ ሀሳብ ዙሪያ የጃይካ ጥናት ቡድን የንግድ ልዉዉጥ ሁኔታን ለማሻሻል፣ ጥራት ላለዉ የዝንጅብል ምርት የከተማዉን አስተዳዳር አቅም ለማሳደግና ገበያን ለማስፋፋት ለዝንጅብል አዲስ የገበያ ፋሲሊቲን በከምባታ ጠምባሮ ዞን፣ ሃዳሮ ጡንጦ ወረዳ በሃዳሮ ከተማ ላይ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 07 አማካኝነት አስገንብቷል፡፡

በዚህ ምክንያት ጣሪያና ኮንክሪት ወለል ያለዉ ፋሲሊቲ ፈቃድ ባላቸዉ የዝንጅብል ነጋዴዎችና በአምራቾች መካከል የሚካሄደዉ የንግድ ልዉዉጥ በከተማዉ ዉስጥ ስርዓት እንዲይዝ አስችሏል፡፡ የስራ አመራር አካላት፣ አርሶአገሮች (አምራቾች) እና ነጋዴዎች እንዲሁም ሌሎአ‹ች ባለድርሻ አካላት በፋሲሊቲዉና በአመራሩ ያላቸዉን ርካታ ገልጸዋል፡፡ ይኸዉ ፋሲሊቲ ካስገኛቸዉ ጥቅሞች ዉስጥ ጥቂቶቹ ከዚህ በታች የቀረቡት ይጠቀሳሉ፡

1) የንግድ ልዉዉጡ በተወሰነ ቦታ ፈቃድ ባላቸዉ ነጋዴዎች ስለሚከናወን ህገወጥ ነጋዴዎች በከፍተኛ ሁኔታ ቁጥራቸዉ ቀንሷል፡፡ ስለዚህ ከገበሬዎችና ነጋዴዎች መካከል ተገቢ የንግድ ልዉዉጥ መካሄድ ተጀምሯል፡፡ ህጋዊ ነጋዴዎች የተመረመረ ሚዛን ስለሚጠቀሙ ከገበሬዎች ጋር ኢ-ፍትሃዊ ልዉዉጥ በጣም ቀንሷል፡፡
2) ግዥዉ ከጣሪያና ወለል መሃል ስለሆነ የሚከናወነዉ በርካታ የዝንጅብል ምርት ከአፈርና ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር ተቀላቅሎ ይቀርብ የነበረዉ አሁን በመቀነሱ ጥራቱ በሚታይ

<table>
<tr><td colspan="3">መልኩ ተሻሽሏል፡፡ በምርቱ ዉስጥ ቀደም ሲል የሚታየዉ አቧራ፣ ጭቃና ሌላ ባዕድ ነገር ስለቀነሰ ጥራት ያለዉ ዝንጅብል ለገበያ መቅረብ ጀምሯል፡፡<br>3) ከአዲሱ የገበያ ፋሲሊቲ ከነጋዴዎች የሚሰበሰበዉ ግብር ለወረዳዉ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ አስገኝቷል፡፡<br><br>በዚህ መሰረት በቁጥር 17 ፕሮጀክት ዕቅድ የዝንጅብል ገበያ መሰረተልማት ማሻሻያ ፕሮግራም በሌሎች ወረዳዎች እንዲሰራ ታቅዷል፡፡</td></tr>
<tr><td colspan="3">ድርጊት:</td></tr>
<tr><td>ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ :<br>1. ደረጃዉን የጠበቀ ዲዛይን ማቅረብ<br>2. ደረጃዉን የጠበቀ የጨረታ ዶክመንት ማቅረብ<br>3. የዲዛይንና የጨረታ ሰነድ ለማጠናቀቅ ቴክኒካዊ እገዛ መስጠት<br>4. ረቂቅ የአስተዳደር መመሪያን ጨምሮ በመሰረተልማቱ ስራ አመራር ላይ አውደ ጥናት ማካሄድ</td><td>የወረዳ አስተዳደር/ የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት:<br>1. በነጋዴዎቹ የንግድ ልዉዉጥ መጠን መሰረት የፋሲሊቲዉን ስኬል መወሰን፣<br>2. የታሰበዉን ቦታ የመሬት ገጽ አቀማመጥና ስኬሉን አገናዝቦ የፋሲሊቲዉን ንድፍ ማዘጋጀት<br>3. የዲዛይኑንና የዋጋ ግምት በመከለስ ማጠናቀቅ (በተመረጠ አማካሪ መሀንዲስ የሚሰራ)<br>4. የጨረታ ሰነዶችን ማዘጋጀት<br>5. ማጫረት፣ መገምገምና የጨረታ ዉል መግባት<br>6. ግንባታና የግንባታ ቁጥጥር (በተመረጠ የስራ መሀንዲስ).<br>7. የስራ አመራር ኮሚቴን ማቋቋም<br>8. የስራ አመራር መመሪያን ማዘጋጀት<br>9. መሰረተልማቱን ማስተዳደር</td><td>ሌሎች ለጋሾች : ለስራዉ የሚሰጥ ቴክኒካዊና የፋይናንስ ድጋፍ በወረዳዉና በከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ይሆናል፡፡</td></tr>
<tr><td colspan="3">ግብአት:</td></tr>
<tr><td>ክልል/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ:<br>1. በቢሮ ስር ያሉ ሰራተኞችን በስራ ያሰማራል<br>2. በወረዳዉ ስር ያሉ ሰራተኞችን በስራ ያሰማራል</td><td>የግብርና ዕድገት ፕሮግራም:<br>1. የፋሲሊቲዉ ግንባታ ወጪ መቻል<br>2. ለዲዛይን ክለሳና ለግንባታ ቁጥጥር ስራ ለአማካሪ መሀንዲስ የሚከፈል ወጪ</td><td>ሌሎች ለጋሾች : የአማካሪ መሐንዲስ ክፍያ እና የሌሎች ተግባራት ወጪ</td></tr>
<tr><td colspan="3">የፋሲሊቲዉ ንድፍና ዲዛይን:<br><br><u>የንድፉ ሀሳብ</u><br>1. አዲሱ ፋሲሊቲ የሚገነባዉ በነባሩ የገበያ ቦታ ይሆናል፡፡<br>2. አዲሱ ፋሲሊቲ በነባሩ የገበያ ቦታ ጥግ የሚገነባ ይሆናል፡፡<br>3. በፋሲሊቲዉ ዙሪያ የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች ይሰራሉታል፡፡<br>4. የፋሲሊቲዉ ህንፃ ንድፈ/ፕላን በአንድ ወይም በሁለትን ተከትሎ ይፈጸማል፡፡<br><br><u>የዲዛይኑ ሀሳብ:</u><br>1. ፋሲሊቲዉ ኮንክሪት ወለል ይኖረዋል፡፡<br>2. ፋሲሊቲዉ በኮንክሪት ኮለኖችና ቢሞች ተደግፎ የቆመ ጣሪያ ይኖረዋል፡፡<br>3. ለንግድ ልዉዉጡ ለእያንዳንዱ የሚቀርብ ቦታ 6ሜ. x 6ሜ. የሆነ ቦታ ሲሆን ይህ ግን ከንግድ ልዉዉጡ መጠን አንጻር ሊሻሻል ይችላል፡፡<br>4. ፋሲሊቲዉ በቂ የፍሳሽ መዉረጃና መፀዳጃ ቤት ይኖረዋል፡፡<br>5. በተቻለ መጠን ከፋሲሊቲዉ ፊት ለፊት ያለዉ መገበያያ ስፍራ የድንጋይ ንጣፍ መልበስ አለበት፡፡<br>6. ወደ ፋሲሊቲዉ የሚያስገባ መንገድ መኖር የግድ ይላል፡፡<br>7. ከመሬቱ ከፍታ አንጻር ደረጃን የጠበቀ የካርታዉ ስዕል እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡</td></tr>
</table>

1) ዓይነት A1: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 5 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 5ሜ. የሆነ 5 የንግድ ቦታዎች
2) ዓይነት A2: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 3 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 6ሜ. የሆነ 5 የንግድ ቦታዎች
3) ዓይነት A3: መጠን 6 ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 2 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 6ሜ. የሆነ 5 የንግድ ቦታዎች
4) ዓይነት A4: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 1 የወለል ደረጃ (ለጥ ያለ)፣ 6ሜ. x 6ሜ. የሆነ 5 የንግድ ቦታዎች
5) ዓይነት B1: መጠን 12ሜ. x 42ሜ.=504 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 3 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 6ሜ. የሆነ 14 የንግድ ቦታዎች
6) ዓይነት B2: መጠን 12ሜ. x 42ሜ.=504 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 1 የወለል ደረጃ (ለጥ ያለ)፣ 6ሜ. x 6ሜ. የሆነ 14 የንግድ ቦታዎች

ወጪ፡

1. የፋሲሊቲዉ ግንባታ ወጪ
   የፋሲሊቲዉ ግንባታ ወጪ የፋሲሊቲዉ ስፋት፣ የመሰረቱ ታዳፋችነት፣ የፋሲሊቲዉ እና የድንጋይ ንጣፍ ዓይነትና ብዛት ከተወሰነ በኋላ ስሌቱ ይታወቃል፡፡
   ጥር 2011 (እ.ኤ.አ) በነበር የተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር የእያንዳንዱ ዓይነት ግምታዊ ዋጋ ቀጥሎ እንደታየዉ ይቀርባል፡
   1) ዓይነት A1: 340,000 ብር በብሎክ
   2) ዓይነት A2: 290,000 ብር በብሎክ
   3) ዓይነት A3: 280,000 ብር በብሎክ
   4) ዓይነት A4: 260,000 ብር በብሎክ
   5) ዓይነት B1: 670,000 ብር በብሎክ
   6) ዓይነት B2: 620,000 ብር በብሎክ
   7) የፋሲሊቲዉ የድንጋይ ንጣፍ ግንባታ በ40 ሳ.ሜ. ዉፍረት: 150 ብር /ስኩዬር ሜ.
2. የጉልበት ስራ የሚጠይቀዉ ዋጋ
   1) ዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥር ስራ : 16,000 በየወሩ ብር x በ5 ወራት = 80,000 ብር
   2) የቴክኒክ አማካሪ ክፍያ ወጪ : 15,000 በየወሩ ዶላር x በ2 ወራት = $30,000 ዶላር
3. የስልጠና ወጪ 5,000 ብር ለአንድ ጊዜ ስልጠና

የጊዜ ሰሌዳ:

ይህ ፕሮጀክት ከግብርና ዕድገት ፕሮግራም ጋር በመተባበርና የነሱን በጀት በመከተል የሚተገበር ነዉ፡፡ ነገር ግን በቀረበዉ ሀሳብ መሰረት የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ቀጥሎ እንደተመለከተው ዞኖች የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይሆናል፡፡ ይህም ማለት በየዞኑ ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም አንድ ዓመት ይጠይቃል፡፡ የፕሮጀክቱ አካሄድ ሁለት ክፍሎችን ያካትታል፡፡ አንደኛዉ የግንባታዉ አስተዳደር ስልጠና ሲሆን ሌላዉ ደግሞ የልምምድ ጊዜ ነዉ፡፡ ለኮንትራቱ የዝግጅት ስራ 2 ወራት፣ ለግንባታዉ 4 ወራት፣ ለስልጠናዉና ለልምምዱ 5 ወራት እንደሚያስፈልግ ተገምቷል፡፡

| ዞን | ወረዳ | ምዕራፍ | | የአፈጻጸም ዕቅድ (እ.ኤ.አ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | | | | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | | 2017 | | | |
| | | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ወለይታ | ቦሎሶ ሶሬ | I | ግንባታ | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ቦሎሶ ቦምቤ | I | ግንባታ | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | ■ | | | | | | | | | | | | | |
| | ኪንዶ ኮይሻ | I | ግንባታ | | | | | | | | | ■ | ■ | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | ■ | | | | | | | | | |
| ከምባታ ጠምባሮ | ጠምባሮ | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | ■ | ■ | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | ■ | | | | | |

አስተያየት:

በዚህ ቁጥር 17 ፕሮጀክት ከቀረቡት ዉስጥ 4ቱ ወረዳዎች በግብርና ዕድገት ፕሮግራም አይሸፈኑም፡፡ የእያንዳንዱ የግብርና ዕድገት ፕሮግራም ወረዳ የገበያ ቦታ ግንባታ ማቀዱ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ስለዚህ ፕሮጀክቱ እዉን ለማድረግ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከግብርና ዕድገት ፕሮግራም ጋር የዚህን ፕሮጀክት አስፈላጊነትንና የየግብርና ዕድገት ፕሮግራም ድጋፍ ወሳኝነትን በተመለከቱ በቅርብ መወያየት ያስፈልጋል፡፡
ከዚህም ሌላ በፕላን፣ ዲዛይን ለዉጥ እና የግንባታ ቁጥጥር ወቅት የቴክኒክ አማካሪ መኖር ወሳኝ ነዉ፡፡ ስለዚህ ከሌሎችም ለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ ይጠበቃል፡፡

እዝል : የዝንጅብል ገበያ ቦታ ፋሲሊቲ ብሎኮች አቀማመጥ

**ምድብ ንድፍ 1**




ለቦታ አቀማመጥ 1 የፕረጀክት ወጪ (የቴክኒክ ማማከር ስልጠና ወጪ ሳይጨምር)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1) የፋስሊቲ ግንባታ | ዓይነት A1 x 2 = | : | 680,000 ብር |
| 2) የደንጋይ ንጣፍ | 360 $m^2$ = | : | 54,000 ብር |
| 3) ዲዛይንና ቁጥጥር | | : | 80,000 ብር |
| 4) መጠባበቂያ | | : | 86,000 ብር |
| | ድምር | : | 900,000 ብር |

**ምድብ ንድፍ 2**




ለቦታ አቀማመጥ 1 የፕረጀክት ወጪ (የቴክኒክ ማማከር ስልጠና ወጪ ሳይጨምር)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1) የፋስሊቲ ግንባታ | ዓይነት A1 x 1 = | : | 340,000 ብር |
| 2) የፋስሊቲ ግንባታ | ዓይነት B2 x 1 = | : | 670,000 ብር |
| 3) የደንጋይ ንጣፍ | 684 $m^2$ = | : | 102,600 ብር |
| 4) ዲዛይንና ቁጥጥር | | : | 80,000 ብር |
| 5) መጠባበቂያ | | : | 127,400 ብር |
| | ድምር | : | 1,320,000 ብር |

## የፕሮጀክት ቁጥር 18

| የፕሮጀክቱ ርዕስ | ለገጠር ግብርና ምርቶች የገበያ መሰረተልማት ማስፋፋት | | |
|---|---|---|---|
| ስልት | 3: የገበያ ተግባራትን ለማከናወን ዉጤታማ የገበያ መሰረተልማት ማጠናከር<br>3-2: በተተኮሩ አካባቢዎች የወረዳ ገበያ ቦታዎች ላይ የገበያ መሰረተ ልማትን ማሻሻል | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | የወረዳ ገበያ ቦታ ማሻሻያ ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | 2013-2017 እ.ኤ.አ (5 ዓመታት) | | |
| የፕሮጀክት አካባቢ | ከግብርና ዕድገት ፕሮግራም 19 ወረዳዎች ዉስጥ የፋሲሊቲ ግንባታ በ2012 (እ.ኤ.አ) የተከናወነባቸዉ 6ቱ ወረዳዎች ሲቀሩ ቀጥሎ ያሉ 13 ወረዳዎች፡<br>(1) በሲዳማ ዞን ወንዶ ገነት<br>(2) በሲዳማ ዞን መልጋ<br>(3) በሲዳማ ዞን ገሬቼ<br>(4) በዳዉሮ ዞን ኢሰራ<br>(5) በጉራጌ ዞን እነሙር<br>(6) በጉራጌ ዞን እንደጋኝ<br>(7) በስልጤ ዞን ምስራቅ አዘርነት<br>(8) በቤንች ማጂ ዞን ደቡብ ቤንች<br>(9) በደቡብ ኦሞ ዞን ደቡብ አሪ<br>(10) በደቡብ ኦሞ ዞን ሰሜን አሪ<br>(11) በከፋ ዞን ጨና<br>(12) የም ልዩ ወረዳ<br>(13) ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | | |
| የተተኮረ እህል / ምርት | ከየወረዳዉ ያሉ ተፈላጊ ገቢ የሚያስገኙ ሰብሎች/ምርቶች | | |
| የትኩረት ቡድን | የወረዳ አስተዳደር፣ የከተማ ማዘጋጃ ቤት፣ ነጋዴዎች፣<br>የተተኮሩ ሰብሎች አምራች አርሶአደሮች | | |
| ፈጻሚ አካል | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ፣<br>የወረዳ አስተዳደር፣<br>የከተማ ማዘጋጃ ቤት | ደጋፊ አካል | የግብርና ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች ለጋሾች |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች:

እ.ኤ.አ በ2010 (እ.ኤ.አ) በዓለም ባንክ ድጋፍ የግብርና ልማት ፕሮግራም ሶስት ዋና የሥራ ክፍሎች ያሉት አዲስ ፕሮግራም አስጀመረ፡፡ የገጠር መሰረተልማት ማስፋፊያ ከሶስቱም ክፍሎች አንዱ ሆኖ ዓላማዉም ለክልላዊ ልማት የተለያዩ ፋሲሊቲዎችን መገንባት ነዉ፡፡ የገበያ ፋሲሊቲዎች ግንባታ ደግሞ በዚህ ዉስጥ ቁልፍ ትኩረት የተሰጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ የግብርና ልማት ፕሮግራም ለግንባታዉ ወጪ ከመቻል ባሻገር ሌሎችን ቴክኒካዊና የአመራር ድጋፎች አያደርግም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የጃይካ ጥናት ቡድን ደግሞ የንግድን ስነ ምህዳር ለማሻሻል፣ ለጥራት መሻሻል እና ለገበያ መስፋፋት የፋሲሊቲዎችን አስተዳዳር ለማፋጠን የዝንጅብልና የቦሎቄ የገበያ ፋሲሊቲዎችን እንደ ናሙና ያስገነባል፡፡

በዚህ መሰረት ተገቢ የገበያ ፋሲሊቲ አቅርቦት፣ ፈቃድ ባላቸዉ ነጋዴዎች የሚካሄድ ፍትሃዊ ንግድ እዉን ስለሆነ በባለድርሻ አካላት ከፍተኛ አድናቆት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ ዋናዎቹ ዉጤቶችም፡

1) የንግድ ልዉዉጡ በተወሰነ ቦታ ፈቃድ ባላቸዉ ነጋዴዎች ስለሚከናወን ህገወጥ ነጋዴዎች በከፍተኛ ሁኔታ ቁጥራቸዉ ቀንሷል፡፡ ስለዚህ ከገበሬዎችና ነጋዴዎች መካከል ተገቢ የንግድ ልዉዉጥ መካሄድ ተጀምሯል፡፡ ህጋዊ ነጋዴዎች በተመረመረ ሚዛን ስለሚጠቀሙ ከገበሬዎች ጋር ኢ-ፍትሃዊ ልዉዉጥ በጣም ቀንሷል፡፡

2) ግዥዉ ከጣሪያና ወለል መሃል ስለሆነ የሚከናወነዉ ጥራቱ በሚታይ መልኩ ተሻሽሏል፡፡
3) ከአዲሱ የገበያ ፋሲሊቲ ከነጋዴዎች የሚሰበሰበዉ ግብር ለወረዳዉ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ አስገኝቷል፡፡

በዚህ መሰረት የፕሮጀክት ዕቅድ ቁጥር 15 እና 17 የቦሎቄና የዝንጅብል የገበያ መሰረተልማት ማስፋፊያ ልማት በማስተር ፕላን ፕሮግራም ተይዟል፡፡ በዚህ ፕሮጀክት ፕላን ቁጥር 18፡ ለገጠር ግብርና ምርቶች የገበያ መሰረተልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ሀሳብ ሲቀርብ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮም የግብርና ዕድገት ፕሮግራም ለገበያ ፋሲሊቲ ግንባታ ቴክኒካዊ እና የአመራር ድጋፍ እንደሚሰጥ ይጠበቃል፡፡

ድርጊት:

| ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ : | የወረዳ አስተዳደር/ የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት: | ሌሎች ለጋሾች : |
|---|---|---|
| 1. ደረጃዉን የጠበቀ ዲዛይን ማቅረብ<br>2. ደረጃዉን የጠበቀ ጨረታ ዶክመንት ማቅረብ<br>3. የዲዛይንና የጨረታ ሰነድ ለማጠናቀቅ ቴክኒካዊ እገዛ መስጠት<br>4. ረቂቅ የአስተዳደር መመሪያን ጨምሮ በመሰረተልማቱ ስራ አመራር ላይ አዉደጥናት ማካሄድ | 1. ለገበያ ፋሲሊቲ የተተኮረዉን የግብርና ምርት መወሰን<br>2. በነጋዴዎቹ የንግድ ልዉዉጥ መጠን መሰረት የፋሲሊቲዉን መጠን መወሰ<br>3. የታሰበዉን ቦታ የመሬት ገጽ አቀማመጥና ስፋትን አገናዝቦ የፋሲሊቲዉን ንድፍ ማዘጋጀት<br>4. የዲዛይኑንና የዋጋ ግምት በመከለስ ማጠናቀቅ (በተመረጠ አማካሪ መሀንዲስ የሚሰራ)<br>5. የጨረታ ሰነዶችን ማዘጋጀት<br>6. ማጫረት፣ መገምገምና የጨረታ ዉል መግባት<br>7. ግንባታና የግንባታ ቁጥጥር (በተመረጠ የስራ መሀንዲስ).<br>8. የስራ አመራር ኮሚቴን ማቋቋም<br>9. የስራ አመራር መመሪያን ማዘጋጀት<br>10. መሰረተልማቱን ማስተዳደር | ለስራዉ የሚሰጥ ቴክኒካዊና የፋይናንስ ድጋፍ በወረዳዉና በከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ይሆናል፡፡ |

ግብአት

| ክልል/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ: | ግብርና ዕድገት ፕሮግራም : | ሌሎች ለጋሾች: |
|---|---|---|
| 1. በቢሮ ስር ያሉ ሰራተኞችን በስራ ያሰማራል<br>2. በወረዳዉ ስር ያሉ ሰራተኞችን በስራ ያሰማራል | 1. የፋሲሊቲዉ ግንባታ ወጪ መቻል<br>2. ለዲዛይን ክለሳና ለግንባታ ቁጥጥር ስራ ለአማካሪ መሀንዲስ የሚከፈል ወጪ | የአማካሪ መሐንዲስ ክፍያና የሌሎች ተግባራት ወጪ |

የፋሲሊቲዉ ንድፍና ዲዛይን:

<u>የንድፉ ሀሳብ</u>

1. አዲሱ ፋሲሊቲ የሚገነባዉ በነባሩ የገበያ ቦታ ይሆናል፡፡
2. አዲሱ ፋሲሊቲ በነባሩ የገበያ ቦታ ጥግ የሚገነባ ይሆናል፡፡
3. በፋሲሊቲዉ ዙሪያ የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች ይሰራለታል፡፡
4. የፋሲሊቲዉ ክፍሎች የንድፍ ፕላን አንድ ወይም ሁለትን ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

<u>የዲዛይኑ ሀሳብ፡</u>

1. ፋሲሊቲዉ ኮንክሪት ወለል ይኖረዋል፡፡
2. ፋሲሊቲዉ በኮንክሪት ኮለኖችና ቢሞች ተደግፎ የቆመ ጣሪያ ይኖረዋል፡፡

3. ለንግድ ልዉዉጡ ለእያንዳንዱ የሚቀርብ ቦታ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ ቦታ ሲሆን ይህ ግን ከንግድ ልዉዉጡ መጠን አንጻር ሊሻሻል ይችላል፡፡
4. ፋሲሊቲዉ በቂ የፍሳሽ መዉረጃና የመፀዳጃ ቤት አገልግሎት ይኖረዋል፡፡
5. በተቻለ መጠን ከፋሲሊቲዉ ፊት ለፊት ያለዉ መገበያያ ስፍራ የድንጋይ ንጣፍ መልበስ አለበት፡፡
6. ወደ ፋሲሊቲዉ የሚያስገባ መንገድ መኖር የግድ ይላል፡፡
7. ከመሬቱ ከፍታ አንጻር ደረጃን የጠበቀ የካርታዉ ስዕል እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡

**Layout Plan**




1) ዓይነት A1: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 5 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ 10 የንግድ ቦታዎች
2) ዓይነት A2: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 3 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ 10 የንግድ ቦታዎች
3) ዓይነት A3: መጠን 6 ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 2 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ 10 የንግድ ቦታዎች
4) ዓይነት A4: መጠን 6ሜ. x 30ሜ.=180 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 1 የወለል ደረጃ (ለጥ ያለ)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ 10 የንግድ ቦታዎች
5) ዓይነት B1: መጠን 12ሜ. x 42ሜ.=504 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 3 የወለል ደረጃዎች (ደረጃዎች)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ 28 የንግድ ቦታዎች
6) ዓይነት B2: መጠን 12ሜ. x 42ሜ.=504 ስኩየር ሜ.፣ ከፍታ=3.5ሜ፣ 1 የወለል ደረጃ (ለጥ ያለ)፣ 6ሜ. x 3ሜ. የሆነ 28የንግድ ቦታዎች

ወጪ:

1. የፋሲሊቲዉ ግንባታ ወጪ

የፋሲሊቲዉ ግንባታ ወጪ የፋሲሊቲዉ ስፋት፣ የመሰረቱ ተዳፋትነት፣ የፋሲሊቲዉ እና የድንጋይ ንጣፍ ዓይነትና ብዛት ከተወሰነ በኋላ ስሌቱ ይታወቃል፡፡
ጥር 2011 (እ.ኤ.አ) የተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር የእያንዳንዱ ዓይነት ግምታዊ ዋጋ ቀጥሎ እንደታየዉ ይቀርባል:

1) ዓይነት A1: 340,000 ብር በብሎክ
2) ዓይነት A2: 290,000 ብር በብሎክ
3) ዓይነት A3: 280,000 ብር በብሎክ
4) ዓይነት A4: 260,000 ብር በብሎክ
5) ዓይነት B1: 670,000 ብር በብሎክ
6) ዓይነት B2: 620,000 ብር በብሎክ
7) የፋሲሊቲዉ የድንጋይ ማጠናከሪያ ግንባታ በ40 ሳ.ሜ. ዉፍረት: 150 ብር /ስኩዩር ሜ.

2. የጉልበት ስራ የሚጠይቀዉ ዋጋ
   1) ዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥር ስራ : 16,000 በየወሩ ብር x በ5 ወራት = 80,000 ብር
   2) የቴክኒክ አማካሪ ክፍያ ወጪ : 15,000 በየወሩ ዶላር x በ2 ወራት = $30,000 ዶላር

3. የስልጠና ወጪ 5,000 ብር ለአንድ ጊዜ ስልጠና

* ከላይ በተቀመጠው አቀማማጥ መሠረት የሚገነባው የገበያ ማዕከል (የቴክንክ አማካሪና ስልጠና ወጪን ሳያካትት)

a. የፋሲሊቲ ግንባታ ዓይነት A1 x 2 = : 680,000 ብር
b. የድንጋይ ንጣፍ $360\ m^2$ = : 54,000 ብር
c. የዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር : 80,000 ብር
d. መጠባበቂያ : 86,000 ብር
ድምር : 900,000 ብር

የጊዜ ሰሌዳ:

ይህ ፕሮጀክት ከግብርና ዕድገት ፕሮግራም ጋር በመተባባር የሚፈጸም ሲሆን የነሱን በጀት በመከተል ይተገበራል፡፡ ነገር ግን በቀረበዉ ሀሳብ መሰረት የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ቀጥሎ በመለከተው ዞኖች የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይሆናል፡፡ የፕሮጀክቱ አካሄድ ሁለት ክፍሎችን ያካትታል፡፡ አንደኛው የግንባታዉ አስተዳደር ስልጠና ሲሆን ሌላዉ ደግሞ የልምምድ ጊዜ ነዉ፡፡ ለኮንትራቱ የዝግጅት ስራ 2 ወራት፣ ለግንባታዉ 4 ወራት፣ ለስልጠናዉና ለልምምዱ 5 ወራት እንደሚያስፈልግ ተገምቷል፡፡

| ዞን | ወረዳ | ምዕራፍ | | የአፈጻጸም ዕቅድ (እ.ኤ.አ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | | | | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | | 2017 | | | |
| | | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ሲዳማ | ወንዶ ገነት | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | መልጌ | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ገርቼ | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ዳውሮ | እሰራ | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ጉራጌ | እነሞር እኒር | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | እነንደገኝ | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ስልጤ | ምስራቅ አዝርነት | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ቤንች ማጂ | ደቡብ ቤንች | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ደቡብ ኦሞ | ደቡብ አሪ | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ሰሜን አሪ | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ከፋ | ጨና | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የም ልዩ ወረዳ | | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | | I | ግንባታ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | II | አስተዳደር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

አስተያየት:

የእያንዳንዱ የግብርና ዕድገት ፕሮግራም ወረዳ የገበያ ቦታ ግንባታ ማቀዱ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ስለዚህ ፕሮጀክቱ እዉን ለማድረግ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከግብርና ዕድገት ፕሮግራም ጋር የዚህን ፕሮጀክት አስፈላጊነትንና የግብርና ዕድገት ፕሮግራም ድጋፍ ወሳኝነትን በተመለከቱ በቅርብ መወያየት ያስፈልጋል፡፡

## የፕሮጀክት ቁጥር 19

| የፕሮጀክቱ ርዕስ | ደረጃዉን የጠበቀ የግብርና መጋዘን ማስፋፋት | | |
|---|---|---|---|
| ስልት | 3: የገበያ ተግባራትን ለማከናወን ዉጤታማ የገበያ መሰረተልማት ማጠናከር<br>3-2: አዲሱን የግብርና መጋዘን ግንባታና ለዉጤታማ አጠቃቀም ነባሩን መጋዘን ማሻሻል፡፡ | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | የግብርና መጋዘን ግንባታና ነባሩን መጋዘን ማሻሻል | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | 2013-2017 እ.ኤ.አ (5 ዓመታት) | | |
| ፕሮጀክት አካባቢ | 6 ዞኖች (ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ከምባታጠንባሮ፣ ወላይታ፣ ሃዲያ፣ ሲዳማ) እና አላባ ልዩ ወረዳ | | |
| የትኩረት እህል / ምርት | የእህል ምርትና የቅባት እህሎች | | |
| የትኩረት ቡድን | ማዘጋጃ ቤቶች፣ የህብረት ስራ ዩኒየኖች፣ መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት | | |
| ፈጻሚ ድርጅት | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ፣ ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ፣ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ድጋፍ ሰጪ ድርጅት | ግብርና ዕድገት ፕሮግራም ወይም ሌሎች |

*መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች*:

የግብርና መጋዘኖች በአጠቃላይ በሀገራችን በመንግስት ድርጅቶች፣ በህብረት ስራ ማህበራት እና በግሉ ሴክተር አመራር ስር ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ በመጋዘኑ ዉስጥ መተላለፊያ መስመር፣ በቂ ስፋት ያለዉ መዝጊያና የጥራት ቁጥጥር እንደ የአየር ማስገቢያና ፀረ-ተባይ መከላከያ የላቸውም፡፡ ከዚህም ሌላ የመጋዘኖቹን ግንባታ፣ የተፈለገዉን መጠንና ዓላማ የሚያሳይ ግልጽ የሆነ መመሪያም አለም፡፡ አብዛኛዎቹም ደግሞ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጡ የተሰሩም አይደሉም፡፡ ስለዚህ እነዚህ መጋዘኖች ተገቢ መሻሻልና መታደስ ያስፈልጋቸዋል፡፡ አንዳንድ መጋዘኖች ጥራጥሬን/ የቅባት እህሎችን ከዘር ጋር ወይም ማዳበሪያንና ኬሚካሎችን ምንም ክፍፍል ሳያበጁ በተመሳሳይ ክፍል ያከማቻሉ፡፡

በዚህ ሀሳብ ዙሪያ የጀይካ ጥናት ቡድን ዉጤታማ የግብርና ግብይት ስርዓትን ለማሻሻልና የክምችት ብክነትን ለማስቀረት በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 08 እንደተሰራዉ ዓይነት ቀልጣፋና ደረጃዉን የጠበቀ መጋዘን መገንባት አለበት፡፡ ደረጃዉም ለህብረት ስራ ዩኒየን አገልግሎት 500 ቶን መያዝ የሚችል ሆኖ የዩኒየኑ አካላት አያያዙንና አስተዳደሩን በተመለከተ ተገቢ ስልጠና ሊሰጣቸዉ ይገባል፡፡

የፕሮጀክቱ ፕላን ለግብርና ምርቶች ደረጃዉን የጠበቀ መጋዘን ለማስፋፋት አልሞ ባለ 500 ቶን እና ባለ 1000 ቶን ደረጃን የጠበቀ ዲዛይን፣ የተቋራጭ አመራረጥ እና ለአዲሱ መጋዘን ግንባታ የሚያግዙ ሌሎች ቴክኒካዊ ምክሮች ያቀርባል፡፡

ትኩረቱ በ6 ዞኖች ማለትም (ጉራጌ፣ ስልጤ፣ በከምባታ ጠምባሮ፣ ወላይታ፣ ሃዲያና ሲዳማ) እንዲሁም አላባ ልዩ ወረዳ በዓለም ምግብ ፕሮግራም/ግዢ ለዕድገት የታቀፉ ዩኒየኖች መካከል ነዉ፡፡

የትኩረት ቡድኖችም አዲሱን መጋዘን ለግብርና ምርቶቻቸዉ ለመገንባት ፍላጎት ያላቸዉ ማዘጋጃ ቤቶች፣ የህብረት ስራ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ናቸዉ፡፡ ትኩረት የተደረገባቸዉ ዞኖች ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ አዲሱን መጋዘን ለማስገንባት ፍላጎት ያለዉን አካል ለማግኘት በዓመት አንድ ጊዜ ኮንፈረንስ ይጠራል፡፡ የዲዛይንና ቁጥጥር ስራ ወጪን ጨምሮ የግንባታ ወጪ በመጋዘኑ ባለቤት ድርጅት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ ቢሮዉ ግን ለፋይናንስና ግዥ አፈጻጸምን በተመለከተ እገዛ ያደርጋል፡፡

ድርጊት:

ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ :

1. በፕሮጀክት ፕላን ተግባራት ላይ ስብሰባ ማድረግ/ በዞን ደረጃ ቦታ ለመምረጥ
2. ከለጋሾች የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ መደገፍ
3. የዲዛይን ስዕልና የጨረታ ሰነዶችን ማቅረብ
4. በዲዛይን ማሻሻልና ጨረታ ማስፈፀም ዙሪያ ድጋፍ ማድረግ

የትኩረት ቡድኖች:

1. የግንባታ በጀት ለማግኘት/ የድጋፍ ጥያቄ ማመልከቻ ማቅረብ
2. ዲዛይንና የዋጋ ግምት ለማጠናቀቅ
3. ለግንባታ ቁጥጥር ስራ አማካሪ ለማግኘት
4. የተገነባዉን መጋዘን ማስተዳደር

ግብአት:

ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ:

1. በቢሮ ስር ያሉ ሰራተኞችን በስራ ያሰማራል
2. ለትኩረት ቡድኖች ቴክኒካዊ ምክር መስጠት

የትኩረት ቡድኖች:

1. የግንባታዉ ፈንድ
2. ለዲዛይን ማሻሻልና ግንባታ ቁጥጥር አማካሪ መሀንዲስ መቅጠር

ወጪ:

* የፕሮጀክቱ ወጪ የተገመተዉ በዓመቱ ዉስጥ አንድ ወይም ሁለት መጋዘን እንደሚገነባ ታሳቢ በማድረግ ነዉ፡፡

የቢሮ ድጋፍ ተግባራት ወጪዎች፡

የመጓጓዣና የዉሎ አበል ወጪ: 64,000/ዓመት x 5 ዓመታት

(ዝርዝር)

* መጓጓዣ ወጪ ለ2 ቀናት ጉዞ 340 x በዓመት 12 ጊዜ = በዓመት 4,080 ብር

* መጓጓዣ (ነዳጅ) በ5,000/ጊዜ x በዓመት 12 ጊዜ በዓመት = በዓመት 60,000 ብር

| | |
|---|---|
| ንዑስ ድምር | : 320,000 ብር |
| መጠባበቂያ (10%) | : 32,000 ብር |
| ጠቅላላ ድምር | : 352,000 ብር |

የጊዜ ሰሌዳ:

መጋዘን ለማስገንባት የቀረበዉ ጥያቄ ባሁኑ ጊዜ ዉሳኔ ገና ያላገኘ ስለሆነ ዝርዝር የአፈጻጸም ጊዜ ሰሌዳን ለማሳየት አሁን አይቻልም፡፡ የታሰቡ የመጋዘን ባለቤቶችን ማወቅ ሲቻል በግልጽ የሚታይና ትክክለኛዉን የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ለግንባታዉ ታሳቢ የተደረገዉ ጊዜ2 ወር ለዝግጅት እና 4 ወር ለግንባታ ይሆናል፡፡

| አስፈጻሚ አካል | ድርጊት | አፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ (እ.ኤ.አ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | | | | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | | 2017 | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ግብይና ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | ከዞን ጋር መደበኛ ስብሰባ ማካሄድ/ በጀት ከለጋሽ አካል ማግኘት | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ |
| ዞን | ከዩየንና ሕ/ሥራ ማህበር ጋር ማካሄድ/ መጋዘንባለቤት መምረጥ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ | ■ ■ |

የግንባታዉ ስራ የሚጠይቀዉ ወጪ ማገናዘቢያ:

ለግንባታዉ የሚያስፈልግ ገንዘብ በመጋዘኑ ባለቤት ወገን (ማዘጋጃ ቤት፣ ህብረት ስራ ዩኒየን) ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡ ይኸዉ ወጪ እንደየመጋዘኖቹ መጠን ልዩነት የተለያየ ይሆናል፡፡

ቀጥሎ የሚቀርቡ አሀዝ በ2011 (እ.ኤ.አ) ባለዉ የዋጋ ሁኔታ መሰረት ለባለ 500 እና ባለ

1000 ቶን መጋዘን የተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር የተገመተ የግንባታ ወጪን የሚገልጽ ነዉ፡፡

1) የባለ 500 ቶን ደረጃ መጋዘን ግንባታ ወጪ
መጠኑ ቁመት x መሰረት x ከፍታ = 24ሜ. x 11ሜ. x 4.5ሜ. (264 ካሬ ሜ.)፣ ከ2 ተንሸራታች በሮችና የአየር ማስገቢያ መስኮቶች ጋር፡፡
በኮንክሪት ምሰሶዎችና ቢሞች የተጠናከረ ግድግዳዉ ብሎኬት የሆነና በባለብረት ወራጅ ጣሪያዉ ቆርቆሮ የሆነ ባለ አንድ ወለል (ፎቅ የሌለዉ)፡፡

ግምታዊ ዋጋ:

| | | |
|---|---|---|
| - መጋዘን | : | 530,000 ብር |
| - ዲዛይንና ግንባታ | : | 50,000 ብር |
| - መጠባበቂያ | : | 50,000 ብር |
| ድምር | : | 630,000 ብር |

2) የባለ 1000 ቶን ደረጃ መጋዘን ግንባታ ወጪ:
መጠኑ ቁመት x መሰረት x ከፍታ = 36ሜ x 11ሜ x 5.5ሜ (396ካሬ ሜ.), ከ2 ተንሸራታች በሮችና የአየር ማስገቢያ መስኮቶች ጋር፡፡
በኮንክሪት ምሰሶዎችና ቢሞች የተጠናከረ ግድግዳዉ ብሎኬት የሆነና በባለብረት ወራጅ ጣሪያዉ ቆርቆሮ የሆነ ባለ አንድ ወለል (ፎቅ የሌለዉ)፡፡

ግምታዊ ዋጋ:

| | | |
|---|---|---|
| - መጋዘን | : | 720,000 ብር |
| - ዲዛይንና ግንባታ | : | 50,000 ብር |
| - መጠባበቂያ | : | 60,000 ብር |
| ድምር | : | 830,000 ብር |

## ፕሮጀክት ቁጥር 20

| የፕሮጀክቱ ርዕስ | ነባር የግብርና ምርት መጋዘኖችን ማሻሻል | | |
|---|---|---|---|
| ስልት | 3: የገበያ ተግባራትን ለማከናወን ዉጤታማ የገበያ መሰረተልማት ማጠናከር<br>3-4: ለዉጤታማ አጠቃቀም አዲስ የግብርና ምርት ማከማቻ መጋዘኖችና ነባሮችን የማሻሻል ስራ መስራት | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | የግብርና መጋዘኖች ግንባታና ነባሮችን መጋዘኖች የማሻሻል ፕሮግራም | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | 2014-2017 እ.ኤ.አ (4 ዓመታት) | | |
| ፕሮጀክት አካባቢ | ወላይታ ዞን (6 ወረዳዎች), ሃዲያ ዞን (3 ወረዳዎች),<br>ከምባታ ጠምባሮ ዞን (1 ወረዳ), ጉራጌ ዞን (6 ወረዳዎች),<br>ስልጤ ዞን (3 ወረዳዎች), አላባ ልዩ ወረዳ | | |
| የትኩረት እህል / ምርት | የሰብል እህሎችና የቅባት እህሎች | | |
| የትኩረት ቡድን | ካሉት 65 መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ዉስጥ የራሳቸዉ መጋዘን ያላቸዉ እና ለፕሮጀክት ቁጥር 7 ትኩረት የሆኑ | | |
| ፈጻሚ ድርጅት | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ፣<br>ዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪ፣<br>ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | ድጋፍ ሰጪ ድርጅት | |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎቹ:

አብዛኛዎቹ የመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት መጋዘኖች ከእንጨትና ከጭቃ የተሰሩ ባለ አንድ በር መጋዘኖች ስለሆኑ ለእህል ማከማቻነት ተገቢ አይደሉም፡፡ የአየርና የፀሐይ ማስገቢያ ክፍተቶች የሉአቸዉም፡፡ የማከማቸት አቅማቸዉም በጣም ዉሱን ነዉ፡፡ የራሳቸዉ የግብርና ምርት መጋዘን የሌላቸዉ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ከማዘጋጃ ቤቶች የሚከራዩ ቢሆንም እነዚህ መጋዘኖች ከመጀመሪዉ ለመጋዘንነት ዓላማ የተሰሩ ቤቶች አይደሉም፡፡ ስለዚህ ለግብርና ምርት መጋዘንነት እንዲያገለግሉ የሚስችል ተገቢ መሰረት የላቸዉም፡፡ ለግብርና ምርቶች መጋዘን ግንባታ ብዙ ትኩረት የሚያሻቸዉ ጉዳዮች ተያይዘዉ መቅረብ ያስፈልጋል፡፡

በመጋዘኖች ተገቢ አመራርና አስተዳደር የህብረት ስራ ማህበራት አባላትና ሰራተኞች አሁን ባሉት ጉዳዮችና ችግሮች ዙሪያ ግንዛቤ አግኝተዉ በክምችት ወቅት የሚያጋጥመዉን ብክነት በመቀነስ ጥራትን ለማሻሻል የሚያስችል ቴክኒካዊ ስልጠና በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት ወቅት ተሰጥቷል፡፡ የመጋዘኖች እድሳትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ የተነሱበት ከላይ የተጠቀሰዉ ስልጠና ከተሰጠ በኂላ አነስተኛ ቁጥር ያላቸዉ በመጋዘን አያያዝ የሰለጠኑ የህብረት ስራ ማህበራት የተሻሻለ መጋዘን አስተዳደርና አያያዝ ስራ ከማህበራቸዉ አንጻር የተጀመረ መሆኑን ተረድተዋል፡፡ የፕሮጀክት ቁጥር 7 ዕቅድ ዋና ተግባሩ በሙከራ ፕሮጀክቱ ስልጠና ላልተሰጣቸዉ ለ65 መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት የመጋዘን አስተዳደርና እድሳት ስልጠናን መስጠት ነዉ፡፡ ይህ ፕሮጀክት በፕሮጀክት ቁጥር 7 ተሳታፊ የሆኑና ለግንባታ የሚሆኑ መሳሪያዎች የተሰጣቸዉ መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራትን በገንዘብም ይደግፋል፡፡

በ65ቱ የህብረት ስራ ማህበራት ጥቅም ላይ የሚዉሉ መጋዘኖች ዝርዝር ገና አልተጨበጠም፡፡ በመሆኑም የወረዳ ጽ/ቤት ሰራተኞች የመሰረታዊ ማህበራት መጋዘን ግንባታን ጉዳይ በተመለከተ እና ከአመልካቾች መካከል መርጦ በማቅረብ የራሳቸዉን ሁኔታ ማረጋገጫ መስጠት አለባቸዉ፡፡ በዚህም መሰረት 26 መሰረታዊ ማህበራት በፕሮጀክቱ ትኩረት ይሰጥባቸዋል፡፡ ይህም ቁጥር የተወሰነዉ ከአጠቃላዩ 65 ህብረት ስራ ማህበራት ዉስጥ የራሳቸዉ መጋዘን ያላቸዉን ከመቶ 40 ያህሉን መሰረታዊ ማህበራት ለመድረስ ያስችላል፡፡

የዕድሳቱ ስራ ይዘቱና ዓላማዉ ከዚህ በታች እንደሚቀርበዉ ይሆናል:

- ተጨማሪ የመዝጊያ በር ስራ: ለማስገቢያና እና ማዉጫ በሮች ቀድሞ ያስገባዉን ክምችት ቀድሞ ለማስወጣት ለሚል የስራ ፍሰት እንዲያግዝ መክፈት ያስፈልጋል፡፡ ቀድሞ የነበረዉ መዝጊያ

| |
|---|
| እንዳለ ሆኖ አዲስ (መጠኑ 2ሜ. x 2ሜ. ቁመት ያላቸዉ በ2 በኩል ወደ ዉጭ ሊያስከፍት የሚችል) ይጨመራል፡፡<br>- የአየር ማስገቢያ ክፍተት: ከእንጨት በጥልፍልፍ ተሰርቶ የአየር ማስገቢያ ባልተከፈተለት ግድግዳ የላይኛዉ ክፍል ከፍቶ የማስገባት፡፡ ጥቅሙ ለመጋዘኑ በተፈለገዉ መጠን ሙቀትም ሆነ እርጥበት ለማስገባት እና ከዉጭ ሊገባ ከሚችል ተባይ ተከላክሎ እህሉ በክምችት ወቅት ጥራቱን ጠብቆ እንዲቆይ ለማስቻል ነዉ፡፡ የአየር ማስገቢያ ክፍተት በመጠን፣ በብዛትና በመጋዘኑ ቅርፅ የተለያየ ቢሆንም በእያንዳንዱ መጋዘን 6 ከእንጨት የተሰሩ ፍሬሞች (ስፋቱ 200ሚ.ሜ. x ከፍታዉ 400ሚ.ሜ.) ማግጠም ያስፈልጋል፡፡<br>- የላስቲክ ሻራ ንጣፍ: በህብረት ስራ ማህበራት መጋዘኖች ዉስጥ ወለሉ በአብዛኛዉ አፈር ነዉ፡፡ ነገር ግን ባለ አፈር ወለሎችን ለግብርና ምርቶች ማከማቻነት ማዋል ብዙ ቆሻሻ ያለዉ ስለሆነ ጥሩ ስለማይሆን ለእርሻ ምርቶች ማሸጊ ጆኒያዎች፣ ኬሚካሎች እና ዘሮች በአንድነት በቀጥታ በአፈር ወለል ተዝረክርከዉ ይቆያሉ፡፡ የላስቲክ ሸራ ምንጣፍ ማንጠፍ ጠቀሜታዉም ከእርጥበት የተነሳ ከአፈሩ ሊደርስ የሚችለዉን መበስበስ ከአፈርና ከሌሎች ባዕድ ነገሮች እና ከዝቃጭ ፀረ-ተባይ መርዞች ለመከላከል ነዉ፡፡ አምስት የላስቲክ ሰራ ምንጣፎች (4ሜ. x 5ሜ.) ለእያንዳንዱ መጋዘን ተብሎ ይቀርባል፡፡ |
| ድርጊት:<br>[ በ2014 ]<br>1. ቢሮዉ ለዚህ ፕሮጀክት ሙሉ ጊዜዉን ሰጥቶ የሚሰራ ሰዉ በማስቀመጥ ለመጋዘን ማሻሻል ስራ የሚያስፈልግ ገንዘብ አፈላልጎ ማግኘት ይጠበቃል፡፡<br>[ በ2015 ]<br>2. የወረዳዉ ጽ/ቤት ሰራተኞች በየዓመቱ ስልጠና ወቅት አሁን ያሉትን መጋዘኖች ሁኔታ አይቶ በስልጠናዉ ፍጽሜ ዝርዝር አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡ የመጋዘኖችንና መጋዘኖች እንዲታደሱላቸዉ ጥያቄ ያቀረቡ የህብረት ስራ ማህበራትን ማመልከቻ ሁኔታ ካረጋገጠ በኋላ ቢሮዉ ያቀርባል፡፡<br>3. ቢሮዉ 26 የህብረት ስራ ማህበራትን ይመርጣል፡፡<br>4. ከእንጨት የተሰሩ በሮች፣ ከእንጨት የተሰሩ የመስኮት ሸራ ፍሬሞች እና የላስቲክ ምንጣፍ የመሳሰሉትን ቢሮዉ ያቀርባል፡፡<br>5. ቢሮዉ እነዚህን የስራ ማቴሪሎች ለ26ቱም ህብረት ስራ ማህበራ ያሰራጫል፡፡ በተጨማሪም ለዕድሳቱ ደረጃዉን የጠበቀ የዲዛይን ንድፍ ይሰጣል፡፡<br>6. የህብረት ስራ ማህበራት የማሳደሱን ስራ በራሳቸዉ ይወጡታል፡፡<br>7. የወረዳ ጽ/ቤት ቴክኒካዊ ድጋፍና ቁጥጥር ያደርግላቸዋል፡፡ ይኸዉ ስራ መጠናቀቁን ለክልል ቢሮ ወረዳዉ ሪፖርት ያቀርባል፡፡<br>8. ቢሮዉ የታደሱ መጋዘኖች አስተዳደርን በተመለከተ ክትትል ያደርጋል፡፡<br>[ በ2016 ] እንደ 2015 ሆኖ ይቀጥላል፡፡<br>[ በ2017 ] እንደ 2015 ሆኖ ይቀጥላል፡፡ |
| ግብዓት:<br>ክልል/ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ:<br>1. ለገንዘብ/በጀት ፍለጋ የሚያስፈልግ ወጪ<br>2. የዕድሳት ስራ የሚያገለግሉ ማቴሪሎች ግዥ ወጪ<br>መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት:<br>1. ለዕድሳቱ ስራ የጉልበት አቅርቦት |
| ወጪ:<br>1. ለገንዘብ/በጀት ፍለጋ የሚያስፈልግ ወጪ:<br>(1) የመጓጓዣና የዉሎ አበል ወጪ (ቢሮ/ወረዳ ጽ/ቤት): 12,000<br>(2) ለመኪና የነዳጅ ወጪ: 20,000<br>(3) የመገናኛና የሚቀርቡ ማቴሪሎች ወጪ: 2,000<br>ንዑስ ድምር 1: 34,000 ብር |

2. ለዕድሳት ስራ የሚዉሉ ማቴሪሎች ወጪ:

   (1) ከእንጨት የተሰራ በር: 20,800 (አንዱን በ800 ሂሳብ x 1 መሰረታዊ ማህበር x 26 ማህበራት)

   (2) በመረብ የተጠላለፈ ባለ እንጨት ፍሬም: 46,800 (አንዱን በ300 x 6 ለእያንዳንዱ ማህበር x 26 ማህበራት)

   (3) የላስቲክ ምንጣፍ: 78,000 (አምስቱን በ600 x ለ1 መሰረታዊ ማህበር x 26 ማህበራት)

   (4) ማቴሪያሉን ለማጓጓዝ የሚጠይቅ ወጪ: 30,000 ብር

   ንዑስ ድምር 2: 175,600

| | |
|---|---|
| ንዑስ ድምር 1+2 | : 209,600 ብር |
| መጠባበቂያ (10%) | : 20,960 ብር |
| ድምር | : 231,000 ብር |

የጊዜ ሰሌዳ:

* ለገንዘብ/በጀት ማፈላለጊያ ጊዜ 1 ዓመት ነዉ።
* ከፕላን ቁጥር 7 ጋር ጎን ለጎን የሚከናወን ይሆናል።
* የዕድሳቱ ስራ ከፕላን ቁጥር 7 ስልጠና ቀጥሎ በሚመጣ ዓመት ይከናወናል።
* የእያንዳንዱ መጋዘን እድሳት የሚጠናቀቅበት ጊዜ ከግማሽ እስከ አንድ ወር ሙሉ ሲገመት የዕድሳቱ ስራ መጋዘኑ ባዶ በሚሆንበት (ከሓምሌ እስከ መስከረም) ባሉት ጊዜያት መሆን ይኖርበታል።
* ይህ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ በ26ቱም ህብረት ስራ ማህበራት መጋዘኖች የተቀመጡ ዓላማዎች ይከናወናሉ።

| ድርጊት | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | | 2017 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 1 ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ለገንዘብ/በጀት ማፈላለግ | ▬ | ▬ | ▬ | ▬ | | | | | | | | | | | | |
| 2 የሚታደሱ መገዘኖች ማፈላላግ፣ መመዝገብ፣ ማመልከቻ መቀበል በግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ባለሙያ | | | | | ▬ | | | | ▬ | | | | ▬ | | | |
| 3 ሕ/ሥራ ማህበራትን መምረጥ በግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | | | | | ▬ | | | | ▬ | | | | ▬ | | | |
| 4 የማቴሪያል ግዥ (በር፣ የሽቦ ፍሬም፣ ፕላስቲክ ሸራ) በግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | | | | | | ▬ | | | | ▬ | | | | ▬ | | |
| 5 የሚስፈልገውን ማቴሪያል መመደብና ለዕድሳት የሚያሆን ዲዛይን መስጠት | | | | | | | △ | | | | △ | | | | △ | |
| 6 የሕ/ሥራ ማህበራት ዕድሳት ያደርጋሉ | | | | | | | ▬ | | | | ▬ | | | | ▬ | |
| 7 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ የቁጥጥርና ሥራ መጠናቀቀ ሪፖርት ያቀርባል | | | | | | | ▬ | | | | ▬ | | | | ▬ | |
| 8 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ዕድሳት የተደረገላቸው መጋዘኖችን አሥራ አመራር ክትትል | | | | | | | | ▬ | | | | ▬ | | | | ▬ |

## የፕሮጀክት ቁጥር 21

| የፕሮጀክቱ ርዕስ | የመንገድ ዳር ገጠር ማስፋፊያ ማዕከል ልማት | | |
|---|---|---|---|
| ስልት | 3: የገበያ ተግባራትን ለማከናወን ዉጤታማ የገበያ መሰረተልማት ማጠናከር<br>3-5: በመንገድ ዳር መሰረተ ልማት የግብርና ምርቶች ሽያጭን ማስፋፋት | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | በመንገድ ዳር መሰረተልማት ፕሮግራም የገጠር ምርቶች ሽያጭ ማስፋፊያ | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | 2013-2017 እ.ኤ.አ ( 5 ኣመታት ) | | |
| ፕሮጀክት አካባቢ | | | |
| የትኩረት እህል / ምርት | | | |
| የትኩረት ቡድን | የአካባቢ አስተዳደር፣ የገበሬዎች ቡድን፣ መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበር | | |
| ፈጻሚ ድርጅት | ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ፣ የአካባቢ አስተዳደር | ድጋፍ ሰጪ ድርጅት | የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ፕሮገራም (ምግብ ዋስትና)፣ ግብርና ዕድገት ፕሮግሮግራም፣ የጃፓን ዕርዳታ እና ሌሎች ለጋሾች |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች፡
በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ዋናዎቹ የንግድ መንገዶች የሚያካትቱት፡ 1) የሀዋሳዻ መስመር፣ 2) የሆሳዕና-አርባምንጭ መስመር፣ እና 3) የጂማ መስመር ናቸዉ፡፡ በነዚህ መስመሮች በከተሞችም ሆነ በከተሞች አካባቢ በመንገድ ዳር በአካባቢዎቹ የሚመረቱትን የግብርና ምርቶች የሚያቀርቡ ግለሰቦች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የመንገድ ዳር ነጋዴዎች ምንም ዓይነት ፋሲሊቲ የሌላቸዉ ግለሰብ ስለሆኑ ላልተረጋጋ ሽያጭ የተጋለጡ ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩል ሲታይ በነዚህ መንገዶች በጣም ዉሱን ማረፊያ ጣቢያዎች ስላሉ ረዝም ርቀት ሹፌሮች እና የመንገዱ ተጠቃሚዎችን ሲጓዙ ምቾት ይቀንሳል፡፡ እነዚህን ሁለቱንም ችግሮች ለመቅረፍ አንዳንድ ተገቢ የመሸጫ ስፍራዎች በስትራቴጂያዊ ቦታዎች በመንገድ ዳር ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በመሸጫ ቦታዎች የመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች፣ መፀዳጃ ቤቶች፣ ለምርት ሻጮች የመንገድ ዳር ሱቆች ወዘተ ለሹፌሮችና ሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች ጭምር የተዘጋጀላቸዉ መሆን ያስፈልጋል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚጨምር የገዥዎች ቁጥር የገዥዎች የመግዛት አቅምና የግዥ መጠን እየጨመረ እንደሚሄድ ይታሰባል፡፡

ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ የመንገድ ዳር ፋሲሊቲዎች ልማት መሰረተ ሀሳብ ይጠቅማል ተብሎ የሚታሰበዉ ለአካባቢ ነዋሪዎች እንጂ ለሹፌሮችና መንገድ ተጠቃሚዎች ተብሎ ስለማይታቀድ ገና ዘርፉ አላደገም ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ የመንገድ ዳር ፋሲሊቲዎች የአካባቢ ምርቶችን ለመንገድ ተጠቃሚዎች ለመሸጥ ቋሚ ገበያዎች እና የአካባቢዉ ህዝቦች ከመንገድ ተጠቃሚዎች ጋር የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸዉ፡፡ ስለዚህም ፋሲሊቲዉ "የመንገድ ዳር ገጠር ማስፋፊያ ማዕከል ይባላል"፡፡

ማዕከሉ የሚሰራበት ስፍራ የሚወሰነዉ ቀጥሎ በሚቀርቡት ነጥቦች ላይ ተመስርቶ ነዉ፡፡
1) የራሱ የሆነ ዲሲፕሊን ያለዉ የተቋሙ/የፋሲሊቲዉ አስተዳዳር መምራት አለበት፡፡
2) በቂ የሆነ የተሳላፊ ቁጥር መታወቅ አለበት፣
3) ለፋሲሊቲዉ መስሪያ ቦታ ሊገኝ ይገባል፣
4) ሽያጩ ለየት ያለ የግብርና ምርት በአካባቢዉ ያለበት መሆን ይኖርበታል፣

በፋሲሊቲዉ ዉስጥ የሚከተሉት አገልግሎቶች መገኘት አለባቸዉ፡
- የመግቢና መዉጫ መተላለፊያ
- በጠጠር ንጣፍ የተጠናከረ 20 መካከለኛ መጠን ያላቸዉ መኪኖች እና 5 ትልልቅ መኪኖች ማቆሚያ ቦታ
- መፀዳጃ ቤት
- ቡና ቤቶችና ሱቆች
- ለግብርና ምርቶች መሸጫ ሱቆች

የተገነቡ የመንገድ ዳር ፋሲሊቲዎች የገጠር ኢኮኖሚን በማነቃቃት የህዝብ ለህዝብ ቅርርብን ያፋጥናል ተብሎ ይገመታል፡፡

ድርጊት:

| ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/የአካባቢ አስተዳደር: | የማኔጅሜንት አካል : | ለጋሽ ድርጅት: |
|---|---|---|
| 1. በዞንና ወረዳ ደረጃ ተግባር ስብሰባዎችን ማካሄድ<br>2. በእጩ የሥራ አመራር አካላት ጥቆማ በመንተራስ ቦታን መምረጥ<br>3. የዲዛይኑን ማዘጋጀት<br>4. በጀትን ማግኘት<br>5. ተገቢ ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት | 1. የቢዝነስ ፕላን ማዘጋጀት<br>2. የተቋሙን አመራር ማቋቋም<br>3. የፋሲሊቲዉ ማስተዳዳር | ከለጋሹ ድርጅት ፕሮግራም አንጻር የተጣጣመ መሆኑንና በጀት በተገቢዉ እንደተጠቀመ ማረጋገጥ |

ግብአት:

| ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ/ የአካባቢ አስተዳደር: | የአመራር አካል : | ለጋሽ ድርጅት: |
|---|---|---|
| 1. በቢሮ/ወረዳ ስር ያሉ ሰራተኞችን በስራ ያሰማራል<br>2. በጀትን ለማግኘት የስራ ጉዞ ማድረግ<br>3. ከባለድርሻ አካላት ጋር ወቅታዊ ስብሰባዎችን ማካሄድ<br>4. የዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥር ማድረግ | 1. ለግንባታዉ መሬትን ማግኘት<br>2. የአገልግሎት ክፍያ | ለፋሲሊቲዉ ግንባታ በጀት መመደብ |

መነሻ ሀሳብና ዓለማዎች:

መሰረታዊ ዲዛይን በሥራ አመራር አካሉ እና በቢሮዉ ይወሰናል፡፡ የፋሲሊቲዉ ረቂቅ ንድፍ ከዚህ በታች ይቀርባል፡





ወጪ:

1. የግንባታ ወጪ (አብዛኛዉ በለጋሹ ድርጅት የሚሸፈን) ቦታን ሳይጨምር 4,500,000 ብር በእያንዳንዱ ቦታ
2. የሰራተኛ ጉልበት ወጪ (በቢሮዉ የሚሸፈን)
   ዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥር ስራ : በየወሩ 16,000 ብር x 5 ወራት = 80,000 ብር
3. የሥራ ማስኬጃ ወጪ
   5,000 ብር/ጊዜ : በቢሮዉ የሚሸፈን
   1,000 ብር/ጊዜ : በየዞኑ የሚሸፈን
   200 ብር/ጊዜ : በማኔጅሜንት አካል የሚሸፈን
4. የጉዞ ወጪ
   በየወጪዉ ወቅት (እንደ ደንቡ ይሆናል)

የጊዜ ሰሌዳ:

የዚህ ፕሮጀክት ወደ ስራ የሚስገባ የጊዜ ሰሌዳ የፋሲሊቲዉ አመራር አካል ከተመረጠ በኋላ ይዘጋጃል፡፡ ለትግበራ እንዲያግዝ ከለጋሽ ድርጅት በጀትን ማግኘት፣ ቦታን፣ የአመራር አካላትን እና የአስተዳደር ዘዴን መምረጥና መወሰን፣ የዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር፣ ወዘተ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ስለዚህ የቢሮዉ ጠንካራ አመራር ያስፈልጋል ማለት ነዉ፡፡ ከዚህ በታች የሚቀርበዉ የጊዜ ሰሌዳ በአንደ ቦታ የታሰበዉን ፋሲሊቲ ለመገንባት ታሳቢ የተደረገ ነዉ፡፡ ነገር ግን ከአንድ በላይ ቦታዎች ተመርጠዉ ከሆነ በነዚህ ቦታዎች ግንባታዉ በተመሳሳይ ጊዜ ዉስጥ ሊከናወን ይችላል፡፡

| አስፈጻሚ አካል | ድርጊት | አፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ (እ.ኤ.አ) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | | | | 2014 | | | | 2015 | | | | 2016 | | | | 2017 | | | |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ግብይና ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | ገንዘብ አፈላልጎ ማግኘት | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ስለፕሮጀክቱ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | የቦታ መረጣ | | | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ፈጻሚ አካል | ቢዝነስ ዕቅድ ማዘጋጀት | | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ሥራ አመራር አካል ማቋቋም | | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ዲዛይን/ ግንባታ | | | | ■ | ■ | ■ | | | | | | | | | | | | | | |

### 6.4.4 የሕብረት ሥራ ማህበራት/ ዩኒየኖች አቅም ማጠናከሪያ ዕቅድ

**ፕሮጀክት ቁጥር 22**

| | | | |
|---|---|---|---|
| የፕሮጀክቱ ርዕስ | በቡድን ግብይት የእህል ንግድ ሕ/ሥራ ማህበራት አቅም ማሳደጊያ | | |
| ስልት | 4: ከግብርና ግብይት ተቋማዊ ስርዓት ጋር ስለመጣጣም<br>4-3: የሕ/ሥራ ማህበራት/ዩኒየኖች የድጋፍ ስርዓትን መጠናከር<br>4-4: የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሰራተኞችን አቅም ማሳደግ<br>2: በግብይት ስርዓት በከፍተኛ ሁኔታ እሴት በመጨመር ትርፍ ማሳደግ<br>2-2: በጥራት ተኮር ገበያዎች ተሳትፎ ማድረግና ይህንኑ ማጠናከር<br>2-5: የቡድን ግብይትን ማሳደግ | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | የሕ/ሥራ ማህበራት/ ዩኒየኖች አቅም ማጠናከሪያ ዕቅድ | | |
| የፕሮጀክቱ ጊዜ | 2013-2018 እ.ኤ.አ (5 ዓመታት) | | |
| የፕሮጀክት ሳይት | ሲዳማ፣ ሲልጤ፣ሐዲያ፣ጉራጌ፣ ወላይታ፣ ከምባታ ጠምባሮ ዞኖችና አላባ ልዩ ወረዳ | | |
| የትኩረት ሰብል/ምርት | ጥራጥሬዎችና የቅባት እህሎች | | |
| የትኩረት ቡድን | 9 የእህል ንግድ ሕ/ሥራ ዩኒየኖች እና 84 የእህል ንግድ መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት | | |
| አስፈጻሚዉ ድርጅት | ክልል፤ የዞንና የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | ደጋፊ ድርጅት | ለጋሽ (የልማት አጋር) |

መነሻ ሀሳብና ዓላማዎች :

ከሰኔ 2012 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ 9 የሕ/ሥራ ዩኒየኖችና 84 መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት በዓለም የምግብ ፕሮግራም/ግዥ ለዕድገት ተሳትፈዋል። ይህ ፕሮጀክት የሕ/ሥራ ማህበራቱ በእህል ግብይት ዙሪያ ቴክኒካዊና የአደረጃጀት አቅም እንዲፈጥሩ ለማስቻል መሰረታዊ ስልጠናዎችን ሰጥቷል።

ፕሮጀክቱ ከስልጠና ፕሮግራሙ ጎን ለጎን ፕሮጀክቱ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ መዋቅር የሕ/ሥራ ማህበራትን ድጋፍ ስርዓት የመዘርጋት ዓላማ ያለው ሲሆን ይህም ቢሮው ካለምንም የዉጭ ድጋፍ የስልጠናን ፕሮግራም ማስፈጸም እንዲቻል ያደርጋል።

ፕሮጀክት ቁጥር 7 በታቀደዉ መሰረት ከተፈጸመ በፕሮጀክት ቁጥር 7 የሚፈጸሙ እንደ ጥራት ቁጥጥር፣ የመጋዘን አስተዳደር እና ማሻሻል ያሉትን ቴክኒካዊ የስልጠና ፕሮግራሞች አይሰጥም።

ድርጊት:

0. ለፕሮጀክቱ አፈጻጸም ተገቢዉ ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል።
   - 0-1. በክልሉ ቢሮ በኩል የፕሮጀክቱ ቡድን ተዋቅሯል።
   - 0-2. ለዞን/ ወረዳ ጽ/ቤቶች እና የሕ/ሥራ ዩኒየኖች በፕሮጀክቱ አካሄድና አፈጻጸም የግንዛቤ ማሳደጊያ አውደ ጥናት ተሰጥቷቸዋል።

1. የሕ/ሥራ ማህበራት (በተለይ መሰረታዊ የሕ/ሥራማህበራት) ድርጅታዊ አቅም አድጓል።
   - 1-1. በድርጃታዊ አመራር አቅም ማሳደጊያ የሚሆኑ የስልጠና ማቴሪያሎች ተዘጋጅተዋል (የስልጠና ርዕሶች በአስተያየት ሠንጠረዥ ላይ ተገልፀዋል)።
   - 1-2. ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ሰራተኞች የአሰልጣኞች ስልጠና ተዘጋጅቷል።
   - 1-3. ለሚመለከታቸዉ የሕ/ሥራ ማህበራት የወረዳ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ስልጠናን ይሰጣሉ።
   - 1-4. የክልል ቢሮ/ የወረዳ ጽ/ቤት ሰራተኞች የክትትል ተግባራትን ያዘጋጃሉ። (የሕ/ሥራ ዩኒየኖች)
   - 1-5. ለሕ/ሥራ ዩኒየኖች የዳሰሳ ጥናት ስልትና ይዘት ዉሳኔ ላይ ተደርሶ ተዘጋጅቷል፣
   - 1-6. የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፣
   - 1-7. የዳሰሳ ጥናቱ ዉጤቶችን መሰረት በማድረግ የሕ/ሥራ ዩኒየኖችን አቅም የሚያጎለብቱ ዕቅዶች ዲዛይን ተደርገዋል፣
   - 1-8. የተዘጋጁት ዕቅዶች ስራ ላይ ዉለዋል፣
   - 1-9. የክልል ቢሮዉ የክትትል ስራን ያካሂዳል።

2. በቡድን ግብይት የሕ/ሥራ ማህበራት አቅም አድጓል፣

በዚህ ዉጤት ስር ያሉ ተግባራት የሚተገበሩት እንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከተዉ የሕ/ሥራ ዩኒየን ጋር በመሆን ነዉ፡፡

2-1. በግብይት የስልጠና ማቴሪያል ተዘጋጅቷል፣
2-2. ለወረዳ ጽ/ቤት ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተደራጅቷል፣
2-3. የወረዳ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ኃላፊነቱ ለሚመለከታቸዉ መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት ስልጠናዉን ይሰጣሉ፣
2-4. የክልል ቢሮ/ የወረዳ ጽ/ቤት ባለሙያዎች የክትትል ስራን ይሠራሉ፣

3. ለሕ/ሥራ ማህበራት ድጋፍ ለማድረግ የክልል ቢሮና በስሩ ያሉ ጽ/ቤቶች አቅም ተጠናክሯል፣

3-1. የክልል ቢሮዉ "የመሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት አቅም ግንባታ ፓኬጅ" ያዘጋጃል፣ ለዉጤት 1 እና ከዚያ በላይ ላሉት ማቴሪያሎችን ያዘጋጃል፡፡
3-2. ቢሮዉ ራሱ ፓኬጁን ለማስፈጸም እንዲያስችለዉ ዞኖችና የወረዳ ጽ/ቤቶች የተግባርና የበጀት ዕቅድ ሲያዘጋጁ ይደግፋል፣
3-3. የወረዳ ጽ/ቤት ከላይ በ3-2. ላይ የተዘጋጀዉን ዕቅድ በክልል ቢሮና በዞን ጽ/ቤት ክትትል ይፈጽማል፣

ግብአት:

| የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ: | የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት: |
|---|---|
| 1. የፕሮጀክት ቡድንን ማዋቀር<br>2. የተግባር ዕቅድ ማዘጋጀት<br>3. የስልጠና ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት<br>4. የአሰልጣኞች ስልጠናን ማስፈጸም<br>5. ክትትል ማድረግ<br>6. በሕ/ሥራ ማህበራት ድጋፍ ሲስተም ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ድጋፍ መስጠት | 1. በአሰልጣኞች ስልጠና መሳተፍ<br>2. የመሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ስልጠናን ማስፈጸም ፣<br>3. ክትትል ማድረግ ፣<br>4. ለመሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት ስልጠና የተግባርና የበጀት ዕቅድ ማዘጋጀት<br>5. ለሌሎች መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የሚሰጠዉን ስልጠና ማስፈጸም |
| **የዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መመሪያ:**<br>1. በአሰልጣኞች ስልጠና መሳተፍ<br>2. የወረዳ ጽ/ቤቶችን መደገፍ<br>3. በአሰልጣኞች ስልጠና ላልተሳተፉ የወረዳ ጽ/ቤቶች ተከታትሎ ስልጠናዉን መስጠት | **መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት:**<br>1. በፕሮጀክቱ ለመሳተፍ ከአባሎቻቸዉ ጋር ስምምነት ላይ መድረስ<br>2. አባላት በስልጠናዉ በንቃት እንዲሳተፉ ማረጋገጥ<br>3. በስልጠናዉ የተማሩትን ለሌሎች በስልጠናዉ ላልተሳተፉ አባሎቻቸዉ ማዳረስ፣ |
| **የሕ/ሥራ ዩኒየኖች:**<br>1. በስልጠናዉ ላይ መሳተፍና መደገፍ | **የልማት አጋሮች:**<br>1. ዓለም አቀፋዊ ብቃት ያለዉን ባለሙያ መቅጠርና ለፕሮጀክቱ ተግባራት ማስፈጸሚያ አስፈላጊ በጀት መመደብ፣ |

ወጪ:

1. የስልጠና ማቴሪያሎች ዝግጅትና ህትመት: 2,000 ብር x 84 ወረዳ ጽ/ቤቶች = 168,000 ብር
2. ለአሰልጣኞች ስልጠና ቦታ: 1,000 ብር x 5 ቀናት x 4 ቡድኖች = 20,000 ብር
3. ለአሰልጣኞች ስልጠና ተሳታፊዎች አበልና መጓጓዣ:
   (50 ብር x 7 ቀናት + 150 ብር x 5 ቀናት +100 ብር) x 84 ወረዳ ጽ/ቤቶች = 100,800 ብር
4. ለአሰልጣኞች ስልጠና አሰልጣኞች አበልና መጓጓዣ:
   (50 ብር x 9 ቀናት + 150 ብር x7 ቀናት +200 ብር) x 3 C/P = 5,100 ብር
5. ለመሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት አባላት አሰልጣኞች አበልና መጓጓዣ:
   350 ብር x 5 ቀናት x 84 ወረዳ ጽ/ቤቶች = 147,000 ብር
6. ለክትትል ስራ አበልና መጓጓዣ: 350 ብር x 2 ቀናት x 84 ወረዳ ጽ/ቤቶች = 58,800 ብር
7. ለክትትል ስራ አበልና መጓጓዣ: 500 ብርr x 15 ቀናት x 3 C/P = 22,500 ብር
8. ለፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አበልና መጓጓዣ: 10,000 ብር
9. ከለሚቀጠረዉ ከፍተኛ ባለሙያ ጋር የሚያያዙ ወጪዎች

የጊዜ ሰሌዳ:

ፕሮጀክቱ ተሳታፊ መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራትን በአራት ቡድኖች ከፍሎ ለእያንዳንዱ ቡድን በየዓመቱ ስልጠናዉን ያቀርባል፡፡ በሚቀጥለዉ ዓመት በስልጠናዉ ሳይሳተፉ የቀሩ የወረዳ ጽ/ቤቶችን የዞን ጽ/ቤት ያሰለጥንና ስልጠናዉን የወሰዱ የወረዳ ጽ/ቤት ባለሙያዎች መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትንና በወረዳዉ ዉስጥ ያሉ የአርሶአደር ቡድኖችን እንዲያሰለጥኑ ያደርጋሉ፡፡

| | ዞን | ዩኒየኖች (የትኩረት ማህራት ቁጥር) |
|---|---|---|
| ሀ | ሲዳማ/ ሲልጤ | ሲዳማ ኤልቶ (8) / መህልቅ (5) |
| ለ | አላባ ልዩ ወረዳ | ማንቼኖ (20) |
| ሐ | ሃዲያ/ ጉራጌ | ሊቻ (6) / ዋልታ (12) / አድማስ (10) |
| መ | ወላይታ/ ከምባታ ጠምባሮ | ዳሞታ (10) /አምበሪቾ (5) /አንጋጫ (8) |




አስተያየት:

(1) የስልጠና ርዕሶች

ድርጅታዊ ስራ አመራር
- የሕ/ሥራ ማህበር ምንድነዉ
- የስራ አመራር ኮሚቴና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሚናና ኃላፊነት
- በድርጅቱ ዉስጥ የሚኖር የስራ ግንኙነት

ስርዓተ ጾታን በልማት ማካተት
- ስርዓተ ጾታ ምንድነዉ
- በድርጅታዊ ስራ አመራር የሴቶችና ወንዶች እኩል ተሳትፎን ስለማሳደግ

የሂሳብ አያያዝ
- የሂሳብ መዝገብ አያያዝ
- ወርሃዊ ዉጤቶችን ስለማጠቃለልና ስለ ወርሃዊ ዉጣ ዉረዶች ክለሳ ማድረግ

የግብይት ስርዓት
- የእህል ግብይትና የዋጋ ዘዴ ምንነት
- በአባላት ኑሮ መሻሻል ላይ የሕ/ሥራ ማህበራት የሚኖራቸዉ ሚና

የጥራት ቁጥጥር
- ከሙከራ በትግበራ ፕሮጀክት 02 ስልጠና ጋር አንድ ይሆናል

የመጋዘን አያያዝና አስተዳደር
- ከሙከራ በትግበራ ፕሮጀክት 08 ስልጠና ጋር አንድ ይሆናል

## ፕሮጀክት ቁጥር 23

| የፕሮጀክቱ ርዕስ | የእህል ንግድ ያልሆኑ ሕ/ሥራ ማህበራት/ዩኒየኖች አቅማቸዉን ማጠናከር | | |
|---|---|---|---|
| ስልት | 4: ከግብርና ግብይት ተቋማዊ ስርዓት ጋር ስለመጣጣም<br>4-3: የሕ/ሥራ ማህበራት/ ዩኒየኖች የድጋፍ ስርዓትን መጠናከር<br>4-4: የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሰራተኞችን አቅም ማሳደግ<br>4-5፡ በግብይት ስርዓት በከፍተኛ ሁኔታ እሴት በመጨመር ትርፍን ከፍ ማድረግ<br>4-6፡ በጥራት ተኮር ገበያዎች ተሳትፎ ማድረግና ይህንኑ ማጠናከር<br>4-7: የቡድን ግብይትን ማሳደግ | | |
| የማስተር ፕላን ፕሮግራም | የሕ/ሥራ ዩኒየኖች/ ማህበራት አቅም ማጠናከሪያ ዕቅድ | | |
| ፕሮጀክቱ የሚፈጸምበት ጊዜ | 2013-2017 እ.ኤ.አ (4 ዓመታት) | | |
| የፕሮጀክት ሳይቶች | ወላይታ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ሲዳማ፣ ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ጋሞጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖችና አላባ ልዩ ወረዳ | | |
| ትኩረት የተደረጉ እህሎች/ምርቶች | ዝንጅብል፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ካሳቫ፣ በርበሬ | | |
| የትኩረት ቡድን | - 26 መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት/ በቡድን ሽያጭ ላይ ተሰማሩ ከእህል ግብይት ዉጭ የሆኑ የገበሬዎች ቡድኖች<br>- የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች | | |
| ፈጻሚዉ ድርጅት | ክልል፣ ዞንና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ | ደጋፊ ድርጅት | ለጋሹ (የልማት አጋር) |

*መነሻ ሀሳብና ዓላማዎቹ*:

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ መንግስት ዉስጥ በእህል ግብይት የተሰማሩ መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራትና የገበሬዎች ቡድኖች ቀስ በቀስ እያደገ መጥቷል፡፡ ነገር ግን ከእህል ግብይት ዉጭ ያሉ ሸቀጦች ግብይት ላይ የተሰማሩ እስካሁን በቁጥር አነስተኛ ሆነዉ ንግድን ለመጀመር የሚያስችል ዕዉቀትና ክህሎት እንኳን የሌላቸዉ መሆኑ ተስተዉሏል፡፡ ከእህል ንግድ ዉጭ ባሉ ሸቀጦች የተሰማሩ ማህበራት ምርታማነት በእህል ንግድ ከተሰማሩት ማህበራት የተሻለ ስለሆነ የነዚሁ ማህበራት የቡድን ግብይት አነስተኛ ይዞታ ላላቸዉ ገበሬዎች የኑሮአቸዉ መሻሻልን ሊያመጣ ይችላል፡፡

በጥናት እንደታወቀዉ ማንጎ፣ አቪካዶ፣ ዝንጅብል፣ ካሳቫ እና በርበሬ ያሉ ሰፋ ያለ ጠቀሜታ ያላቸዉ ገቢ አምጪ ሰብሎች ናቸዉ፡፡ በዚህ ፕሮጀክት ድጋፍ (1) በተመረጡ ሰብሎች የቡድን ግብይት ለማድረግ ፈቃደኛ የሆኑ የሕ/ሥራ ማህበራት ወይም የአርሶአደር ቡድኖች፣ (2) ቢሮዉ በአዲሱ ንግድ የሕ/ሥራ ማህበራትንና የገበሬ ቡድኖችን ለማጠናከር ተግባራዊ የሚሆን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በክልሉ ዉስጥ በተመረጡ ሰብሎች ግብይት የተሰማሩ የሕ/ሥራ ዩኒየኖች፡ ጋሞጎፋ ሕ/ሥራ ዩኒየን (በማንጎ)፣ ዳሞታ ዩኒየን (በዝንጅብል)፣ አምበሪቾ ዩኒየን (በዝንጅብል) ናቸዉ፡፡ ስለዚህ ለጊዜዉ ፕሮጀክቱ ከነዚህ 3 የሕ/ሥራ ዩኒየኖች ጋር ይሰራል፡፡ የዝንጅብል ንግድን ለመደገፍ በተቀረፀዉ ፕሮጀክት ቁጥር 12 ለትኩረት ቡድን የመሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ምርጫ ይህ ፕሮጀክት መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትን ከመደገፍ አንጻር ከፕሮጀክት ቁጥር 12 ጋር ይተባበራል፡፡

*ተግባራት*:

0. ለፕሮጀክቱ አፈጻጸም ተገቢዉ ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡
   - 0-1. በክልሉ ቢሮ በኩል የፕሮጀክቱ ቡድን ተዋቅሯል፡፡
   - 0-2. በአጠቃላይ 26 መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት ተመርጠዋል (ስለ ትኩረት ቡድኖች መረጣ ቀጥሎ የቀረበዉን አስተያየት ይመልከቱ)፡፡
   - 0-3. ለዞን/ ወረዳ ጽ/ቤቶች እና የህብረት ስራ ዩኒየኖች በፕሮጀክቱ አካሄድና አፈጻጸም የግንዛቤ ማሳደጊያ ወርክሾፕ ተሰጥቷቸዋል፡፡

1. የሕ/ሥራ ማህበራት (በተለይ መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት) ድርጅታዊ አቅም አድጓል፡፡
   - 1-1. በድርጃታዊ አመራር አቅም ማሳደጊያ የሚሆኑ የስልጠና ማቴሪያሎች ተዘጋጅተዋል (የስልጠና ርዕሶች በአስተያየት ሰንጠረዥ ላይ ተገልፀዋል)፡፡
   - 1-2. ለወረዳ ጽ/ቤት ሰራተኞች የአሰልጣኞች ስልጠና ተዘጋጅቷል፡፡
   - 1-3. ኃላፊነቱ ለሚመለከታቸዉ የህብረት ስራ ማህበራት የወረዳ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ስልጠናን ያቀርባሉ፡፡
   - 1-4. የክልል ቢሮ/ የወረዳ ጽ/ቤት ሰራተኞች የክትትል ተግባራትን ያዘጋጃሉ፡፡
2. በቡድን ግብይት የሕ/ሥራ ማህበራት አቅም አድጓል፡፡ በዚህ ዉጤት ስር ያሉ ተግባራት የሚተገበሩት እንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከተዉ የህብረት ስራ ዩኒየን ጋር በመሆን ነዉ፡፡
   - 2-1. መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት የተወሰኑ ሊያሰሩ የሚችሉ ሸቀጦችን መርጠዋል
   - 2-2. አመቺ የሆኑ ሸቀጦችን ለመምረጥ የገበያ ሁኔታን ለማሰስ አንድ አውደ ጥናት ይካሄዳል፣
   - 2-3. የመሰረታዊ ማህበር ወይም የአርሶአደሮች ቡድን በ2-2 መሰረት አመቺ ሸቀጦችን ይመርታሉ፣
   - 2-4. ስለተመረጠዉ ሸቀጥ ጥራት ቁጥጥርና ድህረምርት አያያዝ ጋር ተዛማጅነት ያላቸዉ የስልጠና ማቴሪያሎች ይዘጋጃሉ፣
   - 2-5. ለወረዳ ጽ/ቤት ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተካሄዷል፣
   - 2-6. የወረዳ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ለመሰረታዊ ማህበራትና የአርሶአደሮች ቡድን ስልጠና ይሰጣሉ፣
   - 2-7. የክልል ቢሮ/ የወረዳ ጽ/ቤት ሰራተኞች የክትትል ተግባራትን ያዘጋጃሉ፡፡
3. ለሕ/ሥራ ማህበራት ድጋፍ ለማድረግ የክልል ቢሮና በስሩ ያሉ ጽ/ቤቶች አቅም ተጠናክሯል፣
   - 3-1. የክልል ቢሮዉ "የመሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት አቅም ግንባታ ፓኬጅ" ያዘጋጃል፣ ለዉጤት 1፣ 2 እና ከዚያ በላይ ላሉት ማቴሪያሎችን ያዘጋጃል፡፡
   - 3-2. ቢሮዉ ራሱ ፓኬጁን ለማስፈጸም እንዲስችለዉ ዞኖችና የወረዳ ጽ/ቤቶች የተግባርና የበጀት ዕቅድ ሲያዘጋጁ ይደግፋል፣
   - 3-3. የወረዳ ጽ/ቤት ከላይ በ3-2. ላይ የተዘጋጀዉን ዕቅድ በክልል ቢሮና በዞን ጽ/ቤት ክትትል ይፈጽማል፣

ግብአት:

| | |
|---|---|
| የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ:<br>1. የፕሮጀክት ቡድንን ማዋቀር<br>2. የተግባር ዕቅድ ማዘጋጀት<br>3. የስልጠና ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት<br>4. የአሰልጣኞች ስልጠናን ማስፈጸም<br>5. ክትትል ማድረግ<br>6. በሕ/ሥራ ማህበራት ድጋፍ ሲስተም ለወረዳ ጽ/ቤቶች ድጋፍ መስጠት | የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት:<br>1. በአሰልጣኞች ስልጠና መሳተፍ<br>2. የመሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ስልጠናን ማስፈጸም ፣<br>3. ክትትል ማድረግ ፣<br>4. ለመሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት ስልጠና የተግባርና የበጀት ዕቅድ ማዘጋጀት<br>5. ለሌሎች መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የሚሰጠዉን ስልጠና ማስፈጸም |
| የዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ:<br>1. በአሰልጣኞች ስልጠና መሳተፍ<br>2. የወረዳ ጽ/ቤቶችን መደገፍ<br>3. በአሰልታኞች ስልጠና ላልተሳተፉ የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ተከታትሎ ስልጠናዉን መስጠት | መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት:<br>1. በፕሮጀክቱ ለመሳተፍ ከአባሎቻቸዉ ጋር ስምምነት ላይ መድረስ<br>2. አባላት በስልጠናዉ በንቃት እንዲሳተፉ ማረጋገጥ<br>3. በስልጠናዉ የተማሩትን ለሌሎች በስልጠናዉ ላልተሳተፉ አባሎቻቸዉ ማዳረስ፣ |
| የህብረት ስራ ዩኒየኖች:<br>1. በስልጠናዉ ላይ መሳተፍና መደገፍ | የልማት አጋሮች:<br>1. ዓለም አቀፋዊ ብቃት ያለዉን ባለሙያ መቅጠርና ለፕሮጀክቱ ተግባራት ማስፈጸሚያ አስፈላጊ በጀት መመደብ፣ |

ወጪ:

1. የስልጠና ማቴሪያሎች ዝግጅትና ህትመት: 2,000 ብር x 26 ወረዳ ጽ/ቤቶች = 52,000 ብር
2. ለአሰልጣኞች ስልጠና ቦታ: 1,000 ብር x 5 ቀናት x 3 ቡድኖች = 15,000 ብር

3. ለአሰልጣኞች ስልጠና ተሳታፊዎች አበልና መጓጓዣ:
   (50 ብር x 7 ቀናት + 150 ብር x 5 ቀናት + 100 ብር) x 26 ወረዳ ጽ/ቤቶች = 31,200 ብር
4. ለአሰልጣኞች ስልጠና አሰልጣኞች አበልና መጓጓዣ:
   (50 ብር x 9 ቀናት + 150 ብር x7 ቀናት + 200 ብር) x 3 C/P = 5,100 ብር
5. ለመሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት አባላት አሰልጣኞች አበልና መጓጓዣ:
   350 ብር x 5 ቀናት x 26 ወረዳ ጽ/ቤቶች = 45,500 ብር
6. ለክትትል ስራ አበልና መጓጓዣ: 350 ብር x 2 ቀናት x 26 ወረዳ ጽ/ቤቶች = 18,200 ብር
7. ለክትትል ስራ አበልና መጓጓዣ: 500 ብር x 10 ቀናት x 3 C/P = 15,000 ብር
8. ከሚቀጠረዉ ከፍተኛ ባለሙያ ጋር የሚያያዙ ወጪዎች

የጊዜ ሰሌዳ:

ፕሮጀክቱ ተሳታፊ መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራትንና የአርሶአደር ቡድኖችን በአራት ቡድኖች ከፍሎ ለእያንዳንዱ ቡድን በየዓመቱ ስልጠናዉን ያቀርባል፡፡ በሚቀጥለዉ ዓመት በስልጠናዉ ሳይሳተፉ የቀሩ የወረዳ ጽ/ቤቶችን የዞን መምሪያ ያሰለጥንና ስልጠናዉን የወሰዱ የወረዳ ጽ/ቤት ባለሙያዎች መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትንና በወረዳዉ ዉስጥ ያሉ የገበሬ ቡድኖችን እንዲያሰለጥኑ ያደርጋሉ፡፡

| | ዞን | የተመረጡ ሸቀጦች | መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ብዛት |
|---|---|---|---|
| ሀ | ወላይታ/ ከምባታ ጠምባሮ | ዝንጅብል፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ካዛቫ | 6 |
| ለ | ሲዳማ/ አላባ ልዩ ወረዳ/ ስልጤ/ ጉራጌ | በርበሬ፣ አቮካዶ | 14 |
| ሐ | ጋሞጎፋ/ ደቡብ ኦሞ | ማንጎ | 6 |




አስተያየት:

(1) የትኩረት መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት/የአርሶአደር ቡድኖች ምርጫ
  ይህ ፕሮጀክት ከእያንዳንዱ (የማንጎ፣ አቮካዶ፣ ዝንጅብል፣ ካዛቫና ቀይ በርበሬ) አቢይ አምራች ዞን 3 የአርሶአደር ቡድኖችን ይመርጣል፡፡
  ለመሰረታዊ ማህበራት ምርጫ የተዘጋጀ መስፈርት ቀጥሎ ይቀርባል፡፡
  - በተመረጡት ሸቀጦች እስካሁን በቡድን ግብይት ተሳታፊ የሆነ ወይም ለመሳተፍ ፈቃደኛ የሆነ
  - በፕሮጀክቱ ለመሳተፍ የሕ/ሥራ ማህበሩ አባላት ስምምነት
  - ሴት አባላትን ቁጥር ለማሳደግ ፈቃደኛ የሆነ
  - ከአንድ ወረዳ አንድ መሰረታዊ የሕ/ሥራ ማህበር

(2) የስልጠና ርዕሶች
  ድርጅታዊ ስራ አመራር
  - የሕ/ሥራ ማህበር ምንድነዉ

- የስራ አመራር ኮሚቴና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሚናና ኃላፊነት
- በድርጅቱ ዉስጥ የሚኖር የስራ ግንኙነት

ስርዓተ ጾታን በልማት ማካተት

- ስርዓተ ጾታ ምንድነዉ
- በድርጅታዊ ስራ አመራር የሴቶችና ወንዶች እኩል ተሳትፎን ስለማሳደግ

የሂሳብ አያያዝ

- የሂሳብ መዝገብ አያያዝ
- ወርሃዊ ዉጤቶችን ስለማጠቃለልና ስለ ወርሃዊ ዉጣ ዉረዶች ክለሳ ማድረግ

የግብይት ስርዓት

- የእህል ግብይትና የዋጋ ዘዴ ምንነት
- በአባላት ኑሮ መሻሻል ላይ የሕ/ሥራ ማህበራት የሚኖራቸዉ ሚና

የምርት መሰብሰብና ድህረምርት

- ምርት መሰብሰብ
- ድህረምርት አያያዝ
- ማቀነባበር

(ለምርት አሰባሰብ የስልጠና ማቴሪያልና የስልጠና ይዘት በማዘጋጀት ሂደት የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች 03፣ 04 እና 05 ተሞክሮ ተግባራዊ ይሆናል)።

# ምዕራፍ 7 ማሳሰቢያ

የግብርና ግብይት ሰርዓት መሻሻል የሚችለው ሁሉም የገበያ ተዋንያን ከአምራች እስከ ሸማች ድረስ ያለው የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ጨምሮ ሥራዎቻቸውን በአግባቡ ሲወጡ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከመንግሥት አስፈፃሚ አካላት የሚጠበቀው ፖሊሲዎችን በመቅረጽ እነዚህ የገበያ ተዋንያኖችን የግብይት ሚዛናዊና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲያካሂዱ ማበረታታትና አስፈላጊውን በጀት መመደብና ፖሊሲውን ተፈፃሚ ማድረግ ይሆናል፡፡

ምዕራፍ 4 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርና ግብይትን በማሻሻል ረገድ ወደ ኂላ የሚጐትቱ ጉዳዮች ተብራርተዋል፡፡ እነዝህም ጉዳዮች የሰው ኃይልና የገንዘብ እጥረት፣ ያልዳበረ ማህበራዊ መሠረተልማቶች፣ በቂ የመረጃ መረብ ያለመኖርና ቴክኖሎጂዎችን የመለማመድ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆን ናቸው፡፡ ምዕራፍ 6 ለግብርና ግብይት ስርዓት መሻሻል አስፈላጊ የሆነ አራት መሠረታዊ እስትራቴጂዎችንና ተግባራዊ የሚሆኑበትን ዝርዝር ሁኔታ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪ የኘሮጀክት ዕቅድ በምዕራፍ 7 ቀርቧል፡፡

በእነዚህ ምዕራፎች የተመለከተውን ኘሮጀክቶች ተግባራዊ የማድረግና ማስፋፋት ኃላፊነት የክልሉ ግብይትን ሕ/ሥራ ቢሮ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ መንግሥትና የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የሚከተሉት ነጥቦችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለበረታቱ ይገባል፡፡

### (1) ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር ለፕሮጅክቶች ማስፈጸሚያ የሚስፈልገውን በጀት ለማመቻቸት ኃላፊነት መውሰድ ይኖርበታል

የግብይት ሕ/ሥራ ቢሮ የሚመድበው ዓመታዊ በጀት አነስተኛ በመሆኑ አዳዲስ ኘሮጀክቶች ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛው የልማት አጋሮችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቂ በጀት አላቸው፡፡ ስለዚህ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በበጀት ሊደገፉ የሚችሉ የኘሮጀክት ዕቅዶች በማዘጋጀት የአጋሮችን ትኩረት ማሰብ እንዲያስችለው አቅሙን ማጎልበት አለበት፡፡

የሙከራ ትግበራ ኘሮጀክቶች አካል የሆነው የገበያ ማዕከል ግንባታ በማዕከሉ የተመረጠው ሰብል ግብይት በማሻሻል የአካባቢውን ኢኮኖሚ ለማጠናከር ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ የዓለም ባንክ/የግብርና ዕድገትን ኘሮግራምም የአካባቢ ገበያ መሻሻል የሚሰጠውን ጥቅም ይቀበላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የገበያ መጠሪያ ለመገንባት አቅዷል፡፡ ይሁንና የገበያ ማዕከላትን በመገንባት ምን ለማግኘት እንደታሰበ በአግባቡ ግልጽ ያደረገ አይመስልም፡፡ ለተመረጠው ከፍተኛ ሰብል ተጨማሪ እሴት መጨመርን፣ ወይንም የተሠራውን የገበያ መሠረተልማትን በመጠቀም የግብይት ስርዓቱን ማሻሻል አስመልክቶ የታቀደ ተግባር የለም፡፡ በዝህ ዓይነት የሚገነባው የገበያ ማዕከል ምናልባት ለጥቂት ነጋዴዎች ጥቅም ያስገኝ ይሆናል እንጂ የብዙሃኑን የገበያ ተዋኒያን ጥቅም አያስጠብቅም፡፡ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከገበያ መሠረተልማት የሙከራ ትግበራ ኘሮጀክቶች የተገኘውን ተሞክሮ መሠረት ማድረግ ሰፋ ያለ የተመረጡ ምርቶችን ግብይትን ማሻሻል የሚያስችል ኘሮጀክት ዕቅድ ከአዘጋጀ በኂላ ለኘሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት ከግብርና ዕድገት ኘሮራም ቢያስመድብ ይሻሻላል፡፡

የሙከራ ትግበራ ኘሮጀክት 02 ለወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት ባለመያዎችና ሕ/ሥራ ማህበራት በእህል ሰብል እና ጥራጥሬ ጥራት ማሻሻያና የመጋዘን አያያዝ ስልጠና ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በአካባቢ ቋንቋ የተሠጠው ስልጠና፣ የስልጠና ቁሳቁስና ግልጽ አድርጐ የሰልጠናውን ይዘት ማስቀመጥ በብዙ የሚመለከታቸው አካላት አድናቆትን አትርፏል፡፡

የዓለም ምግብ ኘሮግራም/ግኘ ለዕድገት ይህንን የስልጠና ቁሳቁስ አትም በማባዛት ረገድ የገንዘብ ድግፍ ማድረግ ይፈልጋል፡፡ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከዓለም ምግብ ኘሮግራም/ ግኘ ለዕድገት ጋር በመመካከር ውጤታማ የሥራ ትብብር እንዲኖር መሥራት አለበት፡፡

በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ 40 ወረዳዎች ኢፋድ በግብርና ግብይት ማሻሻያ ኘሮጀክት አማካኝነት በድኅረምርት ቴክኖሎጂዎችና በጥራት ማሻሻያ ለአነስተኛ አርሶአደሮች ስልጠና አካሄዷል፡፡ ከስልጠና በኂላ አርሶአደሩ በቡድን በመደራጀት ኘሮጀክት አዘጋጅቶ ከግብርና ግብይት ማሻሻያ ኘሮጀክት ብድር እንዲያገኝ አቅጣጫ ተቀምጦ ነበር፡፡ ስልጠናው በአካባቢ በአለ አማካሪዎች አማካኝ የተሰጠ ሲሆን ምንም ዓይነት አዲስ ቴክኖሎጂ ሰልጣኞች እንዲያውቁና እንዲለማመዱ የተደረገው የለም፡፡ የኘሮጀክት ኘሮፖዛል አዘገጃጀት ላይ ያለው ልምድ እጅግ ውስን በመሆኑ ጥቂት የአርሶአደር ቡድኖች ብቻ ኘሮጀክት ፖሮፖዛል በማዘጋጀት ለግብርና ግብይት ማሻሻያ ኘሮጀክት ማቅረብ ችለዋል፡፡

በዚህ ረገድ ከጥናት ቡድን በተስማሚ ቴክኖሎጂ ልማት ስልጠና ያገኙ ከወረዳ እስከ ክልል ያሉ የግብይትና ሕ/ሥራ መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች ለአርሶአደር ቡድኖች ጥቅም በኘሮጀክት ኘሮፖዛል ዝግጅት እገዛና መስጠት ይገባቸዋል፡፡

የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከልማት አግሮችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ቢሮው የሚያደርገውን የሥራ ትብብር የሚያመቻችና የሚከታተል አዲስ የሥራ ክፍል ቢያቋቋም ጥሩ እንዲሆን ሀሳብ ቀርቧል፡፡

### (2) የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትንና የሕ/ሥራ ዩኒያኖችን አቅም ማጎልበት

በመሪ ዕቅድ ላይ እንደተብራራው የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮን የሕብርት ሥራ ማህበራት አቅም የሚያጐለብት የኘሮጀክት ቡድን በማቋቋም የሕ/ሥራ ማህበራት/ዩኒያኖች አቅም የመጠናከር ሥራ ማካሄድ አለበት፡፡ እስካሁን ቢሮው አዳዲስ የሕ/ሥራ ማህበራትን ማደራጀት ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት ይንቀሳቀስ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት የነበረ ሕ/ሥራ ማህበራት አቅም የማጐልበትና የማጠናከር ሥራ ላይ ይበልጥ ማተኮር አለበት፡፡ ሌቻ ሃዲያ ዩኒያን በክልል ውስጥ ከአለበት ተወዳዳሪ ዩኒያኖች መካከል አንዱ ነው፡፡ የዩኒያኑ በጀት መጠንና የአባላት ብዛት ክልል ውስጥ ከአሉ ሌሎች ዩኒያኖች ይበልጣል፡፡ በተጨማሪ ሰፋ በአሉ የንግድ ሥራዎች ውስጥ ገብቷል፡፡ የሌቻ ሃዲያ ዩኒያን የሥራ ልምድና የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሌሎች ዩኒያኖችን አቅም ለማጠናከር ይረዳል፡፡

### (3) ለአዳዲስ የንግድ ግርጅት ባለቤቶች ድጎማ የሚያገኙበትን ስርዓት መዘርጋት

አብዛኛው የመንግሥት (ብሔራዊም ሆነ የክል) በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገሮችን ጨመሮ ከፖሊሲው ጋር ተጓዳኝ የሆኑ ሥራዎች ለሚሠሩ የአርሶአደር ቡድን፣ ሕ/ሥራ ማህበራት ወይንም የግል ኩባኒያዎችን የገንዘብ የመደገፍ ሥራ ይሠራል፡፡ ይህም መንግሥት ፖሊሲውን የግሉን ዘርፍ ካፒታልና የሰው ኃይል በመጠቀም እንዲያራምድ ያስችለዋል፡፡

የዝንጅብል ማጠብና ማድረቅ የንግድ ሥራ ኘሮጀክት የታቀደውን አስመልክቶ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋት አምራቹና ነጋዴው አዲስ ሥራ በሚጀምሩበት ወቅት ሊታገዙ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ከህብረተሠቡ የሚመጡ ማመልከቻዎች ተቀብሎ ማስተናገድ የሚችልበት የገንዘብ ድጋፍ ሥርዓት ተዘርግቶ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኃላፊነት እንዲወስድ መደረግ አለበት፡፡

### (4) የብድር አቅርቦት እና የብድር መያዥያ/ዋስትና ሥርዓት መፍጠርና ማጠናከር

በአሁኑ ወቅት ህዝባዊ ድርጅት የሆነው ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም በክልል ውስጥ ግብርና ነክ ለሆኑ የንግድ እንቅስቃሴ ለገጠሩ ሕብረተሰብ ብድር በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ የብድር ዕዳን በመክፈል ረገድ ያለውን ችግር የተነሳ የወለድ መጠኑን 10-18% እንዲሆን ተቋሙ አድርጓል፡፡ በጣም ትንሽ የወደፊቱን መገመት ከሚችሉ የንግድ ሥራዎች በስተቀር ይህንን ከፍተኛ የወለድ መጠን መሸከም የሚችሉ ድርጅቶች አይኖሩም፡፡

የንግድ ባንክ ወለድ ከኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ዝቅ ያለና ወደ 7% ቢሆንም የተወሰኑ ጥቂት ሕ/ሥራ ማህበራትና የአርሶአደሮች ቡድኖች የዋስትና መስፈርቱን ማሟላት የማይችሉት፡፡ ግብይትና የሕ/ሥራ ቢሮ ማህበራትና የአርሶአደር ቡድኖች ግብርና ነክ ለሆኑ የንግድ ሥራዎች ከንግድ ባንክ ብድር የሚያገኙበት ሁኔታ ብድር ዋስትና የመሳሰሉ አዲስ ሥርዓት በመዘርጋት ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ የዚህ አይነት የብድር ዋስትና ሥርዓት አገልግሎት ለማግኘት ከሚሰጠው አስተዋጽኦ በተጨማሪ አዳዲስ የአርሶአደር ቡድኖች ወደ ሥራ እንዲገቡ ይረዳል፡፡

### (5) በአምራቹና በነጋዴ መካከል የገበያ ትስስር መፍጠርና ማጠናከር

በገጠር አካባቢ ያሉ አነስተኛ አርሶአደሮች ስለነጋዴዎች፣ ገበያና በከተማ የሚገኙ ሸማቾች ሁኔታ ያላቸው የመረጃ ተደራሽነት እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ከክልል እስከ ወረዳ ያሉ የግብይትና ሕ/ሥራ ሠራተኞች ለተመረጡ ምርቶች እሴት መጨመር ተግባርን ብቻ ሳይሆን የገበያ ትስስርን በአምራቹ፣ አቀነባባሪዎችና ነጋዴዎች መካከል በመፍጠር መሥራት ይጠበቃል፡፡ አንዱ የዚህ አይነት ገበያ ትስስር ከተፈጠረ አነስተኛ አርሶአደሮች ምርት በማቀነባበር ሥራ ይበልጥ እንዲሰሩ ይበረታታሉ፡፡

### (6) ፍታዊና ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ለግል ነጋዴዎች ድጋፍ መስጠት

በግብርና ምርት ውጤቶች ግብይት ላይ የግል ነጋዴዎች ዋንኛ ተዋንያን ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ስለ እነርሱ ያለው አመለካከት ዝቅተኛ ቢሆንም ትርፍ ምርቶች ከአሉበት ቦታ የሚገዙት እነርሱ ናቸው፡፡ በአምራቹና በነጋዴዎች መካከል የየራሱን ጥቅም የማስጠበቅ የሚያስችል ግንኙነት መፈጠር አለበት፡፡ በዚህ ረገድ ሚዛናዊ የሆነ የንግድ ልውውጥ ስለሚሰጠው ጥቅም መንግሥት ለግል ነጋዴዎች ግንዛቤ የሚያስጨብጥበት ሥራ መሥራት አለበት፡፡

### (7) የእትዮጵያ ምርት ገበያ ጫረታ ሥርዓት

